# የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው

ከ

ማንያለው አባተ ባየህ

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል
ለኤም.ኤ. ዲግሪ መሟያ የቀረበ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 1999 ዓ.ም.

# የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው

ከ

ማንያለው አባተ ባየህ

የጥናቱ አማካሪ

አቶ ዘሪሁን አስፋው

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል

ለኤም.ኤ. ዲግሪ መሟያ የቀረበ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 1999 ዓ.ም.

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የድኅረምረቃ ትምህርት መርሃ ግብር

# የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው

በ

ማንያለው አባተ ባየህ

**በፈተና ቦርድ አባላት ተረጋግጧል**

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |

# ምስጋና

ከትልመ-ጥናት ዝግጅት ጀምሮ ጥናቱ እስከተጠናቀቀበት ዕለት ድረስ ገጽ-ለገጽም ሆነ በቴሌፎን ግንኙነት፣ በመደበኛ የስራ ሰዓታቸውም ሆነ በእረፍት ጊዜያቸው ምክራቸውን በፈለግሁበት ጊዜ ሁሉ በመስጠት ይህ ጥናት በዚህ መልክ እንዲጠናቀቅ የረዱኝን መምህሬንና አማካሪዬን አቶ ዘሪሁን አስፋውን አመሰግናለሁ።

የድህረምረቃ ትምህርትን ስፖንሰር ሆኖ ላስተማረኝ ለኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ በትምህርት ቆይታዬ አስፈላጊውን እገዛ ላደረገልኝ ለጅማ መምህራን ኮሌጅ እንዲሁም ለመስክ ምርምር ቆይታዬ የሚያግዘኝን የፋይናንስ ድጎማ ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአክብሮት ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ለመስክ ጥናቴ በአካባቢው በነበረኝ ቆይታ ትብብራቸው ሁሉ ላልተለየኝ ለቤንች ማጂ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት፣ ለቤንች ማጂ ዞን ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ፣ ለደቡብ ቤንች ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት፣ ለሚዛን ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤትና ለከተማው የህዝብ ቤተመፃህፍት ቤት ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በተጨማሪም በመስክ ጥናቴ ወቅት የሞራል ድጋፋቸው ላልተለየኝ አቶ ጨነቁ ኮንተር፣ አቶ ፀጋዬ ኮርጅቴት፣ አቶ ፀጋዬ አንዳርጌ፣ አቶ ኩንዲሳ ፈርኪ፣ አቶ ዮሐንስ ጊሲያብ፣ አቶ ካሳሁን ከበደ፣ አቶ ደጀኔ በየነ ዜፋ፣ አቶ ስለሺ ታደለ፣ አቶ ጥላሁን ጨዋቃና አቶ ብዙአየሁ አሳሳኸኝ እንዲሁም የቤንች ስነቃሎችን በመንገር ለተባበሩኝ የደቡብ ቤንች ወረዳ ቀበሌ ገበሬ ማህበራት ነዋሪዎች የአክብሮት ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

በትምህርት ቆይታዬ ወቅት ማበረታታቸው ላልተለየኝ ጓደኞቼ በተለይም አቶ ዝናብ አባኦሊ፣ መሀመድ አደም፣ ምትኩ ድቤሳ፣ አሸናፊ ሲሳይ፣ ውብነህ እምሩና በቃሉ ፈረደ ከልቤ እወዳችኋለሁ፤ አመሰግናችኋለሁ።

በቤንች ስነቃል ላይ የማደርገው ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ካለችበት ቦታ ሆና በምክር፣ በሞራልና በማቴሪያል የአቅሟን ያህል ለረዳችኝ እናቴ ወይዘሮ ሙሉወርቅ አንዳርጌ እንዲሁም ወንድሜ ተዘራና ቤተሰቦቹ ሁል ጊዜ አመሰግናችዋለሁ።

በመጨረሻም በድህረምረቃ ትምህርት ቆይታዬ ሞቾታቸውን፣ ጊዜያቸውንና ትኩረታቸውን ሁሉ ለእኔ አድርገዋልና ባለቤቴ ሙሉዓለም ሽመላሽ፣ ልጆቼ ያሬድና ማህሌት ማንያለው ትዕግስታችሁን ለፍሬ ያበቃው አምላክ የተመሰገነ ይሁን አሜን!

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት የቤንች ብሄረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረክ ማህበራዊ ፋይዳን ትኩረት በማድረግ በብሔረሰቡ ዘንድ ተለይተው የሚታወቁ የዝርው ተረክ ዘሮችን በመለየት ውስን ባህሪያቸውን የሚገልጽ ተንታኝ ጥናት ነው፡፡በዚህም ትረካ ለቤንቾች ምንድን ነው? በተለያዩ ማኅበራዊ አውዶች ዝርው ተረኮች ሲቀርቡ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው? እና የብሔረሰቡ አባላት ዝርው ተረኮቻቸው በአሁኑ ወቅት በምን ይዞታ እንደሚገኙ ያውቁ ይሆን? ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል፡፡ ለዚህ ተግባሩም የሚረዱ 97 ዝርው ተረኮች በምልከታና በቃለ መጠይቅ ዘዴዎች ከመስክ ተሰብስበው ተተንትነዋል፡፡

ቤንቾች ዝርው ተረኮቻቸውን ከክወና አውዳቸው (ጊዜ)፣ ከፈጠራነታቸው፣ ከታሪኩ እውነተኛነትና ከትረካቸው ግብ አላማ አንፃር በሁለት ምድቦች:- ቤንች ቶስና ኤሽሽ በማለት ይከፍሏቸዋል፡፡

ቤንችቶስ እውነተኛ ወይንም እወነተኝነታቸው ሊረጋገጥ የሚችሉ ታሪኮች የሚቀርቡበት የዝርው ተረክ ዘር ነው፡፡ በውስጡም «ቶስ» በሚል የወል መጠሪያ ስም የተሰጣቸው የተረክ አይነቶችን ይዟል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚተረኩት በአንድ የታሪክ አጋጣሚ በአካባቢው የተነሱትን ታዋቂ /ታሪካዊ/ ስዎችን የሚመለከቱ አፈታሪኮችና የብሄረሰቡን ባህላዊ እምነት፣ የአምልኮ ስርዓትና አሰራሮችን የሚመለከቱ ገላጭ ተረኮች ናቸው፡፡ በነዚህም አማካኝነት ባህላዊ እምነቱን ፣ ልዩ ልዩ ማህበራዊ ተቋማቱን ጠቀሜታና አስፈላጊነት በመግለጽ ቀጣይነታቸውን ያረጋግጣል፡፡ ሰናይና እኩይ ማህበራዊ ልማዶችን ለይቶ በመግለጽ ስነምግባር ያስተምራል፡፡ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚታዩ አዳዲስ ማህበራዊ ክስተቶችን (ለውጦች) ይተቻል፡፡
በቤንች ብሄረሰብ ባህል መሰረት «ቶስ» የሚተረከው በቀን (በፀሃይ ብርሃን) ሲሆን በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ሁሉ ይከወናል፡፡ ተራኪዎቹም አብዛኛውን ጊዜ አዋቂዎች (ሽማግሌዎች) ሲሆኑ በተለያዩ አጋጣሚዎች ቤንችቶስን ሲተርኩ ከትረካቸው መጀመሪያ ላይ የሚተርኩትን ጉዳይ ከማን እንደሰሙ ይገልፃሉ፡፡
ኤሽሽ የቤንች ዝርው ተረክ አንድ ዘር ነው፡፡ ታሪኩ የፈጠራ ሆኖ ክወናውም በምሽት ጊዜ በተለይም በአዋቂዎች አማካኝነት ለሕፃናት /ለልጆች/ የሚቀርብ ነው፡፡ የሚተረክበት ዓላማም ለማስደሰትና ሥነ-ምግባር ለማስተማር ተብሎ ነው፡፡
ኤሽሽ መደበኛ የመክፈቻና የመዝጊያ ቀመሮችን ተጠቅሞ የሚቀርብ ሲሆን ገፀባህርያቶቹም በአብዛኛው እንሰሳት ናቸው፡፡ በውስጡም «ኤሽሽ» በሚል የወል ስም የሚታወቁ ረገርዥም ተረቶችን ይይዛል፡፡ ከእነዚህም መሀከል በብዛት ሲተረኩ የሚደመጡት የትሊያ ተረቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን ከቤንች ዝርው ተረክ ዘሮች መሀከል ኤሽሽ በአሁኑ ወቅት ብዙም ሲተረክ አይሰማም፡፡ ትረካውም እየተረሳ ነው፡፡ ስለዚህም ይህን የዝርው ተረክ ዘር በሂደት ከመጥፋቱ በፊት የሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት (እንደ ባህል ቢሮ ያሉ) የኤሽሽ ትረካዎችን ከነክዋኔ አውዳቸው ለመሰብሰብ ጥረት ቢያደርጉ የተሻለ ነው፡፡

## ማውጫ


ምስጋና ........ i

አጠቃሎ ........ ii

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ ........ 1

1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2

1.2 የጥናቱ ዓላማ ........ 2

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 3

1.4 የጥናቱ ወሰን ........ 3

1.5 የጥናቱ ዘዴ ........ 5

1.6 የመስክ ገጠመኝ ........ 6

1.7 ያጋጠሙ ችግሮች ........ 15

ምዕራፍ ሁለት

የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ ምልከታ ........ 16

2.1 የቤንች ብሄረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ ........ 16

2.2 ቋንቋና ማንነት ........ 19

2.3 መልክአ ምድር ........ 20

2.4 ኢኮኖሚ ........ 21

2.5 መሰረተ-ልማት ........ 22

2.6 ባህላዊ እምነት ........ 23

2.6.1 ሚያንካ ........ 23

2.6.2 ካህ ........ 26

2.7. ጋብቻ ........ 28

2.8. ለቅሶና የቀብር ሥርዓት ........ 30

2.9. ባህላዊ አስተዳደር ........ 31

ምዕራፍ ሶስት

የተዛማች ጥናቶችና የንደፈ-ሀሳቦች ቅኝት ........ 39

3.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 39

3.2 የንድፈ ሀሳቦች ቅኝት ............ 44
3.2.1 ዝርው ተረኮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው ............ 45
3.2.2 የቃላዊ ዝርው ተረኮች አመዳደብ ............ 46
3.2.2.1 የመባያ ጉዳዮች እና የወጥ ተረቶች መዘርዝር ............ 46
3.2.2.2 አካባቢያዊና ትንተናዊ የዝርው ተረክ ምደባ ዘዴዎች ............ 47
ምዕራፍ አራት
የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች አካባቢያዊ ምደባና ማህበራዊ ፋይዳ ትንተና ............ 48
4.1 የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች አካባቢያዊ ምደባ ............ 48
4.1.1 ቶስ ............ 48
4.1.1.1 የቶስ አፈ ታሪኮች ............ 50
4.1.1.2 የቶስ ገላጭ ተረኮች… ............ 61
4.1.1.3 አጫጭር ትረካዎች (Anecdote Tales) ............ 64
4.1.2 ኤሽሽ ............ 67
4.1.3 የቤንች ዝርው ተረኮች፥ የክወና አውድ፣ ተራኪ እና ታዳሚዎች ............ 76
4.2 የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች ማህበራዊ ፋይዳ ገላጭ ትንተና ............ 78
4.2.1 ባህልን ጠብቆ ለትውልድ ማስተላለፍ ............ 78
4.2.2 የባህላዊና ማህበራዊ ተቋማትንና እሴቶቻቸውን ጠቀሜታ ከፍ ማድረግ ............ 82
4.2.3 ማስተማርና ማዝናናት ............ 87
4.2.4 ታሪክን መቅረስና ለመጭው ትውልድ ማስተላለፍ ............ 91
ማጠቃለያ ............ 94
የዋቢ መጻህፍትና ጽሁፎች መዘርዝር ............ 98
አባሪዎች
አባሪ አንድ፡- የቤንች ዝርው ተረኮች አቀባዮች ስም ዝርዝር ............ 102
አባሪ ሁለት፡- የቤንች ቶስ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ............ 103
አባሪ ሶስት፡- የቤንች ኤሽሽ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ............ 138
አባሪ አራት፡- የቤንች ማጂ ዞን ካርታ ............ 165
አባሪ አምስት፡- የቤንች ወረዳ ካርታ ............ 166

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ፎክሎር የአንድን ማህበረሰብ መንፈሳዊና ቁሳዊ ህይወት በየፈረጁ አጥንቶ ስለህይወት፣ ስለተፈጥሮ፣ ስለዓለመ ዓለማት (universe) ወዘተ. ያለውን አስተሳሰብ፣ እምነትና ፍልስፍና ይገልፃል፡፡ በዚህና ሌሎችም ፈርጀ ብዙ ተግባራቱ የተነሳ የፎክሎርን ልዩ ልዩ ዘሮች (Genres) ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሰብስቦ በወግ ማጥናትና ሰንዶ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው (ፈቃደ፣ 1991) ፡፡ በዚህም አንድ ህብረተሰብ በዘመናት የኑሮ ውጣ ውረዱ ውስጥ ያዳበረውንና የማህበረ-ባህላዊ ህይወቱ ማንፀባረቂያ የሆኑትን ቃላዊ ዝርው ተረኮች (Oral Prose Narratives) ሰብስቦ በማጥናት፣ ልምዱን፣ እውቀቱን፣ በአጠቃላይም ህብረተሰቡ ስለህይወት ያለውን ፍልስፍና መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ ሀሳብ በመነሳትም የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች በብሄረሰቡ እለታዊ ኑሮ ውስጥ በተለያዩ ማህበራዊና ባህላዊ አጋጣሚዎች የተነሳ ሲከወኑ ያላቸውን ፋይዳ ይህ ጥናት ትኩረት ሰጥቶ ይመረምራል፡፡ ይህ ጥናት አራት ክፍሎች አሉት፡፡

የመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ መግቢያ ሲሆን በውስጡ ዳራዊ መረጃዎችን ይዟል፡፡ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የአጠናን ዘዴው፣ የመላክ ገጠመኝና ያጋጠሙ ችግሮች ተገልፀዋል፡፡

ምዕራፍ ሁለት የቤንችን ብሄረሰብ ማህበረ-ባህላዊ ገጽታ የሚመለከቱ መግለጫዎችን ያካተተ ነው፡፡ በዚህም የቤንች መልክአምድራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ታሪካዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ገፅታዎች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

በምዕራፍ ሶስት የተዛማጅ ጥናቶችና ንድፈ-ሀሳቦች ቅኝት ቀርቧል፡፡ በዚህም በተዛማጅ ጥናቶችና በንድፈ ሀሳቦች ላይ ክለሳ ተደርÕል፡፡ ከርዕሱ ጋር ግንኙነት ያላቸው የመጀመሪያ ዲግሪና የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፎች (ዲማፆች) ተቃኝተዋል፤ እንዲሁም ከጥናቱ ጋር አግባብ ያላቸው የፎክሎር ጽንሰ ሀሳቦችን ክፍል ደግሞ ክለሳ ቀርቧል፡፡

ምዕራፍ አራት ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ክፍል የቤንች ብሄረሰብ ዝርው ታረኩን በየዘሮቻቸው እንዴት እንደሚመድባቸው የሚገልፅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የተረኮቹ ዋና ዋና ማህበራዊ ፋይዳዎች ተተንትነዋል፡፡ በመጨረሻም የጥናቱ ማጠቃለያ ቀርቧል፡፡

## 1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የቤንች ብሄረሰብንና የመኖሪያ አካባቢውን ለዚህ ጥናቱ ትኩረት ሰጥቼ የመረጥኩት በአንድ አጋጣሚ የተነሳ ያስተዋልኩት ማህበራዊ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም በዚሁ አካባቢ የሚኖር ዘመዴን ጥየቃ በሄድኩበት አጋጣሚ በአንዳንድ ግለሰቦች ቀደምት የቤንች ባህልን ልዩ ልዩ ገጽታዎች የሚመለከቱ አስተያየቶች ሲሰጡ እሰማ ነበር፡፡ "አሁንማ ብዙ ነገር እየተረሳ ነው … ልጆች እንኳ ከርቀት ሆነው ቦክንቦክ እየነፉ ሽረሽሪ ሲጫወቱ አይሰማም፡፡ እንኳን ህፃናቱ አዋቂዎቹም ረስተናል" ወዘተ. የሚሉ አስተያየቶችን ከቤንች አዋቂዎች ሰምቻለሁ፡፡ በዚሁም ማድነቅ ጀመርኩ በሂደትም የቤንች ብሄረሰብ ዝርው ታረኮችን ልዩ ልዩ ፋይዳዎች ለማጥናት መነሻ ሆኖልኛል፡፡ እንዲሁም የቤንች ዝርው ታረኮችን አስመልክቶ የተሰሩ ቀደምት አካዳሚያዊ ስራዎች አለመኖራቸው ለጥናቱ ተጨማሪ አነሳሽ ምክንያት ሆኖኛል፡፡

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዋና ዓላማው በቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች ማህበራዊ ፋይዳ ላይ ገላጭ ትንተና ማድረግና የቤንች ብሄረሰብ አባላት የእኛ ናቸው ብለው የሚጠቅሷቸውን የቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮች ለይቶ መግለፅ ነው፡፡ የጥናቱ ዝርዝር አላማዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የቤንች ብሄረሰብ የኔ ብሎ የሚጠቅሳቸው ዝርው ታረክ ዘሮችን ለይቶ ማሳየት፣ ተረኮቹ በየዘሮቻቸው የተመደቡበትን ዘዴና ዋና ዋና ባህሪዎቻቸውን (distinctive features) ማስረዳት፣
2. የዝርው ተረኮችን ጭብጥ በመተንተን ማህበራዊ ፋይዳቸውን መግለፅ፣
3. የቤንች ብሄረሰብ አባላት ዝርው ተረኮችን መቼ እና የት እንደሚተርኩና በብዛት እጥቅም ላይ የሚውለውን የዝርው ተረክ ዘር መግለፅ ነዉ፡፡

በነዚህ አላማዎች መነሻነትም ይህ ጥናት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል፡፡

1. ትረካ ለቤንቾች ምንድነው?
2. በተለያዩ አውዶች ዝርው ተረኮች ሲቀርቡ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ማህበረ-ባህላዊ ልማዶች (ደንቦች) ምን ምን ናቸው?

3. የቤንች ብሄረሰብ አባላት በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ዝርው ተረኮችን የመተረክ ልምዳቸው ምን ይመስላል?

4. ቤንቾች ከቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸው ዘሮች መሀከል የተወሰኑት በአሁኑ ወቅት እምን ይዞታ ላይ እንደሚገኙ ያውቁ ይሆን?

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የቤንች ብሄረሰብ የተለያዩ አውዶችን ተጠቅሞ የሚተርካቸው ዝርው ተረኮች በብሄረሰቡ ህይወት ውስጥ ያላቸውን ማህበራዊ ፋይዳ ተንትኖ ይገልፃል፡፡ በብሄረሰቡ ዘንድ ከቀደሙት አያቶች ጀምሮ በዝርው ተረኮቹ አማካይነት ለአሁኑ ትውልድ የደረሱትን ባህላዊና ማህበራዊ ተቋማት ምንነትና አሰራር ለማስገንዘብ ይረዳል፡፡ ስለዚህም ህብረተሰቡ ዝርው ተረኮቹ በማህበራዊ ህይወቱ ውስጥ ያላቸውን ፋይዳ በመረዳት ለተከታዩ ትውልድ የማስተላለፍ ሀላፊነት እንዳለበት በማሳየት ረገድ ጥናቱ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት ድርጅቶች የቤንች ዝርው ተረኮች በየትረካ አውዳቸው የሚያበረክቱትን ማህበራዊ ጠቀሜታና የሚያነሱትን ጭብጥ ይበልጥ እንዲያውቁ፣ የብሄረሰቡ አባላት ያዳበሩትን የስራ ታታሪነትና ለአካባቢ ጥበቃ ያላቸውን ባህላዊ ግንዛቤ ይበልጥ እንዲረዱ አውቀውና ተረድተውም ህዝቡን ለልማት ለማሳተፍ የሚያግዟቸው አገር በቀል ዕውቀቶችን ሊያቀብል ይችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡትን የቤንች ዝርው ታረኮች መረጃ በማጤን የየተረኮቹ ዘሮች አወቃቀርና የትረካ ቴክኒክን በመመርመር ወይም በተረኮቹ የተገለፁትን ጭብጦች መነሻ በማድረግ የፈጠራ ጽሁፎችን (ልቦለድ፣ ድራማ) ለመድረስ፣ የማስተማሪያ መፃህፍትን ለማዘጋጀት ለሚሹ ሁሉ ይህ ጥናት አስተዋጽኦ እንደሚኖረዉ ይገመታል፡፡

በመጨረሻም የቤንች ብሄረሰብን ታሪክ በስፋት ለማጥናት ለሚሹ ሁሉ ጥናቱ የቃላዊ ታሪክ (Oral history) መረጃን በማቀበሉ ረገድ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የቤንች ዝርው ተረኮችን ማህበራዊ ፋይዳ በመግለፅና በመተንተን ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ስለዚህም በአካባቢያዊ ምደባ ዘዴ የተለዩትን የዝርው ታሪክ ዘሮች ልዩ ባህርያትን ከመክፈቻና ከመዝጊያ ቀመሮች፣ ከገፀባህርያት፣ ከጭብጥና ይዘታቸው አንፃር

ይመለከታል። በየአውዱ ተረኮቹ ሲከወኑ ያለውን የተራኪና የታዳሚ ማንነት ይገልፃል፤ ተረኮቹ ለምን ተግባር እንደተተረኩና መቼና የት እንደሚከወኑ አውድን መነሻ አድርጎ ያጠናል። ሆኖም ጥናቱ የዝርው ተረኮቹን የተረት ክዋኔ (የተራኪውን ድራማዊ እንቅስቃሴ)፣ ሆነ የታዳሚውን ሚና፣ የዝርው ተረኮቹ አወቃቀርን በተመለከተ ዝርዝር ትንተና አያደርግም። በተጨማሪም ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ የመስክ መረጃዎች የተሰበሰቡት የብሄረሰቡ አባላት በብዛት ይኖሩበታል ከሚባለዉ ደቡብ ቤንች ወረዳ ዉስጥ ከሚገኙት ቀበሌ ማህበራት ነዋሪዎች ነዉ።

## 1.5 የጥናቱ ዘዴ

ባስነቃል ላይ የሚከናወን የመስክ ጥናት ጠቃሚ መረጃዎችን ለመሰብሰብና ለመተንተን፣ ተፈጥሯዊ፣ አርቲፊሺያልና ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቶችን ሊጠቀም እንደሚችል ፈቃደ (1991፣ 120-123)፣ Goldstein (1984፣ 82-89) ይገልፃሉ። ምሁራኑ እነዚህ ሶስት የመቼት አይነቶች ስነቃልን ከመስክ ለመሰብሰብ ያላቸውን ጠቀሜታም እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

ተፈጥሯዊ መቼት አንድ ስነቃል ባህሉ በሚፈቅደው መሠረት በተለምዶ የሚከወንበት መቼት (ቦታና ጊዜ) ነው። በዚህ መቼት ውስጥ የሚሰበሰበው የስነቃል መረጃ አስተማማኝነቱ ከፍ ያለ ነው። ይሁን እንጂ በስነቃሉ ክዋኔ ወቅት ተሳትፎ ከሚያደርጉት ታዳሚዎች እንቅስቃሴ፣ የክዋኔው ሁኔታና መሰል ጉዳዮች የተነሳ ስነቃልን በተሟላ ሁኔታ ለመቅረጽ አስቸጋሪ ይሆናል። በነዚህም ምክንያቶች የተነሳ ከሚሰበሰበው ስነቃል ውስጥ የሚጎለውን መረጃ ቅንብር ተፈጥሮኣዊ መቼትንና አርቲፊሻል መቼትን ተጠቅሞ ማሟላት ይቻላል።

ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት፣ ስነቃልን በተፈጥሯዊ መቼቱ ውስጥ ለመሰብሰብ አመቺ በማይሆንበት ጊዜ አጥኚው ባቀናበረው ተፈጥሯዊ መቼት መሰል አውድ ውስጥ ስነቃል የሚሰበሰብበት ነው። ለዚህ ተግባሩም አጥኚው ለመሰብሰብ የሚፈልገውን ስነቃል ይመርጥና ተፈጥሯዊ የመከወኛ መቼቱን ያጠናል፤ በዚህ መሰረትም ጥሩ የክወና እውቀት አለው ብሎ የመረጠውን ስነቃል አቀባይና ጓደኞቹ እንዲከወኑ ያደርጋል። በዚህም የሚፈልገውን ስነቃላዊ መረጃ ይሰበስባል።

አርቲፊሺያል መቼት አንድ ስነቃል ከተፈጥሮኣዊ መቼቱ ውጭ ሲከወን በተገኘበት አጋጣሚ፣ ቦታ፣ ጊዜና ስነቃል አቀባይን ሳይመርጥ አጥኚው ስነቃልን የሚሰበስብበት ነው።

በተጨማሪም በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ በሚከሰቱ ባህላዊና ማህበራዊ ለውጦች ስነቃሎች ሊጠፉ ይችላሉ፡፡ ስለዚህም እነዚህን እየጠፉ ያሉ ስነቃሎች የአከዋወን ስልት እያስታወሱ ለመቅረጽ አርቲፊሺያል መቼት ይጠቅማል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ሶስት የመቼት አይነቶች ውስጥ በቅንብር ተፈጥሯዊና በአርቲፊሽያል መቼቶች አማካይነት የምልከታና የቃለመጠይቅ ዘዴዎችን ተጠቅሜ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ከነክዋኔ አውዳቸው በቴፕሪከርደር ቀርጫለሁ፡፡ ፎቶግራፍም አንስቼአለሁ፡፡

የምልከታና የቃለመጠይቅ ዘዴዎች አጥኚው ለጥናቱ በመረጠው ማህበረሰብ ውስጥ በአካል ተገኝቶ የጠበቀ ሰዋዊ ግንኙነት በመፍጠር ስነቃሎችን ከማህበረ-ባህላዊ አውዳቸው ውስጥ በቀላሉ ለመሰብሰብ ያስችላል (Fatterman 1998፣ Okphewho 1992)፡፡

በምልከታ ዘዴ አማካይነት መረጃው በተሰበሰበበት መቼት ውስጥ የነበሩ ግለሰቦች ቁጥር፣ ፆታ፣ ዕድሜ፣ ስም ተመዝግቧል፡፡ በታዳሚዎች መሀከል የነበሩ ተራክቦዎች (interactions) ማለትም የአካል እንቅስቃሴ፣ የፊት ገጽታ መለዋወጥ፣ ቅጽበታዊ ምላሾች (emotional response) ተጢነዋል፡፡ የተራኪዎቹ የአከዋወን ስልት፣ አቀማመጣቸውንና ትረካቸው በተለያዩ ምክንያቶች (ለአፍታም ቢሆን) ሲቋረጥ የነበራቸው አስተያየት በተመለከተ ሁሉ በምልከታው ወቅት የጽሁፍ ማስታወሻ ይዣለሁ፡፡

በቃለመጠይቆች አማካኝነትም የመረጃ አቀባዮችን ግለታሪክ፣ ስለቤንች ብሄረሰብ ባህል፣ ታሪክ ... ያላቸውን እውቀት፣ አስተያየት፣ የሚተርኳቸውን ታረኮች ትርጉም፣ ከማን እንደሰሙ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ተምሳሌትነት (symbolic) ያላቸውን ጉዳዮች ፍቺ እንዲያስረዱኝ አድርጌያለሁ፡፡ ለዚህ ተግባርም ያግዘኛል በማለት ያቀረብኳቸው ቃለመጠይቆች በአብዛኛው ክፍት (open-ended) ጥያቄዎች ናቸው፡፡ የተወሰኑ ዝግ(close ended)፡ጥያቄዎችም ቀርበዋል፡፡

በምልከታና በቃለመጠይቅ ዘዴዎች አማካይነት የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ከተቀረጹበት (ቴፕ ሪከርደር) ከተባባሪዎቼ ጋር ተርጉሜ ወደ ጽሁፍ ገልብጫለሁ፡፡ ለትርጉም ስራም የተጠቀምኩት በ Okombo (1994) የተገለፁትን የቃል-በቃል እና ተዛማጅ የትርጉም ስልቶችን ነው፡፡ እነዚህን የትርጉም ስልቶች ተጠቅሜ ዝርው ተረኮቹ ከእናት ቋንቋ (ቤንች) ወደ አማርኛ ቋንቋ ስተረጉም የመልዕክትና የፍቺ ተመጣጣኝነትን ለመጠበቅ ጥንቃቄ አድርጌያለሁ፡፡ ከተለያዩ አውዶች ውስጥ የተሰበሰቡትን ዝርው ተረኮች በተሟላ ሁኔታ ሀሳባቸውን ይገልፁልኛል፣ በየትረካው አጋጣሚ የነበሩ ተግባቦታዊ ሂደቶችን ያሳዩልኛል በማለትም የሚከተሉትን ስርዓተ ነጥቦች ተጠቅሜያለሁ፡፡

( ) ተራኪው በየትረካው መሀከል እያቋረጠ የሚሰጠውን መግለጫ፣ ማብራሪያ የሚሹ አባባሎች ወይም የቤንች ቋንቋ አቻ በአማርኛ ቋንቋ ማግኘት ሲያስቸግር ተጠቅሜበታለሁ፣

[ ] በትረካው ሂደት ከታዳሚዎች መሀከል ጣልቃ ገብተው የሰጡት አስተያየት፣ በትረካው ሂደት ያሉ ገፀባህርያት ንግግር ቀርቧል። በግርጌ ማስታወሻም የቃላት፣ የሐረጎችና የጽንሰ ሀሳቦችን ፍቺ አመልክቻለሁ።

## 1.6 የመስክ ገጠመኝ

ከአዲስ አበባ 555 ኪ.ሎ ሜትር ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ የሁለት ቀን ጉዞ (በአውቶብስ) በማድረግ የቤንች ማጅ ዞን ርዕሰ ከተማ ሚዛን የደረስኩት በ6/03/99 ዓ.ም. ከቀኑ 11:45 ሰዓት ነበር። በነጋታው ጥዋት 2:30 ሰዓት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል በቁጥር ቋጥተ/ኢቋስክ/99/60 ቀን 1/03/99 ዓ.ም. ለቤንች ማጅ ዞን አስተዳደር (ቤማዞአ) እና በቁጥር ቋጥተ/ኢቋስክ/99/62 ቀን 1/03/99 ዓ.ም. ለቤንች ማጅ ዞን ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ (ቤማዞባማቢ.) የተጻፉ ደብዳቤዎች ለየጽ/ቤቶቹ አቀረብኩ። የቤንች ማጅ ዞን አስተደደር ጽ/ቤትም በቁጥር 004/1903/99 በቀን 8/3/99 ዓ.ም. በግንባር ለሰሜን ቤንች ወረዳ እና ለደቡብ ቤንች ወረዳ አስተዳደሮች በግልባጭ ለቤንች ማጅ ዞን ባህልና ማስታወቂያ ቢሮና ለአጥኚው በፃፈው ደብዳቤ መነሻነት ለጥናቱ በተመረጠው ዞን ውስጥ የመስክ ጥናቴን በይፋ በመጀመር ለ51 ቀናት የመስክ ቆይታ አድርጌያለሁ። እስከ 11/03/99 ዓ.ም. ቀኑ 4:00 ሰዓት ድረስ በዞኑ ዋና ከተማ ቆይታዬም የሚከተሉትን ተግባሮች አከናውኛለሁ።

የመጀመሪያው የቤንች ብሄረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ከመስክ ለመሰብሰብ በዞኑ ውስጥ በማደርገው ቆይታ ትብብር እንዲያደርጉልኝ የቤማዞአስ ጽ/ቤት የፃፈውን ደብዳቤ ለየተፃፈላቸው ክፍሎች ማድረስ ነበር። በዚህም መሠረት ለሰሜን ቤንች ወረዳ አስተዳደር ጽህፈት ቤትና ለቤማዞባማቢ. አስረከብኩ። በተለይም ሰሜን ቤንች ቆይታዬ ለጥናቴ ትኩረት የሰጠሁት የብሄረሰቡ አባላት አሰፋፈር ሁኔታን ምልከታ (survey) ማድረግ ነበር።

በተጨማሪም በዞኑ ዋና ከተማ ሚዛን ነዋሪ የሆኑና የቤንች ብሄረሰብ ታሪክን፣ ባህልን በተለይም ተረቶችን የሚያውቁና ለጥናቱ ስለተመረጠው አካባቢ እውቀት ያላቸውን ሰዎች አፈላልጌ ነበር። በመሆኑም ለባህልና ስነቃል ጥናት ካላቸው የግል ዝንባሌ የተነሳ

ከፍተኛ እገዛ ባደረጉልኝ አቶ ዮሐንስ ጊሲያብ አማካኝነት ቄስ ተገኝ ማርኩን ማግኘት ችያለሁ፡፡

ቄስ ተገኝ ማርኩ የ "ማርቤት"[1] ሰው ናቸው፡፡ ዕድሜያቸው 62፣ የወንጌላዊት መካነየሱስ ቄስ ሲሆኑ ከ30 ዓመት በላይ በወንጌላዊነት አገልግለዋል፤ አሁንም አገልጋይ ናቸው፡፡ ቄስ ተገኝ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል፤ ባህል፣ ታሪክ፣ ቋንቋ ወዘተ. ጥናቶችን የተመለከቱ ሴሚናሮችን በየጊዜው ተሳትፈዋል፡፡ ለስነቃል ጥናት ካላቸው ከፍተኛ ዝንባሌ የተነሳ የቤንች ስነቃሎችን አሰባስበዋል ሆኖም አላሳተሙም፡፡ ከቄስ ተገኝ ማርኩ ጋር በነበረኝ ቆይታ ሚዛን ከተማ ገ.ቢ. ሰፈር በሚባለው አካባቢ የቤንች፤ ታሪክ፣ ባህል እና ስነቃልን በተመለከተ አንድ ካሴት (c60) የፈጀ የድምፅ ቀረፃ (በቴፕሪከርደር) ያደረግሁ ሲሆን ይህ በመስክ ቆይታዬ የመጀመሪያ መረጃዬ ነው፡፡

በመጨረሻም ይህን ጥናት ለመስራት በተወሰነበት ወቅት የመስክ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የታቀደው ከቤንች ወረዳ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ከሐምሌ 1998 ዓ.ም. ጀምሮ ወረዳው ሰሜንና ደቡብ ቤንች ወረዳዎች ተብሎ ለሁለት በመከፈሉ የመስክ መረጃዎች የሚሰበሰቡበት አካባቢን መምረጥ አስፈላጊ ሆነ፡፡ ስለዚህም የብሄረሰቡ አባላትን አሰፋፈርና (እንደ ቤማዞአስ የ1998 ዓ.ም. ሰነድ ከህዝቡ 90.09% የሚኖረው በገጠር ነው) የገንዘብ አቅም ውስንነትን በማገናዘብ የመስክ መረጃዎችን በተሟላ መልክ ለመሰብሰብ ያስችለኛል በማለት የደቡብ ቤንች ወረዳን መረጥኩ፡፡ ምክንያቱም ከቤማዞአስ ጽ/ቤትና ከዞኑ ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ የሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር ባደረግሁት ውይይት በአሁኑ ወቅት በአንፃራዊነት አብዛኛው የብሄረሰቡ አባላት የሚኖሩት በዚሁ ወረዳ ውስጥ መሆኑን በመረዳቴ ነው፡፡ ስለዚህም የቤንች ዝርው ታሪክን የሚመለከቱ መረጃዎቼ በአብዛኛው የተሰበሰቡት በወረዳው ውስጥ ከሚገኙ ቀበሌ ገበሬ ማህበራት ነዋሪዎች ነው፡፡

የደቡብ ቤንች ወረዳ የቤንች ህዝብ ቀደምት ታሪኩና ባህሉ በወቅታዊ ማህበረ-ባህላዊ የህይወቱ ገጽታው የተተካበትን ሂደት እንዴትነት የምታሳይ አሻራ ናት፡፡ ስለዚህም በወረዳው የጌሊት ቀበሌ ገበሬ ማህበር (ቀገማ) የሚገኘው "ኒያልቶክ" (የጌሊት ቁም ድንጋይ) እነዚህን ሁለት የታሪክ ወቅቶች ለመለየት የሚያገለግል ትዕምርት (symbol) ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ኒያልቶክን ያስተከሉት በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ወደ አካባቢው የመጡት የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት የጦር መሪዎች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ባህሩ ዘውዴ፣ 1991 "History of Modern Ethiopia" በሚለው መጽሐፋቸው እንደገለፁት

[1] ማርቤት ይህ መጠሪያ በደቡብ ቤንች አካባቢ ተወላጅ የሆኑ ሰዎች (የማርቤት) የወል መጠሪያ ስም ነው፡፡

በአፄ ምኒልክ የተፀነሰው የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት ከሰሜን ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ያደረገው ታሪካዊ እንቅስቃሴ ውጤት ከሚገለፁበት አካባቢዎች አንዱ ነው።

በደቡብ ቤንች ወረዳ ቆይታዬ ካከናወንኳቸው ተግባራት መሀከል አንዱ የመስክ ረዳት መፈለግ ነው። በዚህ ተግባር የሚያግዘኝን ሰው ከአካባቢው ለማግኘት የተጠቀምኩበት መስፈርት፣ የአካባቢውን ባህልና ቋንቋ በሚገባ ማወቅን ነዉ። በተጨማሪም፣ በገጠር ይገኛሉ የሚባሉትን ተራኪዎች አድራሻ ወይም መኖሪያ ስፈራቸውን የሚያውቅ፣ እነርሱም የዛው አካባቢ ተወላጅ መሆኑን በቀላሉ የሚለዩትን ሰው መሆኑንም ነው። በአጠቃላይ ባደረግሁት ጥረትም ዘላለም (ማሙሽ) የተባለውን የደብረወርቅ ከተማ ነዋሪ ለማግኘት ችያለሁ።

ማሙሽ የ28 ዓመት ወጣት ሲሆን የደቡብ ቤንች አካባቢ ተወላጅ ነው። የቤንችን ባህልና ቋንቋ በሚገባ ያውቃል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን (ምናልባት በግሉ ምክንያት) ለጊዜው አቋርጧል። በአካባቢ ተወላጅነቱ ወይም በልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዮች የተነሳ በገጠር ነዋሪ ከሆኑ የቤንች ብሄረሰብ አባላት ጋር እጅግ የጠበቀ ግንኙነት መመስረት የቻለ ነው። በመስክ ቆይታዬ በተዘዋወርኩባቸው ገጠራማ አካባቢዎች ማሙሽን የማያውቀው ሰው የለም ማለት ይቻላል። በተለይም ቀልድ (ተረብ) አዋቂነቱ ከዕድሜ እኩዮቹ ጋርም ሆነ ከትልልቅ ሰዎች ጋር ፈጥኖ የመግባባት ችሎታው ተረኮችን በተገኙበት መቼቶች ውስጥ ለመሰብሰብ ረድቶኛል። በአጠቃላይ ማሙሽ በመስክ ጥናቴ ረዳት ብቻ ሳይሆን በተለያዩ አጋጣሚዎች፦ በገጠር ገበያ ቀናት (ቆጪ)፣ በለቅሶ ቦታዎች፣ ደቦ፣ በሽተኞችን በመጠየቅ፣ በጊያዕቶሪ[2]፣ በቡና ለቀማ፣ እርቅ ወዘተ. በመሳሰሉት ማህበራዊና ባህላዊ አጋጣሚዎች ላይ

---

[2] ጊያዕቶሪ (ጨሞ)፦ በአካባቢው እንደ ቡና በጥዋት የሚጠጣ ሲሆን የሚሰራውም ከደረቅ የቡና ቅጠልና እንደ ዝንጅብል፣ ኮረሪማ (ደረቁ)፣ ጤናዳም፣ ቃሪያ፣ በሶብላ፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ጨው ወዘተ. ... የመሳሰሉትን ቅመማት አብሮ በማፍላት ነው። ጊያዕቶሪ (ጨሞ)፦ በቤንች ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ልማድ ነው። ስለዚህም ማንኛውም ሰው የዕለት ተግባሩን ከመጀመሩ በፊት ጥዋት ላይ በየቤቱ ጊያዕቶሪ ይፈላል። አጠጣጡ ግን በጋራ ነው። ስርዓቱ ላይ የሚታደሙት ሰዎች ቤተሰብ ወይም የቅርብ ጎረቤት ብቻ ሳይሆኑ ማንኛውም አልፎ ሂያጅ መንገደኛ ሁሉ "ጊያዕኡሻ" ተብሎ እየተጠራ የሚሳተፍበት ነው።

በጊያዕቶሪ (ጨሞ) መጠጫ አውድ ላይ የማይነሱ ማህበራዊ ጉዳዮች የሉም። የተጣላ ወይም የተኳረፈ ይታረቃል፤ ያጠፋ ይወቀሳል፤ ለደረሰ ጎረምሳ ስለምትታጭ ልጃገረድ ይመከራል፣ ስለአደዲስ ማህበራዊና ተፈጥሯዊ ክስተቶች የአዋቂዎች አስተያየት ይደመጣል፤ ህፃናት ይመከሩበታል፤ በአጠቃላይ ጊያዕቶሪ በርካታ የቤንች ታረኮች መመንጪያነት ያገለግላል።

ተገኝቼ ለመስክ ጥናቴ ጠቃሚ መረጃዎችን ከመሰብሰብ አልፎ በቆይታዬ ከተወሰኑ የቤንች ቤተሰቦች ጋር ለፈጠርኩት ጢባ (ጥብቅ ዝምድና) አግዞኛል። በአጠቃላይ የመስክ ጥናቴን ዓላማ ህብረተሰቡ ተረድቶ በሙሉ ልቡ እንዲተባበረኝ ስላደረገ በመስክ ቆይታዬ የመጨረሻ ሳምንት የአካባቢያው ነዋሪዎች "ቶስ ባብ" በሚል ቅጽል ስም ባገኙኝ አጋጣሚ ሲጠሩኝ መስማቴ በመሀከላቸው የመገኘቴን ዓላማ እንደተረዱልኝ አስገንዝቦኛል።

በመስክ ጥናቴ ወቅት በደቡብ ቤንች ወረዳ ውስጥ በሚገኙ ልዩ ልዩ ቀበሌ ገበሬ ማህበራት እየተዘዋወርኩ ባሳለፍኳቸው 45 ቀናት የተለያዩ የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ለመሰብሰብ ችያለሁ። ይሁን እንጂ የዝርው ተረኮቹ አሰባሰብ የተከናወነባቸው ስልቶችና አጋጣሚዎች የተለያዩ ናቸው። የመጀመሪያው ለጥናቱ በተመረጠው አካባቢ የቤንችን ባህል፣ ታሪክ የሚያውቁና የቤንች ታረኮችን በመከወን ታዋቂ የሆኑ ሽማግሌዎችን ከነዋሪው ባገኘሁት ጥቆማ በየመኖሪያ ቤታቸው ሄጄ፣ ራሴንና ዓላማዬን በማስተዋወቅ ነው። እነርሱም "እስቲ ሌሎች ሰዎችም ስላሉ ተማክሬ ልንገርህ" በማለት ቢበዛ የሳምንት ቢያንስ የሁለት ቀን ቀጠሮ ይሰጡኝ ነበር።

ጊያፅቶሪ (ጨሞ) በወረዳው በገጠራማ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ወደ እለታዊ ስራቸው ከመሰማራታቸው በፊት ተሰባስበው የሚጠጡት ነው። በዚህ ማህበራዊ አጋጣሚም ልዩ ልዩ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች ተነስተው በአዋቂዎች አስተያየት ይሰጥባቸዋል። ለዚህ ተግባርም ልዩ ልዩ ታረኮች እጥቅም ላይ ስለሚውሉ በየአጋጣሚው እየተገኘሁ ዝርው ተረኮችን ለመሰብሰብ ችያለሁ።

"ቤንችቶስ" ያውቃሉ ከሚባሉ ስነቃል አቀባዮች ጋር በዕድሜ አንጋፋ የሆነው ግለሰብ ቤት እንሰባሰብና የአካባቢው ነዋሪዎች በዕረፍት ጊዜያቸው የሚቀማምሷቸውን የባህል መጠጦች አብረን እየተቃመስን ዝርው ተረኮችን ሰብስቤያለሁ። በዚህም የቡድን ውይይትን

ተግባርም ልዩ ልዩ ተረኮች እጥቅም ላይ ስለሚውሉ በየአጋጣሚው እየተገኘሁ ዝርው ተረኮችን ለመሰብሰብ ችያለሁ::



ጊያዕቶሪ በርካታ ማህበራዊ ጉዳዮች እየተነሱ ይተረኩበታል:: ባብ አላ ናካ በቤታቸው ጊያዕቶሪ እየተጠጣ ቤንችቶስ ሲተርኩ:-

በዚህ መሠረትም ቤንችቶስ ያውቃሉ ከሚባሉ መረጃ አቀባዮች ጋር በዕድሜ አንጋፋ የሆነው ግለሰብ ቤት እንሰባሰብና የአካባቢው ነዋሪዎች በዕረፍት ጊዜያቸው የሚቀማምሱትን የባህል መጠጦች አብረን እየተቃመስን ዝርው ተረኮችን ሰብስቤአለሁ:: ለዚህም የቡድን ውይይት የተጠቀምኩ ሲሆን በአውዱ መነሻነት የቀረቡ ዝርው ተረኮች ማህበራዊ ፋይዳ ፣የት እንደሰሙ ወይም በማን እንደተነገራቸው እንዲያስረዱኝ ቃለ መጠይቅ አቅርቤአለሁ::

በስፋት የተጠቀምኩ ሲሆን በአውዱ መነሻነት የቀረቡ ዝርው ተረኮች ማህበራዊ ፋይዳ፣ የት እንደሰሙ ወይም በማን እንደተነገራቸው እንዲያስረዱኝ ቃለመጠይቅ አቅርቤያለሁ፡፡

በአጠቃላይ ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ የተሰበሰቡበት በተገኙበት ማህበራዊ አጋጣሚ ሁሉ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል በቆጪ (ትናንሽ የገጠር ገቢያ ቀናት) ከስራ መልስ (ቡና ለቀማ)፣ ለቅሶ፣ ጊየዕ (የጥዋት ጨሞ ለመጠጣት ጎረቤት፣ ሰፈርተኛ ብሎም አልፎ ሂያጅ ሲሰባሰብ) በዕረፍት ሰዓት (ጓደኛሞች ሲሰባሰቡ)፣ በእርቅ ቦታ (ሽምግልና)፣ የታመሙ ሰዎችን ለመጠየቅ በየቤቱ በመሄድ፣ በጉዞ ላይ እያለሁ ዝናብ ጥሎ ለመጠለል ጎራ ካልኩበት ቤት ሁሉ የተገኙ ዝርው ተረኮችን ሰብስቤያለሁ፡፡

በደቡብ ቤንች ወረዳ የመስክ ቆይታዬ የመጀመሪያውን የቃላዊ ዝርው ታሪክ ቀረጻ (በቴፕ ሪከርደር) ያደረግሁት ባጋጣሚ ነበር፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡፡ የሚያህ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪ በሆኑት አቶ ተስፋ የካርሻክ አማካኝነት በዛው ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪ የሆኑና ቤንችቶስ ያውቃሉ የተባሉ ሰዎች ጋር ተገናኘሁ፤ ከአራት ቀን በኋላም ተመልሼ እንድመጣ ቀጠሮ ሰጥተውኝ ተለያየን፡፡ በቀጠሮው ቀን ከፍተኛ ዝናብ በመጣሉ (እኔ በቦታው ላይ ቀድሜ ደርሼ ነበር) መረጃ አቀባዮቼ መምጣት አልቻሉም ነበር፡፡ ሆኖም በነጋታው ማልጄ ተነሳሁና (የአንድ ሰዓት ከሩብ የእግር መንገድ) ሌላ ቀጠሮ ለመያዝ እነዚሁ ሰዎች መኖሪያ ሰፈር ሄድኩ፡፡ አካባቢው ደርሼ ወደ እነ ባብ[3] ናካ ቤት መሄድ ስጀምር ከሚያህ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ጽ/ቤት ፊት ለፊት ካለችው ትንሽ ሜዳ ሰዎች በተንተን ብለው በቡድን ቆመው አየሁ፡፡ በርቀትም ቀደም ባለው ቀን ከተዋወቅኳቸው የአካባቢው ሽማግሌዎች መሀከል እነ ባብ ጣልና ባብ ፌልን ስላየሁ ወደነርሱ በመሄድ "ቶስተንጌ" (እንደምን አደራችሁ) አልኩ፡፡ "ዲጌ ዲጌ" (ደህና ደህና) በማለት ተቀበሉኝና ተቀላቅዬ ቆምኩ፡፡

እልፍ ብሎ የቆመ ቀይ ዶዘር መኪና ነበር፡፡ በኋላ እንደተነገረኝ ዶዘሩ የመጣው ከሚዛን ሲሆን ደቡብ ቤንች ወረዳ ሚያህ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ የክልሉ መንግስት ለሚያሰራው የኤፍ.ኤም. ሬዲዮ ጣቢያ መስሪያ ቦታ ለመደልደል ነው፡፡ ይህ ሬዲዮ ጣቢያ የት ላይ እንደሚሰራ ትክክለኛ ቦታውን የአካባቢው ነዋሪዎች (ምናልባትም አብዛኞዎቹ) አያውቁም፡፡ ይሁን እንጂ ለሬዲዮ ጣቢያው መስሪያ ቦታ ትኩረት የሰጡት ከሚያህ ቀበሌ

[3] ባብ ማለት አባት ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም ያገቡ ትልልቅ ሰዎችን (አቶ! እንደሚለው) መጥሪያነት ያገለግላል፡፡

ገበሬ ማህበር ጽ/ቤት ፊት ለፊት ያለው ሰፊ ሜዳማ ቦታ መንከር (የቤንች ባህላዊ መሪዎች መካነ መቃብር) ስለሆነ ነው። ከጥንት ጀምሮ ዛሬም ድረስ ማንም ሰው ወደዚህ ቦታ ዝር አይልም፤ አይታረስም፤ ላዩ ላይ የበቀለ ዛፍም ሆነ ቁጥቋጦ አይቆረጥም። ስለዚህም የአካባቢው ሰው ወደዚህ ቦታ መጥቶ የተሰበሰበው ያ ዶዘር ምናልባት ይህንን በባህሉ መሠረት የሚከበር ቦታ "ያርስ ይሆን?" በማለት ወይም ለሬዲዮ ጣቢያው መስሪያነት የተመረጠው ቦታ ያንን መንከር አልፎ ወደ ውስጥ ከሆነ ዶዘሩ በየት በኩል እንደሚያልፍ "ጉድ" ለማየት ነበር። ምክንያቱም ይህ መንከር የሚባለው የቤንች ባህላዊ መሪዎች የቀብር ቦታ የተከበረ ስለሆነ በማንም ይደፈር ዘንድ አይፈቀድምና ነው። ሆኖም ከጥዋቱ 3:45 ሰዓት ላይ የዶዘሩ ሾፌርና ረዳቱ መጥተው ሞተሩን ካሞቁ በኋላ መካነመቃብሩን ሳይነካ በጎኑ አለፉ።

ከርቀትም ሆነ በቅርበት ሆኖ ሁኔታውን ሲመለከት የነበረውም የአካባቢው ነዋሪም ቀስ በቀስ መበታተን ጀመረ። በዚህ ማህበራዊ አጋጣሚ ከተሰባሰቡት የአካባቢው ነዋሪዎች መሀከል፣ የቤንች ባህል፣ ታሪክና ተረቶችን ያውቃሉ የሚባሉ ግለሰቦች ይገኙበት ስለነበር በነ ባብ ጣልና ባብ ናካ አማካኝነት ተሰባሰቡ። ቀጥሎም በባብናታ ካይትናብ ቤት ውስጥ የእለቱን አጋጣሚ መነሻ በማድረግ በቤንች ተረኮች ላይ በተለይም ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በተመለከተ ከአራት ሰዓት ተኩል በላይ የቡድን ውይይት ተደረገ። ዋናው የውይይት ሀሳብ ማጠንጠኛ የነበረው "የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች ምን ምን ይባላሉ? አንዱ የቃል ዝርው ተረክ ዘር ከሌላው በምን ይለያል?" ለሚሉ ጥያቄዎች በሚሰጡ መልሶች ላይ ነበር። በዚህ ዘጋጣሚ መነሻነትም ሁለቱን የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮች ማለትም ቶስና ኤሽሽን ለመለየት ቻልኩ። በዝርው ተረኮቹ ዘሮች ላይ ተሳታፊዎቹ የሰጡትን አስተያየትና ምሳሌዎች በቴፕሪከርደር ቀዳሁ። ፎቶግራፍም አነሳሁ። በዕለቱም የእኔ ሚና እንበለ-ተሳትፏዊ ምልከታ ማድረግ ነበር፤ በዚህም የተራኪና የታዳሚ ውይይትን (atmosphere) የሚመለከቱ ሰፊ ማስታወሻዎች ያዝኩ።

በደቡብ ቤንች ወረዳ የቤንች ቃላዊ ዝርው ታረኮችን ለመሰብሰብ ባሳለፍኩት የመስክ ቆይታዬ ከፍተኛ እገዛ ካደረጉልኝ ጉዳዮች አንዱ በወረዳው ውስጥ ነዋሪ የሆኑና በቤንች ባህል መሠረት ከፍተኛ ቦታ ከሚሰጣቸው የባህላዊ አስተዳደር፣ ዳኝነት፣ እምነት ... መሪዎች (chiefs) ጋር የፈጠርኩት መቀራረብ ነው። በመስክ ቆይታዬ ካነጋገርኳቸው የቤንች ባህላዊ መሪዎች መሀከል አንዱ ቤኑሽታቶ ጋይስ ጊሽቱናንስ ናቸው።

ቤኑሽታቶ ጋይስ ጊሽቱናንስ ቤንችቴት/ቤኑሽታቶ (የቤንች ንጉስ ናቸው) ዕድሜያቸው 70 ዓመት ሲሆን መኖሪያቸውም በደቡብ ቤንች ወረዳ ዞዙ-ካርሽቃ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ነው። የቤንች ባህል፣ ታሪክ፣ ማህበራዊ ግንኙነት በተለይም የቤንች ታሪክን በተመለከተ ከፍተኛ ዕውቀት አላቸው። በባህሪያቸው ተግባቢ ናቸው።

አባ ማትዮስ ሻሽንቴት በደቡብ ቤንች ወረዳ የመስክ ጥናት ቆይታዬ ከፍተኛ እገዛ ካደረጉልኝ ያካባቢው ታዋቂ ሰዎች መሀከል ግንባር ቀደሙ ናቸው። እድሜያቸው በጎልማሳነት ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን መኖሪያቸውም በጌሊት ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ነው። ዘመናዊ ትምህርት የቀሰሙ ናቸው። በቤንች ብሄረሰብ ባህል መሠረት በአሁኑ ወቅት በወረዳው ውስጥ ከሚገኙ ባህላዊ መሪዎች አንዱ ናቸው። በአካባቢው ከሚኖሩ የቤንች ብሄረሰብ አባላትም ሆነ በልዩ ልዩ ምክንያት ወደዚሁ አካባቢ ከመጡ የተለያዩ ብሄረሰቦች አባላት ጋር የጠበቀ ግንኙነት አላቸው። በአጠቃላይ አባማትዮስ ባህላዊ አስተዳደርን፣ ዳኝነትንና እምነትን ከዘመናዊው የመንግስት አሰራር (አስተዳደር) ጋር ተጣጥሞና ተጋግዞ በመስራት የነዋሪውን ህዝብ ህይወት በልማት መለወጥ እንደሚቻል በትክክል የተረዱ ይመስሉኛል። ምክንያቱም በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚሰጧቸው አስተያየቶች ዘመናዊው የመንግስት አስተዳደርና ፍትህ ከባህላዊው አስተዳደር ሊጣጣም የሚችል መሆኑን የሚያሳይ ስለሆነ ነው።

አባ ማትዮስ በመስክ ጥናቴ ወቅት አስተዋጽዋቸው በብዙ መልኩ የሚገለጽ ነው። የመጀመሪያው የቤንች ባህል፣ ታሪክን እምነትን በተመለከተ ያላቸውን እውቀት የማስረዳት ፍላጎትና ችሎታ ሲሆን በተለይም የቤንች ተረኮችን የመተረክ ክህሎታቸው (ቀልድና ጨዋታም አዋቂ ናቸው) ዋናዎቹ ናቸው፣ ሌላው እርሳቸውን ለመጎብኘት ወይም ባህላዊ በሆነ ምክንያት የሚጠይቋቸው ሰዎች ተጠቅመው በአካባቢው የሚገኙና የብሄረሰቡን ባህል፣ ማህበራዊ ልማድ የሚያውቁ ሰዎችን በቀላሉ አፈላልጎ የማግኘት ችሎታ ነው። በተለይም ከጥቂት ወራት በፊት ለሞተው ታላቅ ወንድማቸው (ጣጣ ሻሽንቴት) በቤንች ባህል መሠረት ከፍተኛ የተዝካር ዝግጅት ላይ ስለነበሩ ሊጠይቋቸው ከሚመጡ በርካታ ሰዎች መሀከል የታሪክ ችሎታ ያላቸውን በማፈላለግ አገናኝተውኛል። በጥቅሉ አባ ማትዮስ ሻሽንቴት ባላቸው አቅም ሁሉ በፍቃደኝነት ስለረዱኝ በተደጋጋሚ ቀናት በግቢያቸው (ጊብም) ተገኝቼ የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በማህበረ-ባህላዊ አውዳቸው ሲከወኑ ለመቅረስ ችያለሁ።

አባ ማትዮስ ሻሽንቴት በደቡብ ቤንች ወረዳ የመስክ ጥናት ቆይታየ ከፍተኛ እገዛ ካደረጉልኝ ያካባቢው ታዋቂ ሰዎች መሀከል ግንባር ቀደሙ ናቸው። እድሜያቸው በጎልማሳነት ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን መኖሪያቸውም በጌሊት ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ነው። ዘመናዊ ትምህርት የቀሰሙ ናቸው። በቤንች ብሄረሰብ ባህል መሠረት በአሁኑ ወቅት በወረዳው ውስጥ ከሚገኙ ባህላዊ መሪዎች አንዱ ናቸው።



የቤንች-ቶስ ምንነትና ፋይዳውን በተመለከተ የአዋቂዎች ገለፃና ውይይት በአባ ማቲዮስ ሻሽንቴት ግቢ። (ባብ አሰፋ ወሰኑ መግለጫ ሲሰጡ።)

አባ ማትዮስ በመስክ ጥናቴ ወቅት አስተዋጽዋቸው በብዙ መልኩ የሚገለጽ ነው። የመጀመሪያው የቤንች ባህል፣ ታሪክን እምነትን በተመለከተ ያላቸውን እውቀት የማስረዳት ፍላጎትና ችሎታ ሲሆን በተለይም የቤንች ተረኮችን የመተረክ ክህሎታቸው (ቀልድና ጨዋታም አዋቂ ናቸው) ዋናዎቹ ናቸው። ሌላው እርሳቸውን ለመጎብኘት ወይም ባህላዊ በሆነ ምክንያት ሊጠይቋቸው የሚመጡ ሰዎችን ተጠቅመው የብሄረሰቡን ባህል፣ ማህበራዊ እሴት (Social value) የሚያውቁ ሰዎች በቀላሉ አፈላልጎ የማግኘት ችሎታ ነው። በተለይም ከጥቂት ወራት በፊት ለሞተው ታላቅ ወንድማቸው (ጣጣ ሻሽንቴት) በቤንች ባህል መሠረት ከፍተኛ የተዝካር ዝግጅት ላይ ስለነበሩ ሊጠይቋቸው ከሚመጡ በርካታ ሰዎች መሀከል የተረክ ችሎታ ያላቸውን በማፈላለግ አገናኝተውኛል። በጥቅሉ አባ ማትዮስ ሻሽንቴት ባላቸው አቅም ሁሉ በፍቃደኝነት ስለረዱኝ በተደጋጋሚ ቀናት በግቢያቸው (ጊብም) ተገኝቼ የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በማህበረ-ባህላዊ አውዳቸው ሲከወኑ ለመቅረስ ችያለሁ።

## ያጋጠሙ ችግሮች

ይህ ጥናት በሚካሄድበት ወቅት የሚከተሉት ችግሮች አጋጥመዋል።

1. የቤንች ቋንቋ የራሱ ፊደል ስላልተቀረፀለት ወይም ቋንቋው በጽሁፍ ላይ የዋለ ባለመሆኑ በቋንቋው ለመጻፍ አልተቻለም። በዚህ የተነሳም ከመስክ የሰበሰብኳቸውን የዝርው ተረክ መረጃዎች በምንጭ ቋንቋ (ቤንች) ከቴፕ ሪከርደር ወደ ጽሁፍ መገልበጥ አልቻልኩም። በተጨማሪም በአካባቢው በነበርኩበት ወቅት በቴፕ ሪከርደር ተጠቅሜ በቤንች ቋንቋ የሰበሰብኳቸውን ዝርው ተረኮች እያደመጡ በቤንች ቋንቋ እንዲፅፉልኝ ትብብራቸውን የጠየቅኳቸው ግለሰቦች በሙሉ በዚህ ረገድ ችሎታ እንደሌላቸው በመግለፅ ፍቃደኛ ሊሆኑልኝ አልቻሉም።

2. ይህ ጥናት በተካሄደበት አካባቢ ነዋሪ የሆኑ አብዛኛዎቹ የብሄረሰቡ እናቶች (ሴቶች) የቤንች ዝርው ታሪኮችን ለመንገርም ሆነ ፎቶግራፍ ለመነሳት ፍቃደኛ አልሆኑም። በመሆኑም በተለያዩ አጋጣሚዎች ቤንችቶስም ሆነ ኤሽሽ እንዲነግሩኝ ያደረግሁት ጥረት አልተሳካም።

3. ለጥናቱ በተመረጠው አካባቢ ከጥቅምት እስከ ታህሳስ ወር መግቢያ ድረስ ያሉት ወራት እሸትና ደረቅ ቡና የሚለቀምባቸው ናቸው። ስለዚህም ለጥናቱ ትኩረት የሆነው ብሄረሰብ አባላት የገቢያቸው ምንጭ ከሆኑት ምርቶች አንዱ ቡና ስለሆነ ያለወቅቱ ከሚጥለው ዝናም የቡና ምርታቸው እንዳይጠፋ በለቀማው ስራ ተጠምደው ነበር። በዚህም የተነሳ ወጣ ገባ የመሬት አቀማመጥ በሚበዛበት የደቡብ ቤንች ወረዳ መረጃ አቀባዮችን በየሰፈሩ ፈልጎ የማናገር፣ ቀጠሮ የመያዝና ዝርው ታሪኮቹን የመቅረፅ ተግባር አስቸጋሪ ነበር።

## ምዕራፍ ሁለት

## የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ ምልከታ

### 2.1 የቤንች ብሄረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ

በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ውስጥ የቤንች ብሄረሰብን ኬትመጥነት (origin) በተመለከተ የተሰጡ መግለጫዎች የሚቀርቡ ሲሆን መረጃዎቹ የተገኙት ለጥናቱ በተመረጠው አካባቢ ከሚኖሩ የብሄረሰቡ አባላት ነው፡፡

እንደብሄረሰቡ አባላት አገላለፅ "ቤንች" የሚለው ቃል የብሄረሰቡ የወል መጠሪያ ሲሆን "ቤንቾ" ማለት ደግሞ የብሄረሰቡ ተወላጅ የሆነ ሰው መጠሪያ ስም ነው፡፡ የቤንች ብሄረሰብ መኖሪያው ቤንችዶድ (ሀገረ-ቤንች) ተብሎ እንደሚጠራም ይገልፃሉ፡፡ ቤንችዶድ (ሀገረ-ቤንች) በመባል የሚጠራው አካባቢ የቆዳ ስፋቱ በየዘመኑ የተለያየ ቢሆንም የብሄረሰቡ አባላት ቤንችዶድ (ሀገረ-ቤንች) ብለው በሚጠሩት ክልል ከበርካታ ዓመታት ጀምሮ በባህል፣ በእምነት፣ በታሪክ ወዘተ. እንቀራረባለን ከሚሏቸው፣ የሼኮ፣ የዲዚ፣ የመኤኒት፣ የካፋ ወዘተ. ብሄረሰቦች ጋር አብረው እንደኖሩ ይገልፃሉ፡፡

የቤንች ብሄረሰብን ኬት መጥነት በተመለከተ ላቀረብኩት ጥያቄ ከመረጃ አቀባዮቼ የተሰጡኝ ምላሾች በአብዛኛው ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ በተለይም የቤንች ብሄረሰብ መነሻ/ምንጩ የሆነውን ቦታ በተመለከተ ቤኑሽታቶ ጋይስ ጊሽቱናንስ (እድሜ 70፣ የዘዙ-ካርሽዋ ቀበሌ ገበሬ ማህበር /ቀገማ/ ነዋሪ) የነገሩኝ ታሪክ "የእኛ ቅድመ አያቶች የጥንት መኖሪያ ዛሬ ሼቤንች ተብሎ በሚታወቀው ወረዳ ውስጥ ሲሆን ልዩ ስሙም ዌይት ተብሎ ይጠራል" በማለት ነው፡፡

በሌላ መልኩ የቤንች ብሄረሰብን ኬትመጥነት በተመለከተ የሰማሁትና በመስክ ቆይታዬም በብዙ ስነቃል አቀባዮቼ ያልተነገረኝ ከቄስ ተገኝ ማርኩ (ዕድሜ 62፣ የሚዛን ከተማ ነዋሪ) የሰማሁት ነው፡፡ ይህም፡-

የቤንች ብሄረሰብ ጥንት ይኖር የነበረው፡- በዛሬው የጋምጎፋ ዞን ሩዶልፍ ሀይቅ አካባቢ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት በዚህ አካባቢ በተነሳው ከፍተኛ ወባ መሰል ወረርሽኝ የተነሳ ብዙ ሰው ስላለቀ ይህንን አካባቢ ለቀው ባደረጉት እንቅስቃሴ ዛሬ የሚገኙበት ቤንች ማጅ ዞን በተለይም ሼቤንች ወረዳ ውስጥ መጀመሪያ ሰፈሩ፡፡ (9-03-1999ዓ.ም ሚዛን በከተማ 02 ቀበሌ)

ይሁን እንጂ ለጥናቱ በተመረጠው አካባቢ ነዋሪ የሆኑት ሽማግሌዎች የሚስማሙት በቤኑሽታቶ እና በባብሲግ የተሰጠውን መልስ ነው፡፡

"የቤንች ብሄረሰብ መነሻው ሼቤንች ወረዳ ውስጥ ነው፡፡" የሚለው የአብዛኛዎቹ መረጃ አቀባዮች ምላሽ ለበርካታ የመስክ ጥናት ቃለመጠይቆች መነሻ ሆኖኛል፡፡ ከጥያቄዎቹ መሀከል አንዱ "ቤንችዶድ (ሀገረ-ቤንች) ተብሎ በሚጠራው ሰፊ አካባቢ የብሄረሰቡ አባላት እንዴት ሊሰራጩ ቻሉ?" የሚል ጥያቄ ሲሆን ያገኘሁትን ምላሽ እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ፡፡ ታሪኩም የተነገረኝ በባብ ሲግ እና በቄስ ተገኝ ማርኮ ነው፡፡

በባብ ሲግና በቄስ ተገኝ የተሰጠኝ ምላሽ ባብዛኛው ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ እነዚህ የመስክ መረጃ አቀባዮቼ መጀመሪያ የነገሩኝ፡- ይህንን ታሪክ (ቤንችቶስ) የሰሙት ከቤተሰባቸው መሆኑን በመግለፅ ነው፡፡ ንግግራቸውንም የጀመሩት "ኑ አክስ ኢዝቅን ኑ አይጡሽ ቶስ ..." (አያቶቻችን ጥንት የነገሩን ታሪክ) ..." በማለት ሲሆን

ጥንት ቤንች ሼቤንች ወረዳ ውስጥ ዌይት በተባለው አካባቢ ይኖር ነበር፡፡ በዛንና ቀደም ካሉት ዘመናት ጀምሮ የብሄረሰቡ አባላት የራሳቸው የሆነ ቤንቻቴት (የቤንች ንጉስ) ነበራቸው፡፡ ከነዚህም የቤንች ነገስታት መሀከል አንዱ ዣቹቴት ይባሉ ነበር፡፡ ሶስት ልጆችም ነበሯቸው፡፡ እነርሱም፡- ቦክንቴት፣ ቤንችቴትና ሜርቴት ናቸው፡፡ ታላቃቸው ቦክንቴት ይባላል፡፡

(ባብ ሲግ 27-03-1999 ዓ.ም.)

"ዣቹቴት የብሄረሰቡን አባላት አንድ አድርገው ሲያስተዳድሩ በነበሩበት ዘመን ታላቁ ልጃቸው ቦክንቴት ራሱን እንደአባቱ ንጉስ አድርጎ ወይም ንጉስ ሆኖ ስለነበር ዣቹቴት በህይወት እያሉ ጀምሮ ቦክንቴት ሼ (ጫካ) ውስጥ ገብቶ ተቀምጦ ነበር፡፡" ቄስ ተገኝ ማርኮ፡፡

እስከእዚህ ድረስ ሁለቱ መረጃ አቀባዮች የሰጡኝ መልስ ተመሳሳይነት አለው፡፡ ይሁን እንጂ በተረኩ ቀጣይ ክፍል የሚያቀርቡት ሀሳብ መለስተኛ የሆነ የተጠየቀ (logic) ልዩነት ይታይበታል፡፡ ስለዚህም እንደባብ ሲግ ገለጻ "ህዝቡን እኔ አስተዳድራለሁ የሚል የፉክክር መንፈስ በአንድ አባት ልጆች (ወንድማማቾች) መሀከል ተነሳ፡፡ በዚህም መሰረት በታላቃቸው ድርጊት ያልተስማሙት ቤንችቴትና ሜርቴት እንደዚህ አሉ ይባላል፡፡

"እኛም እንደ አንተ የአንድ አባት ልጆች ነን፡፡ ማንኛችንም ከማንኛችንም አንበልጥም ወይንም አናንስም፡፡ ስለዚህም በአንተ ስር አድረን አንገዛም አሉት፡፡ እንዲያውም እኛም

እንደአንተው የሚከተለንን ህዝብ ይዘን እንሄድና ሼ (ጫካ) ውስጥ ተቀምጠን —ቴት (ንጉስ) እንሆናለን አሉት፡፡ የወንድማማቶቹ ግጭትም እየከፋ ሄደ፡፡ ሆኖም በቤንች ባህል መሠረት በብሄረሰቡ አባላት መሀከል የሚፈጠረው ግጭት እስከ ደም መፋሰስ ድረስ እንዲሄድ አይፈቀድምና ሁለቱ ወንድማማቾች ቤንችቴትና ሜርቴት ቲርግን (ከእንጨት የሚሰራ ሬሽካ) ከኪሳቸው አውጥተው በመንፋት ተከታዮቻቸውን በመያዝ ዣዝቴት (አባታቸውን) እዛው ዌይት ትተው እንደወጡ አብረው የተጓዙት ሲል (ከጋቸብ ወንዝ በላይ) እስከሚባል ቦታ ድረስ ብቻ ነው፡፡

ሲል ደርሰው ጥቂት ቀናት እንደሰነበቱ ቤንቼቴት ወንድሙን ሜርቴትን (ቢያክቴት) እዛው ጥሎት በመጓዝ የዛሬው ደቡብ ቤንች ወረዳ ሚያህ ቀበሌ ገበሬ ማህበር መጥቶ ሰፈረ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሶስቱ ወንድማማቾች እኩል ቤንችቴት (የቤንች ንጉስ) ሆኑ፡፡ እዛው አባቱ ጋር የቀረው ታላቃቸው ሼቴት (የሼ ንጉስ)፣ ሲል የቀረው ሜርቴት እና እዚህ (ደ/ቤንች) የደረሰው ቤንችቴት ተባሉ፡፡ ይሁን እንጂ አባታቸው ዣዥቴት ከሞቱ በኋላ ቤንችቴት (ንጉሰ ነገስት) ሆኖ በሼቴት እና ሜርቴት ላይ ንጉሰ ነገስት ሆኗል፡፡ ቢሆንም "ዛሬም ሆነ ትናንት የቤንች ብሄረሰብ መነሻው አንድ ስለሆነ ወንድማማች ነው፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች (ሼቤንች፣ ሰሜን ቤንች፣ ደቡብ ቤንች ...) ቢኖርም በመሀከሉ ያለው ማህበራዊና ባህላዊ ትስስር አልተበጠሰም!" ብለዋል ባብ ሲግ፡፡

ቤንችቴት ለምን በሜርቴት እና በሼቴት ላይ ንጉሰነገስት ሆነ? ለሚለው ጥያቄ የባብ ሲግ መልስ፡- "በእኛ በቤንች ባህል አባት ሲሞት በርሱ እግር የሚተካውን የሚመርጠው የሮ (እግዚአብሔር) ነው፡፡ እርሱ ከቤተሰቡ መሀከል የፈለገውን ሲመርጥ ሚያንጎ (የአያት መንፈስ) በርሱ ላይ ይወርዳል፡፡ ይኸውልህ ዞዞ የሚኖሩትን ቤኑሽታቶ ታውቃለህ አይደል? እርሳቸው የእኛ የሁላችንም (የሼ፣ የሜር እና የቤንች) ንጉስ ናቸው፡፡ ከሁሉም ቤንችዶድ በባህሉ መሠረት የቤንች ቤተሰቦች (የኮምቲክስ፣ የጋሪናንስ፣ የኪቡ፣ የዳኪራሻ፣ የበርጊናንስ፣ የሻሽንቴት ...) እየመጡ ይጠይቁታል፡፡ እርሱም (ቤኑሽታቶ) በባህሉ መሠረት እየሄደ ይጎበኛቸዋል፡፡ በመሀከላችን የዘር ልዩነት የለም ቤንች አንድ ነው" በማለት ነው፡፡

የቄስ ተገኝ መልስም ከባብ ሲግ ማጠቃለያ ሀሳብ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ዝርዝሩም፡- "የቤንች ንጉስ (ቤንችቴት) የነበረው ዣዥቴት እንደሞተ ልጆቹ ባባታቸው እግር ለመተካት ከፍተኛ ፉክክር አደረጉ፡፡ በተለይ ሜርቴት እና ቤንችቴት መሀከል የነበረው አለመግባባት ተካሮ እንደቤተሰብ የሚተያየውን የቤንች ብሄረሰብ እንዳይከፋፈል ቦክንቴት (እንደ ቄስ ተገኝ ገለፃ ሼቴት ራሱን አላነገሰም) ደረቅ አፈር አመጣና ሁለቱ ወንድሞቹን

ይኸንን አፈር በእጃችሁ ላይ አስቀምጡ፡፡ አፈሩ በእጁ ላይ እንዳለ ወደ ውሃነት የተለወጠለት ባባታችን ቦታ ቤንችቴት ይሁን! አለ፡፡ ሁለቱም አፈሩን ተቀብለው እጃቸው ላይ ሲያደርጉ በሜርቴት እጅ የነበረው ወደ ውሃነት አልተለወጠም ነበርና የወንድሙን ንጉስነት አልተቀበለም፡፡ ይሁንና ይህ 'እኔ እበልጣለሁ!' አሁንም ባለመብረዱ ሽማግሌዎች በተሰበሰቡበት ቦክንቴት ታናሽ ወንድሞቹን ጠርቶ መረቀ ሜር[4] 'አንቃ ሜርቴት!' ወንድሜ ሜር 'ሁላችሁም ንገሱ ብዬ መርቂያለሁ' አለ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሶስት የቤንች ነገስታት ሼቴት[5]፣ ሜርቴት እና ቤንችቴት ተፈጠሩ፡፡" ይሁን እንጂ በወንድማማቾቹ መሀከል የተፈጠረው አለመግባባት በዚህ መልክ ቢፈታም "በቤንች ባህላዊ እምነት የሮ (እግዚአብሔር) ቤንችቴትን በአባቱ እግር ስለመረጠው በንግስናው ላይ ንጉሰነገስትነት ተጨመረለት!" በማለት ከባብ ሲግ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የማጠቃለያ ሀሳብ ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ እንደ ባብ ሲግና ቄስ ተገኝ አስተያየት የቤንች ብሄረሰብ ምንጩ አንድ ነው፡፡ ሆኖም በአንድ የታሪክ ወቅት በሶስት፡- ሼ፣ ሜርና ቤንች ተብለው መከፈሉን ያሳያሉ፡፡

## 2.2 ቋንቋና ማንነት

የቤንች ቋንቋ በ Bender (2000:95)፣ Wedekind (1983፡129) እና Nicolas (1976)፣ "Bencho፣ Bensho፣ Benesho ወይም Benchnon" (የቤንች ቋንቋ) በመባል እንደሚታወቅ ይገልፃሉ፡፡ በተለይም Wedekind 1983፡129 Bencnon (የቤንች ቋንቋ) ቤተሰባዊ ምድቡ በኦሟዊ ቋንቋ ውስጥ ቢሆንም በአንዳንድ ባህሪያቱ ኦሟዊ ቋንቋዎች ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ከሚገኙ ቋንቋዎችም እንደሚለይ በሚከተለው መልክ ገልጸዋል፡፡

Should linguists have anticipated such a complex tone system in East-Africa? Certainly not. It is true that the majority of the world's languages are tone languages, but languages of five or more tones are rare ended especially when it comes to five levels: with the differentiation of five or more degrees

---

[4] ሜር - በቤንች ቋንቋ ትልቅ፣ ግዙፍ ማለት ነው፡፡ ስለዚህም Mertet ማለት ግዙፍ፣ ትልቅ ንጉስ ማለት ነው፡፡

[5] ሼ - በቤንች ቋንቋ ጫካ ወይም ደን ማለት ነው፡፡

along the same dimension, a limited to human perception seems to be reached and human languages tend to avoid too fine a scale. The few areas such languages do occur are clearly marked on the linguistic map of the world.

በማለት Bencnon (የቤንች ቋንቋ) በዓለም አቀፍ ደረጃ በጣም ጥቂት ቋንቋዎች ብቻ የሚያንፀባርቁት የድምፅ (tone) ባህሪ እንዳለው በs'ንsዉ. ላይ ጥናት ያደረጉት ምሁራን ገልጸዋል፡፡

የቤንች ብሄረሰብ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ (የብሄረሰቡ አባላት ባይቀበሉትም) መጠሪያው "ጊሚራ" የሚል ነበር፡፡ "ጊሚራ" የሚለው ቃል በቤንች ቋንቋ ውስጥ ትርጉም የለውም፡፡ ይሁንእንጂ ይህ መጠሪያ ወይም ስም ምንጩ Bendder (2000)፣ Nicolas (1976)፣ Cerulli (1956) የመሳሰሉት ፀሐፍት እንደገለፁት ከሌላ ብሄረሰብ ቋንቋ እንደሆነ በማመልከት ነው፡፡ በተለይም እንደ Wedekind (1983:12) አገላለጽ "Gimira or Ghimirra was the name more widely used, but it regards to be a derogatory term" በማለት ነው፡፡

## 2.3 መልክአ ምድር

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በምትከተለው የፌዴራላዊ መንግስት አወቃቀር መሠረት የቤንች ብሄረሰብ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት (ደብብህክመ) ቤንች ማጂ ዞን (ቤማዞ) ውስጥ ይገኛል፡፡

የቤንች ማጂ ዞን ከ 34°45' እስከ 36°10' ምስራቅና ከ 5°40-7°41' ሰሜን ሀሩር (tropical) ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ከባህር ወለል በላይ ከ500-3000 ሜትር ከፍታ ያላቸውን አካባቢዎች ያካትታል፡፡ የቆዳ ስፋቱም 19326.6 ካሬ ኪ.ሎ ሜትር ሲሆን ስርዓተ ምህዳራዊ ገጽታውም ሲታይ 52% ቆላማ፣ 43% ወይናደጋና ቀሪው 5% ደጋ የአየር ፀባይ ነው፡፡ በዞኑ ውስጥ 10 ወረዳዎች እና አንድ የከተማ አስተዳደር የሚገኝ ሲሆን፣ አዋሳኞቹም በሰሜንና ሰሜን ምስራቅ የከፋ ዞን፣ በሰሜን ምዕራብ የሸካ ዞን፣ በደቡብ ምስራቅ የደቡብ ኦሞ ዞን፣ በደቡብ ምዕራብ የጋምቤላ ክልልና የሱዳን ሪፖብሊክ እንደሆኑ የቤንች ማጂ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት (1998 ዓ.ም) ሰነድ ይገልፃል፡፡

በ1986 ዓ.ም. በተካሄደው የህዝብና የቤቶች ቆጠራ መሰረት በቤንች ማጂ ዞን ውስጥ የሚገኘው ህዝብ ብዛት 449,521 ነው፡፡ የህዝቡ አሰፋፈርም (Population density) በአንድ ካሬ ኪ.. ሜትር ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ብዛት 23 መሆኑን የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ (1998) ሰነድ ያስረዳል፡፡ ይህንኑ የ1986 ዓ.ም. የህዝብ ቆጠራ ውጤት ተንተርሶ በተደረገው ትንቢያ የቤንች ማጅ ዞን አስተዳደር (1998ዓ.ም.) ሰነድ በ1997 ዓ.ም. በዞኑ ውስጥ 462581 ህዝብ እንደሚገኝ ሲገመት፣ ፆታዊ ስብጥሩም ወንድ 231712 (50.09%) እና ሴት 230869 (49.91%) ነው፡፡ የህዝቡ አሰፋፈር 90.01% በገጠር እና 9.99% በከተሞች ነው፡፡

## 2.4 ኢኮኖሚ

በቤንች ወረዳ አስተዳደር (1998) ሰነድ መሠረት የወረዳው ህዝብ ብዛት 206171 ሲሆን ከዚህ ውስጥም 181872 በገጠር እና 24299 በከተሞች አካባቢ ይኖራል፡፡ የወረዳው የቆዳ ስፋት 180716 ሄክታር ነው፡፡ የመሬት አቀማመጡም 70% ተዳፋትና 30% ገደላማ ነው፡፡ የአየር ንብረቱም 28% ደጋ፣ 65% ወይናደጋና 7% ቆላ ሲሆን ዓመታዊ የዝናብ መጠኑ 1000-1454 ሲ.ሲ. ነው፡፡

የቤንች ብሄረሰብ ኢኮኖሚ የተመሰረተው በግብርና ላይ በመሆኑ የብሄረሰቡ አባላት በሰብል ምርት፣ የስራስር ተክል፣ አትክልት፣ ቡና፣ ጫት፣ ሙዝ፣ ትንባሆ፣ ከብት ርባታ፣ ንብ ማነብ እና ዕደጥበባት ናቸው ግርማይ (1993ዓ.ም)፡፡

በቤንች ወረዳ አስተዳደር (1996ዓ.ም) ዓመታዊ ሪፖርት መሰረት በዘመኑ ከወረዳው ጠቅላላ የቆዳ ስፋት ውስጥ በሄክታር፦ በቡና የተሸፈነው 31.4%፣ ሰው ሰራሽ ደን 5.5%፣ የተፈጥሮ ደን 10.6%፣ በቋጥቋጦ የተሸፈነ 1.17%፣ ግጦሽ 1.02%፣ ለእርሻ ስራ የዋለ 11.24%፤ ለእርሻ ስራ ሊውል የሚችል (ያልለማ) 6.83%፣ መንደር 13.61% እና ሊለማ ያልቻለ (ድንጋያማና ረግረጋማ) 17.39% ነው፡፡ በተጨማሪ በዚሁ ዘመን የተመዘገበው የእንስሳት ሀብት መጠን በቁጥር ጠቅሶ ይ¤ዉ የአስተዳደሩ ዘገባ እንዳመለከተዉ

- የዳልጋ ከብት (ላም፣ በሬ፣ ጥጃ) 109882
- በግ 28611
-. ፍየል9337
- ዶሮ 95618

- ፈረስ 2605
- በቅሎ 436
- አህያ 105 መሆናቸን ነው፡፡

## 2.5. መሰረተ ልማት

በቤንች ወረዳ 1996 ዓ.ም ዓመታዊ ሪፖርት መሰረት በዘመኑ በወረዳ ውስጥ ያሉት የመሰረተ ልማት ተቃሞች ይዞታም እንደሚከተለው ነው፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ትምህርት ቤቶች | ብዛት |
| ከ1-4 ክፍል | 43 |
| ከ5-8 ክፍል | 11 |
| ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ | 1 |
| በድምሩ | 55 ናቸው፡፡ |
| ለ. ክሊኒክ (የሰው) | |
| - ጤና ኬላ | 23 |
| - ክሊኒኮች | 8 |
| - ጤና ጣቢያ | 2 ሲሆኑ በድምሩ 33 ናቸው፡፡ |
| ክሊኒክ (የእንስሳት) | |
| - የእንስሳት ጤና ክሊኒክ | 3 |
| - የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ | 1 |
| - የቆዳና ሌጦ ማደራጃ | 2 |
| - የገጠር ቁራ | 1 |
| በድምሩ | 7 ናቸው፡፡ |
| ሐ. መንገድና ትራንስፖርት | |
| - ዋና ጠጠር መንገድ | 63 ኪ.ሜ. |
| - መለስተኛ የጠጠር መንገድ | 27.5 ኪ.ሜ. |
| - የበጋ መንገድ | 61 ኪ.ሜ. |
| በድምሩ | 151 ኪ.ሜ. ነው፡፡ |

## 2.6. ባህላዊ እምነት

የቤንች ብሄረሰብ ቀደም ካሉት ዘመናት ጀምሮ እስካለንበት ዘመን ድረስ የተለያዩ የአምልኮ ባህልና ልማዶች አሉት። ይህ መንፈሳዊ ህይወቱ አንድም ከራሱ የመነጨ ወይም በልዩልዩ የታሪክ፣ የባህልና የማህበራዊ ኑሮ ግንኙነት የተነሳ ከተለያዩ ብሄር/ብሄረሰቦች ጋር የመሰረተው ስሬ ተራክቦ ውጤቶች እንደሆነ Cerulli (1956)፣ Tippett (1970)፣ Nicolas (1976)፣ ኩንዲሳ (1988ዓ.ም) እና ግርማይ (1993ዓ.ም) ያመለክታሉ። የቤንች ብሄረሰብ ሚያንጎ እና ካህ የሚባሉ ሁለት ባህላዊ እምነቶች (ሃይማኖቶች) አሉት። በሁለቱም የብሄረሰቡ ባህላዊ እምነቶች/ሃይማኖቶች የዓለመዓለማቱ ፈጣሪ የሮ/የሮስንዶ ተብሎ ይጠራል።

### 2.6.1 ሚያንጎ

ሚያንጎ የቤንች ባህላዊ ሀይማኖት ነው። ይህንን መልስ የሰጡኝ በመስክ ቆይታዬ ያነጋገርኳቸው የዚሁ ባህላዊ ሀይማኖት ተከታይ የሆኑ ብቻ ሳይሆኑ በአሁኑ ወቅት ሌላ ሀይማኖትን የሚከተሉ ግለሰቦችም ናቸው። ስለ ሚያንጎ እምነት ሲያስረዱም፡-

እግዚአብሄር በዚህ ዓለም ላይ የሚገኙትን ነገሮች በሙሉ ፈጠረ። እነዚህ የ የሮ (ፈጣሪ) ፍጥረቶች በምድር፣ በሰማይ፣ በውሃ ወዘተ. ብቻ የሚኖሩ ሳይሆኑ የሰው ልጅ በዐይኑ ሊመለከታቸው የማይቻለውን መንፈሶች (spirit) ጭምር ነው። እነዚህን ሁሉ የፈጠረው የሮ ፍጡራኖቹን በመንፈስ እንዲመራና እንዲገስፅ የበላይነቱን ለሚያንጎ ሰጠው። ስለዚህም በሰው እና በየሮ መሀከል ያለው አገናኝ ሚያንጎ ነው።

(ቄስ ተገኝ ማርኩ)

"እኔ ሚያንጎ ነው ያለኝ። በግ[6] እበላለሁ። በባህላችን መሠረት ሀላፊነቴ በምድራችን አዝመራ. ጥሩ ምርት እንዲሰጥ፣ ላሞች እንዲረቡ፣ ንቦች ጥሩ ማር እንዲሰጡ፣ በሽታ በሀገር እንዳይገባ ፈጣሪያችንን መለመን ነው። በአጠቃላይ ሚያንጎ የአያት መንፈስ ነው። ማንግባብ (ባለሚያንጎ) ደግሞ ይኸው መንፈስ መርጦ ያደረበት ግለሰብ ነው። ተግባሩም በ ሚያንጎ መንፈስ አማካይነት የሮ (ፈጣሪን) መለመን ነው (ቤኑሽታቶ ጋይስ ጊሽቱናንስ)።

---

[6] በቤንች ባህል መሠረት ካህ ያላቸው ሰዎች በግ አይበሉም።

በተጨማሪም ሚያንንን አስመልክቶ ከተሰጡት አስተያቶች መሀከል፦ “ባለሚያንጎ የሮ የፈጠራቸውን በሙሉ ያዛል። ዝናብ ያስዘንባል ወይም ያስቆማል፤ ሌላው ቀርቶ ፀሃይን ማዘዝ ይችላል። በዚህ የተነሳ በብሄረሰቡ አባላት ብቻ ሳይሆን በሁሉም የአካባቢው ነዋሪዎች ጭምር ይከበራል። በሚያንጎ መንፈሳዊ ስርዓት በማንኛውም የሰው ልጅ ላይ ክፉ ተግባራትን መፈፀም በፍፁም የተከለከለ ነው። የሚያንጎ መንፈስ እጅግ ፍፁምነትን ስለሚጠይቅ በአብዛኛው ሰው ዘንድ ይፈራልም (ባብ ኤደን ሽፈራው ካርጉ)ለ።

Nicolas (1976) የቤንች ባህላዊ ሀይማኖቶችን አስመልክቶ ባደረገው ጥናት ሚያንጎ ሁለት ምድቦች ወይም አይነቶች አሉት። እነርሱም በብሄረሰቡ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ህይወት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የነበራቸው ቤንችቴት/ ቤንቻቲያት እና በተራው ህዝብ (common people) ላይ የሚያድሩ መንፈሶች ናቸው። በተጨማሪምኩንዲሳ (1988:29ዓ.ም) ይህንኑ የ ሚያንጎ ሀይማኖት መንፈሳዊ አሰራር እንዴትነትን በተመለከተም ገልጿል። ይሁን እንጂ ይህን መሰሉ ተዋረዳዊ ግንኙነት (ቀደም ባሉት ዘመናት በባላባትና በተራው ህዝብ መሀከል ብቻ ሳይሆን) በአንፃራዊነትም በሁለቱ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ባሉ አባሎች መሀከልም ያለ መሆኑ ተመልክቷል።

ዩቤንች ሚያንጎ እምነት በብሄረሰቡ መንፈሳዊና ስጋዊ ህይወት ውስጥ ወሳኝ ሚና ስለነበረው ወቅትን ባገናዘበ መልኩ በአመት ውስጥ ሁለት ጊዜ የሚከበር በዓል ነበረው። ይኸውም በቆሎ ሲያሽት (ዲችቲሽ) እና ግራዋ ሲያብብ (ዧምፓም) ነበር።

ዓመታዊ የሚያንጎ በዓል አከባበር ሰፊ ሂደት ያለው ሲሆን በክዋኔው አይቀሬ ናቸው የሚባሉ ጉዳዮችን ባካተተ መልኩ እንደሚከበር የሚከተለውን አባ ማትዮስ ሻሽንቴት (ዕድሜ 50፣ ጌሲት ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪ) የነገሩኝ ናቸዉ።

ባለሚያንጎ ዓመታዊ የሚያንጎ በዓል ሲቃረብ ከምግብ (በተለይም ስጋ) እና መጠጥ (ጠጅ) ይቆጠባል። ቀጥሎም ወይዜስ (ካዳሚው) እና በዚህ ከበራ ላይ ሊገኙ ዘንድ የሚፈቀድላቸው ሰዎች ከከበራው አራት ቀናት ቀደም ብሎ ከግብረስጋ ግንኙነት እንዲታቀቡ ይነገራቸዋል። የሚያንጎ በዓል ሲቃረብም ባለሚያንጎ (ሚያንግባብ) ወደ ኮብቲም (የሚያንጎ መስዋእትነት ማቅረቢያ) ኬት (ቤት) ይገባል። ቀጥሎም ካርሽን (እናት ላም በተለይም ጥቁር) ፀሃይ ሲጠልቅ ለሚያንጎ መስዋእትነት ትቀርባለች። በዚህን ጊዜ “እምቧ!” የሚል ድምፅ ካሰማች መስዋዕቱ ተቀባይነት አግኝቷል ማለት ነው። ቀጥሎም ላሚቱ ትገፈፍና ከላሚቷ ልዩ ልዩ ብልቶች የተቀነጣጠበ ስጋ ጌን

(የባለሚያንን የመጀመሪያ ሚስቱና) ወይዜስ (ካዳሚ) አማካይነት ተጠብሶ በኮይቲ (የሚያንን መስዋእትነት ማቅረቢያ ሲሆን ከእንጨት የሚሰራ ነው) ይደረግና የባለሚያንንው ቤተሰቦች ባሉበት ይቀርባል፡፡ የዚህን ጊዜ ባለሚያንንው ወደ ውጭ ይወጣል፡፡ ከዚያም የተጠበሰውን የመስዋዕት ስጋ ዳንዝ (አጋፋሪ) በጥንቃቄ እንዳይወድቅ ይዞ ይወጣና ለባለሚያንንው የመስዋዕቱን ስጋ ያቀብላል፡፡ እርሱም ፊቱን ወደ ምዕራብ አዙሮ ስለህዝቡ የሮ (ፈጣሪን) ይለምናል፡፡ በመጨረሻም ከያዘው የመስዋዕት ስጋ ይቀምስና ለዳንዝ (አጋፋሪ) ቀጥሎም ለጌን (ባለቤቱ) ይሰጣል፡፡ (20-03-1999 ዓ.ም.)

በተጨማሪ አባ ማትዮስ ሻሽንቴት እንደገለፁልኝ "ይኸን መሰሉ የሚያንን መስዋዕት ሂደት ከጌን (ሚስት) ውጭ አይታሰብም ወይም ሚስቱን አባብሎ የሚያነሳ መስዋዕቱን ለማቅረብ ቢሞክር ውጤቱ ለባለሚያንንው ሞት ይሆናል"፡፡

ባለሚያንንው ከመስዋዕቱ ስርዓት መጨረሻ ላይ ስለህዝቡ ለፈጣሪ የሚያቀርበው ምልጃ የሚከተለው ነው፡፡

ሚያንን፡-

- ሀገሩ ልምላሜን ይልበስ፣
- የተዘራው እህል ጥሩ ምርት ይስጥ፣
- ከብቶች ይርቡ፣
- ጤና በሀገሩ ይብዛ፣
- በቀፎዎች ማር ይብዛ ... እያለ ሚያንንውን ይማልዳል፤ ህዝቡንም ይመርቃል፡፡

የቤንች ባህላዊ እምነት ሚያንንን አስመልክቶ ከቀረቡት ልዩ ልዩ አስተያየቶች መሠረት የባህላዊ እምነቱ አስተምህሮ[7] ማጠንጠኛ ናቸው የሚባሉት እሳቤዎች (concepts) የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሚያንን፡- አንድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በየዘመኑ የተነሱትን ቤንችቴት እና ቤንችቲያት ስም ይዞ ሊጠራ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- የገፐገፐቴት ሚያንን፣ የቤንችቴት ሚያንን፣ የሜርቴት ሚያንን፣ የኮርጅቴት ሚያንን ... በመባል፡፡ በማንም ሰው ስም ሊጠራም ይችላል፡፡

---

[7] አስተምህሮ አንድ የተወሰነ የእውቀት ዘርፍ በውስጡ የያዛቸውን መሰረታዊ ሀሳቦች ወይም ትምህርታዊ ይዘቶች ባጭሩ ይገልጻል፡፡ ማለትም የመርህ ወይም የእምነት ስርዓት (ቀኖና)ን የሚገልጽ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ (ማርክሳዊ ሌኒናዊ መዝገበ ቃላት፣ 1978፣277)፡፡

- የ "አካስ" (የአያት) መንፈስ ነው። ስለዚህም የቀደመውን ትውልድ ከተተኪው ጋር ያስተሳስራል፤ ሆኖም ትስስሩ ቤተሰባዊ (lineage) ነው።
- ፈለጉ ሁል ጊዜ ከአባት ወደ አንጋፋ (መጀመሪያ) ልጅ ነው። ሆኖም በቤተሰብ ውስጥ አንጋፋ ልጅ ከሌላ ቶፅማን (አዋቂ) ከቤተሰቡ ውስጥ ማን ባለሚያንጎ (ማንግባብ) ሊሆን እንደሚችል ይናገራል። ሆኖም ሴት ልጅ ባለሚያንጎ አትሆንም።
- ሁሉም ሰው ሚያንጎ (አያት መንፈስ) አለው። ይሁን እንጂ ሚያንጎ ሁሉ እኩል ሀይል የለውም። ስለዚህም አንድ ሰው የራሱን ሚያንጎ በመተው ጠንካራውን መርጦ በምርጫው ሊከተል ይችላል። ለምሳሌ የቤንችቴት ሚያንጎ ገዥው (dominant) ስለሆነ እንደጥላ ሁሉንም በስሩ ሊያሰባስብ ይችላል።

በአጠቃላይ የቤንች ሚያንጎ እምነት የትውልድ ህልውና የሚጠበቅበት እና የሚታደስበት ነው። ስለዚህም የቀደሙት ትውልዶችና ተተኪያቸው (አዲሱ) መሀከል ያለው ተራክቦ (interaction) እውነነት የሚረጋገጠው በሚያንጎ ብቻ ተብሎ ይታመናል። ለዚህ መሰሉ ተግባር ስኬታማነት ባለሚያንጎው (ማንግባብ) ወሳኝ ሀላፊነት አለበት። ሆኖም ለባለሚያንጎነት ምርጫው በኩርናን የመስፈርቱ ሁሉ መጀመሪያ ያደርጋል። ግቡም በቤንችዶድ ብልጽግና፣ ሰላም፣ ምህረት፣ ፍቅር፣ መቻቻል፣ ቸርነትና እውነትን በማስፈን በ አካስ (አያት) የሚመስለው የቀደመው ትውልድ በተከታዩ (አዲሱ) ውስጥ ህያውነቱን ማስረጽ ነው። በዚህ የተነሳም የሚያንጎ እምነት በብሄረሰቡ ፈርጀ ብዙ ህይወት ውስጥ ወሳኝነት ነበረው። ይከብራል። ይፈራም ነበር።

### 2.6.2 ካህ

ካህ - የቃልቻ መንፈስ ሲሆን ካህናንሳ - ባለቃልቻ (መንፈስ-ያደረበት ሰው) ነው።

የካህ (ቃልቻ) እምነት የቤንች ባህላዊ እምነት አንዱ ዘርፍ መሆኑን Nicolas (1976:175)፣ Tippett (1970:184) ይገልፃሉ። እንደኩንዲሳ (1988:30ዓ.ም) ገለፃ ሁሉ በመስክ ጥናቱ ወቅት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ያነጋገርኳቸው መረጃ አቀባዮቼ በሙሉ ያረጋገጡልኝ የካህ (የቃልቻ) እምነት መሰረቱ ቤንች አይደለም። የቤንች ብሄረሰብ በተለያዩ ታሪካዊ አጋጣሚዎች በአጎራባቻነት ከሚቀርቡት ልዩ ልዩ ብሄረሰቦች ጋር ባህል-ማህበራዊ ግንኙነት ሊመሰርት ችሏል። በዚህም መሠረት (ከአጎራባቹ) የከፋ ብሄረሰብ ጋር በነበረው

ታሪካዊ ግንኙነት የተነሳ የካህ እምነትን እንደተቀበለ ይነገራል፡፡ ይህን መሰሉ ግንኙነት በሁለቱ ተጎራባች ብሄረሰቦች መሀከል ብቻ የተፈፀመ እንዳልሆነ "Kah" የሚለው ቃል ልዩ ልዩ ስነልሳናዊ ቅርፆችን በማውጣት ድርጊቱ በሌሎች የአካባቢው ተጎራባች ብሄረሰቦች በ "Sheko (maji), Nao, Kafa, Chara, Majangir" መሀከል መፈፀሙና ይህን መሰሉ ልሳነ-ባህላዊ (Linguistic-Cultural) ግንኙነት የሚያሳየው የካህ እምነት በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ ስር የሰደደ መንፈሳዊ ዳራ እንደነበረው ያመለክታል በማለት Nicolas (1976:177) ይገልፃል፡፡

የካህ (ቃልቻ) እምነት መሰረቱ የመንፈስ ባለቤትነት (Spirit Possessing) ነው፡፡ ስለዚህም መንፈሱ በማንኛውም የሰው ልጅ ላይ ሊያድር ይችላል፡፡ ከዚህ የተነሳም አንድ ግለሰብ ከአንድ በላይ የቃልቻ መንፈሶች ሊያድሩበት ወይም አንድ አይነት የቃልቻ መንፈስ በተለያዩ ሰዎች ላይ ሊሰፍር ይችላል፡፡

ቄስ ተገኝ ማርኩ የካህ ባህላዊ እምነት እንዴት በቤንች ብሄረሰብ ዘንድ እነደተስፋፋ ጠይቄያቸው የሰጡኝ መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

> ቀደም ባሉት ዓመታት የገረመንዶ ቃልቻ ዓመታዊ ክበራ ከፋ ሀገር ውስጥ ጫራ በሚባል አካባቢ ቦታ ፖዳሹሩንስ (ነጭ ዋርካ) ስር ይከበር ነበር፡፡ በዚህ የገረመንዶ ቃልቻ በዓል ላይ ለመገኘት ከዚህ ከኛ አካባቢ (ቤንች) የሚሄዱ ሰዎች ነበሩ፡፡ በዚህ የተነሳም ብዙዎቹ የብሄረሰቡ አባላት የካህ መንፈስ አድሮባቸው ካህናንስ ሆነው እንደተመለሱ በልጅነቴ በቤተሰቦቼ አካባቢ ሲነገር ሰምቻለሁ፡፡ ለምሳሌ ያህል ባንድ ወቅት አሽ የሚባለው የካህ መንፈስ በቤንች ሀገር ገዥ የቃልቻ መንፈስ ሆኖ ስለነበር ሰው "አሽቶጥ" (አሽ ይግደለኝ) ማለትን አዘውትሮ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ ልምድ ሆኖ ዛሬ ማንኛውም የቤንች ቋንቋ ተናጋሪ በሆነ ሰው ላይ ችግር/አደጋ ደርሶበት ሲያይ በቅድሚያ "አሽቶጥ" ይላል (9/03/99 ዓ.ም፣ ሚዛን ከተማ፣ 02 ቀበሌ)፡፡

በ Tippett (1970፡185) እና ኩንደሳ (1988ዓ.ም) ዘገባ መሠረት የካህ ባህላዊ እምነት የሚከተሉት አጠቃላይ ገጽታዎች ይንፀባረቅበታል፡፡ በካህ (ቃልቻዎች) መሀከል ተዋረዳዊ ግንኙነት ስላለ አንዱ ሌላውን ያከብራል፡፡ ሁለተኛ ሁሉም ቃልቻ የራሱ ግዛት (territory) አለው፡፡ ስለዚህም በአንድ አካባቢ ገዥ የሚሆነው ካህ አካባቢውን ለቆ ወደ ሌላ

የካህ ግዛት ሄዶ መኖር ይችላል። ሶስተኛ የመፈወስ፣ መሀንን የማስወለድ፣ የጠፋን የማስገኘትና መሰል ተግባሮች በህብረተሰቡ ህይወት ውስጥ ያከናዉናል ተብሎ ስለሚታመን በስለትነት የሚቀርብለት ነገር አለው። ይህም ከሰው (አገልጋይ) ጀምሮ ቁሳቁስ ሊሆን ይችላል። አራተኛ በዓመታዊ ከበራ ፃብዛኛው የክርስቲያን ገና (ልደት) ወይንም ፋሲካ ዕለት ለመስዋዕት የሚቀርበው ባብዛኛው "ሀሳቤ ተሟላልኝ" ያለ አማኙ ያቀረበውን የስለት ክብት ስለሆነ ለመስዋዕት የሚታረደውን ክብት ስጋ ማንም ሰው ይበላል። ወይም እንደሚያንጎ የተወሰኑ ሰዎች ብቻ የሚቋደሱት አይደለም። ለዚህ ጥናት ያመች ዘንድ ብሎም የተነሱት የብሄረሰቡ መንፈሳዊ እሴቶች እንዲጎሉ ይረዳል በሚል ልዩ ልዩ ማህበረ-ባህላዊ ተቋማቱ በተናጠል ቀርበዋል። ይሁን እንጂ በሁለቱ መንፈሳዊ ተቋማት መሀከል በዘመናት የተፈጠረ ትስስር አለ። ይህ ትስስር ይፋ ከሚሆንባቸው አጋጣሚዎች አንዱ የሚያንጎ በዓል አከባበር ነው።

ካህ እውነት የሆነ ሀሳብ ያቀርባል። ለምሳሌ ያህል ሚያንጎ በዓል መስዋዕት የቀረበች እናት ላም (ካርሽን) በባህላዊ ልማድ መሠረት መስዋዕት ስትሆን የምታሰማው "እንቧ" የሚል ድምፅ አለ። ድምፁ በዋንኛነት የቀረበው መስዋዕት በሚያንጎ ፊት ተቀባይነት የማግኘቱ ማስረጃ ነው። ሆኖም ይህን መሰሉ ድርጊት ካልተከወነ የአያት መንፈሱ "ቅሬታ አድርበታል" ይባላል። የዚህ ቅሬታ ምንነት ብሎም መፍትሄው የሚጠየቀው ከካህ ነው። ስለዚህም በአካባቢው ያለ ገዥ ካህ (ለምሳሌ በደቡብ ቤንች አካባቢ የሻምቴትንዶ) መንፈስ ይጠየቃል። እሱም ይናገራል። በዚሁ መሰረት ባለሚያንጎው ይፈፅማል። መስዋዕቱም ተቀባይነትን ያገኛል።

የሚያንጎና የካህ ግንኙነትም በዚህ የጥናቱ ንዑስ ክፍል መጀመሪያ እንደተገለፀው በቤንችዶድ ያለውን ሁሉም ነገር በሚያንጎ ስር አድርጓልና በምድራቱ የሚከናወነው መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ ጉዳይ ሁሉ በርሱ ፈቃድ የሆነ ነው።

## ፪.፯. ጋቢቻ

በቤንች ብሄረሰብ ውስጥ ከፍተኛው ባህላዊና ማህበራዊ ቦታ ከሚሰጣቸው ማህበራዊ ጉዳዮች መሀከል ጋብቻ አንዱ ነው። ይህንን አስመልክቶ ባብ ሲግ የተናገሩት ጥንት የሮ (አምላክ) መጀመሪያ ላ የፈጠረዉ ሰት ሰዎችን ብቻ ነዉ። አብረዉ እየኖሩ ሳለ ...መሀከል ፍቅር ገባ ቀጥሎም ተጋቡና...!! በማለት ነዉ።

በቤንች ብሄረሰብ ዘንድ ልዩ ልዩ የጋብቻ አይነቶች አሉ። ሆኖም የትኛውም አይነት ጋብቻ ከተፈፀመ በኋላ ወንዱ ሴቷን ወደ እርሱ ዘመዶች መኖሪያ ሰፈር/ጎጥ ይዟት ይሄዳል። ወይም ከሚስቱ ዘመዶች ጋር አብሮ አይኖርም። ይህን መሰሉ የጋብቻ አካሄድ "ባልከተል" (Patrilocal residende) በመባል ይታወቃል። በተጨማሪም በቤንች ብሄረሰብ ባህል መሠረት ባል የሚስቱን እናት (አማቱ) በተገናኙበት ቦታ ሁሉ ሲያይ ይሸሻል።

በቤንች ብሄረሰብ ውስጥ አራት የጋብቻ አይነቶች ያሉ ሲሆን አፈፃፀማቸውም ለየቅል ነው። በብሄረሰቡ ዘንድ የሚታወቁ አራቱ የጋብቻ አይነቶች፡- የመጀመሪያው፡- ጌርስታ የሚባል ሲሆን በልጁና በልጅቷ ቤተሰቦች ስምምነት መሰረት የሚፈፀም የጋብቻ አይነት ነው። ሁለተኛው ጋሪሳካ ይባላል። ወንዱ ለሚስትነት የሚፈልጋትን ልጅ አባብሎ ይሁንታዋን ካገኘ ብቻ የሚከናወን ነው። ሶስተኛው ጉቻ ሲባል በጠለፋ (ከልጅቷ ፍላጎት ውጭ) ይከናወናል። የመጨረሻው ባርዝ በመባል የሚታወቀው የውርስ ጋብቻ ነው። በዚህም አንድ አባወራ ሲሞት ከወንድሞቹ መሀከል አንዱ (ታናሽ ወይም ታላቅ የማቹን ሚስት ያገባል። ታናሽ ወይም ታላቅ ወንድም ከሌለ የእኅት ልጅ፣ እርሱም ከሌለ የዘር ሃረግ ተቆጥሮ የወርስ ጋብቻው ይፈጸማል። ወራሹም የሚፈጽማቸው ናህላዊ ግዴታዎች አሉ (ኩንዲሳ 1988ዓ.ም)።

በቤንች ብሄረሰብ ዘንድ ጋብቻ ጥብቅ የሆነ ባህላዊ ህግጋት ውስጥ የሚያልፍ በመሆኑ የዘር ግንድ ቆጠራ ከፍተኛ ቦታ አለው። Nicolas 1976 እና ኩንዲሳ 1988 እንደገለፁት በቤንች ጎሳዎች መሀከል የሚፈፀመው ጋብቻ ይህንኑ መሠረት ያደረገ ነው። ከዚህም በላይ በብሄረሰቡ ባህል መሠረት በቤተዘመድ መሀከል ጋብቻ ስለሚከለከል በአንድ ጉሳ ውስጥ ያሉና ተመሳሳይ የቤተሰብ ሐረግ ያላቸው አይጋቡም። በብሄረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው ናቸው ከሚባሉት ጉዳዮች መሀከል አንዱ በጋብቻ ላይ የሚፈፀም አመንዝራነት ሲሆን ውጤቱም በብሄረሰቡ ላይ ከፍተኛ ጥፋት ያደርሳል/ያመጣል የሚል እምነት አለ።

ከአራቱ የጋብቻ አይነቶች መሀከል ጋሪሰካ (ማባበል) የሚባለው በአሁኑ ወቅት በስፋት እየተፈፀመ መሆኑን በመስክ ቆይታዬ ሲነገር ሰምቻለሁ። ይህ አይነቱ ጋብቻ የሚፈፀመው በሴቷ ፍቃድ መሆኑን ከፍ ብዬ ያመለከትኩ ቢሆንም ሂደቱ ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል።

አንድ የቤንች ወጣት በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ለምሳሌ የገበያ ቀናት፣ የሰርግ ጭፈራ፣ ሀዘን (ለቅሶ)፣ ትምህርት ቤት ... በመሳሰሉት ቀልቡን የሳበች ኮረዳ ሲያጋጥመው እና ለማግባት ከወሰነ ስለልጅቷ ቤተሰብ ማንነት ያጠናል።

በመጨረሻም መጋባት የሚችሉ መሆኑን ሲያረጋግጥ በጣም ለሚቀርበው ጓደኛው ወይንም የቅርብ ዘመድ በተለይም ልጅቷን የሚቀርባትን (በሰፈር ...) ፈልጎ ሚስጢሩን ይነግረዋል። በርሱም አማካይነት የፈለጋትን ልጅ ካገኘና ሀሳቡን ከገለፀላት በኋላ የእርሷን ሀሳብ እንድትገልፀለት ይጠይቃታል። ከልጅቷ በኩል የሚሰጠው መልስ "ተደጋጋሚ ቀጠሮ ያለበት ስለሚሆን ትዕግስትን ይጠይቃል።" ሆኖም ልጅቷ እንደርሱ እርሷም ለትዳር የፈለጋትን ጎረምሳ ቤተሰብ ካጠናች በኋላ ፍቃዷን ትገልፃለች። ይህ ፍቃደኝነቷን ጉሽ (የእጅ አንባር) ካለ አንዱን፣ ከሌለ ደግሞ ከአንገት ጨሌዋ አንዱን ዘለላ በጥሳ ታጠልቅለታለች። (አበበች ሽፈራው)

በዚህ መልክ ከጨረሱ በኋላ የሚያመቻቸውን ጊዜ (ከቤተሰብ እውቂያ ውጭ) ጠብቀው ልጁ ይዟት ወደ ቤቱ ይሄዳል። ጥንት ይኸን መሰሉ ጋብቻ እየተለመደ እንዲመጣ ካደረጉት ምክንያቶች ዋናው (ባሬም በመጠኑ እንደሚታየው) የልጅቷ ቤተሰብ የሚጠይቀው ከፍተኛ ጥሎሽ እንደሆነ ይነገራል።

## 2.8. የለቅሶና የቀብር ስርዓት

በቤንች ብሄረሰብ ባህል መሰረት የለቅሶና የቀብር ስርዐት የሚከናወነው የሟቹን ግለሰብ ባህላዊና ማህበራዊ ከበሬታ እና እድሜን በማገናዘብ ነው። በመሆኑም በብሄረሰቡ ዘንድ የሚታወቁትን የለቅሶና የቀብር ስርአቶች እንደሚከተለው ከፋፍሎ ማየት ይቻላል በማለት ደብብህክ ማስታወቂያ ቢሮ(1998) እና ኩንዲሳ (1988፣20-23) ይገልፃሉ።

የመጀመሪያው በቤንች ባህል መሰረት ከፍተኛ ከበሬታ የሚሰጣቸው ታዋቂ ሰዎች/ግለሰቦች ( ባላባቶች፣ ቃልቻዎችና ባለሚያገጊዎች) ሲሞቱ የሚከናወነው የለቅሶና የቀብር ሥርዓት ነው። በመሆኑም አንድ ባላባት ወይም ባለቃልቻ በህመም ወይንም በደረሰበት አደጋ ምክንያት በሚያሸልብበት ጊዜ የሚጠብቀውን ቃልቻ (ካይ ካይ ቀንብ) በቤቱ ተገኝተው ይጠብቁታል። ነፍሱ እንደወጣችም ከዳሚዎቹ (ቆንብ) ሟቹ አንገት ላይ የሚታሰረውን የቃልቻ ጨሌ ( ካህ ኩል)፣ ጥፍሩን እና ፀጉሩን ነቅለው በመውሰድ እቃልቻው ቤትውስጥ ያስቀምጡታል። ይህ ሄደት በሚከናወንበት ጊዜ ከአካዳሚዎቹ በስተቀር ማንም አያውቅም።

ቀጥሎም የሟቹ ቅጥር ጊቢ በስርዓት ፀድቶ፣ የፈረስ አጥር ካለም ከተጠገነ በኋላ ቤተሰብና ዘመድ አዝማድ የሟቹ ግለሰብ ህይወት ማለፍ ይነገራል። ዘመድ አዝማድም ከተሰበሰበ በኋላ በሟቹ ታላቅ ወንድም ወይም በአጎቱ አማካኝነት የሚተካውን ሰው ውቃቢው እንዲመርጥ ይለመናል። በመጨረሻም ከቤተሰቡ መሀከል አንዱ በቃልቻው መመረጡ (መንፈሱ የወረደበት ሰው ያጓራል) እንደታወቀ የሟቹ የቀብር ስርዓት ይፈፀማል። ቀጥሎም ከሟቹ ላይ የተወሰዱት ጨሌ፣አንባርና ሌሎች እቃዎች ለወራሹ ወይም ሟቹን እንዲተካው በቃልቻው ለተመረጠው ግለሰብ ይበረከታል። የማዕረግ ስምም ይሰጠዋል። በመጨረሻም የሟች ቤተሰቦች በመወያየት ቀን ይወስኑና (ቢያንስ አንድ ወር) የለቅሶ ቀጠሮ ይያዛል። በዚህም አካባቢው ሆነ በርቀት የሚኖሩ ሰዎች መጥተው ለሟቹ ሀዘናቸውን እንዲገልፁ (እንዲያለቅሱ ) ይደረጋል።

ሁለተኛው የለቅሶና የቀብር ስርዐት አይነት አዋቂዎች (ጎልማሶች) ሲሞቱ የሚፈፀመው ነው። ይህም አንድ አዋቂ (ጎልማሳ) የሆነ ሰው ሲሞት (ነፍሱ እንደወጣች) ወዲያውኑ ሟቹ በህይወቱ እያለ የሚያጌጥባቸው እቃዎቹና ልብሶቹ በሙሉ ይወጡና ይለቀስባቸውል። በመጨረሻም የሟቹ ዘመዶች በሙሉ ይሰባሰቡና ከበሮ እየተመታ ጦር እየተሰበቀ ከተለቀሰለት በኋላ ሬሳው በተዘጋጀለት መቃብር ውስጥ ያርፋል። ከቀብሩ በኋላም ዘመድ አዝማድበሙሉ ሟቹ ቤት ይሰበሰብና ለሰባትና (ከዚያም በላይ ለሆኑ) ቀናት ከበሮ እየተመት ቃጭል እየተንቃጨለ ይለቀሳል።

ሶስተኛው የለቅሶና የቀብር አይነት ህፃናትና ወጣቶች ሲሞቱ የሚከናወነው ነው። በዚህም የሞተው ወጣት ከሆነ ለሳምንት ያህል ቤተዘመድ ተሰባስቦ ይለቀሳል። በሶስተኛው ወር ላይ ሟቹ በህይወቱ እያለ የሚጠቀምባቸው ልብሶች በሙሉ ተወስደው መቃብሩ ላይ ይጣላሉ። በሌላ መልኩ የሞተው ህፃን ልጅ (በተለይ ከአንድ አመት በታች ) ከሆነ ቶህና ፉርግን የሚባሉ ባህላዊ ጡሩንባዎች እየተነፉ ይለቀሳል። በመጨረሻም ህፃኑ በሞተ በሦስት ወይም በአራተኛው ቀን ላይ ዘመድ አዝማድ የሟቹን ህፃን ጨርቅና የወተት መጠጫ ቀንድ ይዘው በማልቀስ እናትና አባቱን ‹‹ ጌታ ይተካላችሁ ›› እያሉ በመሰናበት ወደየቤታቸው ይሄዳሉ።

## 2.9. ባህላዊ አስተዳደር

የቤንች ብሄረሰብ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት የፖለቲካ፣ አስተዳደርና ዳኝነት ባህላዊ ተቋማት እንደነበሩት Ceruli (1956:91-92)፣ Perham (1969)፣ Wallis

(1966:627) እና የመሳሰሉት ፀሐፍት ገልፀዋል። ይሁን እንጂ እነዚህ የአስተዳደር ተቋማቱ ከ1898 (እ.ኤ.አ.) ጀምሮ እየከሰሙ መምጣታቸውንና ይህ ሂደትም በ1937/38 ዓ.ም. ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ ሲሆን ዋንኛው ምክንያቱም እንደ ባህሩ (1991)፣ በአፄ ምኒሊክ የተጀመረው የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት ምስረታ ነዉ። ይህ ከሰሜን ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ የተደረገው ፈርጀ ብዙ እንቅስቃሴ ነው። መልክአምድራዊ ብቻ አልነበረም።

የቤንች ባህላዊ አስተዳደር እንደ ደቡብ ክልል ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ (1998ዓ.ም) የቤንች ባህላዊ አስተዳደር ሻምቴታል በሚል መጠሪያ የሚታወቁ ነገስታት ስር የሚተዳደር፣ ስድስት የአካባቢ ቤንችቲያት ባላባቶች (ቤንችትያት) እና በርካታ ቤንች ኡክርስ (የቀበሌ/ጎጥ) አስተዳደሪዎች ያሉት ነበር።

ይህ የቤንች ባህላዊ አስተዳደር በአደረጃጀቱ ተዋረዳዊ ግንኙነት ያላቸው ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን ያለው ቤንችቴት (ንጉስ ነገስቱ) ጋ ነው። ቀጣዩ እርከን ቤንችቲያት የሚባሉና የአካባቢ መሪዎች/ባላባቶች ጋ ነው። እነዚህ ሁለት እርከኖች ላይ የሚቀመጡት (ቤንችቴት/ቤንችቲያት) አመራረጥ የጎሳ መሰረት ያለው ስለሆነ Nicolas (1976) ይህን የባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር አደረጃጀቱን ጎሳዊ ስርወ መንግስት (Tribal Dynasty) በማለት ይገልፀዋል።

ቤንችቴት (የቤንች ንጉስ ነገስት) ቀደም ባሉት ዘመናት ውስጥ የቤንች ብሄረሰብ አባላትን በአንድ ላይ አስተባብሮ በመምራት ረገድ ከፍተኛ ሚና ነበረው። በመስክ ቆይታዬ ያነጋገርኳቸው ታዋቂ ሽማግሌዎች መሀከል አንዱ የገለፀልኝ የሚከተለው ነው።

> ቤንችቴት - መሪ ብቻ ሳይሆን የብሄረሰቡ አንድነት ተጠብቆ፣ የወንድማማችነት መንፈስ ተጠናክሮ እንዲቀጥል አድርጓል። ስለህዝቡ ሰላም፣ መሬት ጥሩ ምርት እንዲሰጥ፣ ከብቶች እንዲረቡ፣ ንቦች ጥሩ ማር እንዲሰሩ፣ በሽታ በሀገር ገብቶ ህዝብ እንዳይጨርስ ... ሲል ሁል ጊዜ በአምላካችን እና በህዝቡ ፊት በትጋት ይቆማል። (ባብ ቤላ፣ 27/03/1999 ዓ.ም ዳቻባለ ቀበሌ)።

በቤንች ባህላዊ የአስተዳደርና የፍርድ ስርዓት ውስጥ በህዝቡ ህይወት ላይ ወሳኝ ሚና እንደነበረው የሚገለፀው ቤንችቴት[8] አመራረጥ ሂደት ወሳኝ የሆነውን አካል ማንነት

[8] ቤንችቴት በባህላዊ የቤንች ብሄረሰብ የአስተዳደርና ዳኝነት መዋቅር የውስጥ ንጉስ ነገስትና ቀደም ሲል ለነበሩት ስድስት ባላባቶች የበላይ ነው።

በተመለከተ አንድ ወጥ አስተያየት የለም። ሆኖም የቤንችቴት አመራረጥን በተመለከተ ወሳኝ የሆነው አካል እንደ Girmaye (1988ዓ.ም) የሚያንጎ መንፈስ ነው፣ Nicolas (1976) የቤተሰብ ዘር ሀረግ እና የሚያንጎ መንፈስ ናቸው የሚሉ ሁለት ዋንኛ ሀሳቦች ቀርበዋል።

ይሁን እንጂ በመስክ ጥናቴ ወቅት ቄስ ተገኝ ማርኮ የነገሩኝ "በቤንችቴት አመራረጥ ረገድ በዳንዝ (የሀገር ሽማግሌዎች)፣ ወይዜሰ (የንጉሱ ካዳሚ) እና ቶጽማስ (አዋቂዎች)ን የመሳሰሉት በተለየ መልኩ አስተዋጽኦ ቢኖራቸውም አንድ ቤንችቴት (የቤንች ንጉስ) ሲሞት የተተኪው ማንነት የሚታወቀው በሚያንጎ (የአያት መንፈስ) ምሪት አማካኝነት ነው። በዚህ አይነት ባህላዊ ስልት የሚመረጠው ቤንችቴት ለንግስናው በሚዘጋጀው የዋሻ በዓል (ክብረበዓል) ህዝብ በተሰበሰበበት አደባባይ ቦቅ (ቅብዐንጉስ) ይቀባና ቤንችቴት (ንጉስ) ይሆናል።" በማለት ነበር።

የቤንች ብሄረሰብ እንደአብዛኞቹ የሀገራችን ህዝቦች ሰፊ የጎሳ መዋቅር እንዳለው Nicolas (1976) እናኩንዲሳ (1988 ዓ.ም) ይገልፃሉ። በዚህ የተነሳ የቤንችቴት ማንነትን በተመለከተ ለሚነሱ ጥያቄዎች የሚሰጡት መልሶችን ስንመለከት ተመሳሳይነት የላቸውም። ባብ አሸኩ ባንገርስ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ እንደተናገሩት፡-

| | | |
|---|---|---|
| "ገፕገፕቴት | - ባይኬስ!" | "ገፕገፕቴት ባይኬስ ነው!" |
| "ሜርቴት | - ባይኬስ!" | "ሜርቴት ባይኬስ ነው!" |
| "ቤንችቴት | - ባይኬስ!" | "ቤንችቴት ባይኬስ ነው!" |

የሚል አጠቃሳይነት ያለው እና በቤንች ብሄረሰብ ውስጥ ከሚገኙ በርካታ ጎሳዎች (clans) መሀከል አንዱ የሆነውን የባይኬስ ጎሳ በመጥቀስ ነው። በእርግጥ ይህንን አይነት መልስ በአሁኑ ወቅት አብዛኛው የአካባቢው ነዋሪ የሚሰጠው ነው።

በሌላ መልኩ ሲታይ ደግሞ ይህንን ቤንችቴት ከአንድ ጎሳ ብቻ ይመረጣል የሚለዉን አባባል የማይቀበሉ የብሄረሰቡ ተወላጆች አሉ። ለምሳሌ ቄስ ተገኝ ማርኮ የተናገሩት፡- "እኔን ውሰድ ቤንች ነኝ። በባህላችን መሠረት የባይኬስ ጎሳም ነኝ። እንደ ድሮ አገላለጽ የባላባት ልጅ ነኝ። ይሁን እንጂ ከእኔ የጎሳ ሐረግ ቤንቼትት አይመረጥም! ባህላችን ስለሆነ" በማለት ሁሉም የባይኬስ ጎሳ አባል ወይም በዚሁ ጎሳ ስር የሚገኙ ልዩ ልዩ ነገዶች

---

<u>ቤንችቲያት</u> በስድስት የአካባቢ አስተዳደሮች ተከፋፍሎ ይተዳደር ለነበረው የቤንች ህዝብ አካባቢያዊ ንጉሶች/ባላባቶች ይመለከታል።

(Tribes) በብሄረሰቡ በህል መሰረት ቤንችቴት ሆነዉ ሊ.መረጡ እንደማይቻሉ ገልፀዉ.ልኛል።

ከዚ.ህ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሀሳብ የነገሩኝ በደቡብ ቤንች ወረዳ ጌሊ.ት ቀ.ገ.ማ. ነዋሪ የሆኑት አባ[9] ማትዮስ ሻሽንቴት ናቸው። ጉዳዩ በአንድ ወቅት በደቡብ ቤንች ወረዳ ነዋሪ በሆኑ የቤንች ቤተሰቦች መሀከል የተከሰተን ሁኔታ ይመለከታል። ይህም በአካባቢ.ው ነዋሪ ከነበሩት ቤንችቴት ሞትና በእርሳቸው ቦታ የሚ.ተካውን ሰው ምርጫ በተመለከተ ስለተፈጸመ ድርጊ.ት ከቤተሰባቸው የሰሙትን "ቤንችቶስ" በመጥቀስ ነው።

> አንድ ጊ.ዜ ነው አሉ ቤንችቶት እንደሞቱ በቦታቸው የተተካው ሰው የተመረጠው የህዝብ ግፊ.ት ታክሎበት ከጭልንድ[10] ቤተሰብ ነበር። ሆኖም ይህ ድርጊ.ት በባህላችን እና በእምነታችን ልማዳዊ አሰራር መሰረት ተቀባይነት ስላልነበረው በሀገራችን ከፍተኛ ችግር ተከሰተ። የዶንቃ (ማሽላ) ጎተራዎች ፈነዱ፣ ድርቅ በሀገር ገባ፣ የሚ.በላ ነገር ጠፋ። በዛፎች ላይ እንኳ ቅጠል የሚ.ባል ነገር ማየት ብርቅ ሆነ። በአካባቢ. ያሉ ወንዞች ደረቁ። በአጠቃላይ ህዝቡ በጣም ተቸገረ። በዚ.ህን ጊ.ዜ ህዝቡ ራሱ መልሶ "ምናልባት ይህን መሰል ነገር በአካባቢ.ያችን የደረሰው በአዲሱ ቤንችቴት ምክንያት ሊ.ሆን ይችላል" አለ። በዚ.ህ የተነሳም በተከሰተው አጠቃላይ ነገር ፍርድ እንዲሰጡ ዣዡቴትጋ ሼቴት 12 (ሼቤንቻ ወረዳ) ሽማግሌዎች ተላኩ። ዣገርቴትም ከመጀመሪያው ጀምሮ የተደረገውን ሁሉ ካዳመጡ በኋላ "በቤንችቴት አመራረጥ ረገድ የተደረገው ሁሉ ስህተት ነው" በማለት በአዲሱ ቤንችቴት ቦታ መቀመጥ ያለበት ከአርንድ[11] ነው። ባሉት መሰረት በመጀመሪያ ተመርጦ የነበረው ቀረና ሌላ ቤንችቶት ከአርንድ ተመረጠ። የዚ.ህን ጊ.ዜ ታይቶ የማይታወቅ ዝናብ ዘነበ። ተብሎ ሲ.ነገር ሰምቻለሁ። እኛም እስከዛሬ የምንከተለው ይህንን ነው ብለዋል። (20-03-1999ዓ.ም ጌሊ.ት ቀበሌ ገ/ማህበር)።

---

[9] አባማትዮስ "አባ" የሚ.ለውን ስም የሰጧቸው የአካባቢ.ው ነዋሪዎች ናቸው። እኔም በዚ.ህ ስም ለመጥራት የፈለግሁት ይህንኑ ሀሳብ በመከተል ነው።

[10] ጭልንድ የባይኬሳ ጎሳ አንድ ንዑስ ነገድ ነው።

[11] አረንድ - ከቤንች የባይኬስ ጎሳ አንዱ ንዑስ ነገድ ነው።

ይህ የቤንች ባህላዊ አስተዳዳርና ዳኝነት አፄ ምኒልክ ከ1898 ጀምሮ ወደ አካባቢው ባደረጉት ወታደራዊ ዘመቻ ተዳክሟል። ይሁን እንጂ የቤንች ብሄረሰብ በተለያዩ ጊዜያት ወደ አካባቢው ከመጡ ልዩ ልዩ ሀይሎች ጋር ከፍተኛ ጦርነት ያካሄደ መሆኑን Wallis (1969፣627) እና Perham (1969፣328) ይገልፃሉ።

«ያሱ ወይም ኢያሱ» የሚለውን ስም በደቡብ ቤንች ወረዳ የሚኖሩ የቤንች ብሄረሰብ አዛውንቶች የቅርብ ዘመን ታሪካቸውን (ቤንችቶስ) ሲተርኩ በተደጋጋሚ ያነሱታል። ከነዚህ መህከል አንዱ በደቡብ ቤንች ወረዳ ጌሊት ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ የሚገኘውን ኒያልቶክ (የጌሊት ቋም ድንጋይ) የሚመለከት ነው።



ኒያልቶክ (የጌሊት ቋም ድንጋይ)

ርዝመት፡- 2.48 ሳ.ሜትር

(ቤንች ማጅ ዞን ደቡብ ቤንች ወረዳ ጌሊት ቀበሌ ገበሬ ማህበር)

የሰጡኝ መልስ ተመሳሳይ ቢሆንም ዝርዝሩን ያስረዱኝ ግን ባብ አሰፋ ወሰኑ (ዕድሜ 80 ዓመት፣ የጌሊት ቀገማ ነዋሪ) ናቸው።

ድንጋዩ ጥንትም እዛው አካባቢ ተጋድሞ ነበር። ይሁን እንጂ ልጅ ያሱ (ልጅ ኢያሱ) ወደዚህ እኛ አካባቢ ሲመጡ አብረዋቸው ከነበሩት ሰዎች መሀከል ደጃዝማች ገርቢ የሚባሉት የአካባቢውን ነዋሪ በመሰብሰብ ጉድጓድ ካስቆፈሩ በኋላ አስነስተው ተከሉት። ድንጋዩን ለማንሳት የነበረው ሰው እጅግ ከፍተኛ ነበር። ይህንን የነገረኝ ልጅ እያለሁ ዣገርራት የሚባል ሰው ሲሆን ይህ ግለሰብ በወቅቱ እንደነበርና በኒያልቶክ[12] ተከላም እንደተሳተፈ ነግሮኛል። የሞተውም በጣም አርጅቶ ከጥቂት ዓመታት በፊት ነው ብለዋል።

(ባብ አሰፋ ወሰኑ 20/03/1999ዓ.ም)

ልጅ ኢያሱ በአካባቢው ከሚነሱበት አንዱ ምክንያት ጦርነት ነው። ይኸውም ልጅ ኢያሱ ደቡብ ቤንች እንደደረሱም በጌሊቴት ቦታ ተተክተው የነበሩትንና ወደ ሼቤንች (የአያቶቻቸው ሀገር) ሄደው የነበሩትን ባላባት ዎስ ተደጋጋሚ ሽማግሌ በመላክ ተደራድረው እንዳስመጡ ቀጥሎም የአካባቢውን ህዝብ ሰብስበው፤ ዎስን ነጭ ፈረስ ላይ አስቀምጠው ህዝቡን "ከዛሬ ጀምሮ ንጉሳችሁ ይህ ነው ስሙም ፊታውራሪ ወሰኑ ይሁን" በማለት ከአካባቢው በሰላም ለመውጣት ዘይደው ነበር። ይሁን እንጂ በጉዛቸው ላይ በተከፈተባቸው ድንገተኛ ጦርነት ጥቂት ተከታዮቻቸው በመገደላቸው ልጅ ኢያሱም የወሰዱት አፀፋ ለበርካታ የቤንች ልጆች ህይወት መጥፋት፣ በሺዎች ለሚቆጠሩት ባርነት ስር መውደቅ ምክንያት ሆኗል። Perham (1969:328) ከልጅ ኢያሱ ጋር በተፈጠረው ግጭት አብዛኛው ህዝብ ለውጊያ ጫካ መግባቱን ሆኖም እስከ 80,000 የሚደርስ ሰው መጎዳቱንና መማረኩን ገልጿል። በተመሳሳይ መልኩ ይህንኑ ጉዳይ Bahru (1991:122) የሚከተለዉን ይላሉ።

... he undertook the most nefarious campaign of his career, against the Gimira in South Western Ethiopia, which ended up with the enslavement of tens of thousands of the inhabitants.

ሁለተኛውና በቤንች ብሄረሰብ ዘንድ ወሳኝ ታሪካዊ ክስተት ነው። በማለት ሽማግሌዎች የገለፁልኝ በ1937/8 ዓ.ም. ወይም ከጣሊያን ወረራ በኋላ ከአፄ ሀይለስላሴ ጋር

---

[12] ኒያልቶክ (የጌሊት ቁም ድንጋይ) ከመሬት በላይ 2.48 ሜትር ርዝመት ያለው ወጥ ጠርብ ድንጋይ ነው።

ያደረጉት ጦርነት ነበር። የዚህ ግጭት መነሻውም ከአካባቢው ሽማግሌዎች ከአንዱ የተገለፀልኝ በሚከተለው መልክ ነው።

> በቤንች ምድር የጣሊያን ወራሪ ጦር ለአንድ ቀንም በሰላም አላደረም። በዚህ የተነሳም ለመበቀል ብሎ ፊታዉራሪ ወስኑ ላይ አሰቃቂ ግድያ ፈፀመ።[13] እኛም በድንጋይ ሳይቀር ተፋለምን። በሌላው የኢትዮጵያ ክልል ጫካ ገብተው የነበሩት አርበኞችም እኛ ዘንድ መጥተው ከደቡብ ሱዳን ቦማ ከተማ በእንግሊዝ መንግስት የተሰጠውን ቤልጅግ ጠመንጃ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ጣሊያን ተሸንፎ እስኪወጣ ተዋግተናል። ጦርነቱ እንዳበቃም ንጉሱ ሀይለስላሴ መልዕክት ወደኛ ባለባቶች ጋ ልከው ነበር።
>
> (ባብ ሲግ ባያ 17/03/1999 ዓ.ም ዳቸበለ ቀ/ገ/ማ)።

በዚህም "በእግዚአብሔር እርዳታ፣ እናንተም (ቤንች) አግዛችሁኝ ጠላታችንን ጣልያንን አሸንፈን ከሀገራችን አባረናል። እንግዲህ በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በየአባታችሁ (ባላባቶችን ነው) ሀገር ግቡና ህዝባችሁን አስተዳድሩ። በየአካባቢያችሁም ስትገቡ አንድ ቀን ለገበያ መዋያ አድርጉና ህዝቡ ይገበያይ። የሚል መልዕክት ስላስተላለፉ ሁሉም ባላባት በየአካባቢው ገባ። በዚህ አጋጣሚም የዛሬዋ የደቡብ ቤንች ዋና ከተማ ደብረወርቅ ተመሰረተች ከተማዋንየቀረቀሯትም በጣሊያን ወረራ ምክንያት ከአካባቢው ወጥተው ጎላ (ጨና ወረዳ) የሚባል ቦታ በአርበኝነት ቆይተው የነበሩት ይብራ ሻሻንቴት ናቸዉ። ሲሆኑ የገበያዋ ዕለትም "ሐሙስ" የተመረጠው በኚሁ ባላባት ነው።

ይሁን እንጂ ሀይለስላሴ መጀመሪያ የሰጡትን ቃል በማጠፋቸው እና ደጃዝማች ሙሉጌታ የሚባሉ ሰው ወደ ቤንች ሀገር በመላካቸው የተነሳ መራ ፈኒኮምስ በሚባል ባላባት የሚመራ ሁሉንም የብሄረሰቡን አባላት ያካተተ ከፍተኛ ህዝባዊ ተቃውሞ በመነሳቱ በፊታውራሪ ዓለማየሁ ፍላቴ ከሚመራው የማዕከላዊ መንግስት ጦር ጋር ከፍተኛ ውጊያ ተደርጓል። ከዚህ በኂላም ከጅማ እስከ ሱዳን ድንበር ያለውን አካባቢ "ከፋ ጠቅላይ ግዛት" በሚል ስም ሲቋቋም የቤንች አካባቢም "ጊሚራ አውራጃ" ተብሎ በከፋ ጠቅላይ ግዛት ስር እንዲተዳደር ተደርጓል።

---

[13] የፊታውራራ ወስኑን ጣሊያን የገደለው ህይወታቸው እያለ በገመድ ወገባቸውን አስሮ በመኪና እየጎተተ ነበር በማለት የአካባቢው ሽማግሌዎች ይናገራሉ።

በአጠቃላይ የብሔረሰቡ አባል የሆኑ ሽማግሌዎች (አዛውንቶች) እንደሚገልፁት በቤንች ብሄረሰብ ውስጥ የዘር ልዩነት የሌለ መሆኑን ነው። ይሁን እንጂ በአንድ ወቅት በተከሰተ ሁኔታ የተነሳ ሼ፣ ሜርና ቤንች የሚባሉ ቤተሰቦች (ክፍፍሎች) ሊፈጠሩ ችለዋል። ቢሆንም ዛሬም ድረስ በሼ፣ በሜርና በቤንች መሀከል ያለው ባህላዊና ማህበራዊ ግንኙነትና ትስስር የጠበቀ ነው በማለት ያስረሳሉ። በተጨማሪም ቤንቾች ዛሬ በጉርብትና አብረው ከሚኖሩትና ልዩ ልዩ ብሄረሰቦች ጋር ከረዥም ዓመታት ጀምሮ የጠበቀ ባህላዊ፣ ማህበራዊና ታሪካዊ ግንኙነት መመስረት የቻሉ ቢሆን የራሳቸው የሆነ ባህላዊ እምነት፣ አስተዳደርና ዳኝነት--- እንደነበራቸውም ይገልፃሉ። ሆኑም በተለያዩ የታሪክ ፀሐፍት እንደተገለፀው እነዚህ የቤንች ብሄረሰብ ባህላዊ የአስተዳደርና የዳኝነት ስርዓቶች ከ1890ዎቹ ጀምሮ ወደ ብሄረሰቡ መኖሪያ አካባቢ ( ቤንች ዶድ) በተደረጉ ሰፊ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎች የተነሳ የተዳከሙ መሆናቸው ነው።

## ምዕራፍ ሶስት

## የተዛማጅ ጥናቶችና ንድፈ ሀሳቦች ቅኝት

### 3.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችን ውስን ባህርያት ገልጾ በመለየት እንዲሁም የነዚህ ዝርው ተረኮችን ማህበራዊ ፋይዳ ከብሄረሰቡ ልዩ ልዩ የህይወት ገፅታዎች ጋር በማያያዝ ቀደም ሲል የተካሄደ አካዳሚያዊ ጥናት አላገኘሁም፡፡ ይሁን እንጂ የዝርው ተረኮች ማህበራዊ ፋይዳንና መሰል ጉዳዮችን አስመልክቶ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተሰሩ የዲግሪ ማሟያ ጽሁፎች (ዲማፅ) ይገኛሉ፡፡ ስለዚህም ከነዚህ ዲማጾች መሀከል ከዚህ ጥናት ጋር አግባብ ያላቸው የመጀመሪያ ዲግሪ ዲማጾችና የሁለተኛ ዲግሪ ዲማጾችን አቃኛለሁ፡፡

ያዕቆብ ወልደማርያም (1974) "የከፋ ተረታተረቶች" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት በተረቶች ይዘት ትንተና ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ዓላማውም በተረቶቹ አማካይነት የሚንፀባረቀውን ባህል ለመጠበቅ ይቻል ዘንድ ተረቶቹን ከጥፋት ለመከላከል ነው፡፡ ለጥናቱ የሚረዱትን መረጃዎች እመስክ ተገኝቶ በቴፕሪከርደር ቀርጿል፡፡ በትንተናውም ተረቶች በቅርጽ ቢለያዩም በይዘት ተመሳሳይነት እንዳላቸው ገልጿል፡፡ ከቅርጽ አኳያም፣ የተረቶቹን አጀማመርና አጨራረስ፣ የቦታና የጊዜ አመልካቾች፣ የተረቶቹ ርዕስ፣ በዋና ገፀባህርያት፣ በእንስሳት፣ በእንስሳትና በሰው፣ በሰው፣ እምነትን የሚመለከቱ እንደሆኑ አመልክቷል፡፡ በተጨማሪም የተረቶቹን አወቃቀር ከገፀባህርያት አሳሳልና ቋንቋ አንጻር ለማሳየት ሞክሯል፡፡ ለዚህም 20 ተረቶችን ሰብስቧል፡፡

ደህብ ትኩ (1974) "የትግርኛ ተረቶች" በሚል ርዕስ ያቀረበችው ጥናት ዓላማው የትግርኛ ተናጋሪ ህዝብን የኑሮ ፍልስፍና ማሳየት፣ በቃል ያሉትን ተረቶች በጽሁፍ አስፍሮ ማስቀመጥ ሲሆን ትኩረቷም ተረቶቹን በቅርጽና በይዘት ከፋፍላ የያዙትን አጠቃላይ መልዕክት ማሳየት ነው፡፡ ለዚህ ተግባር ያግዛሉ ያለቻቸውን የትግርኛ ተረቶች የሰበሰበቻቸው በከተሞች አካባቢ ከሚኖሩ የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሽማግሌዎችና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ነው፡፡ በጨረሻም የተሰበሰቡትን የትግርኛ ተረቶች ከቅርጽ አንጻር፥ በስድ ንባብና በግጥም፣ ግጥማዊ ተረትና ድራማዊ ተረት በማለት ለይታ

አቅርባለች፡፡ ተረቶቹ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ይዘቶች እንዳሏቸውም በትንተናዋ አሳይታለች፡፡ ይሁን እንጂ ደሀብ ተረቶቹን በይዘት ለመመደብ የተጠቀመችበትና ያወያየቻቸው ሰዎች "አብዛኛዎቹ የደገፉትን መልዕክት መውሰድ..." በማለት የተጠቀመችበት ዘዴ ከስነቃል የክወና አውድ እና ታዳሚዎች ማንነት አንጻር የሚነሱ የስነቃል ጥናት ፅንሰ ሀሳቦች ጋር ይጋጫል፡፡

ሙሉጌታ ነጋሳ (1976) "በጅባትና ሜጫ አውራጃ የተሰበሰቡ የገበሬን ህይወት የሚያንፀባርቁ የኦሮምኛ ተረቶች" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት በጭብጥ ትንተና ላይ ያተኮረ ሲሆን 80 ተረቶች ሰብስቦ በ25ቱ ላይ ትንተና አድርጓል፡፡ ተረቶቹን ከተለያዩ ማህበራዊ አውዶች፡- ከለቅሶ፣ ከጭውውት፣ ከደቦ ቦታዎች እንደሰበሰበ ገልጿል፡፡ የሰበሰባቸው ተረቶችም ጋብቻን፣ ትግግዝን፣ ዝምድናን፣ ኑዛዜን፣ የሀብት አያያዝን፣ ምርቃትን ወዘተ. የሚመለከቱ ናቸው፡፡ እነዚህ ተረቶች ህብረተሰቡ በእለታዊ ህይወቱ የሚፈፅማቸውን ድርጊቶች፡- የከብት አጠባበቅንና የእህል አመራረትን፣ የስራ ክፍፍልን ወዘተ. እንደሚገልፁ ጠቅሷል፡፡ በጥቅል ይዘታቸውም እምነት፣ ወግ፣ ልማድ፣ ገጠመኝ በአጠቃላይ ባህላዊ ገጽታዎችን እንደሚያሳዩ ገልጿል፡፡ ይህ የሙሉጌታ ጥናት ተረቶችን ከክዋኔ አውድ አንጻር ለመመልከት ያደረገው ጥረት ከያዕቆብና ከደሀብ ጥናቶች ይለየዋል፡፡

ሰውነት መኮንን (1974) "በሞጣ አውራጃ የሚነገሩ የአማርኛ ተረታ ተረቶች" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት ዓላማው የተረቶችን አቀራረብና ይዘታቸውን በመመልከት በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ ያለውን ተዝናኖታዊ እና ልምድን የማካፈል ጠቀሜታ ማሳየት ነው፡፡ በተጨማሪ የትረካን ጥበብነት፣ የተረትን ማህበረ ባህላዊ እሴቶችን የማንፀባረቅ ሁኔታ ማመልከት የሚል ሲሆን አብይ ትኩረቱም የቅርጽና የይዘት ትንተና ማድረግ ላይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የተረቶችን ቅርጽ ከታሪክ መዋቅር፣ ክዋኔ፣ ከቋንቋ፣ ከገፀባርያት አንጻር ተመልክቷል፡፡ የተረቶቹንም ይዘት በስምንት ምድቦች ከፍሎ ትንታኔ የሰጠ ሲሆን ይዘቶቹም የህብረተሰቡን ፍላጎት፣ አስተሳሰብ፣ እምነትና ልምድን እንደሚገልፁ ጠቅሷል፡፡ ተረቶች አንድን ህብረተሰብ ለማጥናት ያላቸውን አስተዋጽኦም አስገንዝቧል፡፡ ለዚህ ጥናት 25 ተረቶች የተሰበሰቡ ሲሆን በአባሪነት በጥናቱ መጨረሻ ላይ ተያይዘዋል፡፡

ሙሉነህ ጉልማ አደሬ (1993) "የክስታኔ ተረቶች" በሚል ርዕስ ባቀረበው ጥናት ያተኮረው የክስታኔን ማህበረ ባህላዊ ህይወት በመግለፅ የህብረተሰቡን የኑሮ መልክ ማሳየት ላይ ነው፡፡ በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች፡- ለቅሶ፣ ጎረቤቶች ሲሰበሰቡ እየተገኘ 22 የክስታኔ ጉራጌ ተረቶችን ሰብስቦ በቅርጽና በይዘታቸው ላይ ትንታኔ አድርጓል፡፡ የክስታኔ ተረቶችን

ከቃላዊ ተለዋዋጭነት፣ ከክዋኔ፣ ከመተረቻ መቼት አንፃር ተነስቶ በሰባት ዋና ዋና ምድቦች ከፍሏል። እነዚሁ ተረቶች የራሳቸው ክዋኔ፣ የቋንቋ አጠቃቀም እና ገፀባህርያት እንዳሏቸው አሳይቷል። በአወቃቀራቸውም የአጀማመር፣ መግቢያ፣ በድርጊቶች ሰንሰለት የተገነባ ሐተታ፣ የትረካውን ውጤት የሚያሳዩና ተረቱ ማብቃቱን የሚጠቁሙ መደምደሚያዎች ያሏቸው ናቸው ብሏል። ተራኪዎቹም በአብዛኛው ወንዶች እንደሆኑ ተገልጿል። በተረቶቹ ይዘት አማካኝነትም የሚነሱት ጉዳዮች በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ወጎችና ልማዶች እንዲሁም የማይቀበሏቸውን ድርጊቶች አሳይቷል።

ሱሩር በድሩ (1995) "የስልጤ ተረቶች ይዘት ጥናት" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት ዋና ዓላማ የስልጤ ተረቶችን ሰብስቦ ይዞታቸውን ማጥናት ነው። ለዚህ የሚረዱ መረጃዎቹን ልዩ ልዩ ባህላዊና ማህበራዊ አውዶችን፡- ግርዛት፣ ባህላዊ ችሎች፣ ለቅሶ፣ ሰርግ ... የመሳሰሉትን ተጠቅሞ በስልጢኛ ቋንቋ የሰበሰባቸውን 33 ተረቶች ወደ አማርኛ ተርጉሞ በአስራ አንዱ ላይ የይዘት ትንተና አድርጓል።

በይዘት ትንተናው መነሻነትም፥ የስልጤ ብሄረሰብን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ከቀደመው ትውልድ (አያትና ቅድመ አያት) ጀምሮ ያሉትን እሴቶች አሳይቷል። በተጨማሪም ለሰላም፣ ለእድገት፣ ለልማትና ለብሄረሰቡ አባላት አደጋ ናቸው የሚሏቸውን ፍሬ ሃሳቦች አስቀምጧል።

ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት አላቸው ተብለው የተቃኙት የ Abdul Kadir Haji (1982)፣ Tesfaye G/Mariam Hailu (1990)፣ Melakneh Mengistu (1990)፣ Yihenew Jembere (1996)፣ Sahilu Kidane (1996)፣ Bayileyegne Tasew (1999) እና Abreham Alemu (2000) ጥናቶች በሙሉ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተዘጋጁ ሆነው በእንግሊዝኛ ቋንቋ የቀረቡ ናቸው።

እነዚህ ሰባት የድህረ ምረቃ ዲማጾች ለጥናታቸው አሰራር ከተከተሉት አንፃር (perspective) ሲታዩ በሁለት ምድቦች የተከፈሉ ናቸው። ይኸውም እያንዳንዳቸው ዲማጾች በዋነኛነት አውድ - ተኮር (contextual) መሆን ወይም አለመሆናቸው ነው ብሎ የዚህ ጥናት አቅራቢ ያምናል።

Abdul Kadir Haji Jama (1982) "Some Cultural Elements As Reflected In Somali Folktales" በሚል ርዕስ ጥናቱን አቅርቧል። የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሱማሌ ፎክሎር የሚገለፁትን ዋና ዋና ባህላዊና ስነልቦናዊ ጉዳዮች ማሳየት ነው። የሱማሌ ህዝብ፡- ቋንቋን፣ ባህልን፣ ኢኮኖሚንና ስነምህዳርን የተመለከቱ መግለጫዎች ቀርበዋል። ለጥናቱ

ከተሰበሰቡት 82 ተረቶች ውስጥ የተወሰኑት ተመርጠው በተደረገው የጭብጥ ትንተና ውጤት የክልሉን ነዋሪ አርብቶአደር ህይወት ያመለክታሉ ብሏል።

Tesfaye G/Mariam Hailu (1990) "A Study of Major Themes in Jablawi Folktales" በሚል ርዕስ ጥናቱን ያካሄደ ሲሆን ትኩረቱ በጀብላዊ ህገረሰብ ተረኮች ጭብጥ ትንተና አማካኝነት የጀብላዊ ብሄረሰብን ማንነት እና የአኗኗር ልማዶቻቸውን ማሳየት ነው። ለዚህ ተግባሩም ከመስክ ከሰበሰባቸው 115 የሀገረሰብ ተረቶች መሀከል ለባህሉቱን ተጠቅሞ ባደረገው ትንተና ጀብላዊ ዓለምን እንዴት እንደሚመለከትና የጀብላዊ እምነትን ያንፀባርቃሉ ያላቸውን ጭብጦች ለይቶ አቅርቧል። በተጨማሪም የጀብላዊ ሀገረሰብ ተረት ዘር ናቸው በማለት ሚቶችን፣ አፈታሪኮችን፣ ፌብሎችን፣ ፌየሪ ተረቶችን ያቀረበ ሲሆን እነዚህም በተናጠል የሚጠሩበት ስያሜ እንደሌላቸው አሳይቷል።

Melakneh Mengistu (1990) "The Major Themes and Motifs of Southern Agaw Folktales" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። የዚህ ጥናት ትኩረት የደቡብ አገው ሀገረሰብተረቶች ማህበረ-ባህላዊ ጠቀሜታቸውን በጭብጣዊ ትንተና ስልት መመርመር፣ ዋና ዋና የሚባሉትን የመባያ ጉዳዮች መለየት ነው። ለዚህ ተግባር ከመስክ የሰበሰባቸውን 60 ያህል የደቡብ አገው ሀገረሰብ ተረቶችን ተንትኖ ዋና ዋና የሚላቸውን ጭብጦች በሁለት ምድቦች፤ የመባያ ጉዳዮቹን ደግሞ ብልህነትና ቂልነት ... በማለት በአስራ ሁለት ምድብ ከፍሎ አሳይቷል። በተጨማሪም Melakneh (1990:45) በጥናቱ ውስጥ ተረቶችን በተለያዩ ምድቦች የመክፈሉን ስራ አስቸጋሪነት " ... categorization may seem to be quite arbitrary since a single tale may lend itself to many related and overlapping themes ... " በማለት አሳይቷል።

Yihenew Jembere (1996) "A Generic Classification of Amharic Oral Prose Narratives of West Gojiam" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት ትኩረት በምዕራብ ጎጃም አካባቢ የሚነገሩ የአማርኛ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ሰብስቦ በየቤተሰባቸው አመመደብ ላይ ነው። ለዚህ ተግባርም የክዋኔ አውድን፣ ርዕሰ ነገርን፣ ጭብጥን፣ አወቃቀርንና የአቀራረብ ስልትን ተጠቅሞ ተረቶቹን ተንትኗል።

በትንተናውም ከመስክ የሰበሰባቸውን 140 ዝርው ተረኮች አይነት፡- ተረት፣ አፈታሪክ፣ የዘርሀረግ/ትውልድ ቆጠራ/ በማለት በሶስት ከፍሎ ከነዝርዝራቸው አሳይቷል።

ይህ የ Yihenew Jembere (1996) ጥናት አውዳዊ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ አስገብቶ ከመስራቱም ባሻገር አካባቢያዊ ስያሜዎችን ለመጠቀም ሞክሯል። በተጨማሪም ተረኮቹን

በየአይነታቸው ለመክፈል ያግዛሉ የሚባሉትን የአካባቢ ምደባ (በህዝቡ) እና የትንተና ዘዴዎች ተረኮችን በየዘሮቻቸው በመክፈሉ ረገድ ያለባቸውን ችግር አመልክቷል፡፡

Sahilu Kidane (1996) "Borana Oromo Prose Narratives. A Contextual Study" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት የቦረናን ዝርው ተረኮች ከአውዳቸው ተነስቶ ያጠና ነው፡፡ በዚህ መነሻነትም በአካባቢ ምደባ ስልት የእያንዳንዱን የዝርው ተረክ ዘር ከዛው ከራሱ ባህሪ በመነሳት ሲገልፅ የየተረክ አይነቶቹን ቅርጽና ይዘት ትንታኔ ሰጥቶበታል፡፡ በትንታኔዎቹም፡- ከመስክ የሰበሰባቸውን 76 የስነቃል መረጃዎች ተጠቅሞ የቦረና ኦሮሞ ዝርው ተረኮች በሶስት ዋና ዋና ምድቦች እንደሚከፈሉ የገለፀ ሲሆን የመጀመሪያ ሁለቱ Duri-Duri (የህፃናት ተረቶች) እና Mamaksa (የአዋቂዎች ተረቶች) ሲሆኑ ሶስተኛው Arga-ageti ነው፡፡ በውስጡም ሚቶችና አፈታሪኮችን ይይዛል፡፡ ጥናቱ እነዚህን ሶስት የዝርው. ተረክ ዘሮች፡- ጭብጥን፣ ገፀባህርያትንና ቋንቋን መሠረት አድርጎ ይተነትናል፡፡ በተጨማሪም "Mamaksa" በቦረና ኦሮሞዎች ዘንድ ያለውን ሰፊ ማህበራዊ ፋይዳ ጥናቱ ለማሳየት ይሞክራል፡፡

Sahilu (1996) በኢትዮጵያ ስነቃል ጥናት አውዳዊ የሆነ አጠናን ዘዴን በሰፊው እጥቅም ላይ ያዋለ፣ አካባቢያዊ ምደባ እና ትንተናዊ/ምሁራዊ ዘዴን አጣምሮ አንድን የዝርው ተረክ አይነት ከነውስን ባህርያቱ ያሳየ ነው፡፡ አካባቢያዊ ስያሜዎችን ከነአውዳቸው በሰፊው ተጠቅሟል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የ Sahilu (1996) ጥናትም በደረጃው ቀደም ሲል ከተሰሩት የተሻለ ቢሆንም ጉድለቶችም ይታዩበታል፡፡ ከነዚህም መሀከል ዋናው በገጽ 13 የቦረና ኦሮሞ ዝርው ተረክ ዘሮችን በተለይም "Mamaksa Adult's tale including <u>proverbs</u> ..." (መስመሩ የአጥኚው ነው) የሚለው አገላለፅ ጥናቱ በርዕሰ ነገርነት ከያዘው ... prose narratives ... ጋር የሚጋጭ ይመስላል፡፡ የተረኮች ዝርውነት የቅርጽ ጉዳይ ብቻ አይደለም፡፡ ምክንያቱም Oring (1986)፣ Potter (2002) እና ሌሎችም የስነቃል ተመራማሪዎች እንደሚገልፁት "አንድ ሀሳብን አሟልቶ መያዝንም" ይጨምራልና፡፡ ምናልባትም ይህንኑ የሳህሉ (1996) ጥናት አስመልክቶ Abraham (2000:11) እንደሚገልፀው ... However, Sahlu has hardly made an attempt to understand the reason behind the dominance of this genre over the others ... በማለት ያቀረበው ሂሳዊ አስተያየት ተገቢነት አለው፡፡ ይኸውም አንድ የተረክ ዘር በሆነ አጋጣሚ ሲተረክ ለትረካው መንስኤ የሆነ ማህበራዊ ግፊት (social pressure) አለና ነው፡፡

Bayileyegn Tasew (1999) “Anyuaa Oral Prose Narratives Ethnic Genres and Social functions” በማለት ያቀረበው ጥናት ዓላማው ትኩረቱ በአካባቢያዊ (indigenous ways of categorization) ምደባ ስልቶች አማካኝነት የአኑዋን ዝርው ተረኮች ተንትኖ በየዘሮቻቸው መመደብ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የአኑዋ ዝርው ተረኮችን በተረኮቹ ይዘት እና የተራኪውን ዕድሜ መነሻ አድርጎ Leere (እውነተኛ ታሪክ)፣ Wae (ተረቶች) እና Angade (ምሳሌያዊ ታሪኮች) Proverbial stories በማለት በሶስት ምድብ ከፍሎ ማህበራዊ ፋይዳቸውንም በዝርዝር አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ Bayilegn (1999) ጥናትን ከ Yihenew (1996) እና Sahilu (1996) ጋር አውዳዊነታቸው ያመሳስላቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ጥናtu የዝርው ተረክ ዘሮች አከፋፈልን ለተረኮቹ ክወና አውድና ለአካባቢያዊ አከፋፈል ዘዴ ልዩ ልዩ ስልቶች በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት ይለያል፡፡

Abreham Alemu (2000) “Jimma Oromo Oral Prose Narratives: A Preliminary Descriptive Analysis” በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት ዋና ትኩረቱ የጅማ ኦሮሞን ማህበራዊና ባህላዊ አውዶች መነሻ አድርጎ ቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸውን መለየትና መግለፅ ነው፡፡ በጥናቱም የጅማና አካባቢውን ስነምህዳር፣ ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ገጽታዎች በሰፋት ገልጿል፡፡ ዝርው ተረኮቹ መቼ መቼ እንደሚቀርቡም 4 ጉዳዮችን በማንሳት አሳይቷል፡፡ ተረኮቹ በቡና አጠጣጥ ስርዓት (Buna Waal Wamu)፣ በገበያ ቀናት (Gabaa)፣ በሀዘን ቤት (Taaziyaa)፣ በጫት (Qimaa)፣ በሰፊው እንደሚቀርቡ ገልጿል፡፡ ከተለያዩ ማህበራዊና ባህላዊ አውዶች የሰበሰባቸውን ዝርው ተረኮችም Seenaa/Taarika (ታሪክ)፣ OduDuri (ተረት) እና Qoosaa (ቀልድ) በማለት ከእውነተኝነትና ከፈጠራ ታሪክነታቸው ብሎም ለምን ለምን ጉዳይ እንደሚተረኩ ገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ የአብርሃም/2000) ጥናትም ለአውድ (context) በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት የጅማ ኦሮሞ ዝርው ተረኮች ልዩ ልዩ ቅርፃዊና ጥበባዊ ባህርያቸውን አልዳሰሰም፡፡

## 3.2 የንድፈ ሀሳቦች ቅኝት

ዝርው ተረክ (Narrative) የሚለው ቃል በውስጡ በርከት ያሉ ፅንሰሀሳቦችን ይይዛል፡፡ እንደ ተረክ ማለት ታሪክነት ያላቸው ተከታታይ ድርጊቶችን ቃላዊነታቸውን ሳይለቁ በዝርው ቅርጽ የሚያቀርብ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተረክ ማለት ተራ የሆነ የድርጊቶች ዘገባ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በተረኮች አማካኝነት ስርዓት ባለው ሁኔታ ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ ድርጊቶች፣

የቋንቋ አጠቃቀም እና በትረካው የሚገለፀውን መልእክት የማያስተላልፉ ገፀባህርያት የሚያካትቱ በመሆናቸው ነው። በውስጡም ሚቶችን አፈ ታሪኮችንና ተረቶችን ይይዛል። በአጠቃላይ ሲታዩም ዝርው ትረካዎች በውስጣቸው የአንድን ኅብረተሰብ ብሎም የተራኪውን አስተሳሰብና ስሜት የሚያንፀባርቁ ናቸው። ስለዚህም በተረኮች አማካኝነት የሚቀርቡ መልእክቶችን ለመረዳት የቀረቡበትን አውድ ማወቅ ተገቢ ነው በማለት Oring (1986) ይገልጻል።

በዝርው ተረኮች አማካኝነት የሚገለፀውን ሀሳብ በተገቢው መንገድ ሊመረዳት ተረኮቹ የሚቀርቡበትን ማህበራዊ አውድ ማወቅ ብሎም ለአውዱ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ Finnegan (1970) እና Ben-Amos (1982) ያስረዳሉ። በተጨማሪም Linda (1972) ተረኮች በሚተረኩበት ጊዜ ከአካባቢያቸው ተጨባጭ ማህበራዊ ሁኔታ ጋር የሚዛመዱ በመሆናቸው ሲጠኑ ለሚከተሉት ሦስት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጥ ይገባል።

1. በተረኮቹ አማካኝነት የሚተላለፈው መልዕክት ምንድን ነው?
2. ለተረኮቹ መፈጠርና መነገር ምክንያት የሆነው ጉዳይ ምንድን ነው?
3. ተረኮቹን ተራኪዎቻቸውና ታዳሚዎቻቸው እንዴት አድርገው ይመለከቷቸዋል?

የሚሉትን ጥያቄዎች ተረድቶ መልስ መስጠት አስፈላጊነቱን ገልፀዋል።

### 3.2.1 ዝርው ተረኮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው

ፎክሎር የአንድን ህብረተሰብ ህይወት ይገልፃል። ስለሆነም የጥናቱ ትኩረት ህብረተሰቡ ውስጥ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ሊመለከት ይገባል Bascom (1965)።

ልዩ ልዩ የፎክሎር ዘሮች /Genre/ ባመነጫቸው ህብረተሰብ ፈርጀ ብዙ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚጫወቱት ሚና አላቸው። ከነዚህ መሀከልም አንዱ የዝርው ተረኮች ማህበራዊ ፋይዳን የሚመለከተው ነው። ይህም ዝርው ተረኮች በአንድ ህብረተሰብ የዕለት ተእለት ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ያላቸውን ፋይዳ በተመለከተ Georges (1969)፣ Finnegan (1970) ፣ Okphewho (1992) በሰፊው ገልፀዋል።

ዝርው ተረኮች በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ያላቸውን ተግባራት በተመለከተ በርካታ የፎክሎር ሊቃውንት በየዘመኑ የተለያዩ ሆኖም እርስ በእርሳቸው የሚደጋገፉ ሀሳቦችን ሰጥተዋል፣ ከነዚህ መሀከል የቃላዊ ዝርው ተረኮች ማህበራዊ ፋይዳ፣ የማስተማር፣ ልዩ ልዩ ማህበራዊ ተቋሚትን ምንነት እና የሚገኙበትን ይዘታ መግለጽ የማህበራዊ ልማዶች ኬትመጥነት ማሳየትን የመሳሰሉት ፈርጀ ብዙ ፋይዳ እንዳሏቸው Georges (1969)፣

Finnenan (1970)፣ Oring (1985) ፊ.ቃዶ (1991) Okphewho (1992) ን የመሳሰሉት ምሁራን ያስገነዝባሉ::

የቃላዊ ዝርው ተረኮች ልዩ ልዩ ማህበራዊ ፋይዳዎችን በተመለከተ የሚከናወኑ ጥናቶች መመስረት ያለባቸው እነዚሁ ዝርው ተረኮች አውድ ውስጥ ሊሆን እንደሚገባ ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ይገልፃሉ:: የዚህ ምክንያቱ የተረቶች መፍለቂያ፣ ክዋኔ፣ ፍቺ እና ጠቀሜታቸው የሚገለፀው በውስጥ ስለሆነ ነው Ben-Amos (1982) Oring /1985/፣ Okphewho (1992)::

በአጠቃላይ ቃላዊ ዝርው ተረኮች የአንድን ህብረተሰብ ማህበረ-ባህላዊ ህይወት የሚያንፀባርቁ በመሆናቸው የጥናታቸው ትኩረት የተረኮችን ፋይዳ በተመለከተ ሊሆን ይገባል:: ከዚህ ጥናት የሚገኘው ውጤትም የአንድን ህዝብ ህይወት ለመለወጥ በሚከናወኑ ልዩ ልዩ የልማት ተግባሮች ላይ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ይኖረዋል::

### 3.2.2 የቃላዊ ዝርው ታሪኮች አመዳደብ

የቃላዊ ታሪኮች ምደባ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ስር ሰደድ ችግር ነው Okphewho (1992-181):: ስለዚህም ከፎክሎር አንፃር የሚደረጉ ሳይንሳዊ ጥናቶች አንዱ ርዕስ ነገራቸው የዝርው ታሪኮችን አመዳደብ ልዩ ልዩ ስልቶችን የሚመለከት ሊሆን ይችላል::

#### 3.2.2.1 የመባያ ጉዳዮች እና የወጥ ተረቶች መዘርዝር

ተረኮችን በየዘሮቻቸው ስልታዊ በሆነ መንገድ አጥንቶ ለመመደብ ቀደም ካሉት ዘመናት ጀምሮ ጥረት ሲደረግ ነበር:: ለመጀመሪያ ጊዜም የህገረሰብ ተረቶችን ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ ለመመደብ ጥረት ያደረገው በ1864 እ..አ. J.V.Hahn ነው:: እስከ አለንበት ዘመን ድረስም ጥረቱ እንደቀጠለ ነው:: ይሁን እንጅ የህገረሰብ ተረቶችን ስልታዊ በሆነ መንገድ ለመመደብ በተረኮች ውስጥ የሚገኙትን የመባያ ጉዳዮች እና ወጥ ተረት ( type) መሀከል ያለውን ልዩነት በውል መረዳት ይገባል፣ Thompson (1946)::

በ Thompson (1946) ገለፃ ወጥተረት ማለት ራሱን ችሎ ፍቺ የሚሰጥ ተረት ማለት ነው:: በውስጡም አንድ ወይም በርከት ያሉ የመባያ ጉዳዮችን አካቶ ሊዋቀር የሚችልና በተረቶች መሀከል ያለውን ቤተሰባዊ ዝምድና ያሳያል:: የመባያ ጉዳይ በተረት ውስጥ የሚገኝ አነስተኛው አሀድና በቀላሉ የማይለዋወጥ ባህሪ ያለው ሲሆን በየአካባቢው የሚገኙ ሀገረሰብ ተረቶች ውስጥ ያሉ የወል አሀዶችን የሚያመለክት ነው:: ስለዚህም የመባያ ጉዳዮች መዘርዝር እና የወጥተረት መዘርዝር (Motif-index & type index) አማካኝነት የሀገረሰብ ተረቶችን በተለያዩ ምድቦች መክፈል እንደሚቻል ይገልፃል::

### 3.2.2.2.. አካባቢያዊና ትንተናዊ የዝርው ተረክ ምደባ ዘዴዎች

ዝርው ተረኮችን በየዘሮቻቸው ለመመደብ እጥቅም ላይ ከዋሉት ዘዴዎች መሀከል የአካባቢያዊ ምደባ ዘዴና የተንተናዊ ምደባ ዘዴዎች ይገኛሉ:: እነዚህ ሁለት የምደባ ዘዴዎች የየራሳቸው የአመዳደብ ስልትን እንደሚከተሉ Ben-Amos (1982) እና Okphewho (1992) ያስረዳሉ::

የትንተናዊ ዘዴ ዝርው ተረኮችን ሚት፣አፈታሪክና ተረት ብሎ በሦስት ይከፍላል:: ይሁን እንጅ ይህ ዘዴ ትኩረቱ በተረኮቹ ዘር ብያኔ፣በጭብጥ፣በምዕላድ ገለፃ ላይ ስለሚያተኩር ልዩ ልዩ የፎክሎር ተግባቦታዊ ዘዴዎችን ይዘነጋል፣ተረኮቹ ለፈለቁበት ማህበረ-ታሪካዊ ዳራ አነስተኛ ግምት ይሰጣል:: በዚህ የተነሳም በርካታ የእውቀት ዘርፎችን በየፈርጃቸው አይመለከትም Ben-Amos (1982)::

Finnegan (1970፣365) ተረኮችን በየዘሮቻቸው በመመደብ ረገድ የአፍሪካ ስነቃል አካባቢያዊ ምደባ ዘዴዎች ወጥነት የላቸውም:: ስለዚህም የአካባቢያዊ ምደባ ዘዴን ስልታዊ በሆነ መንገድ ለመጠቀም ጥናቱን አውዳዊ (contextual) ማድረግ ጠቃሚ ነው:: ምክንያቱም አውድን መሠረት ያደረገ የዝርው ተረክ ምደባ በርካታ ነገሮችን መነሻ ለማድረግ ስለሚችል ነው:: ከነዚህም መሀከል፣ የተረኮች ክዋኔ (ማታ/ቀን)፣ የተራኪው ማንነትና የትረካ ክህሎት፣ ታዳሚውን፣የትረካውን ረብና የመሳሰሉትን ሁሉ የሚያካትት ነው በማለት ይገልፃሉ::

የአካባቢያዊ ምድባ ዘዴ ዝርው ተረኮቹን ላፈለቀው ባህል ትኩረት ይሰጣል:: ስለዚህም በዚህ ምደባ ዘዴ አውድ ወሳኝ በመሆኑ ለክወና አጋጣሚዎች (performance situation) ትኩረት ሊሰጥ ይገባል:: ከዚህ በመነሳትም ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ከስያሜያቸው፣ ከገላጭ ባህሪያቸውና ከማህበራዊ ገጽታቸው አንፃር ተነስቶ በየዘሮቻቸው መመደብ ይቻላል:: የአንድን ዝርው ተረክ ልዩ ባህሪ፣ ከአቀራረብ ስልቱ ከጭብጡና ከማህበራዊ ፋይዳው(ጠቀሜታው) ተነስቶ በተለያዩ ምድቦች መክፈል ይቻላል Ben-Amos (1982)

Okphewho (1992) ቃላዊ ተረኮችን በየዘሮቻቸው ለመክፈል አራት ስልቶችን መጠቀም እንደሚቻል ይገልፃሉ:: ከእነዚህም የተረክ መክፈያ ስልቶች፣ የየተረኮቹን ዋና ዋና ገፀባህርያት መነሻ ማድረግ አንዱ ነው:: ሁለተኛው በተረኩ ይዘት አማካኝነት የሚገልፀው የትረካ ግብ/Purpose/ ነው:: ማለትም አንድ ዝርው ተረክ ለምን እንደሚተረክ / ለማስተማር፣ ለመምክርና የመሳሰለትን ጉዳዮች) መረዳት ይመለከታል:: ሦስተኛው የተረኩን መሠረታዊ ባህሪ (ታሪካዊ፣ ትሊያ ፣ግራገባኝ...) መነሻ በማድረግ የሚመድብ ስልት ሲሆን የመጨረሻው ተረኩ ከሚተረክበት አውድ ወይም አጋጣሚ አንፃር ተመልክቶ መመደብ እንዲቻል እኚሁ ምሁር ይገልፃሉ::

በአጠቃላይ ቃላዊ ተረኮችን በተለይም ዝርው ተረኮችን በየዘሮቻቸው ለመመደብ የሚያስችል አንድ ወጥ የሆነና ሁሉንም የሚያስማማ የምደባ ዘዴ የለም:: እስከ አሁን ድረስ በተረኮች ጥናት እጥቅም

# ምዕራፍ አራት

# የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች አካባቢያዊ ምደባና ማህበራዊ ፋይዳ ትንተና

## 4.1 የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች አካባቢያዊ ምደባ

የዚህ ንዑስ ምዕራፍ ዋና ዓላማ ቤንቾች ቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸውን እንዴት አድርገው በየዘሮቻቸው እንደሚከፋፍሉ ማሳየት ነው፡፡ በተጨማሪም የየዝርው ተረኮቹ ዘሮች መገለጫ የሆኑትን ልዩ ባህርያት መተንተንና መግለፅ ነው፡፡

ቤንቾች ቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸውን ቶስ እና ኤሽሽ በማለት በሁለት ምድቦች ይከፍሏቸዋል፡፡ ቶስ እውነተኛ፣ የተረጋገጠ ወይም እውነትነቱ የሚያደረስበትን ነገር የሚተርክ ነው፡፡ ፋይዳ ወይም ተግባሩም ማስተማር፣ መምከር፣ መተቸት፣ ወዘተ. ሲሆን የሚተረከውም በቀን ብቻ ነው፡፡ በተቃራኒው ኤሽሽ እና እውነትነታቸው አጠራጣሪ የሆነ ወይም የፈጠራ ጉዳዮችን የሚገልፅ ትረካ ነው፡፡ ኤሽሽ የክወና አውዱ በምሽት ሲሆን የትረካ ዓላማውም በዋነኛነት ለማዝናናት እና ለማስደሰት ነው፡፡

ዝርው ተረኮችን ከአካባቢያዊ ምደባ ዘዴ አንፃር ማጥናት ከፍ ያለ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ጠቀሜታ የየተረኮቹ ዘሮችን ልዩ ልዩ ባህርያት ለመረዳት ያስችላል፡፡ በተጨማሪም በያንዳንዱ የተረክ ዘር ውስጥ የሚካተቱ የተረክ አይነቶችን ተመሳስሎና ልዩነት ለመለየት ከማስቻሉም በላይ እንዲሁም በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ ያላቸውን ጠቀሜታ ለመግለፅ ያስችላል፡፡

ከዚህ ሀሳብ በመነሳትም የቤንች ዝርው ተረኮችን ልዩ ልዩ ባህርያት ቀጥሎ በዝርዝር እመለከታለሁ፡፡

### 4.1.1 ቶስ

በቤንች ቋንቋ "ቶስ" ማለት ታሪክ ወይም ታሪክነት ያለው ማለት ነው፡፡ በፎክሎራዊ ዘርነቱ ምንነቱን አስመልክቶ በመስክ ቆይታዬ የብሄረሰቡ አባላት የሆኑ አዋቂዎች (ሽማግሌዎች) የገለፁልኝ እንደሚከተለው ነው፡፡

"ቶስ ማለት ከአባት፣ ከአያት ወይም ከሽማግሌ የተሰማ እውነተኛ ታሪክነት ያለው ነው፡፡" አባማትዮስ ሻሽንቴት 17/03/99፣ ጌሊት ቀገማ)

"ቶስ ማለት በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚነገሩ ታሪኮች ናቸው። የሚነገሩትም ለመምከር፣ ለማስጠንቀቅ ወይም ለማስተማር ነው። ወይም ታሪክ የሆነ ትረካ ሲሆን ይችላል" (ቄስ ተገኝ ማርኩ 9/03/99 ዓ.ም. ሚዛን ከተማ 02 ቀበሌ)

"ቶስ ከአባቶቻችን፣ ከአያቶቻችን የሰማነው እውነተኛ ነገር ነው። ወይም ከአባቴ ሰማሁ፣ ከአያቴ ሰማሁ፣ ከእናቴ እናት ሰማሁ ወይም አንድ ነገር ሲደረግ አይቶ ወይም ተደረገ ሲባል የሰማውን እውነተኛ ታሪክ ሲናገር ነው" (ባብ ጣል ባይባ 19/03/99ዓ.ም. ሚያህ ቀገማ)።

"ቶስ ማለት አባቶች፣ ሽማግሌዎች፣ ትላልቅ ሰዎች የሚናገሩት ወይም ተናግረውታል የሚባል ታሪክ ነው። ወይንም አንድ ሰው በአንድ የሆነ ነገር የተነሳ ያደረገውን ወይም ያየውን ሲናገርና እከሌ የተናገረው ነው ተብሎ ሲነገር ቶስ ይባላል። ያስተምራል፣ ይመክራል፣ ሲተረክም ታሪኩ ሊያስደስት ይችላል" (ባብ ሲግ ባያ 3/04/99)።

በአጠቃላይ "ቶስ" ማለት ታሪክና ታሪክነት ያለው ወይንም እውነትነት ያለው ትክክለኛ የሆነ ጉዳይን፣ ሀሳብን ወይም ድርጊትን የሚተርክ ነው። በትረካው የሚገለፀው ሀሳብ ወይንም ድርጊት ደግሞ የሚታወቅ ወይንም እውነትነቱ የሚደረስበት ነው።

ቶስ ውስጥ የተለያዩ ዝርው የተረክ አይነቶች የሚካተቱበት ሲሆን፤ እነሱም ለየብቻ ስያሜ ወይም መጠሪያ የላቸውም። ሁሉም የሚጠሩት በተረኩ ዘር "ቶስ" ተብለው ነው። አባ ማትዮስ ሻሽንቴት ቶስ 57ን ሲተርኩልኝ "ይህን የአማሽለስንዶ ታሪክ ስነግርህ እንደአፈታሪክ አድርገህ እንዳትቆጥረው፤ እውነተኛ ታሪክ ወይም ቶስ ነው።" የሚል ጠንከር ያለ መግለጫና ምክር አዘል አስተያየት በማከል ነው። ይሁን እንጂ በአካባቢ ምደባ ስልት ቶስ በመባል የሚጠሩት ዝርው ተረኮች፣ አፈታሪክ፣ ገላጭ ታሪኮች (ሚት) እና አጫጭር ትረካዎች የተባሉ ንዑሳን የዝርው ታሪክ ዘሮችን በውስጡ ያካተቱ ናቸው። የቶስ ዋንኛ ተግባሩ አውድን መሰረት አድርገው በሚቀርቡ ልዩ ልዩ ክወናዎች አማካኝነት ማስተማር፣ መምከር፣ በማህበራዊና ግላዊ ህይወት ውስጥ የሚታዩ ህፀፆችን፣ ወቅታዊ ጉዳዮችን ካለፈውና ከመጪ ሁኔታዎች አንፃር አስተያየቶ መሄስ ነው። በቶስ ዝርው ትረካ ማዝናናትና ማስደሰት በሁለተኛ ደረጃ የሚታዩና ብዙም ትኩረት የማይሰጣቸው ናቸው።

የቶስ ዝርው ትረካ በቤንች ብሄረሰብ ባህልና ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው፣ ክወናውም ጥንቃቄ የሚደረግበት ነው። ከዚህ የተነሳም በማንኛውም ማህበራዊ አጋጣሚ ሲቀርብ ለትረካው ማጠንጠኛነት የሚመርጣቸው ይዘቶች በሙሉ የምርን የሆኑ ጉዳዮች ናቸወ ተብሎ ይታመናል። ስለዚህም አንድ ቶስ ባብ (ተራኪ) በአንድ

የትረካ አጋጣሚ ቶስ ሲያቀርብ ከማን እንደሰማ፣ ለምንስ እየተረከ ባለበት አውድ ማቅረብ እንደፈለገ በመግለፅ መልእክቱን መጥኖ ማስተላለፍ ይጠበቅበታል። በተጨማሪም በቤንች ብሄረሰብ ዘንድ ከቀደመው ትውልድ ተያይዘው የመጡና ለአሁኑ እንዲሁም ለቀጣዩ ትውልድ ጠቃሚ ናቸው የተባሉ እሴቶች ማስተላለፊያ ነው ተብሎ ይታመንበታል።

ስለዚህም በየትረካው አውድ የሚቀርቡትን ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች በጥንቃቄ መረዳት ከታዳሚው ይጠበቃል። ይህንንም ጠብቆ ለሌሎች የማስተላለፍ ሞራላዊ ግዴታ እንዳለበት በቤንች ብሄረሰብ ዘንድ ይታመናል።

የቤንች ቶስ ዝርው ተረክ ዘር በውስጡ ያካተታቸው ልዩ ልዩ የዝርው ተረክ አይነቶች ከፍ ሲል ተገልፀዋል። እነዚህን ልዩ ልዩ የተረክ ንዑሳን ዘሮች ባህርያት (ተመሳስሎና ልዩነታቸውን) በውል መረዳት አስፈላጊ ነው። በብሄረሰቡ ማህበራዊና ባህላዊ ህይወት ውስጥ ያላቸውን ፋይዳና በየአውዱ ሲከወኑ ያላቸውን ጠቀሜታ ወስኖ መመልከትም አስፈላጊ በመሆኑ ቀጥሎ ዋና ዋና ናቸው የተባሉትን የቤንች ቶስ ዝርው ተረክ አይነቶች እገልጻለሁ።

ለዚህ ጥናት ከመስክ የተሰበሰቡት የዝርው ተረክ መረጃዎች ብዛት በድምሩ 97 ነው። ከዚህ ውስጥ 77ቱ የቶስ ዝርው ተረኮች ናቸው። ከቶስ ዝርው ተረኮች መሀከልም 50 ዎቹ የቶስ አፈታሪኮች ናቸው። 18ቱ የቶስ ገላጭ ተረቶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ 9ኙ ደግሞ አጫጭር የቶስ ዝርው ትረካዎች ናቸው።

#### 4.1.1.1 የቶስ አፈ ታሪኮች

በአፈታሪክነት የሚጠቀሱት የቶስ ዝርው ትረካዎች በሙሉ ምንጫቸው በአንድ ወቅት የነበሩ ግለሰቦች ወይም በአካባቢው የተፈፀሙ ሁነቶች ናቸው። ስለዚህም ከመስክ የተሰበሰቡት የቶስ አፈታሪኮች በአብዛኛው በግለሰቦች ህይወት ዙሪያ የተነገሩ ሲሆኑ የተወሰኑት ደግሞ ጥናቱ በተከናወነበት አካባቢ የሚገኙ ልዩ ልዩ የቦታ፣ የመንደር ወዘተ. ስያሜዎችን የሚመለከቱ ናቸው። ይዘታቸውም በአብዛኛው ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ እና እምነት-ነክ ጉዳዮችን የሚመለከት ነው።

ሰዎችን/ግለሰቦችን አስመልክተው የሚተረኩ ልዩ ልዩ ተረኮችን በተለያዩ ምድቦች ከፋፍሎ ለማጥናት አንዱ ዘዴ Finnegan (1970:254) እንደገለፁት የነዚህን (የተጠቀሱትን) ግለሰቦች ማንነት መነሻ ማድረግ ነው። በዚህም መሰረት በአፈታሪክነት

የቀረቡት ታሪኮች በታዋቂ ግለሰቦች እና በተራ ሰዎች አንፃር የተነገሩ ተብለው በሁለት ተከፍለዋል፡፡

### ሀ. ታዋቂ (ታሪካዊ) ሰዎችን የሚመለከቱ አፈ-ታሪኮች

ታዋቂ (ታሪካዊ) ሰዎችን አስመልክተው የተነገሩ አፈ-ታሪኮች ትረካቸው በአብዛኛው የሚመለከተው የአካባቢውን ባህላዊ መሪዎች እና በአንድ ታሪካዊ ወቅት የኢትዮጵያ መሪ (አፄ) የነበሩ ሰዎችን ነው፡፡ ታዋቂ ግለሰቦችን የሚመለከቱና ተደጋግመው የሚነሱ አፈ-ታሪኮች መሀከል አብዛኛው ቤንችቴትን እና ልጅ ኢያሱን የሚመለከቱ ናቸው፡፡

ታዋቂ ወይንም ታሪካዊ ሰዎችን የሚመለከቱ አፈ-ታሪኮች በሚተረኩበት ጊዜ እጥቅም ላይ የሚውሉ የመክፈቻና የመዝጊያ ቀመሮች አሉ፡፡ የቶስ አፈ-ታሪኮች ትረካ ሁልጊዜ የሚጀምረው "ኑ አከስ ኢዝቅን ኑ አይጡሽ ቶስ" (አያቶቻችን ድሮ የነገሩን ታሪክ) በሚል የመክፈቻ ሀረግ ነው፡፡ ትረካው ማብቃቱንም ለመጠቆም እጥቅም ላይ የሚውሉት የመዝጊያ ሐረጎች "መኬ ቶሲ ቶስታ" ተብሎ ይተረካል፣ "መኬ መስታ" (ይባላል)፣ "መካስ መስታ" (ተብሎ ይነገራል) … ናቸው፡፡

በቤንች ባህላዊ መሪዎች እና በኢትዮጵያ መሪዎች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ የቶስ አፈ-ታሪኮች ታሪካዊነታቸው ያመሳስላቸው እንደሆነ እንጂ በየተረኮቹ የቀረቡትን ጭብጦች በማስተሳሰር የገቡት አቢይ የመባያ ጉዳዮች (motifs)[14] እየቅል ናቸው፡፡ ለአብነት ያህልም በቤንችቴት (የቤንች ንጉስ) እና በልጅ ኢያሱ አንፃር ከተነገሩት የቶስ አፈ-ታሪኮች መሀከል የተወሰኑትን አቀርባለሁ፡፡

#### ቤንችቴት

ቤንችቴትን እና ሌሎች የቤንች ባህላዊ መሪዎችን (ባላባቶች) በሚመለከት የቀረቡ አፈ-ታሪኮች ባብዛኛው የቤተሰብ፣ የጎሳ ታሪክ፣ የጋብቻ ህይወት፣ ባህላዊ የስልጣን ሽግግር፣ የመሪዎቹን ጉዞ፣ ጀብድ/መንፈሳዊና አለማዊ ተጋድሎ፣ ፍፁምነትና ቸርነት፣ ህልፈተ ህይወትና ከሞት በኋላ ስለሚኖራቸው መታወሻ ወዘተ. የሚመለከቱ ዋና ዋና ጭብጦች ናቸው፡፡ ይዘታቸውም ምድራዊና ሰማያዊውን በረከት ያዛነቁ ሲሆኑ እነዚህኑ አፈ-ታሪኮች (በአብዛኛው ሚታዊ ናቸው) የሚያገናኛቸው ክር ወይም ገገርው የመባያ ጉዳይ ልዕለ-ሰብ ባህርያቸው ነው፡፡ ወይም መሪዎቹ ከተራው ግለሰብ የተለየ ሃይል አላቸው ተብሎ

---

[14] ዮናስ አድማሱ (1998) የኢትዮጵያ ቃል ተረኮች (ኢ.ት.ሥጽ. 721) ለድህረምረቃ ተማሪዎች የማስተማር ርእሰ-ጉዳዮችና የክፍል ውስጥ ዳረጎት (የመጀመሪያ ትምህርት)

መታመኑ ነዉ። ወይም ባብ ሲግ ባያ እንዳሉት "በእኛ (ቤንች) ባህል መሠረት አንድ ሰው ቤንችቴት ሲሆን ተራ ሰው መሆኑ ይቀራል።" በተጨማሪም ይህን መሰል ሚታዊ አፈታሪክ ያላቸው ታዋቂ ግለሰቦች ወይም ባህላዊ መሪዎች፣ ነገስታት፣... የሚመለከቱ ዝርው ትረካዎች ሲጠኑ/ እኒሁ ታዋቂ ናቸው የሚባሉት ግለሰቦች ለስልጣን የበቁበትን ወይም የሚበቁበትን ባህላዊና ማህበራዊ ልማድ የሚመለከቱ አፈታሪኮች ጀምሮ ሊጠኑ ይገባል። Finnegan (1970)። ቤንችቴትን የሚመለከቱ አፈታሪኮች ጭብጥ የሚከተሉት ናቸዉ።

የቤንችቴት ሆኖ ስለመመረጥ፡-

ቶስ 3 ... ቤንችቴት የሚመረጠው ... ንጉስ (ቴት) የነበረው አባቱ ሲሞት፤ ከልጆቹ (ከቤተሰቦቹ) መሀከል ፈጣሪ በመረጠው ላይ የሚያንነ መንፈስ ይወርድበታል ... ።

... ቤንችቴት ሆኖ አንድ ግለሰብ በፈጣሪ ትዕዛዝ/ፍቃድ መመረጡ የሚረጋገጠው በልዩ ልዩ ምልክቶች ነው። ከነዚህም መሀከል ቶስ 3 ... ካሽንካል የተባለች ወፍ ትመጣና በጭንቅላቱ ወይም በትከሻው ላይ ታርፋለች ... ። ወይም ቶስ 9 ... ታይቶ የማይታወቅ ዶፍ ዝናብ ወርዶ ... ። የመሳሰሉት ማስረጃዎች ናቸው።

የቤንችቴት ጋብቻ፡-

አንድ ሰው ቤንችቴት ሆኖ ሲመረጥ የሚያገባት ሚስቱ (ንግስት) የምትመረጠው፡-

ቶስ 4 ... ድንግሊቱ ከኩዌንኬስ ወይም ከኤርሰ ወይም ቶም (ጎርሸ) ከሚባሉት የቤንች ንዑስ ነገዶች መሀከል ከአንዱ ነው። ከመጀመሪያዋ የሚወለደው ልጅ "ታታ ኮይናንስ" ሁለተኛዋ ተመርጣ ከሆነ የሚወለደው ልጅ "ታታ ጋሻናንስ" ወይም በሶስተኛ ደረጃ ከተጠቀሰው ቶም (ጎርሸ) ተመርጣ ከሆነ የሚወለደው ልጅ "ታታ ጊሽቱናንስ" ተብሎ ይጠራል። በተጨማሪም ይህ የናት ዘር ሀረግን ታሳቢ አድርጎ የሚሰጠው ስያሜ በንግስና ዘመንም ቀጣይ ነው። ለምሳሌ ያህል በአሁኑ ወቅት በደቡብ ቤንች ወረዳ ዞዞ ካርሽታ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪ የሆኑት አምስተኛው ቤንችቴት መጠሪያ ስማቸዉ ቤኑሽታቶ ጋይስ ጊሽቱናንስ የሚል ነው።

ቤንችቴትን በሚመለከት የተነገሩ የቶስ አፈ-ታሪኮች የሚከተሉትን ጭብጦች ይመለከታሉ፡፡

**በረከት**

ቤንችቴት የቤንች ባህላዊ አስተዳደር የመጨረሻው ከፍተኛ እርከን ላይ የሚገኝ -ቴት (ንጉስ/ንጉሰ ነገስት) ነው፡፡ በቤንች ባህላዊ እምነትና አስተዳደር ከፍተኛው እርከን ላይ የሚገኝ በመሆኑም ሀላፊነቱን ለመወጣት ልእለሰብ የሆነ ስልጣን አለው ተብሎ ይታመናል፡፡

> ቶስ 5 ... እርሱ (ቤንችቴት) ምድርን (ሀገረ-ቤንች) ስለሚባረክ ከብቶች ይረባሉ፤ እህል ይትረፈረፋል፣ ንቦች ማርን በቀፎ ይሞላሉ፤ ዝናብን ያዘንባል፤ ድርቅን (የፀሐይ ሀሩርን) ይገስፃል፤ የበሽታ መንፈስ በሀገር እንዳይገባ ያዛል፤ ፍቅር እና ብልፅግናን ያትረፈርፋል ...፡፡ በማለት በብዛት ይተረካል፡፡

በተጨማሪም በአብዛኛዉ በብሄረሰቡ አባላት ዘንድ ቤንችቴት ይፈራል፣ ይከበራል፡፡ ቶስ 7 አኗኗሩም ሆነ እንደ ቶስ 8 አመጋገቡም ልዩ ነው ተብሎ ስለሚታመን፡፡ አይጨበጥም " ... ተራ ሰው መሆኑ ይቀራል፡፡" ስለሆነም በባህላዊ መሪነቱ ፍፁም ነው ተብሎ ስለሚታመን፡፡ ለየትኛውም ወገን አያዳላም ይባላል፡፡ ወይም አያደላም፡፡ ባብ ሲግ እንደገለፁትም፡-

> ... ቤንችቴት አንዱ መለያቸው ባለባበሳቸውም ሆነ በማህበራዊ ኑሮ ግንኙነት ሁል ጊዜ ራሳቸውን ወደ ተራው ህዝብ ያቀርባሉ፡፡ ግጭታቸው በስራቸው ካሉትና በባህላዊ የስልጣን ተዋረድ መሰረት በሚታዘዟቸው ባለባቶች (ቤንችቲያት ...) ጋር ነው፡፡ ስለዚህም ቤንችቴት ባገኙት አጋጣሚ ከተራው ሰው ጋር ለመቅረብ በሚያደርጉት ጥረታቸው እና ባላባቶቹ በሚሰሯቸው ተግባራት በሚፈጠር ግጭት የተነሳ ህይወታቸው ለአደጋ ይጋለጣል (29/03/1999 ዓ.ም ዳቸበስ ቀገማ፡፡)

## ልጅ ኢያሱ

ከ1898 እ.ኤ.አ. ጀምሮ እስከ አለንበት ዘመን ድረስ የቤንች ብሄረሰብ ከኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት ጋር የመሰረተው ታሪካዊ ግንኙነት አለው። በዚህ የተነሳም በተለያዩ የታሪክ ወቅቶች የተነሱ የኢትዮጵያ ነገስታትና ታዋቂ የጦር መሪዎች ምድረ-ቤንች (ቤንች ዶድ) ተጉዘው ከህዝቡ ጋር ቆይተዋል። ይሁን እንጂ ወደ አካባቢው ከሄዱት መሪዎች እና የጦር አዛገዦች መሀከል በዝርው ተረኮች ተገልጾ የሚገኙት ልጅ ኢያሱን የሚመለከቱ አፈታሪኮች ናቸው። ልጅ ኢያሱን በአሉታዊም ሆነ በአዎንታዊ መንገድ የሚገልፁ በርካታ ዝርው ተረኮች በቶስ አፈታሪክነት ይነገራሉ። ምናልባትም ከቤንችቴት ቀጥሎ የሚተረኩ አፈታሪኮች በልጅ ኢያሱ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ለመሆናቸው ለዚህ ጥናት የተሰበሰቡ ጥቂት መረጃዎች ያሳያሉ። በአካባቢው ነዋሪ (አረጋውያን፣ ጎልማሶች) ዘንድ "ያሱ"፣ "ጃሱ" የሚሉ ስሞች በቶስ ትረካ ወቅት በተደጋጋሚ ሲነገሩም ይሰማል።

ስለዚህም ልጅ ኢያሱ በቤንች ቶስነት መነሳታቸው በሁለት ምክንያቶች ነው። ከግለሰቡ ማንነትና ወደ አካባቢው ገብተው የወጡበት አቅጣጫ ነው ብሎ የዚህ ጥናት አቅራቢ ያምናል። እነርሱም፡- አንደኛ የልጅ ኢያሱ (ለጥቂት ዓመታትም ቢሆን) የኢትዮጵያ መሪ (ንጉስ) መሆናቸው ነው።

> ቶስ 12 በእኛ በቤንች ሀገር ከቤንችቴት (ከቤንች ንጉስ) በስተቀር ሌላ ንጉስ አናውቅም ነበር። ይሁን እንጂ ያሱ (ልጅ ኢያሱ) ወደዚህ አካባቢ ለመጀመሪያ ጊዜ የመጡ ቤንች ያልሆኑ ንጉስ ናቸው። የቤንች ምድርን መሀል ለመሀል (እንብርቱን) ሰንጥቀው በመግባት ለመጀመያ ጊዜ ምድሩን የረገጡ ቤንች ያልሆኑ ንጉስ "ያሱ" ናቸው። ... (ባብ አስፋ ወሰኑ) 20-03-1999 ዓ.ም ጌሲት ቀገማ)

ሁለተኛው ምክንያት እኚሁ ታዋቂ ግለሰብ (የሀገር መሪ) ወደ ቤንች ዶድ (ሀገረ ቤንች) የገቡበትና የወጡበት አቅጣጫ ነው። እንደሌሎቹ የቤንች አዋቂዎች (ሽማግሌዎች) ባብ አሽኩ ባንገርስም ልጅ ኢያሱን የሚመለከተውን የቤንች ቶስ ሲነግሩኝ ያሉት (በጣቶቻቸው ደቡብ አቅጣጫን እያመለከቱ) "ቶስ አሽ ኢያርዳ" (በዚህ ታች በኩል ገቡ) በተመሳሳይ ሁኔታ (በጣታቸው ሰሜን/ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫን እያመለከቱ) "ዚያፅ አንቀዎ ..." (በላይ በኩል ሂዱ/ውጡ ...) በማለት ነበር።

ይህም ቶስ 13፦ ልጅ እያሱ ወደ ቤንች ሀገር የመጡት (የገቡት) (በዛሬው ደቡብ ቤንች ወረዳ) በፓሻ (አይናምባ) በኩል ወይም ኪታች በብርሃን (የቦታ ስም ነው) በኩል አድርገው ነው …

የልጅ ኢያሱ አወጣጥን አስመልክቶ በቶስ 15 እንደተገለፀውም፦

"… ይሁን እንጂ ሲዝ (የዛሬው ሼ ቤንች ወረዳ አካባቢ) ሲደርሱ ከፍተኛ ውጊያ ገጠማቸው። ኢያሱ ጋርም ባደረጉት ውጊያ በሲዝ አካባቢ ነዋሪ በሆኑት የብሄረሰቡ አባላት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደረሰባቸው። እስከ አርባ ሺህ የሚደርስ ሰው ምርኮኛ ሆኖ በባርነት ወደ ሆጨጫ (አዲስ አበባ)፣ ጉሬና ሌሎች አካባቢዎች ተግዟል …" (ቄስ ተገኝ ማርኮ)

በቶስ 13 እና ቶስ 15 ትረካዎች ውስጥ የሚነሱት "በፓሻ በኩል ከታች …" እና "ሲዝ (ሼቤንች) …" የሚባሉት ሁለት አካባቢዎች (ቦታዎች) በቤንች ቶስ ትረካ ውስጥ ሃይማኖታዊ ይዘትን የሚመለከት ዱራ አላቸው። ለምሳሌ ያህል በቶስ 25 በሰው ልጅ ክፉ ባህሪያትና ድርጊት አዝነው "ያረጉት" የሄዱትን የኦማሸለስንዶ ገድል እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ።

> ኦማሸለስንዶ በዓለም የመጨረሻ ቀን (ምፅኣት) ለፍርድ ይመጣሉ። ይሁን እንጂ እርሳቸው ከመምጣታቸው በፊት የሚፈፀሙ ትንቢቶች አሉ። ከነዚህም መሀከል … የመጨረሻው ምልክትም ክፉ ረሃብ በሀገር ሙሉ ይገባል። ይህም የፍርድ ቀን (የኦማሸለስንዶ መመለሻ) የመጨረሻው መቃረቢያ ነው። ኦማሸለስንዶም ለፍርድ ሲመጡ የመጨረሻ ሁለት ድንኳኖች ያጊጦል እና ሲዝ ላይ ይተከላሉ። የሰው ልጅም በእውነተኛ ስራው ይፈረድበታል (ባብ ዊኒያ ዳቹ 20-03-1999 ዓ.ም. ጌሲት ቀገማ)።

በቶስ 25 ውስጥ የተጠቀሱት ሁለቱ ቦታዎች "ያጊጦል" እና "ሲዝ" በቅደም ተከተል የመጀመሪያው ደቡብ ቤንች ወረዳ አይናምባ (ፓሻ) በታች የሚገኙ ቦታዎችን የሚመለከት ሲሆን "ሲዝ" ሼቤንች ወረዳ ውስጥ የሚገኝ ነው በማለት እኚሁ የቤንች ቶስ አቀባይ አስረድተውኛል። በተጨማሪም ይህ ሲዝ ይገኝበታል በማለት የተገለፀው የሼቤንች ወረዳ የቤንች ብሄረሰብ መነሻ እንደሆነ ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ተመልክቷል።

በመጨረሻም የልጅ ኢያሱ በደቡብ ቤንች ወረዳ (አካባቢ) ቆይታን አስመልክቶ ከሚነገሩት የቶስ አፈታሪኮች መሀከል አንዱ በነባብ አበሽ ቱጊ የተገለፀው ነው። አባቴ በልጅነቴ ከነገረኝ ቤንችቶስ አንዱ ልጅ ኢያሱ ከዚህ የእኛ አካባቢ (መከተን) እየተነሱ ማጅ

ደርሰው ይመለሱ ነበር፡፡ አንዴ ከማጅ ወደ እኛ ሲመለሱ (የካሹ ወንዝን ተሻግረው) በአካባቢው በብዛት የሚበቅለው የኪርሹ ቁጥቋጦ እየጠለፈ ይጥላቸው ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ይናደዱና በአካባቢያቸው የነበሩትን የቤንች ተወላጆች፡- "… የዚህ አገር ገበሬ ይህንን ለም መሬት ለምን አያርሰውም፡፡ በሉ ከዛሬ ጀምሮ እናንተ ይህን አካባቢ መንጥሩና እረሱት እኔ ደግሞ ከሌላ ቦታ የቡና፣ የሙዝ፣ የፓፓያ ዘር አመጣላችኋለሁ አሉ ይባላል"፡፡ (አበሽቱጊ)

በዚህ የተነሳም ዛሬ በቤንች ቋንቋ ውስጥ ገበሬ የምትለዋ ቃል በውስት የመጣችው በጊዜው የነበሩት አያቶቻችን ከኢያሱ ሰምተዋት ነው፡፡ በተጨማሪም ዛሬ በደቡብ ቤንች ወረዳ በብዛት የሚመረተው ቡና እና ልዩ ልዩ የፍራፍሬና አትክልት ዘር በመጀመሪያ በኢያሱ ቀጥሎም በፊታውራሪ ዓለማየው ፍላቴ የመጣ ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ ታዋቂ ግለሰቦችን ማዕከል አድርገው የሚተረኩ የቤንች ቶስ አፈታሪኮች የወል ባህርያቸው በመክፈቻ ቀመርነት ከማን እንደተደመጡ መገለፁ፣ በጭብጣቸውም የሚያነሱት ጉዳይ አንድ መሆኑ፣ በነጠላ ገጠመኝ ወይም ድርጊት ላይ የሚያተኩሩ መሆናቸው ነው፡፡

### ለ. ተራ ግለሰቦችን አስመልክቶ የሚነገሩ የቶስ አፈ ታሪኮች

ከመስክ ከተሰበሰቡት የቶስ አፈታሪኮች መሀከል በዚህ ንዑስ ምድብ ስር የሚካተቱት 18 ናቸው፡፡ እነዚህ ተራ ግለሰቦችን አስመልክተው የሚነገሩ አፈታሪኮች ከሌሎቹ የቶስ ዝርው ትረካዎች በአቅራረብ ስልታቸው፣ በታሪካቸው አወቃቀርና በሚያነሷቸው ጭብጦች ይለያሉ፡፡

ተራ ግለሰቦችን የሚመለከቱ አፈታሪኮች በአቀራረብ ስልታቸው በትረካው መጀመሪያ ላይ የገፀባህርያቱን ዳራ የሚመለከቱ አጠቃላይ መግለጫዎችን በማቅረብ በግል ስም (የተፀውዖ ስም) ተለይተው የማይጠሩ ገፀባህርያትን አስተዋውቀው ወደ ተረኩ ትልም የሚገቡ ናቸው፡፡ በትረካቸው መጨረሻ ላይም "መኬ ቶሲ ቶስታ" (ተብሎ ይተረካል)፤ "መኬ መስታ፡፡" ( … ይባላል) እና "መስታ" (ይባላል) በሚሉ ሀረጎች የትረካውን ማብቃት ለታዳሚዎቻቸው በተራኪዎቹ አማካኝነት የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ ምሳሌዎች፡-

ቶስ 32 "ካብቴት በሚባሉ አማልክት ታምነው የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ አሉ፡፡"

ቶስ 33 "አንድ ባላባት ነበር አሉ፡፡ የመሞቻው ጊዜ ደርሶ ስለነበር ከመሞቱ በፊት እያቃሰተ ልጁን አስጠርቶ መናዘዝ ፈለገ፡፡"

ቶስ 35 "ድሮ ነው አሉ፡፡ አንድ በጎረቤቱ መበልፀግ እየተቆጨ የሚኖር ሰው ነበር አሉ፡፡

ተራ ግለሰብን አስመልክተው የሚነገሩ የቶስ አፈ-ታሪኮች ጭብጥ በእለታዊ የማህበራዊ ኑሮ ግንኙነት ውስጥ የሚከሰቱ ልዩ ልዩ ጉዳዮችን በጭብጥነት የሚያነሱ ናቸው፡፡ ከነዚህም መሀከል እምቢኝታ፣ እርቆ አሳቢነት (ብልጠት)፣ የአዋቂ (ሽማግሌዎች) ምክርን የመቀበል አስፈላጊነት በተደጋጋሚ በየተረኮቹ ውስጥ ይገኛሉ፡፡

ትዕዛዝ ማፍረስ

አንድ የተከለከለ ነገር ወይንም እገዳን አለመቀበል ወይም ለመቀበል ፍቃደኛ አለመሆን ተራ ግለሰብን በሚመለከቱ የቶስ አፈ-ታሪኮች ውስጥ በተደጋጋሚ የሚነሳ ጭብጥ ነው፡፡

ቶሷ 32 ... ካብቴት በሚባሉ አግልክት ታምነው የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ አሉ፡፡ በአንድ ዘመን እነዚህ ባልና ሚስቶች በሚኖሩበት አካባቢ እህል በአገር ጠፋና ችግር ሆነ፡፡ "ምን ይሻለናል?" ብለው ባልና ሚስቱ አሰቡ፡፡ በዚህን ጊዜ ባልየው፡-

"እንደው ምስጢር የማታወጪ ከሆነ አንድ ነገር ብናደርግ ምናለ?" አላት፡፡

"ምንድነው?" አለች ሚስቱ፡፡

"አይ ይህ የርሃብ ዘመን እስኪያልፍ የሚደማ ነገር አግኝተን ብንበላ ምናለበት?" አላት፡፡

"የሚደማ ነገር?"

"አዎ!"

"የሚደማ ነገር ከተገኘማ ምን ችግር አለ?" አለችው፡፡

"የሚደማ ነገር በልተን ነገ ሚስጢር ካወጣሽ ግን ስማችን ይጠፋል፡፡ ሆኖም የሚደማ ነገር አግኝተን ከበላን በኋላ ይህ ቀን አልፎ አንድ ቀን ብንጣላ እንኳ ምስጢር የማታወጪ ከሆንሽ እንማማልና ሄጀ ላምጣ" አላት፡፡

ሚስቱም ዛሬ በሚስጢር የሚያደርጉትን ሁሉ ይህ የርሃብ ዘመን ሲያልፍ ላታወጣ ማለች። ሰውየው ከባለቤቱ ጋር ምስጢር ላያወጡ ከተማማሉ በኋላ ጫካ ሄዶ አውሮ ገድሎ መጣ። ... በላ።

በቶስ 32 እንደተመለከተው ገፀባህርያቱ በልማድ እንዳይመገቡ የሚከለከለውን "የሚደማ ነገር" ተመገቡ።

ቶስ 33 ... አንድ ባላባት ነበር አሉ። የመሞቻው ጊዜ ደርሶ ስለነበር ከመሞቱ በፊት . እያቃሰተ ልጁን አስጠርቶ መናዘዝ ፈለገ። ተጠርቶ የመጣው ልጁም ወደ አባቱ ቀርቦ፡-

"ምነው አባቴ ደከመህ ወይ?" ብሎ ጠየቀው።

"አዎ ልጄ ደከመኝ ከመሞቴ በፊት የምነግርህ ነገር ስለአለ ነው ያስጠራሁህ" አለው። ቀጠለናም፡-

"ልጄ በህይወት ዘመንህ እመንገድ ዳር ጥንቅሽ እንዳትዘራ፣ የሰውን ሚስት እንዳታባልግ፣ የሰው ዲቃላም ወደ ቤትህ አምጥተህ እንዳታሳድግ" ብሎ መከረውና ሞተ።

ይሁን እንጂ በቶስ 33 ልጅ ከአባቱ የተቀበለውን የኑዛዜ አደራ ሽሮ "አታርግ" የተባለውን ደርጊት ፈፀመ።

በአጠቃላይ ተራ ግለሰብን የሚመለከቱ አብዛኛዎቹ አፈታሪኮች ውስጥ የሚገኙ ገፀባህርያት አንድ የሆነ እገዳ/ክልከላን ማለትም መሃላ (ቃል ኪዳን)፣ ምግብና የመሳሰሉትን አስመልክቶ የተጣሉ እገዳዎችን "አሜን" ብሎ ከመቀበል ይልቅ በተቃራኒው ሲፈፅሙ ይታያሉ።

እነዚህን የእምቢኝታ ጭብጥ አላቸው ተብለው የቀረቡትንና ሌሎች ተመሳሳይ አፈታሪኮችን በተመለከተ ሊገለፅ የሚገባው ጉዳይ አለ። ይኸውም አንድን እገዳ/እቀባ መቀበልን እምቢ በማለት የሚነሱት በሙሉ ወንድ ገፀባህርያት ሲሆኑ እነርሱን በመቃወም የተሳሉት ሴት ገፀባህርያት ናቸው። እንዲሁም በአብዛኛዎቹ አፈታሪኮች ውስጥ ትረካው የሚያጠነጥነው በቤተሰብ/ትዳር ህይወት ዙሪያ መሆኑ ነው። ለምሳሌ ከላይ በተከታታይ በቀረቡት 2 አፈታሪኮች ውስጥ የሴት ገፀባህርያቱ ተግባር የተገለፀው በሚከተለው መልኩ ነው።

ቶስ 32 … በሽማግሌዎች ፊትም ቆመው እያሉ፦

"አንተ ሰውዬ ከፊሰግክ ጉድህ ነው የማወጣው" አለችው።

"ምን ጉድ አለኝ?" አላት ባልየው።

"እንዴት! አንተ እኮ በዛ ክፉ ቀን ከጫካ የማይበላ አውሬ አድነህ የበላህ ነህ!" …

ቀጥሎ በቀረበው የቶስ 33 ትረካ ተመሳሳይ ሀሳብ ተገልጿል። … የአባቱን ምክር ረሳና … እመንገድ ዳርም ጥንቅሽ ዘራ። … ያቺ መንገድ ዳር የዘራትን ጥንቅሽ እረኞች ሰብረው ሲበሏት አገኘ። … ወደ ቤቱም እንደደረሰ ሚስቱን "አንቺዬ ያ እመንገድ ዳር የዘራሁትን ጥንቅሽ እረኞች ሰብረው ሲበሉት ደረስኩ። ተናድጀም ስለነበር አንዱን እረኛ መትቼ ገደልኩት" ብሎ ነገራት። እሷም መልሳ "እንዴ የሰው ሰው እንዴት ትመታለህ/ትገላለህ?" አለችውና … እየሮጠች ሄደችና ሞተ ለተባለው ልጅ አባት ባሏ ልጃቸውን እንደገደለ ነገረች …

## የሽማግሌ (አዋቂዎች)ን ምክር የመቀበል አስፈላጊነት

ቶስ 43 … ኩዣብ (አዋቂ) እንድ ሰውዬ መጥቶ "ሰው ሁሉ ጠላኝ ምን ይሻለኛል? እባክም ለዚህ የሚሆን መፍትሄ እርስዎ አይጠፉም ይምከሩኝ" በማለት ቤቱ ደረሰ ሄዶ ጠየቀው "ነገ ጥዋት ተመልሰህ ና" ብሎት ኩዣብ ሰውየውን አሰናበተው። ባለጉዳዩም በተሰጠው ቀጠሮ መሰረት በነጋታው ጥዋት እኩዣብ ቤት ተመልሶ መጣ። በዚህን ጊዜ ኩዣብ በሩን ከፍቶ ራቆቱን በመሆን አፉን በአንድ እጁ፣ ብልቱን እንዲሁ በአንድ እጁ ሸፍኖ ቆመ። ያ ባለጉዳይ ሰውየው ወደ ኩዣብ እንዳይጠጋ ራቁቱን ሆኖ መቆሙ፣ እንዳያናግረውም አፉን በእጁ የከደነ በመሆኑ ተጨነቀና በርቀት ቆመ። ኩዣብ ወዲያው ብልቱንና አፉን ለቆ የሆነ ምልክት (የምንጣሮ እና የእርሻ) አሳየው። ይህንን ጉዳይ የተመለከተው ሰውዬ ወደ ቤቱ እንደተመለሰ የኩዣብ ድርጊት የሚፈታለት አዋቂ ሽማግሌ ፈልጎ አገኘና ሁኔታውን ሁሉ እንዲህ ብሎ አስረዳ … ወዲያውም ሽማግሌው "አይ ልጄ! ኩዣብ ችግርህን ተረድቶ መልሱን ነግሮሃል፤ አንተ ባለመረዳትህ ነው እንጂ!" አሉት " … ልጄ ኩዣብ እንደነገረህ አንደኛ እጁን በአፉ ላይ አድርጎ መቆሙ" አላግባብ ሰውን አትዝለፍ፣ አታዋርድ ማለት ነው። ሁለተኛው ብልቱን በእጁ አፍኖ መቆሙ "የሰው ሚስት በመድፈር ወይም

በማባለግ ትዳር አትበጥብጥ" ማለቱ ነው፡፡ ስለዚህ ከሰው ጋር አትጣላ፣ ጭቅጭቅ አታንሳ፣ ፀባይህን አሳምረህ የግብርና/እርሻ ስራህን በትጋት ስራ፡፡ ትበለጽጋለህ፣ የዛኔ ሰውም ይወድሃል፡፡ .... አሉት አዋቂው ሽማግሌ ... ሰውዬውም ምክሩን ተጠቅሞ፣ ራሱን ለውጦ ቀሪ ዘመኑን በደስታ ኖረ ይባላል፡፡

## አርቆ የማሰብን ጠቃሚነት

ተራ ግለሰብን አስመልክቶ ከተነገሩ አፈታሪኮች መሀከል ተደጋግመው የሚተረኩት የአርቆ ማሰብ (ብልጥ የመሆንን) አስፈላጊነት የሚገልፁ ተረኮች ይገኛሉ፡፡

ቶስ 41 ... ድሮ ጊዜ አንድ ባላባት ነበር፡፡ በዚህ ባላባት ቤት ውስጥ የነበረው አገልጋይ አንድ ብቻ ነበር፡፡ ባላባቱ በቤቱ ውስጥ የተለያዩ አገልግሎቶች የሚሰጡ ሌሎች ሰዎችን መጨመር ፈለገና አብሮት ያለውን አገልጋይ ሀሳብ ጠየቀው፡፡

አገልጋዩም ሌሎች አጋሮች ወደ ባላባቱ ቤት ከመጡ የእርሱ ተፈላጊነት የሚቀንስ መስሎ ተሰማው፡፡ ወዲያው ለአሳዳሪው "ጌታዬ ይቺ አንዷን ጆሮየን ቢቆርጡዋት እኮ እሷን እያዩ ሌሎች አገልጋዮች ወደ እርስዎ ዘንድ ለመቀጠር ይመጣሉ" አለው፡፡ ይህንን የሰማው ባላባት የአገልጋዩ ሀሳብ እውነት መስለውና የአገልጋዩን አንድ ጆሮ ቆርጦ ጣለው፡፡

ይህ አንድ ጆሮው የተቆረጠበት የባላባቱ አገልጋይ በየመንደሩ ሲዞር ያገኙት ሰዎች "እባክህ እንዴት አድርገን ነው ያንተ አሳዳሪ ጋ መቀጠር የምንችለው?" ብለው ይጠይቁታል፡፡ እርሱም" ይቺን የእኔን የተቆረጠች ጆሮ እያያችሁ ግቡ "እያለ ይመክራቸዋል፡፡ እንዲህ እያለ በብልጠቱ፡- አንድ ጆሮውን ያስቆረጠው አገልጋይ ለብቻው እየተጠቀመ ኖረ ይባላል፡፡

በቶስ 41 እንደተገለፀው ሁሉ በቶስ 42፣ ቶስ 49 የግልም ሆነ በቤተሰብ ደረጃ ጥቅምን ለማስጠበቅ የሚከናወኑ ተግባራት ሁሉ በአርቆ አሳቢነት (በብልጠት) ሊሆኑ እንደሚገባ የቶስ አፈታሪኮች ይገልፃሉ፡፡

### 4.1.1.2 የቶስ ገላጭ ተረኮች

ቶስ በውስጡ ከሚያካትታቸው ዝርው ተረኮች መሀከል ሁለተኛው ምድብ ገላጭ ተረኮችን የሚመለከት ነው፡፡ እነዚህ ገላጭ ተረኮች፣ በቅርፃቸው አጫጭር ናቸው፡፡ የትረካቸው ትኩረትም በየተረኮቹ ጭብጥ አማካኝነት በሚነሱት ጉዳዮች ላይ ገለፃ ማድረግ ወይም ማብራሪያ መስጠት ነው፡፡

የቶስ ገላጭ ተረኮች አንዱ መለያቸው የመክፈቻና የመዝጊያ ቀመራቸው ነው፡፡ ልክ እንደ የቶስ አፈታሪኮች በተለይም 4.1.1.1. ሀ. በትረካቸው መክፈቻ ላይ "ኑ አከስ ኢዝቅን ኑ አይጡሽ ቶስ ..." አያቶቻችን እንደነገሩን ታሪክ ... በማለት የዝርው ተረኩን ዘር "ቶስ" በመጥቀስ ትረካቸውን በቀጥታ የሚጀምሩ መሆናቸው ነው፡፡

በተጨማሪም የቶስ ገላጭ ተረኮች በገፀባህርያትና በሚያስተላልፉት መልዕክት (ጭብጥ) የሚከተለውን ይመስላሉ፡፡

#### ገፀ ባህርያት

የቶስ ገላጭ ተረኮች ገፀባህርያት፣ ልዕለ ተፈጥሮኣዊ/ልዕለ ሰብ ሀይላት፣ እንስሳትና እፅዋት ናቸው፡፡

ልዕለ ተፈጥሮኣዊ/ልዕለ ሰብ ገፀባህርያት በገላጭ ተረኮቹ ትረካ ውስጥ፣ የፈጣሪነት (የመለኮት) ሀይል አላቸው፡፡ መፍጠር፣ መፍረድ፣ መስጠት፣ መንሳት የሚችሉ ናቸው፡፡ እነዚህም፡-

ምሳሌ፡- በቶስ 51 ... የሮ/የሮስንዶ (ፈጣሪ)

በቶስ 57 ... ኦማሸለስንዶ

ሁለተኛው የገላጭ ትረካ ገፀባህርያት እንስሳት (የቤትና የዱር) ናቸው፡፡ እነዚህ ገፀባህርያት በተፈጥሮኣቸው መደበኛ (ተራ) ባህርያት አይታዩባቸውም፡፡ እንደ ሰው ያስባሉ፣ ይናገራሉ፣ እምቢ ይላሉ ...

ምሳሌ፡- ቶስ 62 ... ውሻ

ቶስ 63 ... እባብ

ሶስተኛው የገላጭ ተረኮች ገፀባህርያት እፅዋት ናቸው፡፡ በተለይም ከአምልኳዊ ስርዓት አንጻር የሚታዩ ሆነው የልዕለ ተፈጥሯዊ ሀይል መከሰቻ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- ቶስ 56 ... አድባር

በአጠቃላይ በቶስ ገላጭ ተረኮች ውስጥ የሚገኙ ገፀባህርያት በጋራ የሚያንፀባርቁት ባህርያቸው ልዕለ ተፈጥሮአዊነት ነው፡፡

### ጭብጥ

የቶስ ገላጫ ተረቶች አንዱ መለያቸው በነጠላ (አንድ) ጭብጥ ላይ የሚያጠነጥነው ገለፃቸው ነው፡፡ በእነዚህ ገላጭ ተረቶች አማካኝነት የተገለፁት ጭብጦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### ዘፍጥረት (Creation)

ቶስ 51 "የሮስንዶ መሬትን (ዓለምን) ሲፈጥራት መጀመሪያ ላይ እጥፍጥፍ አድርጓት ነበር፡፡ ኋላ ላይ የሰው ልጅን ለመፍጠር ፈለገና ዘረጋጋት፡፡ የሰው ልጅም ከዛን ጊዜ ጀምሮ በምድር ላይ መኖር ጀመረ፡፡ ከሰው ልጅ በፊት የተፈጠረ ፍጡር የለም፡፡ ከሰው ልጅ ቀጥሎ በርካታ እንስሳት ተፈጥረዋል፡፡ ..."

### አምልኳዊ ስርዓት

ቶስ 56፡- የእኛ "ቤተክርስትያን" ማለት አድባራችን ነው፡፡ እዛው ስር ሆነን ፈጣሪያችንን ስለተለያዩ ጉዳዮች መለመን ወይም ማመስገን እንችላለን፡፡ ለዚህም ተግባር መጀመሪያ ለአድባሩ ቤት ይሰራል፡፡ ቀጥሎም ጥቁርና ቀይ በሬ ወይም በግ ይታረዳል፡፡ ይህም ፈጣሪያችን ጥሩ አዝመራ እንዲሰጠን ስንለምን ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ጥቁር በሬ ለጥሩ የበቆሎ አዝመራ፣ ቀይ በሬ ደግሞ ለጥሩ የማሽላ (ዶንቃ) አዝመራ ፈጣሪ እንዲሰጠን ስንለምን መስዋእት እናቀርባለን፡፡ በተጨማሪም በሰቀልነው ቀፎ ውስጥ ንብ ገብቶ ጥሩ የማር ምርት እንድናገኝ ጠጅ ይጠመቅና በመንደሩ የሚገኙ ሽማግሌዎችና አሮጊቶች በመሉ ተገኝተው እንዲመርቁ ይደረጋል፡፡ በእኛ ባህል መሰረት እንደዚህ አድርገን የሮስንዶን (ፈጣሪ) እናመልካለን፡፡ አምላካችንንም የምናገኘው በዚህ አድባር ስር ሆነን ስንለምነው ነው፡፡

በዚህ መሰል ገላጭ ትረካዎች የብሄረሰቡ ባህላዊ እምነት/ሃይማኖት ስርዓቶች ይገለፃሉ፡፡

**ቅጣት**

ቶስ 62 … "ሴቲቱ (መጀመሪያ የተፈጠረችዋ ናት) ውሻን ልትጎበኝ መጣችና አኩኄ! … አኩኄ! እያለች ተጣራች፡፡ ውሻ ግን ዝም አለች፡፡ በዚህ ድርጊቷም የተነሳ "ኡንክም ጋህ …" (ከዛሬ ጀምሮ ጭራሽን እያወዛወዝሽ ተናጋሪ) ተብላ በፈጣሪ በመረገሚ እንደሰው ልጅ መናገሯ ቀረ፡፡"

**መባረር**

ቶስ 60 … እንስሳት ጥንት ከሰው ልጅ ጋር በተቀራረበ አካባቢ አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ከእነዚህ እንስሳት አብዛኞቹ ሰርቶ መኖርን አልወደዱም፡፡ በዚህም ዛፍ ላይ የሚኖሩት መሬት ወርዶ ከመስራት፣ ምድር ላይ የሚኖሩት ወደ ሰው ልጅ ቀርቦ እየተጋገዙ ከመስራት ይልቅ የሰው ልጅ የሚያመርተውን እህል መፍጀት ስራቸው አደረጉ፡፡ በዚህም የተነሳ ሁሉንም የፈጠረው የሮ (አምላክ) እነዚህን እንስሳት በሙሉ ወደ ጫካ እንዲባረሩ አደረገ፡፡

**መመረጥ (ሽልማት)**

ቶስ 61 … "የሮሰንዶ ከፈጠራቸው እንስሳት መካከል ላም ከነጎሽ ጋር ተባራ ጫካ ውስጥ ትኖር ነበር፡፡ በኋላ ላይ ግን የሮሰንዶ መረጣትና የሰውን ልጅ እንድታገለግል ብሎ ወደ ቤት መለሳት፡፡ ከሰው ጋርም መኖር ጀመረች፡፡"

**የልዩ ልዩ ስርዓቶችና ልማዶችን ኬት መጥነት መግለፅ**

ቶስ 52 … ጥንት የሮ (አምላክ) መጀመሪያ ላይ የፈጠረው ሁለት ሰዎችን ብቻ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ወንድና ሴት ነበሩ፡፡ አብረው እየኖሩ ሳለ በወንዱና በሴቷ መሀከል ፍቅር ገባ፡፡ ቀጥሎም ተጋቡና ጐጆ ሰርተው የመጀመሪያው ትዳር ተመሰረተ፡፡ ከዚህ በኋላ ተዋለዱ፡፡ በተወለዱትም መሀከል ጋብቻ በመፈፀሙም በሰዎች መሀከል ዝምድና (ቤተሰብነት) ተጀመረ፡፡

በዚህ ንዑስ ምድብ ውስጥ ያሉ ገላጭ ትረካዎች ልዩ ልዩ ስርዐቶችና (የእምነት፣ የአሰራር፣ ግብርና ...)፣ ልማዶች መቼ እንደተጀመሩ፣ ምክንያታቸውንና ምንጫቸውን አስመልክቶ ገለፃ ያደርጋሉ።

**ምፅኣት**

የቶስ ገላጭ ተረቶች ምፅኣትን በሚመለከቱ ጭብጦች አማካኝነት የዓለመ ዓለማት ፍጻሜ፣ የሰው ልጅን የመጨረሻ እጣ ፈንታ ... ይገልፃሉ።

ቶስ 59 ... ኦማሽለስንዶ በዓለም የመጨረሻ ቀን ለፍርድ ይመጣሉ። ይሁን እንጂ እርሳቸው ከመምጣታቸው በፊት የሚፈፀሙ ትንቢቶች አሉ። ... የመጨረሻው የምፅኣት ምልክትም ከፉ ርሃብ በሀገር ሙሉ መግባት ነው። ... ኦማሽለስንዶ ለፍርድ ሲመጡም ሁለት ድንኳኖች “ያጊጦል” እና “ሲዣ” እሚባሉ አካባቢዎች (ደቡብ ቤንችና ሼቤንች ወረዳ ውስጥ ይገኛሉ) ይተከላሉ። የዚያን ጊዜ በየቦታው ጡርንባ ይነፋል። የሰው ልጅም በእውነተኛ ስራው ይፈረድበታል።

በአጠቃላይ የቶስ ገላጭ ተረቶች ጭብጥ የዓለመ ዓለማት እና የህይወት አፈጣጠርና ፍፃሜ፣ የብሄረሰቡን ባህላዊ እምነት አስተምህሮ፣ የሰው፣ የእንስሳት፣ የተፈጥሮ ክስተቶች ኬት መጥነትን ያስረዳሉ። በተጨማሪም በባህላዊና ማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ያሉ ስርዓቶች፣ ልማዶች (አሰራሮች) ምንጫቸውን ይገልፃሉ።

### 4.1.1.3 አጫጭር ትረካዎች (Anecdote Taes)

አጫጭር ትረካዎች በመባል በዚህ ጥናት የቀረቡት የቶስ ዝርው ተረኮች በአንድ አጋጣሚ ወይም በንግግር መከል በተለይም እየተነገረ ካለው ጉዳይ፣ አውድ ጋር አግባብነት ኖሯቸው የቀረቡ ዝርው ተረኮችን ናቸው። መደበኛ የመክፈቻም ሆነ የመዝጊያ ቀመር የላቸውም። ዋናው ግባቸውም በአጋጣሚ የተገለፀውን ሀሳብ አጉልቶ ማሳየት ነው። ከተሰበሰቡት መረጃዎች መሀከል እነዚህ አጫጭር ትረካዎችን የሚመለከቱት ቁጥራቸው እጅግ አነስተኛ ነው።

## ገፀ ባህርያት

የቶስ አጫጭር ትረካዎች ገፀባህርያት አይነታቸው በርከት ያለ ነው። እንስሳት፣ የአካል ክፍሎች፣ እፅዋት፣ የሰው ልጅ ባህርያት ሁሉ በነዚህ የቶስ አጫጭር ትረካዎች ውስጥ ገፀባህርይ ሆነው ገብተዋል። ለምሳሌ ያህልም፡-

ቶስ 69 ... እፉኝት

ቶስ 71 ... ዘላይዋ ሚዳቋ

ቶስ 74 ... ዋንዛና ፍሬዎቿ

ቶስ 70 ... የአባዩ በሬ ቆዳ

ቶስ 75 ... አፍና ጆሮ ... የመሳሰሉት።

## ጭብጥ

የቶስ አጫጫር ትረካዎች ዋና ግብ በጭብጣቸው አማካኝነት በተለይዩ ባህርያት፣ አሰራሮች፣ ላይ አስተያየት በመስጠት ታዳሚውን ማስተማር (መምከር) ነው።

ቶስ 75 ... አፍ ልክ ጥዋት ላይ ጆሮን ትጠራና፡-

"ኧረ ለመሆኑ እንዴት ነሽ ወይ?" ብላ ትጠይቃታለች። ጆሮም "አንቺ በውስጥሽ የደበቅሻት ያለችው (ምላስን ነው) እያለች ምን ደህና እሆናለሁ። ጠዋት ማታ በጥፊ እጠፈጠፋለሁ አለቻት አሉ።

እንደ ቶስ 75 በመሳሰሉ አጫጭር ትረካዎች አማካኝነት መጥፎ ባህሪ ያለው ሰው (አፉ እንዳመጣ የሚናገር፣ ለፍላፊ፣ ተሳዳቢ ...) ከራሱ አልፎ በቤቱም ሆነ በአካባቢው ላሉት ችግር የሚያመጣ መሆኑን ያሳያሉ።

ቶስ 73 ... እድል ይሁን አጋጣሚ አይታወቅም አንዳንዴ ነገሮች በተቃራኒ ሲፈፀሙ ይታያል። ለምሳሌ በሬ መሬትን አርሶ፣ አለስልሶ በቆሎ ይዘራል። ቡቃያ ሲሆን እንደገና በዛው በሬ ማሳው ይሸለሽላል (በአንድ ቦታ የበዛ ቡቃያ እህልን ማሳሳት ነው)። ታድያ ምርቱ ደርሶ ወደ ጎተራ ከገባ በኂላ ለልዩ ልዩ ምግብ አይነቶች መሰሪያ ይሆናል። ተመልከት! በቆሎ ይለነቀጥና ተጨምቆ ቂጣ ይጋገራል። ለበሬ የሚሰጠው "ፋጭ" (ገለባ) ነው። ሆኖም ከሚጋገረው ቂጣ ባለቤቷ ቆርሳ የምትሰጠው ምንም

- ሳይሰራ ቀኑን ሙሉ ከቤት ጥላ ስር ተኝቶ ለሚውለው ውሻ ነው፡፡ የለፋው ተቀምጦ ያልሰራው ተጠቀመ ይላሉ አባቶቻችን፡፡

በዚህ አይነት አንዳንድ ተለምዷዊ አሰራሮች የአንድን ወገን ጥቅም ብቻ የሚያስጠብቁ መሆኑ ቶስ 73 ያስገነዝባል፡፡

በተጨማሪም ቶስ 69 የታላቆችን ምክር አለመስማት እና የሚያስከትለውን መዘዝ፤ ቶስ 70 የክፋት መጨረሻው ጥሩ እንዳማይሆን፤ ቶስ 72፡- እርስ በእርስ የመስማማትን ጠቃሚነት እና ቶስ 77 ነገሮችን አርቆ አለማየት ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን ይገልፃል፡፡

በዚህ ንዑስ ምዕራፍ መግቢያ ላይ እንደተገለፀው እነዚህ አጫጭር ትረካዎች በአጋጣሚ ወይም እየተነገረ ካለው ነገር ጉዳይ አውድ ጋር ተጣጥመው በንግግር መሀከል ይገባሉ፡፡ በአጋጣሚ ወይም በንግግር መሀከል ገብተው እየተገለፀ ያለውን ሀሳብ አጉልቶ ምስላዊ አድርጎ ለማቅረብ የሚጠቀሙበት ቋንቋ ዘይቤያዊ መሆኑ ነው፡፡ ይህንንም በሚከተለው ምሳሌ አቀርበዋለሁ፡፡

በ07/04/99 ዓ.ም. ጌሊት ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ በሚገኘው የአባ ማትዮስ ቤት ግቢ ውስጥ የቤንችን ታሪክ፣ ባህልና እምነትን አስመልክቶ እውቀት አላቸው ከሚባሉ የአካባቢው ሽማግሌዎች ጋር ተሰብስቤ (ተወያይቼ) ነበር፡፡ በዕለቱ ከቀኑ 5፡00 ሰዐት ጀምሮ የተሰበሰብነው 9 ሰዎች (አጥኚውና የመስክ ረዳቱን ጨምሮ) ነበርን፡፡

በአካባቢው (ደቡብ ቤንች ወረዳ ውስጥ) ያለው "የቤንች ማህበራዊ አኗኗር፣ ባህል እየተለወጠ ነው፡፡ ሰዎች በትንሽ በትልቁ ነገር ሲጨቃጨቁ ይሰማል፤ በአባቶቻችን ጊዜ እንደዚህ አልነበረም" በማለት አባ ማትዮስ ሻሸንቴት አስተያየት ይሰጣሉ፡፡ በተለይም ይህ ሁኔታ የተከሰተው "ሰው ከባህሉ፣ ከእምነቱ፣ እየራቀ መሄዱ ነው" ሲሉ ባብ ዊኒያ ዳቹ ሀሳባቸውን ገልፀው በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባብ አሰፋ ወሰኑ ቀጠል በማድረግ "ችግሩ የአዋቂ (ሽማግሌ) ምክር አለመስማትም ነው፡፡ ተው ይኸ ነገር ጥሩ አይደለም ብሎ ሽማግሌ ሲናገር ልጆች ብቻ ሳይሆኑ አንዳንዱ ትልቅ ሰውም (ጎልማሳ) አይደነግጥም፡፡ ይኸ ደግሞ በእኛ (ቤንች) ባህል የተለመደ አይደለም፡፡" በማለት የሚከተለውን ቶስ 69 ተናገሩ፡፡ "እፉኝት እባብ መልካ ያምራል፡፡ አይ ይቺ ነገር መልካ ያምራል፥ እስቲ ወገቤ ላይ እንደቀበቶ ልሰራት የሚል ሰው በእፉኝቷ ተነድፎ ይሞታል፡፡ የሰው ምክርም የማይሰማ ሰው እንደዚሁ ነው፡፡ መጨረሻው ክፉ ሞት ነው ይባላል፡፡"

በዚህ የባብ አሰፋ ንግግር መሰረት የሰው ምክር አለመስማት ባህሪ በእፉኝነት (የአባብ .ዘር) ተመስሎ ቀርቧል። ይህ የእባብ ዘር (ጠይቁ እንደተገለፀልኝ) ረግረጋማ (ጨፌያማ)፣ ሞቃት አካባቢዎች በብዛት ይገኛል። ከሌሎች የእባብ ዘሮች በሁለት ምክንያቶች ይለያል። የመጀመሪያው መልኩ (ቆዳው) በተለያየ ቀለማት ያጌጠ መሆኑ ነው። ሁለተኛው አንድን ሰው ወይም እንስሳ የሚያጠቃበት ባህሪው ነው። ይኸውም አብዛኛዎቹ የእባብ ዘሮች ሰውን ሆነ ሌሎች እንስሳት የሚነድፉት ሲጠጓቸው በመንከስ ነው። እፉኝት ግን በርቀት በትንፋሹ ነው። በዚህም ባንዴ መላ አካልን መመረዝና መግደል ይችላል። ስለዚህም የእፉኝትን መልክ (ቆዳ) ማማር ተመልክቶ ለማየት ወይም ለመያዝ የሚጠጋ ሞኝ ወይም የእባቡን ዘር ባህሪ የማያውቅ ብቻ ነው። ሁለቱም ግን በሚያደርጉት ሙከራ በትንፋሹ ተመርዘው ሊሞቱ ይችላሉ። የሰው (የሽማግሌ/አዋቂ) ምክርን የመናቅ፣ ያለመቀበል፣ የትዕቢት ባህሪ ባንድ ሰው ውስጥ ሲያድር ባለቤቱ ለጊዜው ምንም አይመስለው ይሆናል። ሆኖም ይህ ባህሪ ያለው ሰው ሁል ጊዜ ራሱን ለአደጋ ያጋልጣል። በዚህም ሊሞት ይችላል። ስለዚህም እንደእፉኝቱ መልክ የንቀት/ትዕቢት ባህሪ ከውጪ ሲታይ (ላንዳንዱ) ጥሩ ይመስላል። ሆኖም እንደእፉኝቱ መርዛማ ትንፋሽ በሰው ውስጥ ከገባ መጨረሻው ሞት ነው። "የአባቶቻችን ምክርና ተግሳፅ የማይሰማ ሞኝ ወይም አእምሮው የታመመ ብቻ ነው።" በማለት ባብ አሰፋ አስተያየታቸውን ደምድመዋል።

### 4.1.2 ኢሽሽ

ኢሽሽ- እውነትነቱ ፣ የማይታመን፣ ወይም የፈጠራ ታሪክ ወይም የቀልድ ነገርን፣ የማይሆን፣ ተቀባይነት የሌለው "አጣጥቃይፅ አይጡሽ ..." የሚናገር ትረካ ነው በማለት በቤንች ብሄረሰብ አባቶች ዘንድ ይገለፃል።

የኢሽሽ ዋና ተግባር ማስደሰትና ማዝናናት ሲሆን የሚተረከውም በምሽት ነው። ባብ ሲግ እንዳሉት "አድማጩም ዝም ብሎ መስማት እንጅ ተሳትፎ አያደርግም።" ተራኞቹም አብዛኛውን ጊዜ እናቶችና ጎልማሳ ወንዶች ናቸው። ሆኖም በሁለቱም ፆታ የሚገኙ አዋቂ ሰዎች አግኝነት በምሽት ጊዜ የሚከወነው ኢሽሽ ታዳሚዎች ህፃናት (ልጆች) ናቸው። የትረካው ዓላማም ህፃናት/ልጆች እራት ደርሶ እስኪመገቡ ድረስ እንዳይተኙ፣ የሚያለቅሱ ህፃናትን ለማባበል ወይም እራት ከተበላ በኋላ ልጆች እንቅልፍ እስኪይዛቸው ድረስ እንዲያዳምጡ በማለት ነው።

"ልጆች ለምን ቀን ላይ ኤሸሽ አይተረክላቸውም?" ለሚለው ጥያቄ ባብ ኤደን ቀጥሎ የሰጡት መልስ በቤንች ባህል መሰረት ኤሸሽ ለምን በምሽት እንደሚተረክ ምክንያቱን ያሳያል።

> እኔ በልጅነቴ ሲነገረኝ የነበረው፤ ዛሬም እኔ በተለይ ለልጆቼ የምመክረው ማታ ከቤት ሲነገር የሰሙትን ኤሸሽ ቀን ላይ ከብት ሲያግዱም ሆነ ጭራሮ ለመልቀም ከጓደኞቻቸው ጋር ወደ ጫካ ሲሄዱ እንዳይተርቱ ነው። ምክንያቱን በትክክል አላውቅም፤ ሆኖም ቀን ላይ ኤሸሽ ሲተረት የሚያዳምጡ ልጆች "ቀንድ ያበቅላሉ" ስለሚባል ነው (ባብ ኤደን ሸፈራዉ 28-03-99ዓ.ም ደቸበላ ቀገማ)።

ከዚህ የባብ ኤደን አባባል ጋር የሚገጣጠም ድርጊት በ21/03/99 ዓ.ም. ባብ ናካ ቤት ጊያዕቶሪ ሲጠጣ የተከሰተው ሁኔታ ነው። በዕለቱ የሰፈሩ ሰዎች፣ መንገደኞች ሰብሰብ ብለው ጨሞ ሲጠጣ ነበር። ባብ ናካ (ሲበዛ ጨዋታ አዋቂ ናቸው) "ለዚህ ሰው (ለእኔ) ቤንች ቶስ ንገሩት" በማለት ከጎረቤቶቻቸው ጋር አስተዋወቁኝ። ቀጥሎም ጎልማሳ የሆኑት ወንዶች ቶስ በመናገር ስፊ ተሳትፎ አደረጉ። ይሁን እንጂ የቤቱ እማወራም (ኬት ባይ) ሆኑ ከጎረቤት ለጨሞ ተጠርተው የመጡት ሴቶችም ሆኑ ልጆች አንድም ቃል አልተነፈሱም። በስተመጨረሻም እኒሁ የቤቱ አባወራ (ባብ ናካ) ድምፃቸውን ከፍ አድርገው "ኤሸሽ የሚናገር የለም እንዴ" የሚል ጥያቄ አዘል አስተያየት ጣል አደረጉ።

ከጥቂት ቆይታ በኋላም በዕለቱ የቤቱ እንግዳ የነበሩት ሽማግሌ ባብ ሶቴ ዳቻብ እንደማሳል አሉና "እኔ አንድ ኤሸሽ ልንገራችሁ ..." አሉና ከእግራቸው ስር ያስቀመጡትን ጨሞ አንስተው ለመጠጣት ጎንበስ አሉ። በዚህ ቅጽበት በቤቱ ሳሎን ውስጥ የነበሩ ልጆች ሹልክ እያሉ (አብዛኞዎቹ በጓሮው በር) ወጡ። ምክንያቱም ህፃናት/ልጆች ኤሸሽ በቀን ሲተረክ እንዲያዳምጡ አይፈቀድምና ነው። ባብ ሶቴም ያነሱትን ጨሞ አንድ ሁለቴ ፉት አሉና ብርጭቆውን መልሰው እግራቸው ስር በማስቀመጥ ኤሸሽ 15 የጅብ ዘፋኝ አጃቢ ልጃገረዶችን ተረት አሰሙ። በአጠቃላይ ኤሸሽ ለህፃናት ማዝናኛነት ተብሎ በዋንኛነት ይተረክ እንጂ በሁለተኛ ደረጃ ህፃናት (ልጆችን) ስነምግባር ማስተማርያ ተብሎም ይነገራል።

የኤሸሽ ዝርው ተረክ በትረካው መጀመሪያም እና መጨረሻ ላይ የመክፈቻና የመዝጊያ ቀመሮችን ይጠቀማል። በተደጋጋሚ እጥቅም ላይ ከሚውሉት የኤሸሽ የመክፈቻ ቀመሮች ውስጥ፡-

"ማጥ ጎቅን ..." (ከእለታት አንድ ቀን ...)

"ማጥ ናንሲ ..." (አንድ ሰው ነበር ...)

የሚሉት ናቸው፡፡

በኤሽሽ የመዝጊያ ቀመርነት የሚያገለግሉና ትረካው ማብቃቱን ለአድማጨ ጥቁምታ የሚሰጡትና የተዘወተሩ አባባሎች፡-

"መኬ መስታ ..." (አለ ይባላል)

"መስ መስታ ..." (ተብሎ ይባላል)

"መስታ ..." (ይባላል) የሚሉ ሐረጎች ናቸው፡፡

በኤሽሽ ትረካ ውስጥ በርካታ ገፀባህርያት የግል መጠሪያ ስም ሳይሰጣቸው በድርጊት ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡ ከነዚህ ገፀባህርያት አይነቶች መሀከል እንስሳት፣ ሰው፣ ልዕለሰብ ፍጡራን ይገኙበታል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በኤሽሽ ዝርው ትረካዎች ውስጥ በአቢይነት ወይም በንዑሳን ጭብጥነት የሚካተቱት ጭብጦች እንዲሁ በርካታ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ናቸው፡፡

ሀ. የትሊያ ተረቶች (Trickester Tales)

በኤሽሽ የትሊያ ተረቶች ውስጥ በመጠንና በአስተሳሰብ የተራራቁ የተለያዩ እንስሳትና የሰው ልጅ በዋና ገፀባህሪነት ተሳትፈው ልዩ ልዩ የማታለል፣ የማጭበርበር ... ድርጊቶችን ይፈፅማሉ፡፡ በተጨማሪም በነዚህ ተረቶች ዉስጥ የሚገኙት ገፀባህሪያት ዘብዛኛዉን ጊዜ የሚከሰቱት ጥንድ ሆነዉ ነዉ፡፡ ምሳሌ

ኤሽሽ 3 ... ሰውና አባብ

ኤሽሽ 4 ... ጦጣና ጅብ

ኤሽሽ 8 ... ነብርና ድኩላ

ኤሽሽ 16 ... ዝንጀሮና አዞ

ኤሽሽ 18 ... ንብና ዝንጀሮ የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

በተጨማሪም ከመስክ ከተሰበሰቡት የኤሽሽ ዝርው ተረኮች ውስጥ አብዛኛዎቹ በዚህ የትሊያ ተረቶች ውስጥ የሚመደቡ ናቸው፡፡ በትሊያ ተረቶቹ አማካኝነት የተገለፁት ዋና ዋና ጭብጦች፡- ማታለልን፣ ማጭበርበርን፣ ሐሰት መናገርን፣ ማስመሰልን በትላልቅ እና

በትናንሽ እንስሳት መሀከል የሚደረግ ፍልሚያን የሚገልፁ ናቸው። እነዚህ ጭብጦች የሚገልፁት ድርጊት የተረቶቹ አበይት ተጋዳሊዎች (heroes) ሆነ ብለው በተቀናቃኞቻቸው ወይም በየዋሆች ላይ በሚፈፀሟቸው ጊዜ ነው። ከድርጊቶቹም ውስጥ ወይም ከድርጊቶቹ የሚገለፁ ጭብጦች፡-

አታሎ ማምለጥ

ኤሽሽ 2 መንገደኛው አልለቅም ብሎ ይዞ ያደረውን የነብር ጭራ በአጠገቡ እያለፈ ለነበረው እንጨት ቆራጭ፥ አስይዞ ራሱ ያመለጠው በተደጋጋሚ ሲያቀርብለት በነበረው ልብን የሚያራራ ልመናው ነበር።

ሀሰት በመናገር (መዋሸት)

ኤሽሽ 4 እመንገድ ዳር የታሰረችው ጦጣ እንዳጋጣሚ የመጣው ጅብ ለምን እንደታሰረች በጠየቃት ጊዜ "ለእናትና ለአባቴ ተዝካር የተዘጋጀውን ምግብ አልበላም ብየ ነው" በማለት የሰጠችውን መልስ የሰማው ጅብ፥ "ይኸማ ምን ችግር አለው። እኔ እታሰርልሻለሁ አንቺ ሄደሽ የተዝካሩን ድግስ አምጪና እበላለሁ።" ባላት መሰረት በቦታዋ ተክታው ለማምለጥ ችላለች።

ቃልኪዳንን ማፍረስ

ኤሽሽ 8 የጠገበው ነብር ቅጠላ ቅጠል ፍለጋ ሲሄድ ያገኘውን ድኩላ እንዲያመልጠው ስላልፈለገ "የእስከዛሬው ጠላትነታችን ይብቃ፤ በጓደኝነት አብረን እንኑር ..." በማለት ያግባባውን ድኩላ መልሶ ሊበላው በያዘው ጊዜ በተፈጠረው ግብግብ የድኩላው ቀንድ የነብሩን ሆድ ተርትሮታል።

የወሰዱትን (የተቀበሉትን) መከልከል

ኤሽሽ 18 ንብና ዝንጀሮ መሀከል ለተፈጠረው ግጭት መነሻው፡-

... ወንድሞቻችን ዝንጀሮዎች እንዛመድ አላችሁ፤ እኛም እሽ አልን። የመጀመሪያውን የሠርግ ድግስ ደግሱ አላችሁ፤ እኛም የናንተን ወዳጅነት ስለፈለግን ድግሱን

በአምላካችንና በሰው ፊት በሚቀርበው ማር አደረግን፡፡ ... ይህንን የመሰለ አስፀያፊ ነገር (የዝንጀሮ ኩስ) ድግስ ብላችሁ ማቅረባችሁ ተገቢ ነው?

በአጠቃላይ በትሊያ ተረቶች ውስጥ የተገለፁት ጭብጦች የሚገለፁት የየተረኮቹ ዋና ተጋዳሊዎች በተቀናቃኞቻቸው ወይንም በየዋሆች ላይ በሚፈፅሟቸው ድርጊቶች ነው፡፡

## ለ. የአስማት ተረቶች /Magic Tales)

ከኤሽሽ ዝርው ትረካዎች መካከል የአስማት ተረቶች ምድብ ሁለኛው ነው፡፡ እነዚህ የአስማት ተረኮች ውስጥ አስማታዊ ተግባር ጎልቶ ይታያል፡፡ በተጨማሪም በአንድ የተረት ቅጽ የቀረቡት ወጥ ተረቶች በውስጣቸው ሁለት ወይም ሦስት ተረኮችን አካተው የሚይዙ ናቸው፡፡

የአስማት ተረቶች ገፀ ባህርያት እንስሳትና ልዕለሰብ /*Superhuman*/ የሆነ ባህሪ ያላቸው ፍጡራን ናቸው፡፡ የተረቶቹ ተጋዳሊዎችም የተለየ ተክለሰውነት (እጅና እግር የሌላቸው፣ ባለ አራት ቅንድብ . .... ) የተላበሱ ናቸው፡፡ ከነዚህም መካከልም የሚከተለትን በምሳሌነት መመልከት ይቻላል፡፡

**ኤሽሽ 1 ኩንድሌ - እጅና እግር የላትም፣ የተለየ የማስተዋል ችሎት ያላት ልጃገረድ**

- ሶቴት
- የጦጣ ቃልቻ
- የጉሬዛ ቃልቻ
- የድኩላ ቃልቻ
- የቃምጡት ልጅ

***ኤሽሽ 2 አዲኬ፡- ባለአራት ቅንድብ ልጃገረድ***

- የጫሪቴን ልጅ
- ጫርቴት

የኤሽሽ አስማታዊ ተረቶች በዋንኛነት አስማታዊ ተግባራት በማሳየት ላይ ያተኩሩ እንጅ በውስጣቸው የተለያዩ ንዑሳን ጭብጦችንም ይይዛሉ፡፡ ከነዚህም መካከል በአንድ ወይም በተለያዩ ተረቶች ውስጥ በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ጭብጦችን ቀጥሎ አቀርባለሁ፡፡

**መለወጥ**

***ኤሽሽ 1፡-***

ሀ. ...ኩንድሌን ለመብላት እጅግ የከጀለው ጅብ ባይሳካለትም ተስፋ አልቆረጠም፡፡ ምናልባት ሀሳብ ዘዴ ላገኝ እችላለሁ ብሎ የድኩላ ቃልቻን ሊያማክር ሄደ፡፡ ድኩላውም «አንተ እኛንስ አሳደህ ትበላን የለም ወይ! ስለምን ብለን ነው ላንተ የምንጠነቁል! እባክህ ጊዜህን ሳታጠፋ ሌላ ቃልቻ ጋ ሂድ» ብሎ አሰናበተው፡፡ ጅብም ሌላ ቃልቻ አሰበና፣ የጦጣ ቃልቻን ለመጠየቅ ሄደ፡፡ የጦጣ ቃልቻም «እኛ

ሰው የዘራውን እህል በልተን ስናመልጥ አንተ አይደለህም ወይ እየተደበቅህ አድፍጠህ ስትበላን የነበረው ስለዚህ ላንተ አልጠነቀልም» አለው:: ተስፋ ያልቆረጠው ጅብም "እስቲ እድሌን ልሞክር" ብሎ ወደ ጉሬዛ ቃልቻ ጋር ሄደ:: የጉሬዛ ቃልቻም የጅቡን ንግግር አዳመጠና እንዲህ አለው:-
«አሁን ቶሎ ወደ ቤትህ ሂድና ግቢህን አጽዳ:: እያፀዳህም እንዳለ ከግቢህ አጥር አንድ ጥግ ድቡልቡል ድንጋይ ታገኛለህ:: ያንን ድንጋይ እሳት ውስጥ ከተህ አግለው:: ድንጋዩ ግሎ ቀይ ሲሆን አውጣና በሞራ ጠራርገህ ዋጠው:: የዛኔ ጉሮሮህ ይሰፋል:: አለው:: ጅብም የጉሬዛ ቃልቻ በነገረው መሠረት ወደ ቤቱ ተመልሶ ግቢውን ሲያፀዳ ድቡልቡል ድንጋይ አገኘ:: ያንንም ድቡልቡል ድንጋይ አጋለና በሞላ ጠራርጎ ሲውጠው ጠባብ የነበረው ጉሮሮው ሰፋ! ድምፁንም እንደሰው ልጅ በፈለገው አይነት መለዋወጥ ቻለ:: በዚህ የተደሰተው ጅብ ወደነ ኩንድሌ ቤት እየሮጠ ሄደ:: ድምፁንም እንደሚያቱሽ / ወንድሟ ነው/ በማስመሰል

ኩንድሌ ቲድን !
እጅየለሽ ቲድን !
እግር የለሽ ቲድን !
መጣሁልሽ ቲድን !

ብሎ ሲጠራት የጅቡ ድምጽ የወንድሟ መስላትና ኩንድሌ መልስ ሰጠችው::

ለ. ... በጅቡ ከመበላት የተረፈችው ኩንድሌን ወንድሟ ተሸክሟት በመጓዝ ላይ እንዳለ ከመንገዳቸው ዳር ገላጣ በሆነ ቦታ ላይ የሀገር አዋቂዎች ተሰብስበው ጥሬ ከቺ /ስሩ የሚበላ ተክል/ ሲመገቡ ደረሰ:: በዚህ ድርጊት የተገረመው ወንድሟ ቆም ብሎ አዋቂዎቹን:-
"ጥሬ ከቺ ይበላል ወይ?" ብሎ ጠየቀ::
"ታድያ እንዴት ተደርጎ ነው የሚበላ?" ብለው ጠየቁት
«በስሎ ነው የሚበላ!" ብሎ መለሰላቸው:: አዋቂዎቹም «እስቲ እንዴት በስሎ እንደሚበላ አሳየን» አሉት:: እሱም:-
«ለእህቴ እግርና እጅ የምትሰሩልኝ ከሆነ ቀቅዬ አበላችኋለሁ::" አላቸው::
አዋቂዎቹም! «ይህማ በጣም ቀላል ነው:: አንተ ሂድና ከቺያችንን አብስል እኛ እስከዚያ ድረስ ለእህትህ እጅና እግር እንሰራላታለን» አሉት::

አዎቂዎቹም በገቡለት ቃል መሠረት ኩንድሌን እግርና እጅ አበጅተውለት:- ጫማ አድርገውለት፣ ቀሚስና ነጠላ፣ እንዲሁም ሻሽ አስረውላት አጠገባቸው ካሉት በርካታ ልጆች መካከል አስቀመጧት::

የኩንድሌ ወንድምም በታዘዘው መሠረት ከችውን ቀቅሎ አመጣና ለአዋቂዎቹ አቅርቦ መብላት ጀመሩ:: ...

ሐ. ... ኩንድሌ የወንድሚን ሚስት ፀጉር ቅማል መልቀሙ ስላደከማት «ወንድሜ በልቶ ያስተረፈው ምግብ የለም? አራብኝ» ብላ ሚስቱን ጠየቀቻት። እሷም ሂጅና ጓዳ ውስጥ ፈልጊ አለቻት። ኩንድሌ.... ጓዳ ውስጥ ያገኘችውን መሶብ ስትከፍተው የወንድሚን የተቆረጠ ጭንቅላት (ከነፀጉሩ) ሳይላጭ/ አገኘች። / ድንጋጤ ወረራት/ ወድያው የወንድሚን የተቆረጠ ጥንቅላት ብድግ አድርጋ ያዘችና ወደ ቤቷ ሮጠች። ቤቷም እንደደረሰች ለባሏ ለሶቴት እያለቀሰች አስረከበችው። ሶቴትም ኩንድሌን ካረጋጋት በኋላ የሰጠችውን የወንድሚን ጥንቅላት ወሰደና በአንድ ጎድጓድ እቃ ወስጥ አስቀመጠው። ቀጥሎም ወተትና ማር አፈሰሰበት (በእቃው ሞላበት) ጥቂት ቆይቶም ጭንቅላቱ ቀስ በቀስ ወደትልነት ተለወጠ። ቀጥሉም ቀስ በቀስ ሙሉ ሰው ሆነ /ዳነ/ ።

ይህ ሁኔታ እንዳበቃም ሶቴት ወደ ሚስቱ (ኩንድሌ) ቀረብ አለና፡- " ይኸውልሽ ፈጣሪያችን ወንድምሽን አድኖት ከሞተበት ወደ ሰውነት ለውጦታል" አላት። እሷም በወንድሚ ወደ ሰውነት መመለስ እጅግ ተደስታ እያለች፡- "..... እንግዲህ ተነሽና ወንድምሽን ወደ ቤቱ ውሰጅው" አላት። ... ኩንድሌም ወንድሚን አስከትላ ቤቱ ደረሰች። «ይኸውልህ ያንተ ቤት፣ አንተን ገድላ የበላችው ሚስትህ ይች ናት" አለችው። እርሱም አንገቷን ቀልቶ ሚስቱን ገደላት። ሚስቱም ወደ ትልነት ተለወጠች........።

እነዚህ ከኤሸሽ 1 ተረት ውስጥ የወጡት አስማታዊ ተግባርን የሚመለከቱ ተረኮች ጭብጣቸው ተመሳሳይ / መለወጥ/ ነው። የመለወጡ ተግባር ግቡም ተመሳሳይ ነው። ማለትም በ«ሀ» ና በ«ለ» ትረካ ውስጥ መለወጥ ለበቀል መሳሪያነት ውሏል። በተጨማሪም በኤሸሽ ውስጥ የጫርቴት ልጅ ሞቶ ከተቀበረበት በመነሳቱ አዲኬን በሠርግ እለት ተበቅሏታል።

ጋብቻ

በኤሸሽ አስማታዊ ተረት ወስጥ በተደጋጋሚ ከሚነሱት ጭብጦች መሀከል ሁለተኛዎቹ ትዳር /ጋብቻን የሚመለከቱት ናቸው።

..... ኩንድሌ አንድ ቀን ወንድሚ ከሄደበት ሲመለስ «ወንድሜ ሆይ የእናቴን ጨሌ እያንጠባጠብኩ እሄዳለሁ። አንተም ይህንኑ እየተከታተልክ ፈልገኝ። ጨሌው እመንገዳችን ላይ ያለውን ወንዝ ተሻግሮ ካገኘህ የጫርቴት ልጅን አግብቻለሁ ማለት ነው። ይሁን እንጅ ጨሌው ወንዙን ሳይሻገር ካለቀ የሶቴት ልጅን አግብቻለሁ ማለት ነው።» አለችው።

ወንድምየውም እህቱ በነገረችው መሠረት በየመንገዱ የተጣሉትን የእናቱን ጨሌዎች እየተከተለ ሲጓዝ ጨሌውን ያገኘው እመንገዳቸው ላይ እስካለው ወንዝ ዳር ድረስ ብቻ ሆነ። በዚህን ጊዜ የያዘውን ቦክንቦክ አወጣና እየነፋ ሽሪሽሪ መጫወት ጀመረ።

የሽሪሾሪውን ድምጽ እንዳሰማችም ኩንድሌ ሶቴትን / የውሃ ጌታ/ « ይህ የምሰማው ሽሪሾሪ የወንድሜ ነው» አለችው:: ሶቴትም «ወንድምሽ ከሆነ ታድያ ይግባ?» ብሎ ጠየቃት:: በእርሷ ፍቃድ መሠረትም ጠባቂዎቹን ላከና ወደ ቤቱ አስገባው ( ውሃ ውስጥ ነይ)....

በዘህም መሠረት በኤሸሽ 1 እና በኤሸሽ 6 ተረኮች ውስጥ ጋብቻ / ትዳር ና ፍቅር የሚመሰረተው ከልዕለሰብ ሀይላት ጋር ነው::

*ብልጠት*

በኤሸሽ አንድና ሁለት ውስጥ ብልጠት በጭብጥነት /በንዑስ/ ገብቷል:: በዚህም ተጋዳሊዎቹ:- እንደ ኤሸሽ 1. ከጠላቶቻቸው ለማምለጥ /ኩንድሌ ከጅብ/፣ እንደኤሸሽ 6 ለሰሩት ጥፋት መሸፈኛ የሚያቀርቡት ምክንያት መናገር «አዲኬ ከጫርቴት ልጅ ጋር ስትላፋ ለደረሰው የንብረት ጥፋት የምትሰጠው መልስ» ሁሉ የብልጠትን አስፈላጊነት ያሳያሉ::

## ሐ. የሞራል /ስነምግባር ተረቶች (Moral Tales)

ሞራላዊ (ስነምግባር) ተረቶች /moralistic Tales/ በኤሸሽ ዝርው ተረቶች ውስጥ ይገኛሉ:: እነዚህ ሞራላዊ ተረቶች መለያቸው በየተረኮች ማብቂያ ላይ ስናይና እኩይ የሆኑ ባህርያቶችን ያመለክታሉ:: ወይም «ይህ ጥሩ ነው፣ ይኸ ደግሞ መጥፎ ባህሪ /ድርጊት ነው» ብለው በመለየት የሚያስተምሩ ናቸው::

### የሞራላዊ ተረቶች ገፀባህርያትና ጭብጥ

የኤሸሽ ሞራላዊ ተረቶች ገፀባህርያት እንስሳት ናቸው:: በነዚህ ገፀባህርያት አማካኝነት በመምከሪያ/ማስተማሪያነት የተነሱት ጭብጦች የሚከተሉት ናቸው::

### የራስ ያልሆነ ነገርን አለመፈለግ/አለመመኘት

ኤሸሽ 7 ... ድሮ ጊዜ ነው አሉ:: አንድ ውሻ ከበሬ ኋላ ቁማ ሳለ ድንገት የበሬ ቆለጥ /ፍሬዎች/ ታያለች:: በሬው በተንቀሳቀሰ ቁጥር ቆለጡም ከግራ ወደ ቀኝ ሲንቀሳቀስ «ወድቆልኝ እበላለሁ/»እያለች ቀኑን ሙሉ ስትከተል ትውላለች:: የበሬው ቆለጥም የሚበጠስ አይደለምና አልወደቀም:: በሬው ቀኑን ሙሉ ሳር ሲግጥ እሷም አብራው ውላ ትመጣለች::

ይቺው ውሻ ማታ ላይ በሬው ቀኑን ሙሉ ሲበላ የዋለውን ሳር በማያመነዥግበት ጊዜ ምናልባት ያቀኑን ይወድቃል ብላ የጠበቀችው ቆለጥ በአፉ ይወጣል ብላ ከፊት ለፊቱ በኩል ብትጠብቅ አይወጣም:: በኋላ ነገሩ ገርሟት ...... "አንተ በሬ ፣ ከኋላህ ሆኜ ብጠብቅ ብጠብቅ ቆለጥህ ተበጥሶ አይወድቅም ፣ ስታመነዥግ ምናልባት ባፍህ ይወጣል ብዬ ብጠብቅ አልወጣም ነገሩ እንዴት ነው ብላ ጠየቀችው::

የዚህን ጊዜ በሬው «አይ ውሾ እንዴት ያልለፋሽበትን የሰውን ነገር አገኛለሁ ብለሽ ትጠብቂያለሽ? የሌላውን ነገር /ያልለፋበትን ነገር/ አገኛለሁ ብሎ መጠበቅ ጥሩ አይደለም» አላት ይባላል፡፡

*የሀሰት ጓደኝነትን መጥፎነት ማሳየት*

በኤሽሽ ትረካ ውስጥ የሀሰት ጓደኝነት ተገቢ አለመሆኑን የሚመክሩ ተደጋጋሚ ተረቶች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህም መሀከል፡-

ኤሽሽ 10 ...... ውሻና አህያ አንድ ዘመን ጓደኛሞች ስለነበሩ በጋራ አንዲት ላም ገዙ፡፡ ይቺን የጋራ ንብረት አብረው በጋራ ይጠብቋት ነበር፡፡ ሆኖም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ላሚቷን ውሻ እንዲጠብቃት ሆነ፡፡ ይሁን እንጅ ውሻው ይቺን የጋራ ላም አንድ ቀን ሲርበው ጊዜ በላት፡፡
አህያም « ጓደኛዬ ሆይ በጋራ የገዛናት ላም የት ገባች » ብሎ ጠየቀው፡፡
ውሻም በንዴት «እንዴት እንዲህ አይነት ጥያቄ ትጠይቀኛለህ?» እኔ አላየሁም ብሎ መለሰለት፡፡ አህያም «የዚህን አይነት መልስ እንዴት ትሰጠኛለህ?» ላሚቷን የበላሀት አንተነህ አለው፡፡ በውሻውና በአህያው መካከል የተፈጠረው ግጭት ተባባሰ፡፡ የዚህን ጊዜ ውሻው «በል ጓደኛዬ ስልህ ካላመንከኝ እውነተኛ ዳኛ ይፍረደን፡፡ ስለዚህም "ትልቅ ረግረግ ያለበት ቦታ እንሂድ" ተባባሉና ረግረጋማ ቦታ ፍለጋ ሄዱ፡፡

እረግረጋማውን ቦታም እንደደረሱ ውሻው ቀደም ብሎ በል እንግዲህ « እውነት እኔ ላሚቷን በልቼ ከሆነ ይህንን ረግረጋማ ቦታ ሳቋርጥ ሰጥሜ ልሙት" አለና ወደረገርጉ ዘሎ ገባ ፡፡ ክብደቱ ቀላል ስለነበረ ተሻገረ፡፡

የዚህን ጊዜ አህያ «እውነተኛው እኔ እንጅ አንተ አይደለህም «አለና እንደውሻው ረገረጉን ለማቋረጥ ብሎ ዘሎ ገባ፡፡ የዚህን ጊዜ አህያው ክብደቱ ከፍ ያለ ስለነበር መስመጥ ጀመር፡፡ የዚህን ጊዜ ውሻውም «አንተ የሰመጥከው ውሸታም ስለሆንክ ነው፡፡» አለውና ዞሮ ተመልሶ መጣና ጓደኛውን /አህያውን/ መብላት ጀመረ፡፡

ይህንን የውሻና የአህያ ታሪክ አንበሳ ሰማ አሉ፡፡ «እስቲ አንተ ብትሆን ለማት ትፈርድ ነበር» አሉት፡፡ አንበሳም «የውሸት ጓደኛ ጥሩ አይደለም፡፡ ከማይመስላችሁ ሰው ጋር አትማማሉ /ቃል አትግቡ/ እኔ እንደሆንኩ ማንንም አልፈራም፡፡ «አለ ብለው በልጅነታችን አባቶቻችን ይነግሩናል፡፡

በኤሽሽ 10 ተረት እንደተገለፀው ሁሉ በኤሽሽ 16ትም የሀሰት ጓደኝነት የመጨረሻው ውጤቱ አሳዛኝ እንደሚሆን ያስተምራሉ፡፡ ስለዚህም ተረቶች በጓደኛሞች መካከል መተማመን፣ ቃል ኪዳንን /መሀላ/ የማክበር ሞራላዊ ግዴታ ሊኖር እንደሚገባ ያሳያሉ፡፡

የኤሽሽ ሞራላዊ ተረቶች ጭብጥ ሰናይ እና እኩይ ባህርያትና ድርጊቶችን በማሳየት ታዳሚውን «እንዲህ ማድረግ ጥሩ ነው» እንዲህ ማድረግ ደግሞ መጥፎ ነው» በሚል አቀራረብ የማስተማር እና የመምከር ተግባር ያከናውናሉ።

በአጠቃላይ ከተሰበሰቡት 20 የኤሽሽ ዝርው ተረቶች ውስጥ በድግግሞሽ ብዛታቸው፦ የትሊያ ተረቶች፣ ሞራላዊ ተረቶችና የአስማት ተረቶች በማለት በሦስት ለመክፈል ሞክሬያለሁ። በነዚህ ተረቶች፣ ውስጥ በተከታታይ የሚከሰቱ ባህርያት፣ ጦጣ፣ ውሻ፣ አህያ እና እባብ ናቸው። ጦጣ ብልጥ፣ ቀጣፊና እውነተኛ ዳኛ ሆና ተስላለች። ውሻም እንዲሁ ከሀዲና ታማኝ ጓደኛ ሆኖ ቀርቧል። አህያም እውነተኛ/ታማኝና ነገሮችን አርቆ የማይመለከት /ጥጋብ የማይችል/ ሆኖ ተስሏል። እነዚህ ሦስት ገባህርያት በሙሉ የተሳሉት ሁለት ተቃራኒ ባህርያቶችን እንዲያንፀባርቁ ሁነው ነው። የእባብ ግን ይለያል። እባብ በቀረበባቸው ሁሉም የኤሽሽ ተረቶች ውስጥ ተንኮለኛና አሳሳች ሆኖ ነው።

### 4.1.3 የቤንች ዝርው ተረኮች፣ የክወና አውድ፣ ተራኪ እና ታዳሚዎች

የቤንች ቶስ እና ኤሽሽ በብሄረሰቡ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ የሚጫወቱትን ሚና ለመገንዘብና የነዚህን የዝርው ተረክ ዘሮች ልዩ ባህርያት በውል ለመረዳት ከሚረዱ ተግባራት መሀከል እነዚህ ተረኮች መቼ፣ የት፣ ይከወናሉ? ተራኪዎቻቸውስ እነማን ናቸው? በአንድ የትረካ አጋጣሚ የሚሰባሰቡት ታዳሚዎችስ እነማን ናቸው? የሚሉ ጥያቄዎችን አንስቶ መመልከቱ ጠቃሚ ነው።

ይህ የቤንች ቶስ እና ኤሽሽ፥ በቀን ወይም በምሽት የመከውናቸው ጉዳይ እነዚህ ዝርው ተረኮች ለምን እንደሚተረኩ፤ የት እንደሚተረኩ? በማን እንደሚተረኩና የታዳሚዎቹን ማንነት መለያም ሆኖ ያገለግላል። በተጨማሪም ይህ የዝርው ተረኮቹ የመከወኛ ጊዜ፥ እነዚሁ ተረኮች ከብሄረሰቡ ባህል ልዩ ልዩ እሴቶች ጋር ያላቸውን ትስስርም ያመለክታል።

"ይህ ነገር ሚዳቋ ማታ የተናገረችው እንዳይሆን!" የሚለው አባባል በሁለት ጓደኞሞች ወይም ባለጉዳዮች መሀከል ባንዱ ሲነሳ በቤንች ባህል መሰረት የሚያሳየው ነገር አለ። ይኸውም በግለሰቦች መሀከል የተደረገው ስምምነት/ቃል ኪዳን እውነትን የሚያረጋግጥ መሆኑን ለማሳየት ነው። ማለትም ተጠያቂው /ቃል የሚገባው ሰው" "ሚዳቋ ማታ የተናገረችው አይደለም/አይሆንም ...." ብሎ በሚመልስበት ጊዜ "ቃሌን እፈፅማለሁ!" ብሎ ማረጋገጫ መስጠቱን ያሳያል።

በተመሳሳይ መልኩ ሲታይ በሁለት ግለሰቦች ምሳሌነት የቀረበው ባህላዊ ጉዳይ የኤሽሽን ምንነት አስመልክቶ በምዕራፉ መግቢያ ላይ ከተሰጠው ገለፃ ጋር ግንኙነት አለው። ይኸውም በመስክ ቆይታዬ እንደተረዳሁት በብሄረሰቡ ባህል መሰረት "በምሽት ጊዜ የሚነገር ነገር/ቃል የሚገባ ነገር ተግባራዊ ሊሆንም ሳይሆንም ይችላል። ወይም ተግባራዊነቱ

አጠራጣሪ ነው።" ምክንያቱም "ቀን በስራ ላይ ደክሞ የዋለ ሰው ምሽት ላይ ቤቱ ገብቶ በማረፍ ለበነጋው ስራ ራሱን ማዘጋጀት አለበት። ሊደክምና ሊያንቀላፋ ይችላል ስለዚህም ምር የሆነን ነገር በዚህ ጊዜ ማንሳት ተቀባይነት የለውም ....." በማለት ባብ ሲግ ነግረውኛል።

ስለዚህም በኤሽሽ ትረካ የሚቀርቡት ጉዳዮች ሁሉ ተአማኒነት የላቸውም ወይም ፈጠራ ታሪክ ናቸው። በአባማትዮስ ግቢ የቤንች ቶስና ኤሽሽን በተመለከተ ውይይት ተደርጎ ነበር። በዚህ አጋጣሚም የኤሽሽ (ተረት) ምሳሌ ነው በማለት ባብ ግርማ ኤሽሽ 20ን ተርቶ ነበር። ይሁን እንጂ ትረካውን ... መኬ መስታ።" (ይባላል...) በማለት አጠናቀቀ። ከጥቂት ቆይታ በኋላ አባ ማትዮስ "ያቀረብከው ኤሽሽን (ተረት) መልዕክት አላስረዳኸንም?" የሚል ጥያቄ ያቀርባሉ? በተራቹ የተሰጠውም ምላሽ ... ለመሆኑ ከመቼ ጀምሮ ነው አንበሳና ጦጣ ጓደኛ የሆኑት፤ አንበሳ (ዶድባብ ዶድ-መሬት፤ ባብ፥ አባት (ጌታ) የእንስሳት ንጉስ ነው። ጦጣ እንዴት ደፍራ እንፋለም ትላለች.... ጦጣ አንበሳን አሸነፈች... ተብሎ በኤሽሹ የተገለፀው የማይሆን ነገር/ፈጠራ ነው የሚል ነበር።

"ቤንችቶስን የሚተርከው ማነው?" ለሚለው ጥያቄ ተቀራራቢነት ያለው መልስ ከተለያዩ ስነቃል አቀባዮች ያገኘሁ ሲሆን በተለይ ባብ ሲግ የሰጡኝ ምላሽ የሁሉንም አስተያየት ያካተተ ነው።

> ቶስ ... ይኸውላችሁ ቤንችቶስን ማነው የሚናገረው ላልከው፥ ለምሳሌ እናንተ እኔ ጋ ለምን መጣችሁ? ቶስ ለመስማት አይደል። ለምሳሌ አንተ ማሙሽ ዛሬ ከኔ የሰማኸውን ነገ አንድ ቦታ ላይ ከባብ ሲግ ሰማሁ ብለህ ትናገራለህ። እንግዲህ ቶስን ማን ይተርካል? ላልከው፥ ዋናው ተራኪዎች አዋቂዎችና ሽማግሌዎች ናቸው። ከነርሱ የሰሙትን ደግሞ በዕድሜ አነስ ያሉት ይናገራሉ። ሌላው ቀርቶ ልጆች ከትምህርት ቤት ሲመለሱ መንገድ ላይ አንድ ነገር ሲደረግ ሲያዩ ለጓደኛቸው "ለካስ አባቴ የነገረኝ ቶስ ትክክል ነው" ብለው ሊናገሩ ይችላሉ... (ባብ ሲግ ባያ)

በአጠቃላይ የቶስ ተራኪ ማንነትን ለይቶ ይህ ነው ብሎ መናገር አስቸጋሪ ነው። (ለጊዜው በዚህ ጥናት) ምክንያቱም ማንም ሰው የሰማውን ቤንች ቶስ በተለያዩ አጋጣሚዎች መልሶ ሊናገር ይችላል። ይሁን እንጂ በመስክ ቆይታዬ እንዳየሁት የቤንች እውነተኛ ታሪክን፣ ታዋቂ ግለሰቦችን፣ እምነት ነክ ጉዳዮችን የሚመለከት ቶስ የሚናገሩት

አዋቂዎች ወይም ሽማግሌዎች ብቻ ናቸው። በትረካውም የሴቶችና የልጆች ተሳትፎ በጣም ዝቅተኛ ነው። በአብዛኛው ተናጋሪዎቹ ትላልቅ ወንዶች ብቻ ናቸው። የሚተረከውም፥ ለመምከር፣ ለመገሰጽ፣ አዳዲስ ተፈጥሯዊና ማህበራዊ ክስተቶችን ለመተርጎም፣ ባህላዊ ልማድን፣ ወግን ... ለመግለፅ ... ተብሎ ነው።

## 4.2 የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች ማህበራዊ ፋይዳ ገላጭ ትንተና

Bascom (1960) ፎክሎር በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ አራት ዋና ዋና ፋይዳዎች (functions) እንዳሉት ገልጿል። ከነዚህ የፎክሎር ፋይዳዎች መሀከል አንዱ በህብረተሰቡ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ የሚጫወተው ሚናው ነው። ይህ ማህበራዊ ፋይዳውን ለመረዳት (ለማጥናት) የሚረዱ መረጃዎች ከመስክ ሲሰበሰቡ እንደሚገባና በትንተናም በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ምን ምን አይነት ፋይዳዎችን እንደሚያበረክቱ ማሳየት እንደሚቻል Georges (1970) አስረድቷል።

የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች ማህበራዊ ፋይዳ በአብዛኛው በሚከተሉት አምስት ማህበራዊና ባህላዊ ርዕሰ ነገሮች ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው። እነዚህ ስነቃላዊ ጭብጦች በህብረተሰቡ እለታዊ የማህበራዊ ኑሮ ግንኙነት ውስጥ የሚከወኑና በዝርው ተረኮች አማካኝነት የሚንፀባርቁ ናቸው።

### 4.2.1 ባህልን ጠብቆ ለትውልድ ማስተላለፍ

ቶስ ዝርው ተረኮች በተለይም ገላጭ ተረቶች የቤንች ብሔረሰብ ባህላዊ ህይወትን በተለይም የባህላዊ እምነቱን ምንነት፣ የአምልኮ ስርዓትና አሰራሩን ሁኔታ ይገልፃሉ። በዚህም ባህላዊ እምነቱን ያስረዳሉ፤ ልዩ ልዩ ባህላዊ ልማዶችን ይቀርፃሉ። እምነቱን ማሰረት አድርጎ በቀረፃቸው ማህበራዊ ልማዶቹ ደንብ መሠረት ስነምግባርን፣ የወልና የግል ህይወት ኑሮ መመሪያዎችን ብሎም ከአምላኩ (የሮ/የሮስንዶ)፣ ከሰብአዊ ፍጡራን፣ ከተፈጥሮ በጥቅሉ ከዓለመዓለማቱ ፍጡራን ጋር ያለውን ግንኙነት ይገልፃሉ። የህይወት ፍልስፍናውን ያንፀባርቃሉ። የቤንች ብሄረሰብ ባህላዊ እምነቱን አሰራር መሠረት ያደረጉ የቶስ ገላጭ ዝርው ተረኮቹ የሚከተሉት ናቸው።

ዘፍጥረት (Creation)

ዘፍጥረትን የሚመለከቱ ጭብጦች ያሏቸው የቶስ ገላጭ ትረካዎች ፈጣሪ ማነው? ሰውን፣ .እንስሳትን፣ እፅዋትን፣ መናፍስትንና ግዑዝ አካላትን በጥቅሉ የዓለመዓለማት አፈጣጠርና የህይወት አጀማመርን እንዴትነት የሚያሳዩ ናቸው።

የሮ (ፈጣሪ) መጀመሪያ ላይ የፈጠረው ሁለት ሰዎችን ብቻ ነው። እነዚህ ሰዎች አንድ ወንድና አንድ ሴት ነበሩ። አብረው እየኖሩ ሳለ በመሀከላቸው ፍቅር ገባ። ቀጥሎም ተጋቡና (ጎጆ ሰርተው) የመጀመሪያው ትዳር ተመሰረተ። ከዚህ በኋላ ተዋለዱ። በነዚህም (በተወለዱት) መሀከል ጋብቻ በመፈፀሙ በሰዎች መሀከል ዝምድና (ዚያም) ተጀመረ። በዚህም አንዱ አንዱን እየጠበቀ የሰው ልጅ መኖር ጀመረ።

ከላይ በቀረበው ቶስ 52 በቤንች ባህላዊ እምነት የሰው ልጅና የሁሉም ፍጥረት ወይም የህይወት ጅማሬ እንዴትነት ተገልጿል። ይህንን ሁሉ ለሰጠው የሮስንዶ የአምልኮ ስርዓቱን በተመለከተም፡-

ቶስ 56 እኛ በባህላችን መሠረት "ቤተክርስትያናችን" አድባር ነው፡" በዛ ስር ሆነን ፈጣሪያችንን ስለተለያዩ ጉዳዮች ማመስገን እንችላለን። ለዚህም ይረዳ ዘንድ መጀመሪያ ለአድባሩ ቤት ይሰራል። ቀጥሎም ጥቁርና ቀይ በሬ ወይም በግ ይታረዳል። ይህ የሚሆነው አምላካችን (የሮስንዶ) ጥሩ አዝመራ እንዲሰጠን ስንለምን ነው። ስለዚህም ጥቁሩ በሬ ለጥሩ የበቆሎ አዝመራ፤ ቀይ በሬ ደግሞ ለጥሩ የዶንቃ (ማሽላ) አዝመራ እንዲሰጠን መሰዋዕት እናቀርባለን። በተመሳሳይ መልኩ በሰቀልነው ቀፎ ውስጥ ንቦች ገብተው ጥሩ ማር እንዲሰጡን ጠጅ ይጠመቅና በመንደር ውስጥ የሚገኙ ሽማግሌዎችና አሮጊቶች በሙሉ ተገኝተው ይመርቃሉ።

(ቤኑሽታቶ ጋይስ ጊሽቱናንስ፣ 17/03/1999)

ከዚህ የአምልኮ ስርዓት የሚመነጩና የባህላዊ እምነት ተከታዮች በልዩ ልዩ የማህበራዊ፣ የቤተሰብ ብሎም የግል ህይወት ዘመናቸው የሚፈፅሟቸው ህጋጋት አሉ።

የቤንች ብሄረሰብ ባብዛኛው በግብርናና በከብት እርባታ የሚተዳደር ነው፡፡ በዚህም የተነሳም በነዚህ የሙያ ዘርፎች ለሚያከናውናቸው ተግባራቱ መመሪያ የሚሆኑ ደንቦች እንዲሁ ከባህላዊ እምነቱ የሚመነጩ ናቸው፡፡

"በባህላችን የአዝመራ ወቅት ሲደርስ አንድ አይነት ዘር ብቻ አይዘራም፡፡ ለምሳሌ የበቆሎ ወቅት ሲደርስ ፍሬው ትልልቅ (ወንዴ) እና ፍሬው አነስ ያለ (ሴቴ) ዘር መርጠን እንዘራለን፡፡ በዚህ መንገድ ካልተዘራ የምናገኘው ምርት አነስተኛ ነው፡፡ በረከትም የለውም፡፡" ባብ ቤላ በተመሳሳይ ሁኔታም በቶስ 67 እንደተገለፀው፡-

> አንድ እናት ላም የወለደቻት ጥጃ ደርሳ ብትወልድ እና እናቷ ላም የምትታለብ ቢሆን የእናት ላሟና የልጇ ወተት የሚቀመጠው ለየብቻ ነው፡፡ አይደባለቅም፡፡ ምክንያቱም ይህንን የተደባለቀ የእናት ላምና የልጇን ወተት እንዳጋጣሚ የሚጠጣ ልጅ ሲያድግ በአንደበቱ መናገር አይችልም ተብሎ ስለሚታመንበት ነው፡፡ (ባብ አላ ናካ)

ከላይ በቶስ 65 እና ቶስ 67 የቀረቡት ባህላዊ ደንቦች መፈፀም ወይም መጣስ በቤተሰብ ብሎም በነዋሪው ላይ የሚያሳድሩት ተጽእኖ አላቸው ተብሎ ይታመንበታል፡፡ ለምሳሌ ሰው በማህበራዊ ህይወቱ አይረካም ስስት፣ ስግብግብነት ወዘተ. ያስከትላሉ፡፡

በተጨማሪም በቤንች ባህላዊ እምነት መሠረት በሂደት የሚከሰቱ ተፈጥሯዊና የማህበራዊ ኑሮ ለውጦች ሁሉ ምክንያታቸው ይገለፃል፡፡ አዳዲስ ባህርያት በሰው ልጅና በእንስሳ ላይ ሲታዩ "ለምን?" ለሚለው ጥያቄም "ተገቢ" መልስ ይሰጥበታል፡፡

በቤንች ባህላዊ እምነት ማንኛውም ፍጡር የሰው ልጅም ሆነ ተፈጥሮ ራሷን ጨምሮ ህልውናቸው ተጠብቆ የሚኖሩት በፈጣሪ የታዘዘውን ስርዓት የመጠበቅ ግዴታቸውን እስከተወጡ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ራሱን ጥብቆ (ከግል ንፅህና ጀምሮ፣ ቤት፣ አጥር ግቢ፣ ብሎም መንፈሳዊነቱን ...) መኖር አለበት፡፡ ፍቅር፣ ቸርነትና እንክብካቤ፣ ለመሰሉ ሰብአዊ ፍጡር፣ ለእንስሳት፣ ለተፈጥሮ አካባቢ ... ማድረግ፣ ከስንፍና፣ ከብኩንነት፣ ሴሰኝነትና ጥላቻ ... መራቅ ግዴታው ነው፡፡

ይህ ካልሆነ የሰው ልጅም ሆነ ማንኛውም ፍጥረት በሚፈጥሩት ስርዓት አልባነት ዓለም ትጠፋለች፡፡ በዚህ የተነሳም በቤንች ባህላዊ እምነት ማንኛውም ተራ የሚመስል ተፈጥሯዊም ሆነ ማህበራዊ ክስተት በሽማግሌዎች (አዋቂዎች ዘንድ) በጥንቃቄ ይመረመራል፡፡

ኦማሽለስንዶ ጊች!

ኦማሽለስንዶ[15] በጥንት ዘመን ከሰው ልጅ ጋር (በፍፁምነት) በምድር ላይ ይኖሩ ነበር። ሆኖም በሰው ልጅ ተግባራት ደስተኛ አልነበሩም። በተለይም አንድ ቀን ካፍቴት የተባለ ሰው አስቀየማቸው። በዚህ ክፉ ተግባሩ ተጨቃጨቁ። በዚህ የተነሳም "እኔ እስከምመለስ ድረስ (ለሀጥኣን/ጻድቃን ላይ ለመፍረድ ነው) የሰጠኋችሁን ነገር (የምድርን ሀብት) ሁሉ ይገፔ ሄጃለሁ ብለው ተሰወሩ/አረጉ።

ይህ የምፅኣት ቀንና የታላቁን ኦማሽለስንዶ የፍርድ ቀን ምፅኣት የሚመለከቱ ቶስ 57፣ ቶስ 58 እና 59 እንደሚያሳዩት አለም የምትጠፋው በሰው ልጅ ክፉ ድርጊትና ስርዓት አልበኝነት የተነሳ በሚፈጠር ትርምስ ነው። ይህን መሰልና ሌሎች የምፅኣት ቀን ፍርድን አስመልክተው የሚቀርቡ የቶስ ገላጭ ተረቶች በአሁኑ ወቅት አንዳንድ የብሄረሰቡ አባላት ከባህላዊ እምነት መራቅ፤ በየጓሮው የሚተከሉ አትክልቶች አንድ አይነት ብቻ መሆን ለምሳሌ ቡና፤ ግድያ … ሁሉ የምፅኣት ቀን መቃረቡን የሚገልፁ ናቸው ይባላል። በተለይም ባብ ዊኒያ ዳቹ፡-

> "እኛ ዛሬ መሽቶ እስኪነጋ ድረስ ወደታች የሄዱት ኦማሽለስንዶ ወደ ላይ (ምድር) የመመለሻቸው ጊዜ ደርሶ ይሆን … በማለት እየፈራን ነው የምንኖረው። እኔ ራሴ ይህንን ትንቢት ላንተ ስነግርህ በፍርሃት ውስጥ ሆኜ ነው (ባብ ዊኒያ ዳቹ፣ 20-03-1999 ዓ.ም ጌሲት ቀገማ)።

ብለው ሲነግሩኝ ዛሬ በአካባቢያቸው ሰው ከባህሉ፣ ከእምነቱ እየራቀ የሚፈፅመው ድርጊት ሁሉ የአለም ፍፃሜና የምፅኣት ቀን መቃረብን እንደሚያሳይ በመግለፅ ነው።

በአጠቃላይ ከላይ በቀረቡት ጥቂት ምሳሌዎች እና በሌሎቹ ገላጭ ተረቶች አማካኝነት የቤንችቶስ ባህላዊ እምነትን፣ ከዚህ የሚመነጩትን ማህበራዊ ደንቦች መጠበቅ ከብሄረሰቡ ህልውናና - ከግል፣ ከቤተሰብ፣ ከማህበረሰብ ጋር በጥብቅ የተያያዘ መሆኑ ይታያል። በዚህም የባህላዊ እምነቱን ትዕዛዛት፣ በግልም ሆነ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ሊተገበሩ የሚገባቸውን ልማዶች፣ ደንቦች በማስረዳት ማህበራዊ መረጋጋትን፣ ሰላምን መቻቻልን ይሰብካል። በዚህም የተነሳ የብሄረሰቡ አባል የባህሉንና የእምነቱን አስተምህሮ ተከትሎ የሚፈፅማቸው ቤተሰባዊና ማህበራዊ ክንዋኔዎቹ ሁሉ የማንነቱ መግለጫ ናቸው።

---

[15] ኦማሽለስንዶ - በቤንች ባህላዊ የካህ እምነት ውስጥ ዋና ዋና ከሚባሉት ፈጣሪዎች (አማልዕክት) አንዱ ሲሆኑ ፍርድ ለርሳቸው የተሰጠ ስርዓት ነው ይባላል።

የማህበራዊ ህይወቱም ሆነ ቤተሰባዊ ግንኙነቱ መሰረቱ ይኸው ባህላዊ እምነቱ ነው። በዕለታዊ ህይወቱ የሚያንፀባርቀው ለጋስነት፣ ፍቅር፣ ሀቀኝነቱ፣ ሰላም ፈላጊነቱ፣ የተረጋጋ ህብረተሰብ መፍጠሩ፣ ለአካባቢው የሚያደርገው ጥበቃ ልምላሜና በረከት ሁሉ መሰረቱ ይኸው ባህላዊ እምነቱ ነው። ከዚህ ህይወት በራቀ መጠን በራሱ፣ በቤተሰቡ፣ በብሄረሰቡ፣ በአካባቢው ወዘተ. የሚከሰት ትልቅ አደጋ እንደሚኖር በመግለፅ ያስጠነቅቃል።

## 4.2.2 የባህላዊና ማህበራዊ ተቋማትንና እሴቶቻቸውን ጠቀሜታ ከፍ ማድረግ

የቤንች ልዩ ልዩ ማህበራዊና ባህላዊ ተቋማት ማለትም ባህላዊ አስተዳደሩ፣ ዳኝነቱ፣ የቤተሰብ ህይወቱ ... ሁሉ መሰረቱ ያሉት በ4.2.1 እንደተገለፀው በባህላዊ እምነቱ ላይ ነው።

በአብዛኛዎቹ የቤንች ብሄረሰብ አባላት ዘንድ ባህላዊና ማህበራዊ ተቋማቱ፥ ባህላዊ አስተዳደሩ፣ ባህላዊ ሽምግልናው፣ የቤተሰብ/ትዳር ህይወትና ወዘተ. የመሳሰሉት እሴቶቹ ከፍተኛ ግምት ይሰጣቸዋል።

### ባህላዊ አስተዳደር

ቤንችቴት/ቤኑሽታቶ የቤንች ንጉስ ሲሆን የብሄረሰቡን ባህላዊና ማህበራዊ ህይወት ይመራል። በዚህም ተግባሩ የባህላዊ እምነቱ "ሊቀካህን" እና የአለማዊው አስተዳደር የመጨረሻው ከፍተኛ ተጠሪ እርሱ ብቻ ነው። የስልጣኑ ምንጭም ከቤተሰብ (ከአባት) የሚወረስ እና ከመለኮት (ፈጣሪ) በመመረጥ የሚሰጥ ነው። ስለዚህ ባብ ሲግ እንደተናገሩት፡-"አንድ ሰው በባህላችን ቤንችቴት ሆኖ ሲመረጥ ተራ ሰው መሆኑ ይቀራል።"

አብዛኛዎቹ የብሄረሰቡ አባላት ቤንችቴት ታህተ-ፈጣሪ (super human) ነው ብለው ስለሚያምኑ ህብረተሰቡን ከተፈጥሮኣዊም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋ እንደሚታደግ ይናገራሉ። በንግስናው ዘመንም ፈጣሪውን የሚለምነው ስለህገሩ ሰላም፣ በረከትና ፍቅር በመሆኑ ለሁሉም ነዋሪ እኩል (የማያዳላ) ያስባል ብለው ይምናሉ።

ባይካሽ (ዕድሜ 55 ዳቸበስ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪ) በ4/04/99 ሚያህ ቀበሌ ገበሬ ማህበር የሚኖረው የልጃቸው ልጅ ሞቶ ቀብር ውለው ወደ ቤታቸው እየተመለሱ ነበር። በዕለቱ ከሰዓት በኋላ ከባድ ዝናብ ይጥል ስለነበር ለመጠለል በማለት ባይካሽ፣ የመስክ ረዳቴና እኔ እንዲሁም ሌሎች ሰዎች ከወ/ሮ እርባነ ቤት ጎራ ብለን ነበር። ዝናቡን

የተጠለለው በሙሉ የሚነጋገረው ያለወቅቱ (በጋ ላይ) ስለሚጥለው ከባድ ዝናብ ነው። በዚህ መሀከል ባይከሻ፡-

> የዘንድሮ መቸም ጉድ ነው። ዘልሚ ወንዝ[16] ከመቼ ወዲህ ነው በጋ ላይ ሞልቶ ከዳሩ (ወንዙ) የታሰሩ ላምና በሬ ገፍቶ የወሰደው? ይህንን ነገር አባታችንን (ቤኑሽታቶ) ማን በጠየቀው? እሱ (ቤኑሽታቶ) እኮ ደግ ነው። ከፋት አያውቅም። በሰው ላይ ችግር እንዲደርስ አይፈልግም። ይህንን ዝናብ ከፈለገ ቀጥ አድርጎ ያቆመዋል። ደግሞ እኮ ደግ ነው። ከፈለገ መሬት በእጁ ነክቶ፣ ትንሽ አፈር ቆንጥሮ ቢያነሳና እጁ ላይ ቢያደርግ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቅቤ ይሆናል። ያን እኮ ለማንም ሊያደርግ ይችላል።

በማለት ተረኩ። ይህንን የባይካሻ ሀሳብ የሚጠራጠር አልነበረም። ስለዚህም ታዳሚው በሙሉ (ለዝናብ ተጠልለን የነበርነው) "ኢበሪጊች" (እውነት ነው) አለ።

ቤንችቴት ባለገድለ ብዙ ባህላዊ መሪ ነው። ስለአወላለዱ፣ ስለቤተሰቡ፣ ስለስደቱ፣ ስለንግስናው፣ ስለሞቱ፣ ስለቀብሩ ወዘተ. በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ያለአሉታ ገድሎቹ ይተረኩለታል። ተምሳሌታትም ነው የበረከት።

የኪቡ ሃገር (ኪቡዶድ) በአሁኑ ወቅት ኮብ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ተብላ የምትጠራ ሲሆን ከደብረወርቅ/ደቡብ ቤንች ወረዳ ዋና ከተማ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ትገኛለች። "የኪቡ ምድር ድርቅ አይነካትም፤ ሁል ጊዜ ለምለም ናት፤ ከብቶቹ ሁል ጊዜ መልካቸው ያማረ ነው።" ይህ የኪቡ ምድር ልምላሜ ከየት የመጣ ነው? ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ቤንችቴት በነዋሪው ዘንድ የተሰጠውን ባህላዊ (እምነት)ና ማህበራዊ ቦታ ይገልፃል።

> በቤንችቴትና በሻሽንቴት[17] ቤተሰቦች መሀከል አልፎ አልፎ አለመግባባት ይከሰት ነበር። በተለይም አንድ ጊዜ መንገድ ዳር በተዘራ ገብስ የተነሳ ከፍተኛ ግጭት ተፈጠረ። በዚህ አጋጣሚም ተጠቅመው ሁለት የሻሽንቴት ልጆች ያደፍጡና ቤንችቴትን በጦር ይወጋሉ። በዚህም ቤንችቴት ሞተዋል ብለው ሁለቱ የሻሽንቴት ልጆች ከአካባቢው ተሰወሩ። ይሁን እንጂ ቤንችቴት

---

[16] ዘልሚ ወንዝ፡- የደቡብ ቤንች ዋና ከተማ ደብረወርቅን ለሁለት ከፍሎ የሚፈስ ወንዝ ነው።
[17] ሻሽንቴት፡- ጥንት መከቷን በአሁኑ ሰዓት የደብረወርቅ ከተማና አካባቢውን የሚያስተዳድሩ ባህላዊ መሪዎች ቤተሰብ መጠሪያ ነው። ይህም በቤንችቴት ስር ከነበሩ 6 ባህላዊ የአካባቢ አስተዳደሮች አንዱ ነው።

በደረሰበት አደጋ የሚፈሰውን ደሙን በቀንድ ዋንጫ እያጠራቀመ (መሬት ላይ እንዳይፈስ ነው) ሲጓዝ ሲጓዝ ኪቡ ሀገር ሲደርስ ዋንጫው ሞላና የቤንቻቴት ደም ፈሰሰ፡፡ በዚህ የተነሳ ያአካባቢ ተመርቆ እስከዛሬ በልምላሜ ይኖራል ይባላል፡፡ (ቄስ ተገኝ ማርኮ)

**ሽምግልና እና ባህላዊ ዳኝነት፡-**

በሽምግልና (ኤርግ) ችግሮችን ወይም ግጭቶችን መፍታት በቤንች ብሄረሰብ ባህል ዘንድ የተለመደ አሰራር ነው፡፡ በዚህም የተነሳም በተለያዩ ጉዳዮች የተነሳ የተፈጠረ ግጭት እየተካረረ ሄዶ ከፍ ያለ ማህበራዊ ጉዳት ወይም ችግር የማስከተል እድሉ ጠባብ ነው፡፡ ስለሆነም የቤንች ብሄረሰብ ለማህበራዊና ለባህላዊ ተቋማቱ ከፍተኛ ቦታ ይሰጣል፡፡ በዚህም የተነሳ በቶስም ሆነ በኤሽሽ ትረካዎች ውስጥ የ"ፀጉረ ነጫጮቹ" ባህላዊ ዳኞች ወይም ሽማግሌዎች ሚና ተመሳሳይነት ባለው ሁኔታ ይተረካል፡፡ በአጠቃላይ የቤንች ባህላዊ የሽምግልና አሰራር የማይዳሰሰው የህይወት ዘርፍ የለም፡፡ ለዚህም ቶስ 9 መመልከት ይቻላል፡፡

> አንድ ጊዜ ነው አሉ፥ ቤንችቴት እንደሞቱ በቦታቸው የተተካው (የህዝብ ግፊት ታክሎበት) ከጭልጎንድ ቤተሰብ ነበር፡፡ በባህላችንና በእምነታችን አሰራር መሰረት ተቀባይነት ስላልነበረው ከፍተኛ ችግር ተፈጠረ … በጉዳዩ ላይ ፍርድ እንዲሰጡም ሽማግሌዎች ገርዝቴት ጋ ተላኩ፡፡ … ገርገርቴትም ከሽማግሌዎቹ ጋር መክረው … "የተደረገው ስህተት ነው" በማለት በአዲሱ ቤንችቴት ቦታ መቀመጥ ያለበት ከአርንድ ነው፡፡ ባሉት መሰረት … እኛም እስከ ዛሬ የምንከተለው ይህንን ነው፡፡ (አባ ማትዮስ ሻሽንቴት)

ይህ ቤንችቶስ በላዕላይ (surface) ደረጃ ሲታይ ጭብጡ ለባህላዊው አመራር በሁለት ወገኖች (አረንድና ጭልንድ) መሀከል የሚደረግን ፉክክር የሚያሳይ ይመስላል፡፡ ይሁን እንጂ ከብሄረሰቡ ባህል አንፃር ሌላም አንድምታ አለው፡፡ ይኸውም የቤንች ባህላዊና ማህበራዊ ህይወት በተረጋጋ ሁኔታ እንዲቀጥል ባህላዊው ሽምግልና (ፍርድ) ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም ሽማግሌዎቹ በዚህ የባህላዊ ሽምግልና ግልግል ያደረጉት በአርንድና በጭልንድ ቤተሰቦች መሀከል ብቻ ሳይሆን ሁለቱ ቤተሰቦች

በሚኖሩበት አካባቢ (መከቲን እና ጊጭ) ባሉ ገገር የካህ መንፈሶች (ሻሞቴእንዶ እና ጊስቴትእንዶ) መሀከልም መሆኑን ነው፡፡

ይህ የቤንች ባህላዊ የሽምግልና (የዳኘነት አሰራር በቤተሰብ፣ እንዲሁም በግለሰብ (የግል ባህሪ) ችግሮች ዙሪያም እንደሚሰራ ይታወቃል፡፡ በቶስ 43 እንደተመለከተውም፡-

"ሰው ሁሉ ጠላኝ፤ ምን ይሻለኛል? እባክዎ ለዚህ የሚሆን መፍትሄ እርስዎ አይጠፋምና ይምከሩኝ ፡፡ ...." በማለት ኩዣብ ጋ ለምክር የሄደው ግለሰብ በግሉም ሆነ በቤተሰብ ህይወቱ ውስጥ ላጋጠመው ችግር መፍትሄን በመሻት ነበር፡፡

ከላይ በቶስ 9 እና በቶስ 43 የተሰጡት የሽምግልና ዳኘነቶች መሰረት የሚያደርጉት ከራሱ ከብሄረሰቡ ባህልና ማህበራዊ ልማድ ውስጥ የወጡ እሴቶቹን ነው፡፡ ይኸውም ቶስ 9 እምነትና ታሪክን ወዘተ ያገናዘበ ሲሆን ቶስ 43 ደግሞ በብሄረሰቡ ዘንድ እንደፀያፍ ልማድ የሚቆጠሩትን ሀሜት ወይም አፍ እንዳመጣ ሳያስተውሉ መናገር (ኩዣብ አፉን ይሏልና)፤ አመንዝራነት (ኩዣብ ብልቱን ይሏልና) እና ስንፍና ሳይሰሩ መቀመጥ ተገቢ አለመሆኑን በማመላከት ነው፡፡ በሁለቱም ትረካዎች የሽማግሌዎቹ ሀሳብ (ምክር) ተግባራዊ በመደረጉ በቀጣይ ህይወት ውስጥ ሰላምና ስኬትን ማምጣት ተችሏል፡፡

## ጋብቻ/ቤተሰብ

ጋብቻ (ትዳር) በቤንች ብሄረሰብ ባህል ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት እና ጥንቃቄ የሚደረግለት ማህበራዊ ተቋም በመሆኑ በቶስ ተረኮች ውስጥ በተደጋጋሚነት የሚነሳ ርዕሰ ነገር ነው፡፡ በዚህ የተነሳ በመንፈሳዊም ሆነ ስጋዊ ህይወት ውስጥ ትዕምርትነት አለው፡፡ ጋብቻ በቤንች ባህል የቤተሰብ፣ የጎሳ ወይም የብሄረሰቡ መሰረት ብቻ ሳይሆን የህልውናም መግለጫ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ልጆች የሚገኙበት በመሆኑ፡፡ በመሆኑም በቶስ 52 እንደተገለፀው፡- የሰው ልጅ ማህበራዊ ህይወት የተሳሰረው በጋብቻ ነው፡፡ እንዲሁም በቶስ 33 እና 34 የመሞቻ ጊዜየ ተደርሷል ያሉ አባቶች በነርሱ ቦታ የሚተኩ ልጆችን (ወንድ) ጠርተው በሚሰጡት ኑዛዜ የመጀመሪያው የአባት ማስጠንቀቂያ ጋብቻን በሚመለከት ሊደረጉ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎች ነው፡፡

በተለይም በቶስ 36፥ ባል አግብታ የሄደች ልጅ ከባሏ ጋር ተጣልታ ወደ ቤተሰቦቿ ቤት ጉዞ ጀምራለች፡፡ እናቷ ደግሞ ከልጅቷ አባት ጋር ተጣልታ ስለነበር ቤቱን ለቃ ወደ ልጇ (ሴት) ቤት በመጓዝ ላይ ሳለች ..... መንገድ ላይ ተገናኙ፡፡

እናት፡- "ልጄ ወዴት እየሄድሽ ነው?"

ልጅ፡- "ባሌ አባሮኝ ነው።" አንቺስ እማየ?"

እናት፡- "እኔም ያንቺ አባት አባሮኝ ነው።" በይ ልጄ የሁለታችንም ችግር ተመሳሳይ ነው። አሁን አንቺን ለማስታረቅ የመጣሁ መስየ ዛሬን አንቺ ቤት ልደርና ከባልሽ ጋር ላስታርቅሽ፤ ነገ ጥዋት ደግሞ ወደኛ ቤት ሄደን ከአባትሽ ጋር እንታረቅ። <u>አየሽ ልጄ! ሁለታችንም ጠፍተንማ እንዴት ይሆናል</u>። ይባላል። (ሠረዝ የእኔ ነው)

ይህ ቶሳዊ አፈታሪክ በኑሮአቸው፣ በተለይም በባሎቻቸው ክፉ ድርጊት የተበደሉ ኮብላይ እናትና ልጅ ታሪክ በቤንች ብሄረሰብ ዘንድ ሴት ልጅ በቤተሰቧ ህይወት ውስጥ ባህሉ የጣለባትን ሀላፊነት በተለይ በልጅ አስተዳደግ (የምግብና መጠጥ እንክብካቤ ብቻ ሳይሆን ባህልን በማስተማር) ረገድ ሀላፊነታቸው ከበድ ያለ (የስራ ጫና ወይም የኢኮኖሚ ጥገኝነት አይደለም) መሆኑን ያሳያል። ስለዚህም ኮብላይዋ እናት ለልጇ እየነገረቻት በነበረችበት ሰዐት የሴት ልጇ ምሬትም ከርሷ ያልተናነሰ መሆኑን በተረዳች ጊዜ የልጇን ስነልቦና ያሸነፈችው "…. ሁለታችን ጠፍተንማ እንዴት ተደርጎ ይኖራል" የሚል ሀሳብ፣ ተግሳፅና ምክር በማቅረብ ነው።

እናት የቤተሰብ፣ የጎሳና የብሄረሰብን ህልውና ቀጣይነት በማረጋገጥ ረገድ ወሳኝ ድርሻ እንዳላት በቤንች ብሄረሰብ ዘንድ ይታወቃል። ይህም በምሳሌ እንዴት ሆኖ እንደተገለፀ በቶስ 74 ቀጥሎ ቀርቧል።

> … ድሮ ነው አሉ የዋንዛ ዛፍ ብዙ ፍሬ ታፈራለች። እነዚህ የዋንዛ ፍሬዎች ደግሞ በየወደቁበት ይበቅሉና እናታቸውን (ትልቋን ዛፍ) ዋንዛ ወደ ላይ እየተመለከቱ፡-
> "እማየ እንደምነሽ?" ብለው ይጠይቋታል።
> "ደህና ነኝ ልጆቼ" ብላ ስትመልስላቸው
> "ደህና ነኝ ስትይ ምን ማለትሽ ነው? አልገባንም" ብለው መልሰው ይጠይቋታል
> "አይ ልጆቼ እናንተን እስካልተውኳችሁ ድረስ እኮ ደህና ነኝ ማለት ነው" ብላ ዋንዛዋ ለልጆቿ መለሰችላቸው ብለው አባቶቻችን ይነግሩን ነበር።

በዚህ አጭር ትረካ እናት (ሴት) ተተኪውን ትውልድ (ልጆች) በማዘጋጀት ረገድ ያላትን ሚና መረዳት ይችላል።

አባ ማትዮስ ሻሽንቴትን "የቤንች ባህልና ሴቶችን" በተመለከተ እንዲያስረዱኝ በጠየቅኋቸዉ ጊዜ ለይተው ያስረዱኝ በቤንች የትዳር ህይወት ውስጥ የወንድና የሴት

ግንኙነት እና ሚና ተመጣጣኝ መሆኑን ብቻ ሳይሆን የቤተሰብን ህይወት በመምራት ረገድ ሴት (ሚስት) ያለባትን ባህላዊ ሀላፊነት በመግለፅ ነው፡፡

> አየህ! እኔ በቤንች ባህል መሰረት የብሄረሰቡ የመንፈስ አባትና ባህላዊ መሪ ነኝ፡፡ በቤንች ባህል ከፍተኛ ቦታ በሚሰጠው ባህላዊ እምነታችን መሰረት ዓመታዊ መስዋዕት ፈጣሪያችን ሳቀርብ ከሚስቴ ጋር ሆኜ ነው፡፡ እንዲያውም ወደ ሻተኬት (የካህ ቤተ አምልኮ) የተዘጋጀውን መስዋዕት ይዛ ቀድማ በሩን ተራምዳ የምትገባ እሷ (ሴት-ሚስት) ናት፡፡ እኔ ወንድ ነኝ ብየ ቀድሜ ብገባ - የካህስ ቁጣ ሊያጠፉኝ ይቻላል፡፡ (ሴላ ልጨምርልህ) ቤኑሽታቶን እንግዲህ ታውቀዋለህ፡፡ በኛ ባህል መሰረት ቤንችዶድ ለምንገኝ ባህላዊ መሪዎች ሁሉ የበላይ ቤኑሽታቶ ነው፡፡ ማንም አያዘውም ቤንቻቴት ስለሆነ፡፡ ይሁን እንጂ እርሱ በምድር ላይ የሚያከብረው ወይንም የሚታዘዘው በሚስቱ ብቻ ነው፡፡ ሚስቱ ካልፈቀደች ከቤት አይወጣም፡፡.... ለምሳሌ እዚህ እኔ ጊቢ መጥቶ .... ሰላም ለመባባል እርሱም እኔም ስንዘጋጅ የቤኑሽታቶ ሚስቱ "አይሆንም ተመለስ!" ካለችው እኔን እንደቆምኩ ትቶኝ ዞሮ መንገዱን ይቀጥላል.... በማለት ነው፡፡ (አባ ማትዮስ ሻሽንቴት)

ከሌሎች ያካባቢው ነዋሪዎችም እንደተገለፀልኝ በቤንች ባህል መሰረት በትዳር ውስጥ ሴቶች ሚናቸው ከፍ ያለ ነው፡፡ አቶ ጥላሁን ጨዋቃ እንዳሉትም "…. ሴላው ቀርቶ ሴቷ (ሚስት) ካልፈቀደች ወንዱ (ባል) ቡና ወይንም ከብት እንደፈለገ አውጥቶ መሸጥ በቤንች ባህል ነውር ነው" በማለት ነው፡፡

•

4.2.3 ማስተማርና ማዝናናት

የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች ሶስተኛው አቢይ ማህበራዊ ፋይዳቸው የብሄረሰቡን አባላት አዋቂዎችን፣ ወጣቶችንና እንዲሁም ልጆችን ተከታታይነት ወይም ቀጣይነት ባለው መልኩ የተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎችን ተጠቅሞ ማስተማር ብሎም ማዝናናት ነው፡፡ በዚህም በህብረተሰቡ ውስጥ የጋራ የሆነ አስተሳሰብ ለመመስረት ይረዳ ዘንድ እኛ (ቤንች) ማነን? ከየትስ ነው የመጣን? ወዘተ የሚሉ መረጃዎችን ለማስተማሪያነት ያቀብላሉ፡፡

ሚዳቋ አንድ ጊዜ ዘላ ዘላ ስትሮጥ ከዚህ (ደቡብ ቤንች) ተነስታ ሼቤንች ደረሰች፡፡ እለቱም የገበያ ቀን ነበር፡፡ በገበያ ውስጥ ስትዘዋወር የሚዳቋ ቆዳ አየችና በመገረም "እኔ ያለሁት እዛታች ቆዳየ ከመቼው እዚህ ደረሰ?" አለች አሉ፡፡

በዚህ አጭር ትረካ አማካኝነት ባብ ዶሽ (የዳቸበስ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪ ፡ ዕድሜ 82) የቤንች ብሔረሰብ በሰፊ መልክዐምድራዊ አካባቢ ቢኖርም የጋራ መነሻ ያለውና የወል ባህርያትን በስፋት የሚያንፀባርቅ፣ ተመሳሳይ የሆነ የኑሮ ልማድ ያለው ህዝብ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በተጨማሪም ቤንች መነሻ ምንጩ አንድ ሆኖ እንዴት ወደ ሶስት ሊከፈል እንደቻለ ቶስ 2 ይገልፃል፡፡

... በጥንት ዘመን የቤንች ብሄረሰብ ... የአሁኑ ሼቤንች ወረዳ ደርሶ መኖር በጀመረበት ጊዜ ህዝቡን ሲመሩት የነበሩ ንጉስ ዣዥርቴት አረፉ (ሞቱ)፡፡ በቤንች ባህል መሰረት ንጉስ ሞቶ ከመቀበሩ በፊት በቦታው የሚተካው ልጅ ይታወቅ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በጊዜው ንጉሱ ይህንን አልፈፀሙም፡፡ ስለሆነም የንጉሱ አስከሬን ከመቀበሩ በፊት ከልጆቹ መሀከል የአባቱን ቦታ ወራሽ የሚሆነውን ለመምረጥ ከፍተኛ ችግር ፈጥሮ ነበር፡፡ ... በተለይም በሁለቱ የንጉሱ ልጆች መሀከል ከፍተኛ ውዝግብ ተፈጥሮ በቤንች ብሄረሰብ አባላት መሀከል ግጭት ሊፈጥር ነበር፡፡ ... የዚህን ጊዜ ይህ "የአባቴን ቦታ የምተካው እኔ ነኝ" የሚል የወንድማማቾች ግጭት ወደ ቦክንቴት (ታላቅ ወንድማቸው) ዘንድ ሄዶ ውሳኔ ማግኘት አለበት ተባለ፡፡ ... ቦክንቴትም ካቤቱ ግድግዳ ላይ የደረቀ የምርጊት አፈር አምጥቶ እንዲህ አላቸው፡፡ "ይህንን ደረቅ አፈር በእጃችሁ ላይ አድርጉና እሹት፡፡ ከመሀከላችሁ አፈሩ በእጁ ላይ እንዳለ ወደ ውሃነት የተለወጠው በአባቱ ቦታ ላይ ተቀምጦ ይንገስ" አላቸውና አፈሩን ሰጣቸው፡፡ ... በታናሹ እጅ ላይ የበረው "ደረቅ የምርጊት አፈር ረጥቦ ውሃ ሆነ" ይባላል፡፡ ቦክንቴትም "የመረጥኩት እኔ ሳልሆን የአባታችሁ አምላክ ነው" አላቸው ይባላል፡፡ ሆኖም በወንድማማቾች መሀከል የተፈጠረው ግጭት እንዳያገረሽ በማለት በአባቱ ቦታ ንግስናውን ያላገኘውንም ልጅ ... አንቃ ሜርቴት ... (ግዙፍ ንጉስ ሁን ብያለሁ) ብሎ

መረቀ ይባላል። ... ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አንድ የነበረው ቤንች ሼ፣ ሜር እና ቤንች ተብሎ በሶስት ተከፈለ ...

የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች የብሄረሰቡን ማህበራዊና ባህላዊ ልማዶችን፣ አሰራሮችን እና ሰዋዊ ግንኙነትን የሚመለከቱ ዝርው ተረኮችን እየተረኩ የህብረተሰቡን ልዩ ልዩ ክፍሎች በተለይም ታዳጊዎችና ወጣቶችን እንዲሁም ጎልማሶችን እያዝናኑ ያስተምራሉ። ለዚህ ተግባር ከዋሉት ተረኮች መሀከል በተደጋጋሚ የሚነሱትን ጭብጦች እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

**የወላጅ/ቤተሰብን ምክር መቀበል**

በዝርው ተረኮች አማካኝነት የወላጅ/የቤተሰብ ምክርን የመቀበልን አስፈላጊነት የሚያስተምሩ ዝርው ተረኮች ዋነኛ ተግባራቸው ህብረተሰቡ ያዳበራቸውን ማህበራዊና ባህላዊ ልማዶች ተተኪው ትውልድ (ልጆች) እንዲቀበሉ በማድረግ ቀጣይነቱን ማረጋገጥ ነው። ለዚህ ተግባርም የወላጅ/ቤተሰብ ምክርን መቀበል እና አለመቀበል ውጤት ጎን ለጎን ይገለፃል። ምሳሌ ቶስ 34 እና ኤሸሽ 13 መመልከት ይቻላል።

በቶስ 34 አንድ ሰው የአባት (የቤተሰቡን) ምክርና ተግሳፅ ካልተቀበለ በህይወቱ ውስጥ ከፍተኛ ችግር እንደሚከሰት ለማሳየት አርጅቶ የመሞቻው ጊዜ የተቃረበው አባት ልጁን፡-

" ... መንገድ ዳር ቤት አትስራ፤ ትልቅ እንጨት ቤትህ ደጃፍ አትትከል፤ የሰው ደካማ ልጅም አታሳድግ፣ የሰው ሚስት የሆነች ሴትንም አፋተህ አታግባ ..."

ብሎ ተናዞ ሞተ። ሆኖም ልጁ ይህንን የአባቱን ኑዛዜ በመናቅ የፈፀመው ድርጊት መጨረሻውን እደጁ አጠገብ በተከለው ዛፍ ተሰቅሎ እንዲሞት ምክንያት ሆኗል።

ከቶስ 34 በተቃራኒ በኤሸሽ 13 የወላጅን ምክርና ተግሳፅ መስማት ጠቃሚነትን ያሳያል።

... ድሮ ጊዜ አንድ የነብርና አንድ የድኩላ ልጅ ነበሩ አሉ። እናቶቻቸው ወደ ምግብ ፍለጋቸው ከሄዱ በኋላ ሁለቱ ሳይተዋወቁ ይገናኙና ሲጫወቱ ውለው ማታ ወደ ቤት ይመለሳሉ። አንድ ቀን ማታ ከእናቶቻቸው ጋር ሲጫወቱ ቀን ላይ ስላጋጠማቸው ጉዳይ ይናገራሉ አሉ።

... የድኩላ ልጅ፦ ለእናቷ የቀኑ ውሎዋን እንዲህ ብላ ነገረቻት፡፡ "እማየ አንዲት የምታምር ዝጉርጉር አውሬ መጥታ ከእኔ ጋር ስትጫወት ውላ ሄደች፡፡ ምንም ነገር አላደረገችም፡፡" ብላ ስትነገራት የድኩላዋ እናት፦ "አንቺዬ ዘር ማንዘርሽን ሁሉ እኮ የጨረሱት የእነርሱ ዘሮች ናቸው፡፡ እኔ ጫካ ለጫካ ከእነርሱ ዘር ስደበቅ ቆይቼ ነው እኮ አንቺን የወለድኩት፡፡ ልጄ ሁለተኛ ያቺን ዝንጉርጉር አውሬ እንዳትቀርቢያት" ብላ ልጇን መከረቻት አሉ፡፡ በነጋታው ጠዋት የነብሪቷ ልጅ ... ትናንት የተጫወቱበት ቦታ በመገኘት "ድኩሊት ድክሊት ቶሎ ነይና እንደትናንቱ አብረን እንጫወት" ብላ ጠራቻት፡፡ የድኩላዋ ልጅም ጥሪዋን እንደሰማች "ያንቺ እናት እንደመከረችሽ ሁሉ የእኔ እናትም መክራኛለችና አልመጣም" ብላ አለቻት አሉ፡፡

ይህ ኤሸሽ 13 የወላጅ/ቤተሰብ ምክር ጠቃሚነትን ያስተምራል፡፡ ቤተሰብ ካለው ህይወቱ/ታሪኩ ተነስቶ ለልጆቹ የሚያስተምረው ወይም የሚሰጠው ምክር ልጆችን ከአደጋ እንደሚጠብቃቸው ያሳያል፡፡

## ያልለፉበትን (የራስ ያልሆነ) ነገር አለመፈለግ

ቀፎ ሰቅሎ የማያውቅ ሰውዬ ነበር፡፡ አንድ ቀን እሰው ቤት ሄዶ ጠጅ ጠጥቶ (ቀምሶ) አየ፡፡ ለካስ ይህ ጠጅ የሚሉት የሚሰራው ከማር ነው አለና "እኔስ እዛ ጎረቤቴ የሰቀለው ቀፎ ጋ ሄጄ ማሩን አውርጅ እስኪበቃኝ ድረስ ጠጅ አልጠጣም!" አለና እቃውን ይዞ ወደ ቀፎው ሄደ፡፡ ቀፎው ጋ ደርሶም ከስሩ በያዘው ዱላ በሳው፡፡ በዚህን ጊዜ እቀፎው ውስጥ የነበሩት ንቦች እንዳሉ ረገፉበትና ነደፉት፡፡ ሰውየውም ያልሰራበትን ነገር ለመጠቀም ሄዶ በንብ ተነድፎ ሞተ፡፡

ቶስ 48'ን የመሳሰሉ ዝርው ተረኮች ጭብጥ አንድ ሰው ሰርቶ መጠቀም/ማደግ የሚችለው በላቡ (በጉልበቱ) ብቻ መሆኑን ያሳያሉ፡፡ ይሁን እንጂ በተለያዩ አጋጣሚዎች የራስ ያልሆነን ንብረት፣ ገንዘብ ... የመሳሰሉትን የሌላ ሰው ንብረቶች አላግባብ ወስዶ/ቀምቶ/ ሰርቆ ለመጠቀም መሞከር መጨረሻው እንደማያምር ያስተምራሉ፡፡

## የብልጠት (አርቆ አሳቢነትን) አስፈላጊነት

የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች በተደግጋሚ ከሚያነሷቸው ጭብጦች ውስጥ ብልጠት (አርቆ አሳቢነት) ይገኛል፡፡ በዚህም አንድ ግለሰብ ወይንም ቤተሰብ ማንኛውምንም ነገር አርቆ በማየት ሊፈጠር ከሚችል ችግር ራስንና ሌላንም ማዳን እንደሚቻል ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም የራስንና የቤተሰብን ጥቅም ለማስጠበቅ ብልጠት (አርቆ አሳቢነት) አስፈላጊ መሆኑንም ያሳያሉ፡፡ ምሳሌ፡-

በቶስ 36 በባሎቻቸው የሀይል ተግባራት የተነሳ የተማረሩት ኮብላይ እናትና ልጅ ወደ ቤታቸው ተመልሰው ከባሎቻቸው ጋር ለመታረቅ የወሰኑት የትዳራቸው መፍረስ በራሳቸውና በቤተሰባቸው ላይ የሚያስከትለውን ጣጣ አርቆ በማሰብ ነው፡፡

በቶስ 41 እንዲሁ አገልጋዩ አንድ ጆሮውን አሳዳሪው እንዲቆርጠው በዘዴ የነገረው የወደፊቱን ወይም የራሱን ጥቅም ቀጣይነት ለማረጋገጥ በማሰቡ ነው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በኤሸሽ 4 “ሌባዋ ጦጣ” እና በኤሸሽ 14 “ትንሿ አይጥ” ራሳቸውን ከአደጋ ያወጡት ከሌሎቹ የተሻሉ ብልጦች በመሆናቸው ነው፡፡

በተጨማሪም የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች ቃልኪዳንን ማክበር፣ ለጓደኛ መታመን፣ አስቸጋሪ ጊዜያትን በዘዴ ማሳለፍ እና የመተባበር ፋይዳን በየጭብጦቻቸው ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች እለታዊ የግልና ማህበራዊ ህይወትን እንዴት መምራት እንደሚገባ ለማስተማር የሚረዱ የስነምግባር ኮዶችን (codes) ያቀብላሉ፡፡ በብሄረሰቡ ባህል፣ እምነትና ማህበራዊ ልማድ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውን አስተሳሰቦችና አሰራሮችን ማለትም፡- ለስራ መትጋትን፣ ኑሮን ባግባቡ መምራትን፣ ታማኝነትን፣ የቤተሰብና የማህበረሰብ ፍቅርን በወጣቱ አዕምሮ ውስጥ ያሰርፃሉ፡፡

### 4.2.4 ታሪክን መቅረስና ለመጭው ትውልድ ማስተላለፍ

የቤንች ብሄረሰብ በቃላዊ ዝርው ተረኮቹ አማካኝነት በተለያዩ ጊዜያት ያጋጠሙትን ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ አደጋዎች፣ የብሄረሰቡን ኬት መጥነት፣ የአኗኗር ልማዱን በታሪክነት ቀርሶ ለቀጣዩ ትውልድ ያስተላልፋል፡፡ ከተሰበሰቡት የዝርው ተረክ መረጃዎች ውስጥ ለዚህ ተግባር ማሳያነት የሚከተሉትን አቀርባለሁ፡፡

## ባህላዊ አስተዳደር

ቶስ 4 … ቤንች ማለት የህዝቡ ወይንም የብሄረሰቡ መጠሪያ ነው፡፡ ይህንኑ ህዝብ የሚመሩት ባህላዊ መሪ ቤንችቴት ይባላሉ፡፡ በቤንችቴት ስርም በርጊናንስ፣ ኪቡ፣ ጋሪናንስ፣ ኮምቲካስ፣ ዳኪራሻና ሻሽንቴት የሚባሉ ቤትቲያት ነበሩ፡፡ እነዚህ ስድስቱን ቤንችቲያት አስተባብሮ የሚመራው ቤንችቴት ነው፡፡

በዚህም የቤንች ብሄረሰብ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት ማህበራዊ መዋቅር እንደነበረው በዝርው ተረኩ ይገልፃል፡፡

## የብሄረሰቡን ኬት መጥነት

ቶስ 13 … የቤንች ብሄረሰብ ጥንት ሲኖር የነበረው በዛሬው የጋሞጎፋ ዞን ሩዶልፍ ሀይቅ አካባቢ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በአንድ ወቅት በዚህ አካባቢ በተነሳው ከፍተኛ ወባ መሰል ወረርሽኝ ብዙ ሰው ስላለቀ ይህንን አካባቢ ለቀው ባደረጉት እንቅስቃሴ ዛሬ የሚገኙበት ቤንች ማጅ ዞን በተለይም ሼቤንች ወረዳ ደርሰው ሰፈሩ፡፡

በዚህ አይነት እንደ ቶስ 13፣ ቶስ 14፣ ቶስ 15 የቤንች ብሄረሰብ በተለያዩ ዘመናት ባደረጉት እንቅስቃሴ ከየት ተነስተው የት እንደደረሱ በቃላቸው ይዘግባሉ፡፡

## ጦርነት

የቤንች ብሄረሰብ በተለያዩ ዘመናት ወደ አካባቢው ከመጡ ልዩ ልዩ ሀይሎች ጋር ያደረገውን ጦርነት በቃላዊ ዝርው ተረኮቹ አማካኝነት ቀርሶ ያኖራል፡፡ ለዚህም ማስረጃዎች ቶስ 18፣ ቶስ 19፣ ቶስ 21፣ ቶስ 29ን የመሳሰሉት ተረኮች የቤንች ብሄረሰብ ከኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት ሀይሎች እና ከጣሊያን ፋሽሽት ወታደሮች ጋር ያደረገውን ጦርነት ቀርሷል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ አካባቢዎች ስያሜ ማለትም ቶስ 24፣ ቶስ 25፣ ቶስ 26 እና ቶስ 27 አማካኝነት የተገለፁት የቦታ ስያሜዎች መነሻ ታሪካቸውን በዝርው ተረኩ መዝግቧል፡፡

## ኢኮኖሚ

የቤንች ብሄረሰብ እንደዛሬው የወረቀት ገንዘብ (ብር) ከመጠቀሙ በፊት በአካባቢው የነበረው መገበያያ "ጨሌ" እንደነበር በቶስ 16 ተገልጿል፡፡ በዚህ አይነትም በተለያዩ ዘመናት ለመገበያያ ሲጠቀምባቸው የነበሩትን እቃዎች፣ እንደ እንቁላል፣ ከብት፣ ... የመሳሰሉትን የታሪኩ አንድ ክፍል አድርጎ በመቅረስ ለዛሬው ትውልድ አድርሷል፡፡

በአጠቃላይ የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች በብሄረሰቡ ማህበራዊና ባህላዊ ህይወት ውስጥ ያላቸው ፋይዳ በዚህ ጥናት ውስጥ በዝርዝር ተዳሷል፡፡ ቤንች በዝርው ተረኮቻቸው አማካኝነት ባህላዊ እምነታቸው በእለታዊ ህይወታቸው ውስጥ የሚጫወተውን ዘርፈ ብዙ ሚና ይገልፃሉ፡፡ የልዩ ልዩ ማህበራዊና ባህላዊ ተቋሞቻቸው እሴቶችን አስፈላጊነት አጉልተው ያሳያሉ፡፡ ወጣቱና ታዳጊው ብሎም ጎልማሳው የማህበረሰቡ አባል ራሱን እንዴት አድርጎ ከአካባቢው ነዋሪ ጋር አስማምቶና አቻችሎ መኖር እንዳለበት እያዝናኑ ያስተምሩባቸዋል፡፡ በመጨረሻም ባለፈው ትውልድና በዛሬው ብሎም በመጭው ትውልድ መሀከል ያለው ግንኙነት ተጠብቆ እንዲኖር ታሪኩን ቀርሶ እንዲሁ በነዚሁ ተረኮቹ ያስተላልፋል፡፡

ቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸውን ከተረኮቹ መከወኛ ጊዜ፣ ከተረኮቹ ታሪክ እውነትነትና ፈጠራነት እንዲሁም ከተረኮቹ ልዩ ልዩ ተግባራት በመነሳት ቶስ እና ኤሽሽ በማለት በሁለት ይከፍሏቸዋል።

የቤንችቶስ በታሪኩ ውስጥ የሚያቀርበው ታሪክ እውነት የሆነ ወይም እውነትነቱ ሊረጋገጥ የሚችል ነው። ክዋኔውም በቀን (በፀሃይ ብርሃን) የሆነ፣ ዋንኛ ተግባሩም የብሄረሰቡን ባህል፣ ታሪክና የማህበራዊ ኑሮ ዘይቤዎችን መግለፅ፣ ማስተማር፣ በግልም ሆነ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ተግባራዊ የሚደረጉ "መመሪያዎችን" የሚመለከቱና በጥቅሉ የምር የሆኑ ጉዳዮች የሚገለፁበት ነው። በቤንች ቶስ ትረካ የማስደሰት/ማዝናናት ተግባር ብዙም ትኩረት አይሰጠውም ወይም ለማዝናናት ተብሎ አይተረክም። በቤንች ቶስ እውነተኛ፣ ጠቃሚ የሆነው የአያት (የቀደመው ትውልድ) እውቀት፣ ልምድ፣ ታሪክ፣ እምነት ... የሚገለፅበት በመሆኑ ተራኪውም በጥንቃቄ ያቀርባል (ይተርካል) ታዳሚው (አድማጩም) በጥሞና ያዳምጣል።

የቤንችቶስ "ቶስ" በሚለው የወል ስም ተጠቃለው የሚጠሩ ሆኖም የተለያዩ ፋይዳ ያላቸው ዝርው ተረኮችን በውስጡ የያዘ ነው። እነዚህም በጥናቱ ገላጭ ትንተና እንደታየው አፈታሪክ፣ ገላጭ ተረኮች እና አጫጭር ተረቶች በማለት ተከፍለዋል። የነዚህ ዝርው ተረኮች የጋራ መገለጫቸው በአቢይነት ከመደበኛ የመክፈቻ ቀመሮች ቀደም ብለው "'ኑ አከስ ቶስ ኑ አይጡሽ ..." (አያቶቻችን) አባቶቻችን እንደነገሩን ... በማለት ትረካቸውን የሚጀምሩ ናቸው። ይህም የሚቀርበውን ታሪክ ከማስታወቅ ሌላ፤ "በአከስ" አያት የሚገለፀው ሀሳብን ማመስገን፣ ማወደስ ቦታ/ዋጋ መስጠትን የሚያመለክት ነው።

የቶስ አፈታሪክ ከሌሎች የቤንች ዝርው ተረክ ዘሮች ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ ትኩረት ተሰጥቶት የሚተረክ መሆኑን መረዳት ይቻላል። የቶስ አፈታሪክ በአንድ ወቅት የነበሩ ሰዎችን ወይም የታዩ ክስተቶችን መነሻ አድርጎ የሚመሰረት ነው። በውስጡም ከተካተቱት ታሪኮች አብዛኛዎቹ በታዋቂ ግለሰቦችና በተራ ግለሰቦች ዙሪያ የተነገሩ ናቸው። በሁለቱ መሀከል ያለው ዋናው ልዩነትም በታዋቂ ግለሰቦች ላይ የተነገሩት በጭብጣቸው፣ ባህላዊ፣ ታሪካዊ የሆኑ ጉዳዮችን ያመለክታሉ። በተራ ግለሰቦች አንጻር የተነገሩት ደግሞ ተከታታይ ድርጊቶችን አንስላስለው በመተረክ የታሪኩን መዋቅር የሚመሰርቱ ናቸው። በቅርፃቸውም ረዥም፣ በእለታዊ ህይወት ውስጥ የሚንፀባረቁ በርካታ ጉዳዮችን የትረካቸው ማጠንጠኛ የሚያደርጉ ናቸው።

# ማጠቃለያ

የቤንች ህዝብ በተረኮቹ አማካይነት ልዩ ልዩ ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶቹን በቃል ቀርሶ እንዲሁ ቃላዊ በሆነ መንገድ ከትውልድ ትውልድ ያስተላልፋል፡፡ በዚህም ታሪኩን፣ እምነቱን፣ በእለታዊ ህይወቱ የሚመራበትን የስነ-ምግባር ስርዓቶችንና ደንቦችን ይደነግጋል፡፡ ማህበራዊ ልማዶቹን በጥቅሉም የህይወት ፍልስፍናውን በአያት (አከስ) መንፈስ ተምሳሌትነት የቀደመውን ትውልድ አሻራ በዛሬው ውስጥ አስርፆ የመጪውን ትውልድ ህያውነት በዘመኑ ትውልድ መንፈስ ውስጥ ይቃኝበታል፡፡ የማንነቱ መለያ ይሆነው ዘንድ እኔነቱም ከዚሁ ይቀዳል፡፡

ይህ ጥናት የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች በብሄረሰቡ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ያላቸውን ፋይዳ ከልዩ ልዩ ማህበራዊና ባህላዊ ተቋማቱ አንፃር ማሳየት፣ ጥበባዊ የማዝናናት ሚናቸውን እንዴትነት ብሎም የብሄረሰቡ አባላት የእኛ ናቸው ብለው ለይተው የሚያመለክቷቸውን የዝርው ተረክ ዘሮች በመለየት ገላጭ ባህርያቸውንና የአውዳዊ ክወናቸውን እንዴትነት ማሳየት ነው፡፡

የቤንች ዝርው ተረኮች በብሄረሰቡ ማህበረ-ባህላዊ ህይወት ውስጥ ያላቸው ፋይዳ በአራት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር መሆኑ በዚህ ጥናት ታውቋል፡፡ የመጀመሪያው መንፈሳዊ እሴቱ በብሄረሰቡ ልዩ ልዩ የህይወት ገፅታዎች ውስጥ ወሳኝ ሚና እንደነበረው ዛሬም እንዳለው ይህ ጥናት ያሳያል፡፡ በባህላዊ እምነቱ ስለሰው ልጅ ስለእንስሳት አፈጣጠርና ወቅታዊ ባህርያት ይገልፃል፡፡ የብሄረሰቡ አባላት ኬትመጥነት፣ ልዩ ልዩ የአሰራር ስልቶች፥ የእርሻ፣ የከብት እርባታ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ የመሬት አስተራረስ፣ ወዘተ. ያስገነዝባል፡፡ የማህበረ-ባህላዊ ተቋማቱን፥ ማለትም የባህላዊ አስተዳደሩን አስፈላጊነት፣ የባህላዊ ሽምግልና/ዳኝነትን እውነተኛነትና ፍትሃዊነት፣ የቤተሰብ/የትዳርን አስፈላጊነት፣ ጥበቃን ብሎም በማህበራዊ ህይወቱ ውስጥ ያለውን ወሳኝነት ያሳያል፡፡

በተጨማሪም እነዚሁ ዝርው ተረኮች በልዩ ልዩ የብሄረሰቡ ማህበራዊ ልማዶች ውስጥ ሰናይ የሆኑትንና ተቀባይነት የሌላቸውን ባህርያትና አሰራሮችን ለይተው በመግለፅ አንድ ግለሰብ ራሱን ከአካባቢው ነዋሪ ጋር አስማምቶ እንዴት መኖር እንዳለበት ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም የብሄረሰቡ አባላት በልዩ ልዩ ወቅቶች ያሳለፉት ህይወት በዝርው ተረኮቹ ቀርቧል፡፡ በመጨረሻም ህፃናትን/ልጆችን እያዝናኑ በማስተማር፣ የህፃናቱን አስተሳሰብ መቅረጫነትም ያገለግላሉ፡፡

የቶስ ገላጭ ትረካዎች በጭብጣቸው የብሄረሰቡን መንፈሳዊ እሴቶች በስፋት የሚያንፀባርቁ ሲሆኑ በአንድ ጉዳይ ላይ ብቻ ትረካ የሚያደርጉ ናቸው። እነዚህም ስለዓለመዓለማት አፈጣጠር፣ ስለ ባህላዊ እምነት ስርዓትና አፈፃፀም ወቅታዊ የሆነ የእንስሳት ባህርያት ኬት መጥነት ወዘተ. ያሳያሉ።

አጫጭር ትረካዎቹ በቋንቋቸው ዘይቤያዊነት የሚለዩ ሲሆኑ በትረካ መሀከል የሚከሰቱ ናቸው። በተለይም ተራኪው አንድን የትረካ አጋጣሚ መነሻ አድርጎ ሁኔታዎችን ባህርያትን፣ ድርጊቶችንና ወዘተ. ስእላዊ አድርጎ የመግለፅ ብቃቱን ያሳያሉ።

የኤሽሽ ዝርው ተረኮች ታሪካቸው ፈጠራ ነው። ገፀባህርያቱም በአብዛኛው እንስሳት ሲሆኑ አብዛኛዎቹ ተረቶች ረዣዥም ናቸው። አወቃቀራቸውም በዝርው ቅርጽ ብቻ ወይም ዝርውና ግጥማዊ ቅርጽን አጣምረው ነው። የኤሽሽ ዝርው ተረኮች የሚነገሩት በምሽት ጊዜ ሲሆን ዋንኛ አላማቸውም ህፃናትን/ልጆችን ማዝናናት ሆኖ ተራኪዎቹም አባት፣ እናት ወይም ትላልቅ ሰዎች ናቸው። መደበኛ የመክፈቻና የመዝጊያ ቀመሮችን በወጥነት የኤሽሽ ትረካ ይጠቀማል። በኤሽሽ ዝርው ተረኮች ውስጥ ለማስተማር ተግባር የሚሰጠው ቦታ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ነው።

ከተራኪዎቹ ማንነት አኳያ ሲታይም የቤንችቶስ ተራኪ ናቸው ተብለው የሚታወቁ በግልፅ የሌሉ ሲሆን ማንኛውም የቤንች ብሄረሰብ አባል አውዱ እና የትረካው መቼት እስከፈቀደለት ድረስ መተረክ ይችላል። ሆኖም የቶስ አፈታሪኮችንና ገላጭ ታሪኮችን በአብዛኛው የሚናገሩት ጎልማሶችና ሽማግሌዎች ናቸው። ሴቶችና ህፃናት በተለያዩ የትረካ አጋጣሚዎች ለማየት እንደተቻለው የተራኪነት ተሳትፏቸው እጅግ አነስተኛ ነው።

የኤሽሽ ዝርው ተረክ ተራኪዎች አዋቂ ሰዎች ሲሆኑ በአብዛኛው እናቶች ናቸው። ታዳሚዎቹ (አድማጮቹም) ህፃናትና ልጆች ናቸው። በቤንች ባህል ቀን ላይ ኤሽሽ የሚናገር ወይም ሲነገር የሚያዳምጥ ልጅ "ቀንድ ያበቅላል" ስለሚባል የአጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ ቀን ላይ ትላልቅ ሰዎች ኤሽሽ ተረት ሲተርቱ ቢሰማ ህፃናቱ/ልጆች የሆኑት ቆመው አያዳምጡም።

በመጨረሻም የቤንች ዝርው ተረኮችን በተለይም የኤሽሽ ዝርው ተረኮችን በተመለከተ ሊገለፅ የሚገባው ጉዳይ አለ። ይኸውም ከመስክ ከተሰበሰቡት መረጃዎች መረዳት የሚቻለው የተሰበሰቡት የኤሽሽ ተረቶች 20 ያህል ብቻ ናቸው። ተራኪዎቹም የተወሰኑ አዛውንቶች/ጎልማሶች ናቸው። አብዛኞቹ የዝርዉ ተረክ አቀባዮች ኤሽሽ ተረት እንዲናገሩ ሲጠየቁ (ምሽት ጊዜም ቢሆን) እንደማይችሉ ይናገራሉ ወይም ደግሞ "ኤሽሽ እኮ አሁን እየቀረ ነው።" የሚል መልስ ይሰጣሉ። በአጠቃላይ በመስክ ቆይታ ወቅት ያረጋገጥኩት

የኤሽሽ ተረቶችን በተመለከተ ህብረተሰቡ (አዋቂዎቹ) እንደጥንቱ ልማድ ሲተርኩ የማይሰማና ወጣት/ልጆች ለተረቶቹ ብዙም ትኩረት የማይሰጡ መሆናቸውን ነው። ይህን አጠቃላይ ሀሳብ መነሻ በማድረግ በዞኑ ውስጥ የሚገኙ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በተለይም ባህል ቢሮ፣ የሚመለከታቸውን አካላት አስተባብሮ የቤንች ኤሽሽ ተረቶች ከመጥፋታቸው በፊት ከነክዋኔ አውዳቸው የሚሰበሰቡበትን መላ ሊፈልግ ይገባል።

# የዋቢ መጻህፍትና ጽሁፎች መዘርዝር


ሙሉነህ ጉግሳ፣ "የክስታኔ ተረቶች"፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1993 ዓ.ም.።

ሙሉጌታ ነጋሳ፣ "በጅባትና ሜጫ አውራጃ የተሰበሰቡ የገበሬ ህይወትን የሚያንፀባርቁ የኦሮምኛ ተረቶች"፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1976 ዓ.ም.።

ሱሩር በድሩ፣ "የስልጤ ተረቶች ይዘት ትንተና" ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1995 ዓ.ም.።

ሰውነት መኮንን፣ "በሞጣ አውራጃ የሚነገሩ የአማርኛ ተረት ተረቶች" ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1984 ዓ.ም.።

ኩንዲሳ ፈርኪ፣ "የቤንች ብሄረሰብ ታሪክና ባህል ጥናት" ሚዛን ተፈሪ (ያልታተመ)፣ 1988 ዓ.ም.።

ደሀብ ትኩ፣ "የትግርኛ ተረቶች"፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1974 ዓ.ም.።

"የልማት የሰላምና ዲሞክራሲ የሁለተኛው ዙር የአምስት ዓመት መርሀግብር አፈፃፀም ግምገማና የሶስተኛው ዙር አምስት ዓመት መርሃ ግብር ሰነድ"፣ የቤንች ማጂ ዞን አስተዳደር ጽህፈት ቤት፣ ሚዛን፣ 1998 ዓ.ም.።

"የ1998-2000 የወጪ ፕሮግራም (የተሻሻለ) ሰነድ" የቤንች ወረዳ ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣ አማን፣ 1998 ዓ.ም.።

"የ1996 ዓመታዊ ሪፖርት"፣ የቤንች ወረዳ አስተዳደር ጽህፈት ቤት፣ አማን፣1996 ዓ.ም.።

ያዕቆብ ወልደማርያም፣ "የከፋ ተረት ተረቶች"፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1974 ዓ.ም.።

ፈቃደ አዘዘ፣ <u>የስነቃል መመሪያ</u>፣ አዲስ አበባ፣ ኢንተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መረዳጃ ተቋም፣ 1991 ዓ.ም.።

Abbott, Potter H. The Cambridge Introduction to Narrative. Cambridge University Press, 2002.

Abdulkadir Haji Jama. "Some Cultural Elements As Reflected in Somali Folktales." M.A. Thesis. School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 1982.

Abraham Alemu. "Jimma Oromo Oral Prose Narratives: A Preliminary Descriptive Analysis." M.A. Thesis. School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 2000.

Bahru Zewde. A History of Modern Ethiopia 1955-1974 Addis Ababa University Press, 1991.

Bascom, William R. "Four Functions of Folklore" in Alan Dundes, ed. The Study of Folklore. Prentice-Hall, Inc., Englewood Cliffs, N.J.; Prentice-Hall, Inc. 1965.

Ben-Amos, Dan. FOLKLORE IN CONTEXT. South Asian Publishers, New Delhi, 1982.

Bender, Lionel. M. Comparative Morphology of the Omotic Languages. Lincom Euro Freibadstr, Muenchen, 2000.

Bayilegn Tasew. "Anyuaa Oral Prose Narratives Ethnic Genres and Social Functions." M.A. Thesis. School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 1999.

Cerulli, Ernesta. Peoples of South-West Ethiopia and Its Border Land. (Part III). Hazell Watson and Viney, London, 1956.

Fatterman David M. Ethnography. Vol. 17. SAGA Publications, USA, 1988.

Finnegan, Ruth. Oral Literature in Africa. Oxford: Clarendon Press, 1970.

Georges, Robert A. "Towards an understanding of story telling events," Journal of American Folklore 82 (1969): 313-28.

Girmaye Kebede. "Production Practice Among the Bench." M.A. Thesis. School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 1993.

Goldstein, Keneith. A Guide for Field Workers in Folklore. Hatboro, 1965.

Lind, Degh. "Folk Narratives in Dorson", Folklore and Folk life: An Introduction. The University of Chicago Press, ed. 1972.

Melakneh Mengistu. "The Major Themes and Motifs of Southern Agaw Folktales." M.A. Thesis. School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 1990.

Nicolas, Gildas. "The Dizzy of South-West Ethiopia. An Essay in Cultural-History Based on Religious History." Phd. Dissertation, University of California, 1976.

Okombo, Okoth. "Oral Literature and Translation" in Austin Bukenya, Understanding Oral Literature. Nairobi University Press, ed. 1994.

Okpewho, Isidore. African Oral Literature. Bloomington and Indianapolis: Indiana University Press, 1992.

Oring, Elliot. Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction: Logan, Utah: Utah University Press, 1986.

Perham, Margery. The Government of Ethiopia. North Western University Press, London, 1969.

Sahilu Kidane. "Borana Oromo Prose Narratives: A Contextual Study." M.A. Thesis. School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 1996.

SNNPRS Cultural Profile. "Information and Culture Bureau. 1998/2006, Awasa.

Tesfaye Gebre Mariyam. "A Study of Major Themes in Jablawi Folktales." M.A. Thesis. School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 1990.

Thompson, Stith. The Folktale. New York, 1946.

Tippett, Alan R. People of South West Ethiopia. The William Carey Library South Pasadena, Calf, USA, 1970.

Wallis, Budge E.A. A History of Ethiopia. Vol. 2. Anthropological Publications Osterhoat N.B., The Netherlands, 1966.

Wedekind, Klaus. “A Six Tone Language in Ethiopia. Tonal Analysis of Benčnon.” Journal of Ethiopian Studies, Vol. XVI (1983): 129-150.

Yihenew Jembere. “A Generic Classification of Amharic Oral Prose Narratives of West Gojiam.” M.A. Thesis. School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 1996.

# አባሪ አንድ

## የቤንች ዝርው ተረኮችን በመንገር የተባበሩኝ የዝርው ተረክ አቀባዮች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ስም | ፆታ | ዕድሜ | መኖሪያ ቀበሌ | ስራ | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ቤኑሽታቶ ጋይስ ጊሽቱናንስ | ወ | 65 | ካርሽቃ ዞዞ | ባህላዊ መሪ | |
| 2. | አባ ማትዮስ ሻሽንቴት | ወ | 50 | ጌሊት | ባህላዊ መሪ | |
| 3. | ቄስ ተገኝ ማርኩ | ወ | 60 | ሚዛን 02 | ወንጌላዊ | |
| 4. | ባብ ዊኒያ ዳንቹ | ወ | 67 | ጌሊት | ገበሬ | |
| 5. | ባብ አሰፋ ወሰኑ | ወ | 70 | ጌሊት | ገበሬ | |
| 6. | ባብ ዓለማየሁ ወዜብ | ወ | 50 | ጌሊት | አናጢ | |
| 7. | ባብ ግርማ | ወ | 45 | ጌሊት | ገበሬ | |
| 8. | ባብ አሸኩ ባንገርስ | ወ | 75 | ዳቸበስ | ገበሬ | |
| 9. | ባብ ዶሽ | ወ | 82 | ዳቸበስ | ገበሬ | |
| 10. | ባብ ሲልባያ | ወ | 76 | ዳቸበስ | ገበሬ | |
| 11. | ባብ ቤላ | ወ | 70 | ዳቸበስ | ገበሬ | |
| 12. | ባብ ሽፈራው ካርጉ | ወ | 65 | ዳቸበስ | ገበሬ | |
| 13. | ባይ ካሽ ጉንፋ | ሴ | 55 | ዳቸበስ | የቤት እመቤት | |
| 14. | አበበች ሽፈራው | ሴ | 18 | ዳቸበስ | ተማሪ | |
| 15. | ባብ ኤደን ሽፈራው | ወ | 47 | ዳቸበስ | ገበሬ | |
| 16. | ባብ አላ ናካ | ወ | 55 | ሚያህ | ገበሬ | |
| 17. | ባብ ጣል ባይባ | ወ | 65 | ሚያህ | ገበሬ | |
| 18. | ባብ አበሽ ቱጊ | ወ | 65 | ሚያህ | ገበሬ | |
| 19. | ባብ ፌል | ወ | 55 | ሚያህ | ገበሬ | |
| 20. | ባብ ታዝ ጌዱ | ወ | 60 | ሚያህ | ገበሬ | |
| 21. | ባብ ስቴ ዳቸብ | ወ | 65 | ሚያህ | ገበሬ | |
| 22. | መንከሻ ካላ | ወ | 25 | ሚያህ | ገበሬ | |
| 23. | ጴጥሮስ ክፍሌ | ወ | 20 | ሚያህ | ተማሪ | |
| 24. | ሲያን ዜጥና | ወ | 18 | ሚያህ | ተማሪ | |
| 25. | ኩሰላ ማሽንቴት | ወ | 24 | ዳቸበስ | ገበሬ | |
| 26. | መኮንን ጊንተር | ወ | 30 | ዳቸበስ | ገበሬ | |
| 27. | አቶ ጥላሁን ጨዋቃ | ወ | 55 | ደብረወርቅ | ነጋዴ | |

# አባሪ ሁለት

## ቃል በቃልና አዛማጅ ትርጉም በቤንች ቋንቋ ወደ አማርኛ የተተረጎሙ የቤንች ቶስ ቃላዊ ዝርው ተረኮች

### ቶስ 1

ቤንችቴት የቤንች መሪ/ንጉስ ነው፡፡ ስለ ህዝቡ ሰላም፣ መሬት ጥሩ ምርት እንዲሰጥ፣ ከብቶች እንዲረቡ፣ ንቦች ጥሩ ማር እንዲሰሩ፣ በሽታ በሀገር ገብቶ ህዝብ እንዳይጨርስ በማለት ሁል ጊዜ በየሮሰንዶ (ፈጣሪ) እና በህዝቡ ፊት በትጋት ይቆማል፡፡

### ቶስ 2

በጥንት ዘመን የቤንች ብሄረሰብ ሼቤንች ከመድረሱ በፊት ገፖም (በአረንጓዴ ተክል የተሸፈነ ቦታ ማለት ነው) በተባለ አካባቢ ይኖር ነበር፡፡ ከዚያ ተነስቶ የአሁኑ ሼቤንች ወረዳ ደርሶ መኖር በጀመረበት ጊዜ ህዝቡን ሲመሩት የነበሩ ንጉስ ገፕቨቴት አረፉ፡፡ በቤንች ባህል መሠረት ንጉስ ሞቶ ከመቀበሩ በፊት በቦታው የሚተካው ልጅ ይታወቅ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በጊዜው ንጉሱ ይህንን አልፈፀሙም፡፡ ስለሆነም የንጉሱ አስክሬን ከመቀበሩ በፊት ከልጆቹ መሀከል የአባቱን ቦታ ወራሽ የሚሆነውን ለመምረጥ ከፍተኛ ችግር ፈጥሮ ነበር፤ ብለው አባቶቻችን ይነግሩናል፡፡ በተለይም በሁለቱ የንጉሱ ልጆች መሀከል ከፍተኛ ውዝግብ ተፈጥሮ፡ በቤንች ብሄረሰብ አባላት መሀከል ግጭት ሊፈጥር ነበር፡፡ የሀገር ሽማግሌዎች (ኤርግ) ችግሩን መፍታት አቃታቸው፡፡ የዚህን ጊዜ ይህ "የአባቴን ቦታ የምተካው እኔ ነኝ!" የሚለው የወንድማማቾች ግጭት ወደ ቦክንቴት (ታላቅ ወንድም) ሄዶ ውሳኔ ማግኘት አለበት ተባለ፡፡

ቦክንቴትም በሁለቱ ወንድማማቾች መሀከል የተፈጠረውን ጭቅጭቅ ለመፍታት ያቀረበላቸው ሀሳብ ተቀባይነትን አጣ፡፡ ጦርነቱ ሊነሳ፤ ግጭቱም ሊፋፋም ሆነ፡፡ በመጨረሻም ቦክንቴት ከቤት ግድግዳ ላይ የደረቀ የምርጊት አፈር አምጥቶ እንዲህ አላቸው፡- "ይህንን ደረቅ አፈር በእጃቸሁ ላይ አድርጉና እሹት፡፡ ከመሀከላችሁ አፈሩ በእጁ ላይ እንዳለ ወደ ውሃነት የተለወጠው በአባቱ ቦታ ላይ ተቀምጦ ይንገስ" አላቸውና አፈሩን ሰጣቸው፡፡

ዩአምላካቸውን (የሮሰንዶ) ስም ጠርቶ በየእጃቸው ላይ ደረቁን አፈር ሲያስቀምጥ በታናሹ እጅ ላይ የነበረው ደረቅ የምርጊት አፈር ረጥቦ ውሃ ሆነ ይባላል፡፡ በክንቴት "የመረጥኩት እኔ ሳልሆን የአባታችሁ አምላክ ነው" አላቸው ይባላል፡፡ ሆኖም በወንድማማቾች መሀከል የተፈጠረው ግጭት እንዳያገረሽ በማለት በአባቱ ቦታ ንግስናውን ያላገኘውንም ልጅ፡- "አንቃ ሜርቲያት፤ ኒኢች ኤሸንድ ድንግኤትም አቲሸንዳ!" ("አንተም ከወንድሞችህ በታች አትሁን ግዙፍ! ንጉስ ሁን ብያለሁ!") ብሎ መረቀ ይባላል፡፡ ሆኖም የሁለቱም ታላቅ የነበረውም ንጉሱ አባታቸው ከመሞቱ በፊት ጫካ ውስጥ ገብቶ (እንደ ጥንቱ የቤንች ነገስታት ልማድ) ተቀምጦ ስለነበር እርሱም ንጉስ ሆኖ ነበርና አልተነካም፡፡ ስለዚህም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አንድ የነበረው ቤንች ሼቴት፣ ሜርቴት እና ቤንችቴት ተብሎ ለሶስት ተከፈለ፡፡ ይሁን እንጂ ከመጀመሪያ በአባቱ ቦታ እንዲቀመጥ ስለተመረጠ የንጉስነገስትነት ቦታው <u>የቤንችቴት</u> ነው ተብሎ ሲነገር ከአያቶቻችን ሰምተናል፡፡

### ቶስ 3

አንድ ቤንችቴት ሲሞት በእርሱ ቦታ የሚተካውንና ከቤተሰቡ መሀከል የሚመረጠው ግለሰብ ማንነት የሚታወቀው የሚያንጎ (አያት) መንፈስ ሲወርድበት ነው፡፡ በንግስናውም በዓል ላይ ብሽንካል የተባለች ወፍ ትመጣና በጭንቅላቱ ወይም በትከሻው ላይ ታርፍለች፡፡ የዚህን ጊዜ በየሮ (ፈጣሪ) የተመረጠው ሰው ይህንኑ ጌትነት አልፈልግም ብሎ ቢሮጥ እንስሳት፡- አንበሳ፣ ነብር፣ እባብ … ከበውት ወደ ህዝቡ ዘንድ ያመጡታል፡፡ አይነድፉትም፤ አይነክሱትም ያከብሩታል፡፡ በአጠቃላይ አንድ ሰው ቤንችቴት ሆኖ ሲመረጥ ተራ ሰው መሆኑ ይቀራል፡፡

•

### ቶስ 4

ቤንችቴት የሁላችንም አባት እርሱ ነው፡፡ የመሬት አባት፣ የዝናብ አባት፣ የከብት አባት፣ የእህል አባት ሁሉም እርሱ ነው፡፡ የሁሉም ባላባቶች አባት እርሱ ነው፡፡ ከእህል ዘር በቆሎ አይበላም፡፡ የደርግ መንግስት አስሮ ካዋረደው በኋላ ዛሬ በአካባቢያችን ያሉት ችግሮች በሙሉ መጡብን፡፡ እህል ቢዘራ በረከት የለውም፤ ማር ጠፋ፣ ከብቶችም እንደ ድሮ ወተት አይሰጡንም፡፡ በሽታ በዛ፣ እርስ በእርስ መጨቃጨቅ እኛ አናውቅም ነበር፤ አሁን ግን በየአካባቢው እየሰማን ነው፡፡ ይኸ ሁሉ የሆነው እኛ (ቤንች) ቤተሽታቶን ስለተውነው ነው፡፡

•

## ቶስ 5

አንድ ሰው ቤንችቴት ሆኖ ሲመረጥ ከሚፈፀሙት ስርዓቶች አንዱ በንግስናው እለት የሚያገባት ድንግል የሆነች ልጃገረድን መምረጥ ነው። ይህቺ የቤንችቴት ሚስት (ንግስት) ሆኖ የምትመረጠው ልጃገረድ በባህላችን መሠረት ከሶስት ንዑስ ጉሳዎች፡- ከኩዌንኬስ፣ ከኤርስ ወይም ቶም (ጎርሽ) ነው። ከኩዌንኬስ ጎሳ አዲሷ ንግስት ተመርጣ ከሆነ የሚወለደው ልጅ "ታታ ኮይናንስ" ይባላል። ከሁለተኛው (ከኤርስ) ንግስቷ ተመርጣ ከሆነ የሚወለደው ልጅ "ታታ ጋሽናንስ" የሚባል ሲሆን ከቶም (ጎርሻ) ንኡስ ጎሳ ንግስቲቷ ተመርጣ ከሆነ የሚወለደው ልጅ "ታታ ጊሽቱናንስ" ይባላላ። በተጨማሪም ይህ የእናት የዘር ሃረግን ይዞ የሚሰጠው ስም በንግስና ዘመንም ቀጣይ ነው።

## ቶስ 6

ቤንችቴት የሚኖሩት ለብቻቸው ነው። ከህዝብ ጋር አይናገኙም። ይሁን እንጂ በቤንችቴት (ቤኑሽታቶ) ልመና በቤንች ሀገር ላሞች ወተት ይሰጣሉ፤ የተዘራው እህልም ጥሩ ምርት ይሰጣል፤ በሽታም አይገባም። ይሁን እንጂ በእኛ ሀገር (ቤንችዶድ) በአሁኑ ዘመን የምናያቸው ልዩ ልዩ ችግሮች ርሃብ፣ በሽታ፣ ወዘተ. የተከሰቱት ይህ ልማድ በመቅረቱ ነው።

## ቶስ 7

… እኔ ቃልቻ የለብኝም፤ በግ እባለስሁ። የማልበላው ፍየልና ዶሮ ብቻ ነው። ከእህል ዘር የማልቀምሰው ወይም የማልበላው በቆሎ ብቻ ነው። ምክንያቱም ቤንችቴት/ቤኑሽታቶ በቆሎ አይበላም። ድሮ ነው አሉ የእኛ አያት በቆሎ እንዲበላ ሲቀርብለት "ይሄማ እንደ እኔ አስራ ሁለት ልብስ የለበሰስ ነው። እሱም እንደ እኔ ንጉስ ስለሆነ እኔም አልበላውም።" አሉ ይባላል። እኔም (ቤኑሽታቶ) ይህንን መሀላ አፍርሼ በቆሎ ብበላ በአፍና በአፍንጫዬ ደም ፈሶ እሞታለሁ።

## ቶስ 8

ቤንችቴት የቤንች ንጉስ ነው። ኮይስ (በስሩም) በርጊናንስ፣ አዙናንስ፣ ኮሞቲካስ፣ ዳኪራሽ፣ ሻሽንቴት፣ ጋሪናንስና ማተብናንስ የሚባሉ የቤንች ቲያት አሉት። ህዝቡም ቤንች ይባላል። ማንኛውም የብሄረሰቡ አባል ቤንችቴትን ያከብራል። ቤንችቴት፡- አይዋሽም

የሚናገሩትም እውነት ብቻ ነው። ለቤንችቴት ተገቢው ክብር ካልተሰጠ በሀገር (ቤንችዶድ) ችግር ይገባል።

## ቶስ 9

አንድ ጊዜ ነው አሉ፡- ቤንችቴት እንደሞቱ በቦታቸው የተተካው በህዝብ ግፊት ታክሎበት ከጭልንድ ቤተሰብ ነበር (ሆኖም ሊነግሱ አይገባም ነበር)። ድርጊቱ በባህላችን እና በእምነታችን ልማድ ተቀባይነት ስላልነበረው በሀገራችን ላይ ከፍተኛ ችግር ተከሰተ። የደንቃ (ማሽላ) ጎተራዎች ፈነዱ። ድርቅ በሀገር ገባ። የሚበላ ነገር ጠፋ። በዛፎች ላይ እንኳ ቅጠል ጠፋ። በአካባቢው ያሉ ወንዞች ደረቁ። በአጠቃላይ ህዝቡ በጣም ተቸገረ። በዚህን ጊዜ ህዝቡ መልሶ "ምናልባት ይህ ሁሉ ችግር በአካባቢያችን ላይ የደረሰው በአዲሱ ቤንችቴት ምክንያት ሊሆን ይችላል" አለ። በዚህ ጉዳይ ላይ ሽማግሌዎች ተማክረው መልስ እንዲሰጡ ዣገቴት ጋ (ሼቤንች ወረዳ) ተላኩ። ዣገቴትም ከመጀመያው ጀምሮ የተደረገውን ሁሉ ካዳመጡ በኋላ "የአዲሱ ቤንችቴት አመራረጥ ስህተት ነው። ስለዚህ "በአዲሱ ቤንችቴት ቦታ መቀመጥ ያለበት ከአርንድ ነው" ባሉት መሠረት በመጀመሪያ ከጭልንድ ተመርጦ የነበረው ቀረና ሌላ ቤንችቴት ከአርንድ ተመረጡ። ተብሎ ሲነገር ሰምቻለሁ። እኛም እስከዛሬ የምንከተለው ይህንኑ ነው።

## ቶስ 10

ከቤንችዶድ (ሀገረ-ቤንች) አካባቢዎች ሁሉ የኪቡ ምድር ለምለምና ድርቅ የማይመታው ነው ይባላል። የዚህ ምክንያቱንም አያቶቻችን ሲነግሩን እንዲህ በማለት ነው። አንድ ጊዜ በቤንችቴትና በሻሽንቴት ቤተሰብ መሀከል አለመግባባት ተፈጥሮ ነበር። በዚህ የተነሳም ቤንችቴት የቤንች ንጉስ ስለሆነ ልዩ ልዩ ተጽእኖዎች አደረጉ። ለምሳሌ ያህል የሻሽንቴት ቤተሰቦች የዘሩትን ገብስ በማሳ ላይ እንዳለ አስጨፈጨፉ። በዚህና በሌሎችም ምክንያቶች የተነሳ ሁለት የሻሽንቴት ልጆች አጋጣሚ ጠብቀው ቤንችቴትን በጦር ይወጉና ሞቷል ብለው ከአካባቢው ተሰወሩ። ይሁን እንጂ ቤንችቴት በደረሰባቸው ጉዳት የሚፈሰውን ደም በቀንድ ዋንጫ እያጠራቀሙ ሲጓዙ፣ ሲጓዙ ኪቡ ምድር ሲደርሱ ዋንጫው ሞላና ደሙ መሬት ላይ ፈሰሰ። በዚህ የተነሳም ያ አካባቢ ተመርቆ በልምላሜ ዘውትር ይኖራል ይባላል።

## ቶስ 11

መንከር ማለት የቤንችቴት እና ሌሎች ባላባቶች (ቲያት) ሲሞቱ የሚቀበሩበት ቦታ ወይም መካነ መቃብር ነው፡፡ በትላልቅ ዛፎች የተከበበ ሲሆን ማንም ሰው እውስጡ ገብቶ እንጨት ሲቆርጥ ወይንም ሲያርስ አይችልም፡፡ ይህም ክፉ ነገር ይደርስበታል ተብሎ ስለሚታመንበት ነው፡፡

## ቶስ 12

ቤንች ማለት የህዝቡ ወይም የብሄረሰቡ መጠሪያ ስም ነው፡፡ ይህንኑ ህዝብ የሚመሩት ባህላ መሪ ቤንችቴት (ቤኑሽታቶ) ይባላሉ፡፡ በቤንችቴት ስርም፣ በርጊናንስ፣ ኪቡ፣ ጋሪናንስ፣ ኮምቲካስ፣ ዳኪራሽ እና ሻሽንቴት የሚባሉ ቤንችቲያት ነበሩ፡፡ እነዚህ ስድስቱን አስተባብሮ የሚመራው ቤንችቴት ነው፡፡

## ቶስ 13

የቤንች ብሄረሰብ ጥንት ሲኖር የነበረው በዛሬው የጋሞጎፋ ዞን ሩልዶልፍ ሀይቅ አካባቢ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በአንድ ወቅት በዚህ አካባቢ በተነሳው ከፍተኛ ወባ መሰል ወረርሽኝ በሽታ ብዙ ሰው ስላለቀ ይህንን አካባቢ ለቀው ባደረጉት እንቅስቃሴ ዛሬ የሚገኙበት ቤንች ማጅ ዞን በተለይም ሼቤንች ወረዳ ደርሰው ሰፈሩ ይባላል፡፡

## ቶስ 14

በጥንት ዘመን የቤንች ብሄረሰብ ይኖር የነበረው ከጎንደር ደቡብና ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ነበር ይባላል፡፡ በዚህ አካባቢ የብሄረሰቡ አባላት ሲኖሩበት የነበረው ክልል "ቤኑሻ" ተብሎ ይጠራ እንደነበርና ዛሬ "ቤንች" የሚለው የብሄረሰቡ መጠሪያ ስም ከዚሁ ቤኑሻ ከሚባለው ቀደምት የብሄረሰቡ መኖሪያ አካባቢ የተገኘ ነው ይባላል፡፡ ሆኖም በተለይዩ ዘመናት በተደረጉ ጦርነቶችና ልዩ ልዩ የተፈጥሮ አዳጋዎች የተነሳ ይህንን አካባቢ ለቀው በመሸሽ መጀመሪያ ጋሞጎፋ ውስጥ ሩዶልፍ ሀይቅ አካባቢ ይኖሩ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ አካባቢም በተነሳው ወባ መሰል ወረርሽኝ ብዙ ሰው ስለሞተ ይህንን አካባቢ ለቀው ዛሬ እሚኖሩበት አካባቢ በመምጣት ሼቤንች ወረዳ መኖር ጀመሩ ይባላል፡፡

## ቶስ 15

ጥንት የእኛ አያቶች መኖሪያቸው እዚህ አልነበረም። እላይ ሼቤንች እሚባል ቦታ ነው። ወደዚህ አካባቢ የመጡት ቤንችቴት በሚባል መሪ እየተመሩ ነበር። የዛኔ ይኽ ዛሬ (ደቡብ ቤንች) የምንኖርበት ቦታ ሁሉ መከቲን ተብሎ ነበር የሚጠራው። የእኛ አያቶች ጥንት ወደ እዚህ አካባቢ ሲመጡ ይህ አካባቢ ጫካ ነበር። በጊዜው የነበሩት ባላባት ሶርቴት ይባላሉ። አካባቢው በጣም ሳር የበዛበት ከመሆኑ የተነሳ ጅግራ፣ ቆቅ፣ የመሳሰሉትን በቀላሉ ይዘን እንበላ ነበር።

## ቶስ 16

ድሮ ጊዜ ቤንች እንዳዛሬው በብር አይገለገልም ነበር። ልዩ ልዩ ነገሮችን ለመግዛት የምንጠቀመው በጨሌ (ዳግናም) ነበር። ጨሌውን እንደቀበቶ ሰፍተን እንይዝና የምንፈልገውን ነገር ስናገኝ ከዛ ላይ ፈተን በመስጠት እንገዛለን። ለምሳሌ ጠላ ለመጠጣት ብንፈልግ የሁለት፣ የአምስት ጨሌ ... እያልን ነበር የምንናገረው። በድሮ ጊዜ በእኛ አካባቢ ብዙ ብር ያለው የለም። እኔ በህይወቴ የቆጠርኩት ከፍተኛ ብር አንድ ሺህ ብቻ ነው። የአሁኑ ዘመን ልጆች (በትንሿ ኪስ-ህፃናት) ግን ብዙ ገንዘብ ሲቆጥሩ ከመንደራችን ሳይቀር እያየን ነው።

## ቶስ 17

ጌሲቴት እንደ አያቶቻቸው የመከቲን ባላባት ነበሩ። ይሁን እንጂ ፈረስ መጋብ እጅግ የሚውዱ መሆናቸው፣ የመልካቸው ጥቁረት (ሹሩንስ) እና የፈረሳቸው መልክ ንጣት፣ በአካባቢው ከሚኖሩ ልዩ ልዩ የቤንች ጎሳዎች ጋር የነበራቸው ጥብቅ ቀረቤታ፣ ድንበርተኛ ከነበሩት ልዩ ልዩ ብሄረሰቦች ጋር የመሰረቱት መልካም ግንኙነት፣ ተዋጊነታቸው ብሎም በመከቲን አካባቢ የመጀመሪያው ካህ (ሻምቴትእንዶ) ዚብ ወንዝ አጠገብ በርሳቸው በመውረዱ ይለያሉ። ድንገትም ሳያስቡት ጦር መሳሪያ ይዘው ባደፈጡ ሁለት ሰዎች ተገደሉ።

## ቶስ 18

በዚህ በእኛ በቤንች ሀገር ከቤንች ንጉስ በስተቀር ሌላ ንጉስ አናውቅም ነበር። ይሁን እንጂ ልጅ ኢያሱ ወደዚህ አካባቢ ለመጀመሪያ ጊዜ የመጡ ቤንች ያልሆኑ የመጀመሪያው ንጉስ ናቸው። የቤንች ምድርን መሀል መሀሉን (እንብርቱን) ሰንጥቀው በመግባት

ለመጀመሪያ ጊዜ የረገጡ እርሳቸው ናቸው፡፡ ከእርሳቸው ቀጥሎ ሌሎች ሰዎች ከሌላ አካባቢ ወደዚህ በብዛት መጥተዋል፡፡

### ቶስ 19

ልጅ ኢያሱ ወደ ቤንች ሀገር የመጡት (በዛሬው የደቡብ ቤንች ወረዳ) በፓሻ በኩል ከታች በብርሃን (የቦታ ስም) አድርገው ነው፡፡ ወደ አካባቢው ለመግባት በሞከሩ ጊዜ ከፍተኛ ጦርነት ገጠማቸው፡፡ በመጨረሻም እድል ቀንቷቸው የፓሻ አካባቢን ተቆጣጠሩት፡፡ አካባቢውን እየተዘዋወሩ ሲጎበኙ የመሬቱ አቀማመጥ ማረካቸውና በአካባቢያቸው የነበሩትን ሰዎች "የዚህ አካባቢ ስም ምን ይባላል?" ብለው ጠየቁ፡፡ ሰዎቹም "ፓሻ ነው፡፡" ብለው ሲመልስ ልጅ ኢያሱ "እኔስ አይን አምባ ብየዋለሁ" አሉ ይባላል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ "ፓሻ" መባል ቀረና "አይናንባ!" ተባለ፡፡

### ቶስ 20

ልጅ ኢያሱ ከፓሻ (አይናንባ) ወደ መከቲን (ደብረወርቅ አካባቢ) እንቅስቃሴ በማድረግ መጠነኛ ውጊያ አድርገው አካባቢውን ተቆጣጠሩት፡፡ የዚህን ጊዜ በታላቅ ወንድማቸው ጌሲቴት ቦታ የተተኩት ወሰ አካባቢውን ለቀው ወደ ሼቤንች ሄዱ፡፡ ሆኖም ልጅ ኢያሱ ከአካባቢው ሽማግሌዎችን መርጠው ተከታታይ ድርድር በማድረግ ወስ ሻሸንቴትን ወደ መከቲን አስመጧቸው፡፡ ወሰ ወደ አካባቢው እንደተመለሱም ልጅ ኢያሱ የአካባቢውን ህዝብ ሰብስበው ወሰን ነጭ ፈረስ ላይ አስቀምጠው ወደ ህዝቡ እየተመለከቱ "ከዛሬ ጀምሮ ንጉሳችሁ ይኸ ነው ስሙንም ፊታውራሪ ወስኑ ብያዋለሁ!" ብለው በአካባቢው የሰፈረውን ጦራቸውን ነቅለው በሰላም ወጡ፡፡ ብሎ አባቴ የነገረኝ ቶስ ነው፡፡

### ቶስ 21

ልጅ ኢያሱ በዚህ በመከቲን (የዛሬው የደቡብ ቤንች ወረዳ) ቆይታቸው አብዛኛው ነዋሪ ሸፍቶ ጫካ ገብቶ ነበር አሉ፡፡ ስለዚህም ከህዝቡ ጋር ጫካ ገብተው የነበሩትን ባላባት ዋስ ሻሸንቴት (በኋላ ላይ ፊታውራሪ ወስኑ) በሀገር (የቤንች) ሽማግሌዎች አማካኝነት ታርቀው ዎስ ወደ አካባቢያቸው ከተመለሱ በኋላ ልጅ ኢያሱ ከነጦራቸው አካባቢውን ለቀው ወጡ፡፡ ይሁን እንጂ ልጅ ኢያሱ ሲዝ (የዛሬው ሼቤንች ወረዳ) ሲደርሱ ከፍተኛ ውጊያ ገጠማቸው፡፡ ኢያሱም ባደረጉት ከፍተኛ ውጊያ በሲዝ አካባቢ ነዋሪ በሆኑት የብሄረሰቡ

አባላት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደረሰባቸው። እስከ አርባ ሺ.ህ የሚደርስ ሰው ምርኮኛ ሆኖ በባርነት ወደ ሆጨጫ (አዲስ አበባ)፣ ጎሬና ሌሎች አካባቢዎች ተግዟል። በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ የእኔ አያት (የቄስ ተገኝ) ሲነግሩን ያሉት "የተማረከው ህዝብ ከመብዛቱ የተነሳ ለመቁጠር አስቸጋሪ ነበር። ስለዚህም አንድ ሺ.ህ ሰዎች እጃቸው በገመድ ተያይዞ ይታሰርና በኢያሱ ፊት ሲያልፉ "አንድ!" ተብሎ ይቆጠራል። እኔም 40 እስኪደርስ ድረስ መቁጠሬ ትዝ ይለኛል" በማለት ነበር።

## ቁስ 22

ልጅ ኢያሱ በደቡብ ቤንች ቆይታቸው ማጅ እየሄዱ ይመለሱ ነበር አሉ። አንድ ጊዜ ከማጅ በመመለስ ላይ ሳሉ (የካሹ ወንዝን ተሻግረው ጥቂት እንደተጓዙ) የኪርሹ ቁጥቋጦ እየጠለፈ ይጥላቸው ነበር አሉ። በዚህ ሁኔታ ተናደው ሳለ ዞር አሉና ባጠገባቸው የነበሩትን የቤንች ተወላጆች እንዲህ ብለው ጠየቋቸው አሉ "የዚህ ሀገር ገበሬ ይህንን ለም መሬት ለምን አያርሰውም? በሉ ከዛሬ ጀምሮ እናንተ ይህንን መሬት መንጥሩና እረሱት እኔ ደግሞ ከሌላ ቦታ የቡና፣ የሙዝ፣ የፓፓያ ዘር አመጣላችዋለሁ" አሉ ይባላል።

## ቁስ 23

"ኒያል ቶክ"ን (የጌሊት ትክል ድንጋይን) ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሉት፣ ከልጅ እያሱ ጋር ወደ እዚህ (ደቡብ ቤንች) አካባቢ መጥተው የነበሩት ደጃዝማች ገርቢ ናቸው። ይህንንም የነገረኝ ኮይባብ የሚባል በጊዜው የነበረና ድንጋዩን ከነበረበት አንስተው ከተከሉት ሰዎች መሀከል አንዱ ነው። የተተከለበት ምክንያትም ለምልክት (ማስታወሻነት) ተብሎ ነው።

## ቁስ 24

ጌሊት የሚባለው ቦታ በደቡብ ቤንች ወረዳ ውስጥ የሚገኝ አካባቢ ስም ሲሆን ይህንን ስሙን ያገኘው ጌሊቴት ከሚባሉ የአካባቢው ቤንችቲያት (ባላባት) ስም በመነሳት ነው ይባላል።

## ቁስ 25

ልጅ ኢያሱ ፓሻ (አይን አምባ) ቆይታ ካደረጉ በኋላ በታላቅ ወንድማቸው (ጌሊቴት) ሞት ምክንያት የሸፈቱትን ባላባት ወሰኑ ሻሸንቴት ለመክበብ ከአይናንባ ጦራቸውን

አንቀሳቀሱ። አሁንም ከፍተኛ ፍልሚያ ከአካባቢው ስላጋጠማቸው ለአምስት ቀናት ከተዋጉ በኋላ ዳቻባስ (ዳች -ሰፊ ባስ -ሜዳ) እተባለው ቦታ አረፉ። ኢያሱ በዚህ ዳቻባስ (የደብረወርቅ ከተማ ዙሪያ) በተባለው ስፍራ ሁለት ቀን ያህል ቆዩ ይባላል። በነዚህ ቀናት በአካባቢው ሲዋጉ የነበሩት ሰዎች አፈግፍገው ወደ ኪሉ-ካሻ ወንዞች ስለሄዱ ምንም አይነት የጥይት ድምፅ አልተሰማም ነበር። በዚህ የተነሳም ልጅ እያሱ "የዚህ ሀገር (አካባቢ) ስሙ ማን ይባላል?" ብለው ጠየቁ ይባላል። በአካባቢያቸው የነበሩት ሰዎችም "ዳቻባስ!" ይባላል ብለው ነገሯቸው። ከዛሬ ጀምሮ ግን "ማረፊያ ቤቴ!" ብየዋለሁ አሉ ይባላል። ምክንያቱም በዚህ አካባቢ ያሳለፋቸው ሁለት ቀናት ሰላም ስለነበሩ ነው ይባላል። ይሁን እንጂ ማረፊያ ቤቴ የሚለው ስያሜ በጊዜው ለነበሩት የአካባቢው ተወላጆች (ቤንች) አጠራሩ አስቸጋሪ ስለሆነባቸው "ማርቤት!" ብለው ይጠሩ ነበር ይባላል። ከዚህ ጋር በተያያዘም እስከ ዛሬ የዚህ አካባቢ (ደቡብ ቤንች) ተወላጆችን "የማር ቤት ሰው" እያሉ መጥራት ተለመደ ይባላል።

## ቶስ 26

የዛሬዋ አይናንባ የጥንት ስሟ ፓሻ ነው። ልጅ ኢያሱ በጊዜው ወደ ቤንች ሀገር ለመጀመሪያ ጊዜ ሲመጡ ከአካባቢው ነዋሪ ጋር ተዋግተው ፓሻን ይዘው ከነሰራዊታቸው እዛው አርፈው ነበር። ይሁን እንጂ እያሱ በአካባቢው የመሬት አቀማመጥ ውበት ስለተማረኩ ይህንን ቦታ አይናንባ (አይን አምባ) ብየዋለሁ አሉ ይባላል። በዚህም ፓሻ መሆኑ ቀርቶ አይን አምባ ተባለ ይባላል።

## ቶስ 27

የዛሬው ደቡብ ቤንች ወረዳ ዋና ከተማ ደብረወርቅ የተመሰረተችበት ቦታ ድሮ "ሶረን" ተብሎ ይጠራ ነበር። በአካባቢውም ዱባ በብዛት ይበቅል ስለነበር ማንም ሰው እየሄደ ቆርጦ ይወስዳል። ኋላ ላይ ግን በጣሊያን ወረራ ምክንያት ከአካባቢው (መከቲን) ወደ ጎላ (ጨና) አካባቢ ሄደው የነበሩት ባላባት ሻሽንቴት ይብራ ከጦርነቱ በኋላ ወደ አካባቢው ሲመለሱ በዚህ ሶረን በተባለው ቦታ ላይ የዛሬዋን የደብረወርቅ ከተማ በ1938/39 አካባቢ ቆረቆሩ። በሳምንት አንድ ቀን ሀሙስም የገበያ ቀን እንዲሆን ያደረጉ እርሳቸው ናቸው። ሆኖም ከጣሊያን ጦርነት በኋላ አማን የሚገኘውን አውሮፕላን ማረፊያ ለማሰራት ወደ አካባቢው የመጡት ፊታውራሪ ዓለማየሁ ፍላቴ ሻሽንቴት ጋ ውለው አድረው ስለነበር በአካባቢው ልምላሜና ሰላም ተደስተው "ይኸንን ከተማችሁን ደብረወርቅ ብየዋለሁ" ብለው

ለሻሸንቴት ይብራ ተናገሩ። ስለዚህም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሶረን መባሉ ቀረና ደብረወርቅ ተባለ ተብሎ ሲነገር በልጅነቴ ሰምቻለሁ።

### ቶስ 28

አየር ሜዳ (አማን አውሮፕላን ማረፊያ) ሲሰራ እኛ ከዚህ በየተራ እየሄድን የጉልበት ስራ ስንሰራ ነበር። መቆፈሪያ፣ ገጀራ የመሳሰሉትን መሳሪያዎች እና ቀለባችንን ሁሉ ከዚህ ተሸክመን ነበር የምንሄደው። ያንን ሰፊ ሜዳ ቆፍረን፣ ደልድለን አውሮፕላን እንዲያርፍ ያደረግነው እኛ ነን።

### ቶስ 29

በቤንች ምድር የጣሊያን ወራሪ ለአንድ ቀንም በሰላም አላደረም። በዚህ የተነሳም ለመበቀል ብሎ ባላባቱን ፊታውራሪ ወሰኑን በአሰቃቂ ሁኔታ ገደላቸው። እኛም (ቤንች) በድንጋይ ሳይቀር ተፋለምን፣ በሌላው የኢትዮጵያ ክልል ጫካ ገብተው የነበሩት አርበኞችም እኛ ዘንድ መጥተው በጠየቁን መሰረት መንገድ እየመራን ደቡብ ሱዳን ቦማ ከተማ ሄደን ከእንግሊዝ መንግስት የተሰጠውን ቤልጅግ ጠመንጃ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ጣሊያን ተሸንፎ እስኪወጣ ድረስ ተዋግተናል።

### ቶስ 30

ድሮ ድሮ አያቶቻችን ሲነግሩን ባልና ሚስት የግብረስጋ ግንኙነት በቀን አያደርጉም ነበር ይባላል። ምክንያቱም በቀን የግብረ ስጋ ግንኙነት ቢደረግና ምናልባት ተፀንሶ ልጅ ቢወለድ' አይኑ ቀይ (የተበላሸ) ይሆናል ተብሎ ስለሚታመን ነበር። ባልና ሚስት የግብረ ስጋ ግንኙነት ቀን ማድረግ የጀመሩት ልጅ እያሱ ወደ ቤንች ሀገር ከመጡ በኋላ ነው።

### ቶስ 31

ሱትባር ኬት (የደም መሬት) ተብሎ የሚጠራው ቦታ የሚገኘው በዛሬው የደቡብ ቤንች ወረዳ ውስጥ በሚገኘው የሚያሀ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ነው። ይህች ቦታ ይህንን መጠሪያዋን ያገኘችው የአካባቢው ባላባት የነበሩት ጌሲቴት ባደፈጡ ሰዎች በጥይት ተመተው ሲሞቱ ደማቸው (ሱት) የፈሰሰበት ቦታ በመሆኑ ነው።

## ቶስ 32

ካብቴት በሚባሉ አማልክቶች ታምነው የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ አሉ። በአንድ ዘመን እነዚህ ባልና ሚስቶች በሚኖሩበት አካባቢ እህል በአገሩ ጠፋና ችግር ሆነ። "ምን ይሻለናል?" ብለው ባልና ሚስቱ አሰቡ። በዚህን ጊዜ ባልየው፡-

"እንደው ሚስጢር የማታወጪ ከሆነ አንድ ነገር ብናደርግ ምናለ?" አላት።

"ምንድነው?" አለች ሚስቱ።

"አይ! ይህ የረሃብ ዘመን እስኪያልፍ የሚደማ ነገር አግኝተን ብንበላ ምናለበት?" አላት።

"የሚደማ ነገር?"

"አዎ!"

"የሚደማ ነገር ከተገኘማ ምን ችግር አለ?" አለችው።

"የሚደማ ነገር በልተን ነገ ሚስጢር ካወጣሽ ግን ስማችን ይጠፋል? ሆኖም የሚደማ ነገር አግኝተን ከበላን በኋላ ይህ ቀን አልፎ አንድ ቀን እንኳ ብንጣላ ምስጢር የማታወጪ ከሆንሽ እንማማልና ሂጄ ላምጣ! አላት!"

ሚስቱም ዛሬ በሚስጢር የሚያደርጉትን ይህ የረሃብ ዘመን ሲያልፍ ላታወጣ ማለች!

ሰውየው ከባለቤቱ ጋር ሚስጢር ላያወጡ ከተማማሉ በኋላ ባልየው "የሚደማ ነገር" ያለውን ጫካ ሄዶ አውሬ ገድሎ መጣ። ሆኖም ከጫካ አድኖ ያመጣውን አውሬ ከመብላታቸውም በፊት ሰውየው ሚስቱን እንዲህ ብሎ ጠየቃት።

"ይህ ዛሬ የምንሰራውን ሚስጢር ነገር ብታወጪ ምን ይድረስብኝ ነው ያልሽ?" አላት።

"እኔም ሆንኩ አንተ ዛሬ የምንሰራውን ሚስጢር ነገ ብናወጣ ካብቴት ለሁለት ይሰንጥቁን አለችው።"

ይህ ክፉ ቀን አልፎ ባልና ሚስቱ ደህና ኑሮ በመኖር ላይ ሳሉ አንድ ቀን ይጣላሉ። እነዚህን ባልና ሚስት ለማስታረቅም ሽማግሌዎች ተሰበሰቡ። በሽማግሌዎች ፊት ቆመውም እያሉ፡-

"አንተ ሰውዬ ከፈለግክ ጉድህን ነው የማወጣው" አለችው

"ምን ጉድ አለብኝ?" አላት ባልየው።

"እንዴት! አንተ እኮ በዛ ክፉ ቀን ከጫካ የማይበላ አውሬ አድነህ የበላህ ነህ!" ብላ በሰው ፊት አዋረደችው፡፡ ባልየውም፡-

"አይ! ዛሬ ያቀን አለፈልኝ ብለሽ ትናንትና በሚስጢር የሰራነውን ካወጣሽ አንቺና እኔ ስንማማል የጠራነው ካብቴት ይፍረድ!" እንዳለ ከሰማይ መብረቅ ወርዶ ሴትየዋን ገደላት ይባላል፡፡

## ቶስ 33

አንድ ባላባት ነበር አሉ፡፡ የመሞቻው ጊዜ ደርሶ ስለነበር ከመሞቱ በፊት እያቃሰተ ልጁን አስጠርቶ መናዘዝ ፈለገ፡፡ ተጠርቶ የመጣው ልጁም ወደ አባቱ ቀርቦ፡-

"ምነው አባቴ ደከመህ ወይ?" ብሎ ጠየቀው፡፡

"አዎ ልጄ ደከመኝ ከመሞቴ በፊት የምነግርህ ነገር ስለአለ ነው ያስጠራሁህ" አለው፡፡ ቀጠለና ልጄ "በህይወት ዘመንህ እመንገድ ዳር ጥንቅሽ እንዳትዘራ፣ የሰው ሚስት እንዳታባልግ የሰው ዲቃላም ወደ ቤትህ አምጥተህ እንዳታሳድግ" ብሎ አባቱ መከረውና ሞተ፡፡

ያ ልጅ ሲኖር ሲኖር ከእለታት አንድ ቀን የአባቱን ምክር ረሳና የሆነች ጋለሞታ ሴት አገባ፤ እመንገድ ዳርም ጥንቅሽ ዘራ፡፡ ይቺን ጋለሞታ አግብቶ እያለ (እርሷን ጥበቃ ከቦታ ወደ ቦታ ሲዟዟር) ያቺ መንገድ ዳር የዘራትን ጥንቅሽ እረኞች ሰብረው ሲበሏት አገኘ፡፡

ሰውየውም ተናዶ ነበርና ጥንቅሹን ሰብሮ ሲበላ ያገኘውን ልጅ ክፉኛ መታው፡፡ ወደ ቤቱም እንደደረሰ ሚስቱን "አንቺዬ ያ እመንገድ ዳር የዘራሁትን ጥንቅሽ እረኞች ሰብረው ሲበሉብኝ ደረስኩ፡፡ ተናድጀም ስለነበር አንዱን እረኛ መትቼ ገደልኩት" ብሎ ነገራት፡፡ እሷም መልሳ "እንዴ የሰው ሰው እንዴት ትመታለህ" አለችውና እሪ ብላ ጮኸች፡፡ [አይ! የመጀመሪያ ሚስቱ ብትሆን ኖሮ ሚስጢሩን ትደብቅለት ነበር] ወዲያውም እየሮጠች ሄደችና ሞተ ለተባለው ልጅ አባት ባሏ ልጃቸውን እንደገደለ ነገረች፡፡ የልጁ አባትም ገዳይ ነው የተባለውን ሊያሳስሩትና ለመበቀል ሴትየዋን ተከትለው ገዳይ ነው እተባው ሰውዬ ቤት ደረሱ፡፡ የዚህን ጊዜ ሚስቱ በችኮላዋ የተነሳ ስህተት ውስጥ መግባትዋን የተረዳው ባል

"ጌታየ! አይናደዱ፡፡ ልጅዎ በህይወት ቢገኝ ምን ያደርጉልኛል? ብሎ በርጋታ ጠየቃቸው"

"ሙሉ ልብስ!" አሉና ወዲያው መለሱለት፡፡

እንግዲያውስ "ሞተ የተባለ ልጅዎ አልሞተም አለ፡፡" ነገር ግን እኔ አባቴ ከመሞቱ በፊት የሰው ሚስት (ጋለሞታ) አታግባ ያለኝን ረስቼ ይቺን ሴትየው አገባሁ፡፡ ያባቴ ማስጠንቀቂያ ወይም ምክር መድረስ አለመድረሱን ለማረጋገጥ ብዬ ለዚህች ሚስቴ "ሰው ገደልኩ" ብዬ ነገርኳት፡፡ እሷም እኔን ከማፅናናት ይልቅ የጎዳችኝ መስሏት ቸኩላ ሄዳ "ያልሞተ ልጅዎ ሞተ ብላ ነገረችዎት፡፡" ብሎ ተናገረና "ያባቴን ምክር አለመስማቴ ለዚህ አበቃኝ" አለ ይባላል፡፡

## ቶስ 34

አንድ ሰው ነበር፤ አንድ ልጅም ብቻ ነበረው፡፡ አርጅቶ ሊሞት ሲል ለልጁ የሚከተለውን ነዛዜ አደረገ፡፡ ልጄ መንገድ ዳር ቤት አትስራ፣ ትልቅ እንጨት ቤትህ ደጃፍ አጠገብ አትትከል፣ የሰው ደካማ ልጅም አታሳድግ፣ የሰው ሚስት የሆነች አፋተህ አታግባ ብሎ መከረው፡፡

ሆኖም ልጁ አባትየው እንደሞተ ኑዛዜውን በመናቅ እመንገድ ዳር ካለው ማሳ ባቄላ ዘራ፣ እንጨትም (ዛፍ) እቤቱ ደጃፍ አጠገብ ተከለ፣ የሰው ደካማ ልጅም ወስዶ እቤቱ ማሳደግ ጀመረ፡፡ እመንገድ ዳር የተከለው ባቄላም ሲያፈራ አልፎ ሂያጅ ሁሉ እየነቀለ ይበላ ጀመረ፡፡ በዚህ ሁኔታም ልጁ ስለተናደደ "እንዲህ ባቄላዬን እየነቀለ ሚበላውን ሰው ጠብቄ መግደል አለብኝ" ብሎ በስውር ይከታተል ጀመረ፡፡

በመጠበቅ ላይ እያለም በመንገድ ከሚያልፉ ሰዎች መሀከል አንዱ ወደ ማሳው ገብቶ የባቄላ እሸቱን ለመብላት በመንቀል ላይ እያለ አገኘና ተኩሶ ገደለው፡፡ ወደ ቤቱም እንደባ ለሚስቱ "ከማሳዬ ላይ ባቄላ እየነቀለ ሲበላ የነበረ ሰው አገኘሁና ተኩሼ ገደልኩት" ብሎ ነገራት፡፡

ሆኖም አንድ ቀን ይህ ሰውዬ ከባለቤቱ ጋር ተጣላና ክፉኛ ደበደባት፡፡ በዚህ የባለቤቷ ድርጊት የተከፋችው ሚስቱ "ቆይ ጉድህን አወጣዋለሁ!" በማለት እማሳው ውስጥ ሰው ገድሎ መቀበሩን ለአካባቢው ባላባት ተናግራ ሚስጢሩን አወጣችበት፡፡ በዚህም የተነሳ ሰውየው ተያዘና ታስሮ ለፍርድ ቀረበ፡፡

"አንተ ይህን ነገር አድርገሀል?" ብሎ ባላባቱ ጠየቀው፡፡

"አዎን! ፈርቼ ዋሸሁ እንጂ አድርጌያለሁ!" ብሎ መለሰ፡፡ በዚህን ጊዜም ህዝቡ "እኛ ከዚህ በፊት ስንት ቀን ተሰብስበን ገዳዩን ለማግኘት አፈርሳታ ውለን ነበር፡፡ እርሱንም

በማሳው ሰው ተገድሎ መቀበሩን ስንጠይቀው "አላውቅም" ብሎ በመሀላ አረጋግጧል፡፡ አሁን ደግሞ "ገዳዩ እኔ ነኝ!" ካለ መሰቀል አለበት ብሎ ወሰነ፡፡

ሰውየውንም በአካባቢው ለመስቀል በተፈለገ ጊዜ እንጨት ጠፋ፡፡ የዚህን ጊዜ ለመሰቀያው የሚሆን ዛፍ ሲፈለግ እርሱ በደጁ የተከለው እንጨት ተስማሚ ሆኖ ተገኘ፡፡ ሆኖም እንጨቱ በጣም ረዥም ስለነበር ወጥቶ የመስቀያ ገመዱን የሚያንጠለጥል ሰው ታጣ፡፡ የዚህን ጊዜ እርሱ ያሳደገውና ከልጅነቱ ጀምሮ ያቺ ዛፍ ላይ እየወጣ ያደገውና ያሳደገው (ዲቃላ) ልጁ "እኔ እችላለሁ" አለና ወጥቶ የመስቀያ ገመዱን አስሮ ወረደ፡፡ ይህንን ሁሉ የተመለከተው ሟች ለተሰበሰበው ህዝብ እንዲህ አለ "የእኔ ነገር መቼም እንዴ ያበቃለት ነውና በእናንተ እንዳይደርስ አንድ ነገር ልናገር አድምጡኝ" አለ፡፡ የተሰበሰበው ህዝብም ጫጫታ ፀጥ አለ፡፡

ወገኖቼ እኔ እንዲህ የተፃረድኩት የአባቴን ኑዛዜና ምክር አልቀበልም ብዬ ነው፡፡ አባቴ ሲሞት ሲል ጠርቶ "ፊት ሴት አታግባ፣ የሰው ዲቃላ (ደካማ) ልጅ አታሳድግ፣ እቤትህ ደጃፍ ትልቅ ዛፍ አትትከል፣ እመንገድ ዳር ያለ ማሳህ ላይ እህል አትዝራ!" ብሎ ነበር፡፡ እኔ እነዚህን ሁሉ ያባቴን ምክሮች ችላ ብዬ "ፊት አገባሁ፣ ዲቃላ ልጅም አሳደግሁ፣ ትልቅ ዛፍም እደጄ ተከልኩ፣ እመንገድም ዳር ያለ ማሳየ ላይም ባቄላ ዘራሁና ለዚህ በቃሁ! ወገኖቼ እኔ ዛሬ ያበቃልኛል እናንተ ግን የአባቶችን ምክር ችላ እንዳትሉና እንደ እኔ እንዳትሆኑ ብሎ መክሮ ተሰቅሎ ሞተ ይባላል፡፡

## ቶስ 35

ድሮ ነው አሉ፡፡ አንድ በጎረቤቱ መበልፀግ እየተቆጨ የሚኖር ሰው ነበር አሉ፡፡ እንዲህ እርር እያለ መኖር ሰለቸውና ወደ ባለፀጋ ጎረቤቱ ሄዶ እንዲህ ብሎ ጠየቀው፡፡

"አንተ ሰው በየጊዜው ሀብትህ እየጨመረ፤ ኑሮህም እያማረ፤ በሰው መውደድህም እየበዛ ሲሄድ አያለሁ፡፡ እባክህ የዚህን ምክንያት አስረዳኝ?" ብሎ ጠየቀው፡፡

ባለፀጋውም "ወንድሜ! ይህማ የሚያሳስብ አይደለም፡፡ የእኔ ጥረትና የሚስቴ እጅ ውጤት ነው፡፡" ብሎ መለሰለት፡፡

ይህንን የባለፀጋ መልስ የሰማው ሰውዬ ወደ ቤቱ ሄደና የሚስቱን ሁለት እጆች ቆርጦ በስልቻው ውስጥ ደበቀው፡፡ ሆኖም ከዛሬ ነገ እከብራለሁ ብሎ ቢጠብቅ ቢጠብቅ ምንም ነገር አጣ፡፡ ይባስ ብሎ እስልቻው ውስጥ የደበቀው የሚስቱ እጅ ተልቶ መሽተት

ጀመረ፡፡ በዚህ የተነሳም ተናደደና ይህንን ሀሳብ የነገረውን ባለፀጋ ሰውዬ ፈልጎ አገኘውና ሊበቀለው ፈልጎ እንዲህ አለው፡፡

"አንተ ሰው ሀብትህ በዛ፣ የሰው መውደድም አገኘህ" ብዬ ይህ ለምን እንደሆነ ብጠይህ

"የእኔ ጥረትና የሚስቴ እጅ ነው እንዲህ ያደረገኝ አልክ፡፡ እኔም ይህን ሰምቼ ቤቴ ሄጄኩና የሚስቴን ሁለት እጆች ቆረጥኳቸው ነገር ግን ሀብት አላገኘሁም፣ ሰውም አልወደደኝም አታለኸኛል" አለው፡፡

ባለፀጋውም "አይ አንተ ሰው እኔኮ ያልኩት ሚስትህም አንተም እኩል ተረዳድታችሁ ከስራችሁ ታድጋላችሁ፣ ትበለጽጋላችሁ ነው፡፡ መቼ እጇን ቁረጥ አልኩህ?" ብሎ መለሰለት፡፡

በባለፀጋው መልስ የተናደደው ደሀ ሰውዬ ሊበቀለው በመዘጋጀት ላይ መሆኑን ባለፀጋው ስለተረዳ መልሶ "የቸገረው እርጊት ያገባል" ብሎት ከአጠገቡ ተሰወረ ይባላል፡፡

## ቶስ 36

ባል አግብታ የሄደች ልጅ ከባሏ ጋር ተጣልታ ወደ ቤተሰቦቿ ቤት ጉዞ ጀምራለች፡፡ እናቷ ደግሞ ከልጅቷ አባት ጋር ተጣልታ ስለነበር ቤቱን ለቃ ወደ ልጅቷ ቤት (እማቿ ቤት) በመጓዝ ላይ ሳለች ከባሏ ጋር ተጣልታ ወደ እርሷ ዘንድ እየመጣች ካለችው ልጇ ጋር መንገድ ላይ ይገናኛሉ፡፡ እንደተገናኙም፡-

እናት፡-"ልጄ ወዴት እየሄድሽ ነው?"

ልጅ፡- "ባሌ አባሮኝ ነው፡፡ አንቺስ እማዬ ወዴት እየሄድሽ ነው?"

እናት፡-"እኔም ያንቺ አባት አባሮኝ ነው፡፡" ብላ መልስ ከሰጠቻት በኋላ በይ ልጄ የሁለታችንም ችግር ተመሳሳይ ነው፡፡ አሁን አንቺን ለማስታረቅ የመጣሁ መስዬ ዛሬን አንቺ ቤት እንደርና ነገ ጠዋት ደግሞ ወደ እኛ ቤት ተመልሰን ከአባትሽ ጋር እንታረቅ፡፡ "አየሽ ልጄ! ሁለታችንም ጠፍተንማ እንዴት ተደርጎ ይኖራል?" ብላ አንድ እናት ልጇን መከረቻት አሉ፡፡ በዚህም የተጣሉበት ነገር በርዶ ቀረ ይባላል፡፡

## ቶስ 37

በሌብነት የሚተዳደሩ ሁለት ባልና ሚስቶች ነበሩ፡፡ አንድ ቀን ማታ ባልና ሚስቱ አንድ ላይ ሆነው ሄዱና ቆፍረው ሊሰርቁ አንድ ሰውዬ ቤት ገቡ፡፡ የቤቱ ባለቤቶች ተኝተው

ነበርና ሌቦቹ ንብረታቸውን ሙልጭ አድርገው ወደ ውጭ አወጡ። የሌባው ሚስት ምናልባት እቤት ውስጥ የቀረ እቃ ካለ ብላ ለማየት ተመልሳ ገባች። የሚስቱን ወደ ቤት ውስጥ ትመልሶ መግባት ያላስተዋለው ባል መጀመሪያ ወደ ሰዎቹ ቤት የገቡበትን ጉድጓድ በትልቅ ድንጋይ ዘጋውና የቻለውን ያህል እቃ ተሸክሞ ወደ ቤቱ ሄደ።

እውስጥ የቀረችው የሌባው ሚስት እቤት ውስጥ ምንም የቀረ ነገር አለመኖሩን ካረጋገጠች በኋላ ውጭ ለመውጣት ብላ እጉድጓዱ ጋ ብትሄድ በትልቅ ድንጋይ አፉ ተዘግቷል። የምታደርገው ነገር ጠፋት በሩን ከፍታ እንዳትወጣ "ምናልባት ባልና ሚስቱ በሩ ሲከፈት ይሰሙና ከእንቅልፋቸው ይነቃሉ" በላ የምታደርገው ነገር ጠፍቷት ስትጨነቅ አንድ ሀሳብ መጣላት። ወዲያው ወደ ባልና ሚስት ጋ ሄዳ ስታዳምጥ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወስዷቸዋል። ቀስ ብላ ባልና ሚስቱ መሀከል ጉብታ ተኛች።

ትንሽ ከተኛች በኋላ ሙቀት ሲሰማት ሴትየዋን ወደ ጎን ገፋ አደረገችና ወደ ሰውየው (የቤቱ ባለቤት) ተጠጋች። ቀጥሎም በእንቅልፍ ውስጥ የነበረውን ሰውዬ (የቤቱ ባለቤት) ነካ ነካ አድርጋ ቀሰቀሰችውና ሲነቃ፡-

"ሆዴን አሞኛል ውጭ አውጣኝ!" አለችው። ሰውየውም ከእንቅልፉ ነቃ። እስኪነሳም ወደ ምድጃው ጋ ሄደችና እሳት የተዳፈነበትን እንጨት (ጢፎ) አውጥታ ያዘችና የቤቱን በር ከፍታ ወጣች። ሰውየውም ወዲያው ተከተላት። እርሷም ከቤቱ ትንሽ እልፍ እንዳለች የምትቀመጥ መስላ እሳት የያዘውን እንጨት ተከለች። ወደ ሰውየው ስትመለከትም እርሱም ከእርሷ ራቅ ብሎ ለመፅዳዳት ተቀምጦ አየችው። የዚህን ጊዜ ፈጠን አለችና ቅድም ወደ ቤቱ ውስጥ የገባችበት ጉድጓድ ጋ ሄደች። ባለቤቷ የለም። ወዲያው በጉድጓዱ አጠገብ የተቀመጠውን እቃ አንስታ የቤቱ ባለቤት ሳይመጣባት ወደ ቤቷ ሩጫዋን ጀመረች።

ያ የቤቱ ባለቤት ጠብቆ፣ ጠብቆ ቢሰለቸው ጊዜ "ይቺ ስትዬው አለወትሮዎ ዛሬ ምን ሆና ነው ውጭ ወጥታ የቆየችው? የማትገባው ምን ነክቷት ነው?" አለና "አንቺ! አንቺ! ..." እያለ መጣራት ጀመረ። የዚህን ጊዜ እቤት ውስጥ ያለችው ሴትየዋ "አቤት! ..." አለች "ምን ሆነሽ ነው ውጭ ወጥተሽ የማትገቢው?" አላት ሚስቱም "እንዴ እኔ መቼ ወጣሁና ነው? ተኝቼ የለ እንዴ? አለችው። ቀጥሎም

"እንዴት ነገሩ? እኔ ቤት ተኝቻለሁ ለመሆኑ አንተ ውጭ ምን እያደረግክ ነው?" አለችው። ባልየውም "ምነው አንቺ አይደለሽም እንዴት "ሆዴን አመመኝ" ብለሽ እሳት የተዳፈነበትን እንጨት ይዘሽ ወደ ውጭ የወጣሽው?" አላት። ወዲያውም እሱም ከውጭ

ወደ ቤት ውስጥ፤ እሷም ከተኛችበት ተነስታ መብራት አብርተው ቤታቸውን ሲያዩ ምንም እቃ የለም።

ያቺ ሌባዋ ሴትዮ በጨለማው የተሸከመችውን እቃ ይዛ እቤትዋ ትደርሳለች። እንደገባችም ባልየው "መጣሽ እንዴ?" ብሎ ይጠይቃታል። እሷም "ምነው አንተ በህይወቴ ላይ ፈርደህ መጣህ?" ብላ ጠየቀችው። ባልየውም ደንገጥ አለና እንደቀልድ አድርጎ "አይ! ምን ያህል ጎበዝ እንደሆንሽ ልፈትንሽ ብዬ ነው?" አላት።

ከዚያም እነዚህ ሌባ ባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ ሲኖሩ አንድ ቀን ለመስረቅ ብለው ሲሄዱ የተሰቀለ ቀፎ አገኙ። ወዲያው ወደቤታቸው ተመለሱና የሚሰርቁበትን እቃና የቀፎ ማውረጃ ገመድ ይዘው ወደ ቀፎው ተመለሱ።

ሰውዬው ወዲያው ገመዱን ወደ ዛፍ ላይ ወረወረና ወጥቶ ማሩን በያዘው እቃ ወደ ታች ይልከው ጀመር። እንዲህ አድርጎ የሚልከውን ማር ሚስቱ ከስር ሆና እየተቀበለችው አጠራቀመች። መጨረሻ ላይ ማሩ ማለቁን ነግሯት ለመውረድ ሲዘጋጅ ሚስቱ የቀፎ ማውረጃ ገመዱን ከእጁ ላይ መንጥቃ ወሰደችና ማሯን ይዛ ወደ ቤቷ ሄደች። ባልየው በምን ይውረድ? (እሷ ብድሯን ለመመለስ ነው) እቀፎው ዛፍ ላይ የቀረው ሰውዩ ቢጨንቀው ጊዜ "ኧረ እናንተ ሰዎች!" ብሎ እየተጣራ መጮህ ጀመረ። የዚህን ጊዜ የቤቱ ባለቤት ሰማና ቀፎ ወደ ተሰቀለበት ዛፍ ሄደ።

ቀፎ ጋ ደርሶ ወደ ላይ ቢመለከት ቀፎው የተሰቀለበት ዛፍ ላይ የወጣ ሰው አየ። ቀጥሎም

"አንተ ሰው ምን እያደረግክ ነው?" አለው።

"አይ ጌታዬ! የሆነ ሰው ቀፎዋን ሲሰርቅ አይቼ ልይዘው ብዬ ስወጣ ቀድሞኝ ወረደና የቀፎ መውጫ ገመዱን ነጠቀኝ።" ባለው ጊዜ የቀፎው ባለቤት ቶሎ ወደ ቤት ሄደና ልጁን ጠርቶ፤ የቀፎ ማውረጃ ገመዱን አስይዞ እዛፍ ላይ እንዲወጣ አዘዘው።

ልጁም ገመዱን ይዞ እዛፍ ላይ ወጣና ሰውየው (ሌባው) አጠገቡ ሊደርስ ሲል ያ ሌባ ቀድሞ ከልጁ አንገት ላይ የተጠመጠመውን ገመድ ወሰደና ወደ ታች ሲገፋው ልጁ የተቀመጠበት ቅርንጫፍ አንሸራተተውና ወደቀ። የዚህን ጊዜ ከታች ሆኖ እቀፎው ላይ የወጣውን ሰውዬ ጦሩን እየሰበቀ ሲጠባበቅ የነበረው ባለቀፎ ሌባው መስሎት የራሱን ልጅ በጦሩ ወጋው። በጦሩ ተወግቶ የነበረውን ሰው ለማየት ጠጋ ቢል የራሱ ልጅ መሆኑን አየና ደነገጠ። "ወይኔ ልጄ!" እያለ ማልቀስ ሲጀምር እላይ ተንጠልጥሎ የነበረው የማር ሌባ በገመዱ ተንጠልጥሎ ወረደና ሮጦ አመለጠ። ቤቱም እንደደረሰ ሚስቱን "ምነው? እዛፍ ላይ

እያለሁ መውረጃ ገመዱን ይዘሽብኝ ሄድሽ? በምን ይወርዳል ብለሽ ነው" አላትና ጠየቃት። ሚስቱም "አይ ባሌ ምን ያህል ጎበዝና ደፋር መሆንህን ለማየት ብዬ ነው አንተም እኮ አብረን ለመስረቅ እሰው ቤት ጉድጓድ ቆፍረን በገባን ጊዜ ራስህን ካወጣህ በኋላ በእኔ ላይ ጉድጓዱን ደፍነህ መሄድህን ረሳኸው ወይ" አለችው ይባላል።

## ቶስ 38

በድሮ ጊዜ አንድ ሰው ነበር። አንድ ልጅ ብቻም ነበረው። ልጁ ለአካለ መጠን ሳይደርስለት ክፉኛ ታመመና ሊሞት ማጣጠር ጀመረ። የዚህን ጊዜ ጎረቤቱ ያለውን ሰውዬ ጠራና "በል እኔ መሞቻዬ ተቃርቧል ይህ ልጄ ደግሞ ገና ራሱን አልቻለም። ሀብቴን ሁሉ ውረስና ልጄን እንደ አባት ሁነህ አሳድገው" ብሎ ሞተ።

በተሰጠው ኑዛዜ መሰረትም ሰውየው ያንን ልጅ እየተንከባከበ አሳደገው። ሆኖም ልጁ ለአካለ መጠን በደረሰ ጊዜ አሳዳጊውን ሰውዬ እንዲህ አለው።

"አባቴ የሰጠህን ሀብት ተጠቅመህ አሳድገኸኛል። ይህ እውነት ነው። አሁን እኔ ትልቅ ሰው ሆኛለሁ፤ የራሴ ቤትም እንዲኖረኝ ስለፈለግኩ ያንን ትልቁን ቤትህን አፍርስልኝና በቦታው ላይ የራሴን ቤት እሰራለሁ።" አለው።

ሰውየውም ልጁ የጠየቀውን አደረገለት። ሆኖም ልጁ ትንሽ ቆየና አሁንም አሳዳጊውን "ያባቴን ንብረት የወረስክ አንተ ነህ። አሁንም ይህ ፈረስ የአባቴ ስለሆነ ይገባኛልና ስጠኝ" አለው።

በልጁ ድርጊት የተናደደው አሳዳጊ አባት ተናደደና ልጁን ደበደበው። ሆኖም የልጁ ጥያቄ አልተቋረጠም። መጨረሻ ላይ "በል እንዲህ እየጨቀጨከኝ መኖር አልችልም። ተነሳና አዋቂ ቤት ሄደን ይፍረዱን" አለው። ልጅና አሳዳጊ አባቱ አዋቂ እተባሉት ሽማግሌ ቤት እንደደረሱ አሳዳጊው ቀደም አሉና "ይኸውላችሁ ይህ ልጅ አባቱ በተናዘዘው መሠት ተንከባክቤ አሳደግኩት። በጎረመሰ ጊዜም ያባቴ ቦታ ስለሆነ የሰራኸውን ቤት አፍርስልኝና በቦታው የራሴን ቤት ልስራ አለኝ። እኔም እሽ አልኩት። አሁን ደግሞ ይግረማችሁና ያለኝን አንድ ፈረስ ለእኔ ይገባኛል እያለ ይጠቀጭቀኛል። ፍረዱኝ" አላቸው። ሽማግሌዎቹ "ይህ ሰውዬ የሚናገረው እውነት ነው?" ብለው ልጁን ጠየቁት።

"አዎን!" አላቸው።

ሽማግሌዎቹም ወደ ልጁ አሳዳጊ ዞር አሉና "በል አሁንም ፈረሱን በጋራ ተጠቀሙበት" ብለው አሰናበቷቸው።

በሽማግሌዎቹ ፍርድም ሆነ በልጁ ሁኔታ የተናደዱት ባለፀጋ (የልጁ አሳዳጊ ናቸው) ጥቂት ቀናትን አሳለፉና ልጁን ጠርተው "ችግሮኛልና ይህንን ፈረስ አካፍለኝ?" አሉት፡፡

ልጁም የፈረሱ ሁኔታ አሳዘነውና አሳዳጊውን አጥብቆ ለመናቸው፡፡ "እንቢ!" ስላሉት እንደተለመደው ዳኛጋ ሄዱ፡፡

ዳኛውም የሁለቱን ነገር በጥሞና አዳመጠና "ፈረሱን አርዳችሁ ተካፈሉት" ብሎ አሰናበታቸው፡፡ የዳኛ ውሳኔ አይሻርምና ፈረሱን አርደው ለሁለት ተካፈሉት፡፡ ሰውየው ድርሻቸውን ወስደው ለውሾቻቸው ሲያከፋፍሉ ያ ልጅ ግን የደረሰውን የፈረሱን ግማሽ እንዳለ ወስዶ እኚያ ባለፀጋ አሳዳጊ አባቱ ደጃፍ አጠገብ ቆፍሮ ቀበረውና በላዩ ላይ ባቄላ ተከለበት፡፡

አሳዳጊ አባቱ ደጃፍ ላይ ልጁ የተከላት ባቄላ አድጋ አንድ ፍሬ ብቻ አፈራች፡፡ ታዲያ ከእለታት ባንዱ ቀን ሰውየው የወለዱት ልጅ ባቄላዋን ቆርጦ በላት፡፡ የፈረሱን ስጋ በቀበረበት ቦታ ላይ ተተክላ አንድ ፍሬ ብቻ ያፈራችው ባቄላ በአሳዳጊ ሰውዬው ልጅ ተቀጥፋ መበላቷን ያወቀው ልጅ አሳዳጊ አባቱን እንደገና ከሰሳቸው፡፡ "የተከልኳት ባቄላ አንድ ፍሬ አፈራች ይችኑ የባቄላ ፍሬ የእርሳቸው ልጅ ቆርጦ በልቶብኛል፡፡ እባክዎን ዳኛ የልጁ ሆድ ተቀዶ የባቄላዋ ፍሬ ወጥታ ትሰጠኝ" አለ፡፡

ዳኛውም፤ አሳዳጊ አባቱም ቢማፀኑት ልጁ በሀሳቡ ስለፀና ዳኛው "የልጁ ሆድ ተቀዶ የባቄላዋ ፍሬ ወጥታ ለልጁ እንድትሰጠው ወሰኑ" ይባላል፡፡ በዚህም አባቶቻችን አግባብነት የሌለው ውል ከሰው ጋር እንዳንዋዋል ይመክሩን ነበር፡፡

### ቶስ 39

ሁለት ወንድማማቾች ነበሩ፡፡ በአንድ አካባቢ ቤት ሰርተው ሲኖሩ ... [አትፍራ ተናገር ስለማግኘትና ማጣት ሊናገር ፈልጎ ነው] እሺ አንዱ ሀብታም እና አንዱ ድሀ ነበሩ፡፡ ሀብታሙ ልጅ ወልዶ በጥሩ ሁኔታ ያሳድጋል፤ ሌላው ደግሞ ለሰው እየተላላከ ኑሮውን ይገፋል፡፡ አንድ ቀን ሀብታሙ ቤት ቡና ይፈላል፡፡ የዚህን ጊዜ ይኸው ሀብታም ልጁን ይጠራና "ሂድና ያን ልኮ የማያበላ፤ ጠርቶም የማያበላ አጎትህን ቡና ጠጣ ብሎሃል አባቴ" ብለህ ንገረው አለው፡፡ ልጁም እንደታዘዘው ሄዶ "አጎቴ! አጎቴ! አባቴ ልኮ የማያበላ፣ ጠርቶም የማያበላውን አጎትህን ናና ቡና ጠጣ ብለህ ንገረው ብሎ ልኮኛል" አለና ለአጎቱ ተናገረ፡፡ በዚህን ጊዜ ወንድሙ ምን ለማለት ፈልጎ ልጁን እንደላከው ገባውና "እ ... ልኬ

አለሚስጠራቱ አለመውደዱ ነው። ጠርቼ አለመብላቱ ማጣቱ ነው" ብሎ ለልጁ ነገረውና ለአባቱም ይህንኑ እንዲነግረው አሳስቦ ላከው ይባላል።

## ቶስ 40

ስሜ ሰምን ፊል እንደተባለ ታሪኬን (ቶስ) ልንገራችሁ። እኔ ለቤተሰቤ ዘጠነኛ ልጅ ነኝ። አባታችን የሞተው እኔ ገና በጣም ልጅ (ህፃን) እያለሁ ነበር። በመሆኑም እናታችን ቤተሰብ በጣም ስለበዛባት ልትመግበንም ስላልቻለች እኔን ወስዳ "ዳኛ" (መቃብር ቦታ) ጣለችኝ። ከ3 ቀንም በኋላ አጎቴ ከተጣልኩበት ቀብር ቦታ አንሳኝና ወስዶ አሳደገኝ። አጎቴ እኔን ወደ ቤቱ በወሰደኝ ጊዜ የቤቱ ላሞች እየነጠፉ ስለነበር አንድ ቀን እያሳለፈ ከብቶቹን ያልበናቸ እሚያገኘውን ወተት በቀንድ (ፊል) ውስጥ እያጠራቀመ መግቦ አሳደገኝ አጎቴ። በዚህ የተነሳም እኔም ሆንኩ ሌሎች ሰምንት ወንድሞቼ በስሙ እንደተጠራን በልጅነቴ ታሪኬን ነግሮኛል።

## ቶስ 41

ድሮ ጊዜ አንድ አገልጋይ ነበረ አሉ። አሳዳሪው በቤቱ ውስጥ የተለያዩ አገልግሎቶች የሚሰጡ ሌሎች ሰዎችን መጨመር ፈልገና አብሮት ያለውን አገልጋይ ሀሳብ ጠየቀው። ይህ አገልጋይ ሌሎች አጋሮች ወደ አሳዳሪው ቤት ከመጡ የእርሱ ተፈላጊነት የሚቀንስ መስሎ ተሰማው። ወዲያውም ለአሳዳሪው "ጌታዬ ይቺ አንዷን ጆሮዬን ቢቆርጡዋት እኮ እሷን እያዩ ሌሎች አገልጋዮች ወደ እርሶዎ ዘንደ ለመቀጠር ይመጣሉ" አለው። ይህንን የሰማውም አሳዳሪው የአገልጋዩ ሀሳብ እውነት መስለውና የአገልጋዩን አንድ ጆሮ ቆርጦ ጣለው።

ይህ አንድ ጆሮው የተቆረጠበት አገልጋይ በየመንደሩ ሲዞር ያገኙት ሰዎች "እባክህ እንዴት አድርገን ነው የአንተ አሳዳሪ ጋ መቀጠር የምንችለው?" ብለው ይጠይቁታል። እርሱም በፊናው "ይቺን የእኔ የተቆረጠች ጆሮ እያያችሁ ግቡ" እያለ ይመክራቸዋል። እንዲህ እያለ በብልጠቱ አንድ ጆሮውን ያስቆረጠው አገልጋይ ለብቻው እየተጠቀመ ኖረ ይባላል።

## ቶስ 42

ድሮ ነው አሉ፤ አንድ በጣም ሀብታም የሆነ ሰው ነበር። ታላቅ ልጁ ለአካላ መጠን ሲደርስ ከቤቱ ግርጌ ካለው እርሻው መጨረሻ (ጥግ) ወስደውና "በል ልጄ ከዛሬ ጀምሮ እዚህ

ቤት ሰርተህ ኑር፡፡ ጠንካራ ስለሆንክ ከአንበሳም ሆነ ከሌላ አውሬ እኛንም ሆነ ከብቶቻችን ትከላከላለህ" አለው፡፡ የልጁ አባትም ልጁ ደርሶልኛል፤ ከእንግዲህ ወዲህ ማን ይደፍረኛል በማለት በጣም ተደሰተ፡፡ ልጅም አባቱ ባዘዘው መሠረት ቤቱን ሰርቶ እየኖረ ሳለ አንድ ቀን ማታ ድመት "ሚያው! ሚያው!" እያለች በአካባቢው ተመሳልሳ ጮኸች፡፡ በዚህን ጊዜ ልጁ "ይኸው አባቴ አንበሳ ብሎ የነገረኝ መጣ" አለና በጭለማው መንገድ አሳብሮ እየሮጠ አባቱ ቤት ደረሰ፡፡ ወዲያውም "አባዬ አንበሳ ቤቴን እየዞረ በተደጋጋሚ ስለጮኸ ልነግርህ መጣሁ" አለው፡፡ አባቱም ተደናገጠና ጦርና ጋሻውን ይዞ ወደ ልጁ ቤት ሄደ፡፡ እንደደረሰም ያገኘው አንበሳ ሳይሆን ድመት ሆና፡፡ በዚህን ጊዜም የልጁ አባት "ከአንበሳ ትጠብቀናለህ ስል የነበርከው ልጅ በድመት ጩኸት ሮጠህ መጣህ" አለው ብለው ድሮ አያቶቻችን ሲናገሩ ሰምተናል፡፡

## ቶስ 43

ኩዣብ (አዋቂ) ጋ አንድ ሰውዬ መጥቶ "ሰው ሁሉ ጠላኝ፤ ምን ይሻለኛል? እባክዎ ለዚህ የሚሆን መፍትሄ እርሶዎ ጋ አይጠፋምና ይምከሩኝ" በማለት ቤቱ ድረስ ሄዶ ጠየቀው፤ "ነገ ጠዋት ተመልሰህ ና" ብሎት ኩዣብ ሰውየውን አሰናበተው፡፡

ባለጉዳዮም በተሰጠው ቀጠሮ መሠረት በነጋታው ጥዋት እኩዣብ ቤት ተመልሶ መጣ፡፡ በዚህን ጊዜ ኩዣብ በሩን ከፍቶ ራቁቱን በመሆን አፉን በአንድ እጁ ብልቱን እንዲሁ በአንድ እጁ ሸፍኖ ቆመ፡፡ ያ ባለ ጉዳይ ሰውዬም ወደ ኩዣቡ እንዳይጠጋ ራቆቱን ሆኖ መቆሙ፤ እንዳያናግረውም አፉን በእጅ የከደነ በመሆኑ ተጨነቀና በርቀት ቆመ፡፡ ኩዣብ ወዲያው ብልቱንና አፉን ለቆ የሆነ ምልክት (የምንጣሮ እና እርሻ) አሳየው፡፡ ይህንን ጉዳይ የተመለከተው ሰውየ ወደ ቤቱ እንደተመለሰ ይህንን የኩዣብ ድርጊት የሚፈታለት አዋቂ ሽማግሌ ፈልጎ አገኛና ሁኔታውን እንዲህ ብሎ አስረዳ የሆነ ችግር ገጥሞኝ ኩዣብ ጋ ሄድኩ፡፡ ችግሬን ሰማና በነጋታው ጠዋት ተመልሼ እንድመጣ ነግሮኝ አሰናበተኝ፡፡ በቀጠሮዬ መሠረት ጠዋት እቤቱ ስደርስ በሩን ከፍቶ ወጣና ራቁቱን ቆመ፡፡ ወዲያውም አፉንና ብልቱን በእጆቹ ሸፍኖ ቆመ፡፡ ትንሽ ቆየና እጆቹን ከአፉና ከብልቱ ላይ በማንሳት የምንጣሮ ምልክት አሳየኝ፡፡ እኔም ደንግጬ ወደ ቤቱ ሮጥሁ፡፡ ድርጊቱ በሙሉ ስላስፈራኝ ይህንኑ የኩዣብ ድርጊት ምን መልዕክት እንዳለሁ ያስረዱኝ ዘንድ ወደእርሶ መጣሁ አላቸው። ወዲያውም አዋቂው ሽማግሌው "አየ ልጄ! ኩዣብ ችግርህን ተረድቶ መልሱን ነግሮሃል አንተ ባለ መረዳትህ ነው እንጂ" አሉት፡፡

በመቀጠልም ልጁ ኩኀብ እንደነገረህ አንደኛ እጁን በአፉ ላይ አድርጎ አፍኖ መቆሙ፡- አላግባብ ሰውን አትዝለፍ፤ አታዋርድ ማለቱ ነው፡፡ ሁለተኛው ብልቱን በእጁ ሸፍኖ መቆሙ የሰው ሚስት በመድፈር ወይም በማባለግ ትዳር አትበጥብጥ ማለቱ ነው፡፡ ስለዚህ ከሰው ጋር አትጣላ፣ ጭቅጭቅ አታንሳ፤ ሀባይህን አሳምረህ የግብርና/እርሻ ስራህን በትጋት ስራ፡፡ ትበለጽጋለህ፤ የዛኔ ሰውም ይወድሀል፡፡ ብሎ ነው ኩኀብ ያስናበተህ አሉት አዋቂው ሽማግሌ፡፡ በዚህም መሠረት ያ እኩኀብ ጋ ለችግሩ መፍትሄ ፍለጋ የሄደው ሰውዬ ምክሩን ተጠቅሞ ራሱን ለውጦና ቀሪው ዘመኑን በደስታ ኖረ ይባላል፡፡

## ቶስ 44

አንድ ትልቅ ሀብታም የሆነ ሰውዬ ነበር፡፡ ሆኖም አንድ ቀን የራሱን ሚስት አስቀምጦ የሌላ ሰውን ሚስት በመድፈሩ፣ የሰውን ገንዘብ ወስዶ በመክልከሉ የተነሳ ችግር ውስጥ ገባና ወደ አንድ ሽማግሌ ጋ ምክር ለመጠየቅ ሄደ፡፡ ሽማግሌውም ይህንን ሰውዬ ተመልክቶ፡-

"አንተ ሰው ምንድነው ችግርህ? ገንዘብህን ያላግባቡ ታጠፋለህ፣ የራስህን ሚስት አስቀምጠህ የሌላ ሰው ሚስት ታባልጋለህ ችግርህ ምንድነው?" መቼም እኔም ብመክርህ አትሰማም፤ ለማንኛውም ነገ በጠዋት ና ብሎ አሰናበተው፡፡

አጥፊ የተባለው ሀብታም ሰውዬም በማለዳ ተነስቶ መጣና አዋቂው ሽማግሌ ቤት ደረሰ፡፡ በዚህን ጊዜ ያ ሽማግሌ ልብሱን አውልቆ በር ላይ ቆመና በአንድ እጁ አፉን፣ በአንዱ እጁ ብልቱን ያዘ፡፡ ትንሽ እንደቆየም የሆነ ምልክት (የምንጣሮ) አሳየውና ባለጉዳዮን ጥቂት ትኩር ብሎ ተመለከተውና ሳያሰናብተው ዝም ብሎት ወደ ቤቱ ገባ፡፡ በዚህ ሁኔታ የተደናገጠው ጥፋተኛው ሰውዬ ደንግጦ ወደ ቤቱ እየሮጠ ሄደ፡፡ ቤቱ እንደደረሰም ለሚስቱ "አንቺዬ አዋቂ የተባለው ሰውዬ ጋ ብሄድ ራቁቱን ቆሞ ዝም አለኝ" ብሎ ለሚስቱ ነገራት፡፡ በዚህን ጊዜ ሚስቱ (ፈጠን ብላ) "ሽማግሌው ዝም ያለ መሰለህ እንጂ እንደዚያ ሲያደርግ ምክሩን ሰጥቶሀል" አለችው፡፡ "እንዴት? ዝም አለኝ እያልኩሽ?" አላት መልሶ ሚስቱን፡፡ "አይ! ላንተ ዝም ያለህ መሰለህ እንጂ የተናገረው ነገር አለው፡፡ ይኸውም ብልቱን መያዙ የራስህን ብልት በጥንቃቄ መያዝና መጠቀም አለብህ (አታመንዝር) ማለቱ ሲሆን፣ አፉን በእጁ መሸፈኑም፣ ይህ አፍህ እንዳመጣ የመናገር ልማድህን ተው! ሰው ጋር ብዙ እያገጨህ ያለው እርሱ ነው፡፡ ከዚህ ይልቅ አፍህን ሰብስብና ማሳህን እረስ፤ ከዚያም ባለፀጋ ትሆናለህ፤ በዚህም ለቤተሰብህም ሆነ ለሌላው ትተርፋለህ ብሎ መክሮሃል ብላ አስረዳችው፡፡

በዚህም ተፀፅቶ አለቀሰና ሚስቱን ምህረት እንድታደርግለት ለመናት። በሰላምም አብረው መኖር ጀመሩ ይባላል።

## ቶስ 45

አንድ አባት ሁለት ልጆች ነበሩት። ልጆቹን ያሳደገው በከፍተኛ እንክብካቤ ነበር። ይህ የልጆች አባት እንዳጋጣሚ ታመመና ሞተ። ይሁን እንጂ ለሁለቱ ልጆቹ ከመሞቱ በፊት የሚደርሳቸውን ሀብትና ንብረት አካፍሏቸው ነበር።

አባታቸው ሞቶ ትንሽ እንደሰነበተ ታላቅየው በታላቅነቱ ተመክቶ ለታናሹ የተሰጠውን የኑዛዜ ሀብትና ንብረት ከለከለ። ታናሹም "ሁለታችንም እኩል ልጆች ነን አብረን ተወልደን እያለ የሚደርሰኝን ንብረት ልትከለክለኝ አትችልም" ብሎ ክርክር ጀመረ።

የሁለቱ ወንድማማቾች ክርክር በሽምግልና እንዲፈታ ስለፈለጉ ዋቻ ማጅ በሚባል ቦታ የሚኖር አዋቂ ሽማግሌ ጋ ለመሄድ ተስማሙና ጉዞ ጀመሩ። በጉዟቸው ላይ እያሉም አንድ እርጉዝ (እናት) ውሻ ሞታ ጎንጀሬ አፍዋን ውርር አድርጓት፣ በሆዷ ውስጥ ያሉት ልጆቿም ሲወራጩ አዩ። የዚችን ሙት ውሻ ሬሳ አይተውና በዚህም ሁኔታ ተገርመው መንገዳቸውን ቀጠሉ። አሁንም ትንሽ እልፍ እንዳሉ በአንድ ጭው ባለ ሜዳ መሀል ላይ ወፍራም (ወደል) አህያ ቁማ አዩ። ሆኖም አህያዋ በጣም እየፈነጠዘች ነበርና ወንድማማቾቹ ተገርመው "በዚህ አውላላ ሜዳ ላይ የሚበላ ሳር የለም፣ የሚጠጣ ምንጭ ወይም ወንዝ የለም? ታዲያ ምን አግኝታ ነው እንዲህ የምትፈነጥዘው?" በማለት ተገረመው ጉዟቸውን ቀጠሉ። ይሁን እንጂ አሁንም አንድ የሚያስገርም ነገር አጋጠማቸው። ይኸውም አንድ ትልቅ ፈረስ ለምለም በሆነ መስክ ላይ ታስሮ አይግጥም፣ ሰውነቱም ከስቶ አዩ። በመገረምም:-

"ያቺ አህያ በባዶ ሜዳ ጠግባ ትፈነጥዛለች፣ ይህ ፈረስ ደግሞ በለምለም ሳር መሀከል ታስሮ፣ ከስቶ ይታያል፣ ጉዳዩ ምንድነው?" እየተባባሉ በመጫወት ላይ ሳሉ ለሽምግልና የሚፈልጉት ሰውዬ ቤት ደረሱ።

ሽማግሌውም ሁለቱ ወንድማማቾች የመጡበትን ጉዳይ ካዳመጠ በኋላ ሀሳባቸው ገባውና "ስትመጡ እመንገዳችሁ ላይ ምን ምን ነገሮች አጋጥመዋችሁ ነበር ብሎ ጠየቃቸው።

ልጆቹም ከቤታችን ወጥተን ወደ እርስዎ ጋ ለመምጣት መንገድ እንደጀመርን አንዲት እርጉዝ ውሻ ሞታ አፏ በጎንጀሬ ተሞልቶ እሆድዋ ውስጥ ያሉት ልጆች ሲወራጩ

አየን፤ ቀጥሎ ደግሞ አንዲት አህያ ድርቅ ባለ ሜዳ ላይ እያለች ወፍራ ስትፈነጥዝ አየን፤ በመጨረሻም በለምለም ጨፌ/ሳር መሀል ታስሮ በጣም የከሳ ፈረስ አይተናል አሉት።

አዋቂው ሰውዬም "ጥሩ ይህ የነገራችሁኝ ነገር ሁሉ ምልክት ነው። አውቃችሁታል?" ብሎ ጠየቃቸው።

ልጆቹም "አይ! እኛ አናውቅም!" አሉት ሽማግሌውም ይህውላችሁ መጀመሪያ ላይ ያገኛችኃት የሞተች ውሻ፣ እና በውስጧ ሆነው የሚዘሉት ልጆቿና የውሻዋን አፍ የወረረው ጎንጀሬ የሚያሳየው በኋለኛው ዘመን "እኛ እናውቃለን፣ እኛ እንናገር" የሚሉ ልጆች/ትውልድ የሚመጣ መሆኑን ያሳያል።

ሁለተኛ በአውላላ ሜዳ ሰውነቷ አምሮ ስትፈነጥዝ ያያችኋት አህያ የምታሳየው "ምንም አስታዋሽ አጥተው፤ ምንም በእጃቸው ሳይኖር፤ ተረስተው በጫካ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች የሚከበሩበት፣ የሚናገሩት ሁሉ እውነት ነው ተብሎ አድማጭ የሚያገኙበት ጊዜ/ዘመን የሚመጣ መሆኑን ያሳያል።

ሶስተኛው ፈረሱ የሚያሳየው "ራሳቸውን ከፍ የሚያደርጉ፣ በሰው ጉልበት የሚኖሩ ሰዎች ተቸግረው፣ የሚበሉት የሚጠጡት ነገር አጥተው በጎስቁልና የሚኖሩበት ጊዜ እንደሚመጣ ያሳያል።" አላቸው።

ይህን ከነገራቸው በኋላ "በሉ እንግዲህ አሁን ወደ ቤታችሁ ተመለሱና በአባታችሁ መቃብር ላይ ቤት ሰርታችሁ ጠብቁን ከሳምንት በኋላ መጥተን እንፈርዳለን" ብሎ አሰናበታቸው። የቀጠሮው ቀን ደረሰና ሽማግሌዎች መጡ። ሽማግሌዎቹ ልጆቹ እሰሩት ቤት ውስጥ ተቀመጡና የልጆቹን እናት በመጥራት "የነዚህ ልጆች አባት የቀብር ቦታ የት ነው?" ብለው ጠየቋት። እናታቸውም፡-

"ያውና" ብላ አመለከተች።

ሽማግሌዎቹም "በይ አንቺ እናት ከሆንሽ ሄጅና በመቃብሩ ላይ ቁሚና እጅሽን ወደ ግራና ወደ ቀኝ ዘርጊ" አሏት።

"ሄዳ ቆመች!"

"በይ እነዚህ ልጆች [ሁለቱም ማለቱ ነው] የሚቹ ልጆች ናቸው በይና ማይ!" አሏት። እርሷም በጣም ተጨነቀች። ወዲያውኑም ወደ ልጆቹ ዞር አሉና "በሉ እናንተም ቶሎ ቶሎ እያላችሁ የአባታችሁን መቃብር ቆፍሩ!" ብለው አዘዟቸው። ታላቁ ወዲያው የመቃብሩን አፈር እየቆፈረ ወደ ውጭ ይጥል ጀመረ። ታናሹ ግን ልቡ እያዘነ፣ በትካዜ ዝግ በማለት እንደታዘዘው መቃብሩን መቆፈር ጀመረ።

ልጆቹ መቃብሩን ቆፍረው ግማሽ እንዳደረሱ በጭንቀት ውስጥ የነበረችው የልጆቹ እናት "እኔ እናንተ የሀገር ሽማግሌዎች ፊት ቆሜ አልዋሽም! ይህንን ሟቹ ባሌን ሳገባ ቅሪት ሆኜ ነው ወደ ቤቱ የመጣሁት። የሟቹ ትክክለኛ ልጅ ታናሹ ብቻ ነው" ብላ ተናፈሰች።

ሽማግሌዎቹም "በይ እውነቱን በመናገርሽ ጥሩ አደረግሽ። እውነተኛ መሆን ጠቃሚ ነው አንቺ እንዳረጋገጥሽው የሟቹ ወራሽ ታናሹ ልጅ ብቻ ነው። የአባቱን ሀብትና ንብረት ከዛሬ ጀምሮ እንዲረከብ። ታላቅየውም ያው የአባቱን ንብረት ወራሽ የሆነው ልጅ ወንድም ስለሆነ ሳይለያዩ አብረው ይኖሩ" ብለው ፈረዱ ተብሎ ሲነገር ሰምቻለሁ።

## ቶስ 46

ጥንት በቤንች ሀገር ድሮ አራት ቀንድ ያለው ጎሽ ተነስቶ ነበር። ይህንን ጎሽ ለመግደል የታወቁ አዳኞች ተነስተው እስከ ዎቻ ማጅ ድረስ አሳደው ሊገድሉት አልቻሉም። እዛም ደሉት አዳኞች ሊገድሉት ሞክረው አልቻሉምና ተመልሶ ወደተነሳበት ቦታ (ቤንች ሀገር) ገባ። ሁለተኛ ደግሞ ዱኩላዎች፣ አሳማዎች፣ ቆጮ፣ ጎደሬ፣ ከቺ በመብላት ከብቶችም ደግሞ ሆራ መጠጣትና ሳር መብላት የሚችሉት ቆጮ ለመብላት መሮህ ጀመሩ። ሶስተኛ አንዲት ድኩላ ስትወልድ፣ የተወለደውም ግልገል ወድያውኑ እናቱን ሲሰር ሳር አጫጅ በማየቱ ተገርሞ ወደ ቤኑ ሽታቶ ጋይ (በዚያን ጊዜ የነበረው የቤንች መሪ) መጥቶ ተናገረ።

ይህንን ተኣምር የሰማው ቤኑ ሽታቶ የዚህን ፍቺ እንዲነግረው ኩግብ (አዋቂ/ፈላስፋ) ይህ ክስተት ምን አይነት ትንቢት እንዳለው ያስረዳው ዘንድ ፈለገና አስጠራው። ኩግብም ወደ ቤኑ ሽታቶ ቤት መጣ "አደረ" በነጋታው ቀን ላይ ቡና ተፈልቶ እየጠጣ፣ "ለምን አስጠሩኝ?" ብሎ ጠየቀ። ቤኑ ሽታቶም በሳር አጫጁ የተነገረውን ሶስት ተኣምራት ነገረውና ፍቺውን ጠየቀ።

ኩግብም ካደመጠ በኋላ ይህ ባለ አራት ቀንድ ጎሽ መጀመሪያ ላይ ቢገደል ጥሩ ነበር፣ ሆኖም ሊታደን ሲል አምልጦ ከሀገር ወጥቶ ወደ ሀገር እንደገና መመለሱ የሚያሳየው፣ ከዚህ በኋላ በተከታታይ አራት መንግስታት በሀገር ላይ እንደሚነግሱ ያሳያል። ሁለተኛ ደግሞ ሆራና ሳር የሚባሉት ከብቶች ለቆጮ መጮሀቸው የሚያሳየው አሁን "በቤኑ ሽታቶ አምላክ! ያዘጋጀሁትን ቦርዴ ሳትቀምስ አትሄዱም!" እየተባለ የሚለምነው ሰው ከጊዜ በኋላ "ወይኔ! የሚጠጣ ቦርዴ ከየት ባገኘሁ?" ብሎ የሚለምንበት

ጊዜ የሚመጣ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በመጨረሻም ገና እንደተወለደ እናቱን የሚሰረው የዱኩላ ግልገል ደግሞ የሚያሳየው "ልጅ ከእናቱ፣ እህት ከወንድሟ፣ አባት ከልጁ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚፈፅምበት ዘመን የሚመጣ መሆኑን ነው፡፡" የሚል ፍቺ ሰጥቶ ኩገብ ሄደ ይባላል፡፡

## ቶስ 47

ጥሩ አድርጎ መስረቅ የሚችል አንድ ሰው ነበረ፡፡ አንዱን ሰውዬ አንተ "እስኪ ዛሬ አብረን ሄደን እንስረቅ" አለው፡፡ ሰውዬውም በሌባው ንግግር ተገረመና "ወንድሜ! መስረቅ ጥሩ አይደለም፡፡ መስረቅ እኮ ነውር ነው" ብሎ መለሰለት፡፡ በዚህ ጊዜ ሌባው "አይ አንተ ሰው! የምትሰርቀው እኮ ቀስ! ቀስ! እያልክ ሄደህ ነው ለካስ አታውቅምና" ብሎት ሄደ፡፡

ሰውዬውም በሌባው ንግግር ተመሰጠና "ታዲያ እኔ እስከመቼ ድረስ ነው በችግር የምኖረው! እሱ እየሰረቀ ተደስቶ ይኖራል፡፡ እንዲህ ከሆነ ታድያ እኔስ ለምን ቀስ! ቀስ! እያልኩ ሄጄ ያገኘሁትን አልሰርቅም?" ብሎ አሰበና ሊሰርቅ ሄደ፡፡ እንዳጋጣሚ የሰው ቤት አገኘና ለመስረቅ "ቀስ! ቀስ! ቀስ! ቀስ!" እያለ ገባ፡፡ የቤቱ ባለቤቶችም ሰሙትና "ምንድነው ይህ ቀስ! ቀስ! ብሎ እየተናገረ የሚሄደው?" አሉና ሄደው ያዙት ይባላል፡፡ የሚያውቅ ሰው በሌብነቱ ይጠቀማል ስለሆነም የማያውቁት ነገር ውስጥ ዘሎ መግባት ጥሩ አይደለም፡፡ ያልሰሩበት ገንዘብ/ሀብት ሰርቆ መጠቀም ጥሩ አይደለም ብኩን ያደርጋል እያሉ በልጅነታችን አባቶቻችን ይመክሩናል፡፡

## ቶስ 48

ቀፎ ሰቅሎ የማያውቅ ሰውዬ ነበር፡፡ አንድ ቀን እሰው ቤት ሄዶ ጠጅ ጠጥቶ (ቀምሶ) አየ፡፡ ለካስ ይህ ጠጅ የሚሉት የሚሰራው ከማር ነው አለና "እኔስ እዛ ጉረቤቴ የሰቀለው ቀፎ ሄጄ ማሩን አውርጄ እስኪበቃኝ ድረስ ጠጅ አልጠጣም!" አለና እቃውን ይዞ ወደ ቀፎው ሄደ፡፡ ሄደና ቀፎው ጋ ደርሶ (ከዚህ በፊት ቀፎ ሰቅሎ የማይውቅ ሰው ነው) ከስር ሆነና በያዘው ዱላ ቀፎውን ከስሩ በሳ፡፡ በዚህን ጊዜ እቀፎው ውስጥ የነበሩት ንቦች እንዳለ ረገፉበትና ነደፉት፡፡ ሰውየውም ያልሰራበትን ነገር ለመጠቀም ሄዶ በንብ ተነድፎ ሞተ ይባላል፡፡

## ቶስ 49

አንድ ሰው ነበር፡፡ የሀገሩ ንጉስ አንድ ቀን አስጠሩትና "ሂደህ ለቤት መስሪያ የሚሆን ትልቅ ምሰሶ ቁረጥና አምጣ" አሉት፡፡ ሰውየውም (መቼም የንጉስ ትዕዛዝ እምቢ አይባልምና) የታዘዘውን አይነት ረዥም እንጨት የሚያገኝበትን አካባቢ እያሰበ ጉዞ ጀመረ፡፡ እየተጓዙ ሳለም በመንገዱ ላይ አንድ ቦሃ ሰውዬ አገኘ፡፡ ይኸ ቦሃ ሰውየውም፡-

"ወንድሜ ሆይ እንዲህ እየተከዝህ ወዴት ትሄዳለህ?" ብሎ ጠየቀው፡፡ እርሱም መልሶ

"ይኸውልህ ስንት ቀን ሙሉ ጫካ ለጫካ በመንከራተት ላይ ነኝ"

"ምን ሆነህ?"

"ንጉሱ ቤት መስሪያ የሚሆን ረዥም ምሰሶ ቆርጠህ አምጣ ብለውኝ አጥቼ በመንከራተት ላይ ነኝ" አለው፡፡

ቡሃውም "አትጨነቅ፤ ግድየለም እኔ አገኝልሃለሁ" አለው

"የት ታገኝልኛለሁ?"

"ግዴየለም እኔማ አገኝልሃለሁ" አለው፡፡

"ወንድሜ ታድያ ምን እንዳደርግ ትፈልጋለህ" ሲለው

ቡሃው "አሁን ወደ ንጉሱ ተመለስና ቆርጠህ አምጣ ያሉኝን ረዥም የምሶሶ እንጨት አግኝቻለሁ፡፡ የሚፈልጉትን መጠን (ርዝመት) ይንገሩኝና ሄጄ ቆርጬ ላምጣ" በላቸው አለው፡፡

ሰውዬውም የዛን የቡሃውን ምክር ተቀብሎ ወደ ላኩት ንጉስ ዘንድ ሄደ፡፡ ንጉሱም፡-

"መጣህ? የሄድክበት ተሳካ? እንጨቱን አገኘህ?" ብለው ሲጠይቃት "አዎን ጌታዬ!" አለና መለሰ፡፡ "የታለ ታድያ?" ብለው ሲጠይቁት ሰውየው መልሶ "ቀደም ብዬ እንደነገርኩዎት ለሚፈልጉት አይነት ምሶሶ የሚሆን እንጨት አግኝቻለሁ፡፡ የመጣሁት እርሶ የምሶሶውን ርዝመት እንዲነግሩኝና ሄጄ ቆርጬ ላመጣ ነው" ብሎ መለሰላቸው፡፡

ለምሰሶ የሚሆን እንጨት ቆርጦ እንዲያመጣ የላኩት ሰውዬ በጠየቀችው ጥያቄ ተገርመው ንጉሱ እንዲህ አሉት፡-

"መንገድህ ላይ ያገኘኸው ሰው አለ"

"የለም ጌታዬ"

"ተው በሁዋላ እንዳይቆጭህ!" ሲሉት ሰውዬው

"አዎን! አንድ ቡሃ መንገደኛ አግኝቻለሁ" አላቸው፡፡

ንጉሱም ወዲያው "አዎን ይቺን አይነት ምክር የሚነግርህ እሱ ነው" አሉትና አሰናበቱት ይባላል፡፡

### ቶስ 50

ወደፊት ላሞች በረት ሙሉ ሆነው ቢታለቡ፣ እህልም የፈለገውን ያህል ሆኖ ቢታረስ ሰው አይጠግብም፡፡ ልጅ ለአባቱ አይታዘዝም፡፡ ሚስት በባሏ ፍቃድ አታድርም፡፡ ይህ ሁሉ ነገር እንደሚመጣ አስቡ፡፡ ጌታና አሽከር፣ ባሪያና ጌታ የሚባል ይጠፋል፡፡ (በልጅነቴ ይህንን ሲናገር የሰማሁት ጋዴዝ የሚባል ሰው ነው)

### ቶስ 51

የሮ (ፈጣሪ) መሬትን (ዓለምን) ሲፈጥራት መጀመሪያ ላይ እጥፍጥፍ አድርጓት ነበር፡፡ ኋላ ላይ የሰውን ልጅ ለመፍጠር ፈለገና ዘረጋት፡፡ የሰውም ልጅ ከዛን ጊዜ ጀምሮ በመሬት ላይ መኖር ጀመረ፡፡ ከሰው በፊት የተፈጠረ ፍጡር የለም፡፡ ወይም መኖሩ ሲነገር አልሰማሁም፡፡ የሰው ልጅም የሮስንዶ በፈጠረው ምድር ላይ ሲኖር ህግጋትን እንዲፈፅም ታዟል፡፡ ከሰው ልጅ ቀጥሎ በርካታ እንስሳት ተፈጥረዋል፡፡ ሁሉም ፍጡሮች የሰው ልጅን ጨምሮ ራሳቸውን የመሰሉ ልጆችን እየወለዱ እንዲባዙ አደረገ፡፡

•

### ቶስ 52

ጥንት የሮ (አምላክ) መጀመሪያ ላይ የፈጠረው ሁለት ሰዎችን ብቻ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ወንድና ሴት ነበሩ፡፡ አብረው እየኖሩ ሳለ በወንዱና በሴቷ መሀከል ፍቅር ገባ፡፡ ቀጥሎም ተጋቡና ጐጆ ሰርተው የመጀመሪያው ትዳር ተመሰረተ፡፡ ከዚህ በኋላ ተዋለዱ፡፡ በተወለዱትም መሀከል ጋብቻ በመፈፀሙ በሰዎች መሀከል ዝምድና (ቤተሰብነት) ተጀመረ፡፡

### ቶስ 53

የሮ (ፈጣሪ) በዚህ ዓለም የሚገኙ ነገሮችን በሙሉ ፈጠረ፡፡ እነዚህ የየሮ ፍጥረቶች በምድር፣ በሰማይ፣ በውሃ፣ ወዘተ. የሚኖሩትን ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ በአይኑ ሊመለከታቸው የማይቻለውን መንፈሶች ጭምር ነው፡፡ እነዚህን ሁሉ የፈጠረው የሮ በፍጡሮቹ ላይ የበላይነቱን ለሚያንን ሰጠው፡፡ በሰው እና ፈጣሪ መሀከል ያለው አገናኝ ሚያንን ነው፡፡

እንድናገኝ ጠጅ ይጠመቅና በመንደር ውስጥ የሚገኙ ሽማግሌዎችና አሮጊቶች በሙሉ ተገኝተው እንዲመርቁ ይደረጋል፡፡ እኛ በባህላችን መሰረት በዚህ እንደዚህ አድርገን የሮሰንዶ (ፈጣሪን) እናመልካለን፡፡ አምላካችንንም የምናገኘው በዚህ አድባር ስር ሆነን ስንለምነው ነው፡፡

## ቶስ 57

ኦማሽለሰንዶ በጥንት ዘመን ከሰው ልጅ ጋር በምድር ላይ ይኖሩ ነበር፡፡ ኦሚ (ቀይ ዛፍ) የተባለውን የዛፍ አይነት እሮብለት የፈጠሩት እርሳቸው ናቸው፡፡ አንድ ቀን ካፍቴት አስቀየማቸውና ተጨቃጨቁ፡፡ በዚህ የተነሳም "እኔ እስከምመለስ ድረስ (ለፍርድ ነው) የሰጧችሁን ነገሮች ሁሉ ይገቴ ሄጃለሁ" በማለት ረግመው የኪሉ ካሹ ወንዝን ተከትለው ሄዱ፡፡ ስለዚህም "ወደ ታች የሄደው ኦማሽለሰንዶ ተመልሶ ይመጣል፡፡" የዚያኔ ለእውነተኞቹ ይፈረዳል፡፡

## ቶስ 58

ኦማሽለሰንዶ በሰው ልጅ ክፉ ባህርያት አዝነው በዓለም የመጨረሻ ቀን ለመፍረድ እንደሚመለሱ ተናግረው ሲሄዱ በከበሮ፣ በጡርንባ ታጅበው በፈረስ ሰረገላ እየጋለቡ ነው፡፡ በአጠቃላይ ምድርን እያደበላለቁ እንደሄዱ የነገረችኝ አያቴ ናት፡፡

## ቶስ 59

ኦማሽለሰንዶ በዓለም የመጨረሻ ቀን ለፍርድ ይመጣሉ፡፡ ይሁን እንጂ እርሳቸው ከመምጣታቸው በፊት የሚፈፁሙ ትንቢቶች አሉ፡፡ ከነዚህም መሀከል፦ የሰው ልጅ የቤቱን መዝጊያ ትቶ ጣሪያውን በስቶ ወደ ውጪ ሲወጣ፤ ሚስት ባሏን ስትገድል፤ አባት ልጁን ሲገድል፤ ልጅም አባቱን ሲገድል፤ ሰው አደራ የተቀበለው ሲክድ፤ ሰው ሰውን በጭካኔ መግደል ሲጀምር ሰው ከዘመዱ ጋር ግብረስጋ ግንኙነት መፈፀም ሲጀምር ... የመሳሰሉት ሁሉ የኦማሽለሰንዶ መምጫ ቀናት መቅረብን ያሳያሉ፡፡ እርሳቸውም (ኦማሽለሰንዶ) በፈረሳቸው ላይ ተቀምጠው ነጋሪት እያስመቱ ሲሄዱ የተናገሩት እነዚህን እንደነበር አያቴ ከእናቷ የሰማቸውን ነግራኛለች፡፡ በተጨማሪም የመጨረሻው የምፅኣት ምልክትም ክፉ ረሃብ በሀገር ሙሉ መግባት ነው፡፡ ይህም የፍርድ ቀን የመጨረሻው መቃረቢያ ነው፡፡ ኦማሽለሰንዶ ለፍርድ ሲመጡም ሁለት ድንኪኖች "ያጊጦል" እና "ሲዝ" እሚባሉ አካባቢዎች

## ቶስ 54

የሚያንጎ ዓመታዊ ክብረበዓል ሲደርስ ባለሚያጎው (ማንግባብ) ከምግብ (በተለይም ስጋ) እና መጠጥ (ጠጅ) ይቆጠባል። ቀጥሎም ካዳሚዎቹ (ወይዜስ) እና በዚህ በዓል አከባበር ላይ እንዲገኙ የሚፈቀድላቸው ሰዎች ከበአሉ አራት ቀናት ቀደም ብለው ከግብረስጋ ግንኙነት እንዲታቀቡ ይነገራቸዋል። የሚያንጎ በዓል ቀን ሲቀርብ ባለሚያንጎው ወደ ቤተ-ሚያንጎ (ኮብቲም) ይገባል። ቀጥሎም መልኳ ጥቁር የሆነች እናት ላም (ካርሻን) ፀሐይ ሲጠልቅ ለመስዋዕት ትቀርባለች። በዚህን ጊዜ "እምቧ!" የሚል ድምፅ ካሰማች መስዋዕቱ ተቀባይነት አግኝቷል ማለት ነው። ቀጥሎም ከላሚቷ ልዩ ልዩ ብልቶች የተቀነባጠበ ስጋ የባለሚያንጎው የመጀመሪያ ሚስት (ጌን) እና ጠብሰው ካዳሚው (ወይዜስ) በደም (ገበቱ ሆኖ የሚያንጎ መስዋዕት ማቅረቢያ ነው) የባለሚያንጎ ቤተሰቦች ባሉበት ይቀርባል። በዚህን ጊዜ ባለሚያንጎው ወደ ውጭ ይወጣል። ከዚያም የተጠበሰውን ስጋ አንጋፋ (ዳንዝ) የሆነ በጥንቃቄ ይዞ ባለሚያንጎውን በስም ጠርቶ ይሰጠዋል። በዚህን ጊዜ ባለሚያንጎው የመስዋዕት ስጋውን ይቀበልና ፊቱን ወደ ምዕራብ (አበርያርድ ኬት) አዙሮ ስለህዝቡ፣ ስለህገሩ ይማልዳል። በመጨረሻም ከያዘው የመስዋእት ስጋ ይቀምሳል፤ ቀጥሎም ለአጋፋው (ዳንዝ) ይሰጣል፤ ከእርሱ ቀጥሎም ሚስቱ (ጌን) ትቀምስና እድሜያቸው ከፍ ካሉት ታዳሚዎች ጀምሮ ሁሉም ይቀምሳል።

.

## ቶስ 55

ካህ የታመመን የመፈወስ፣ መሀንን የማስወለድ፣ የጠፋን የማስገኘት፣ ስለሚችል ሀሳቡ የተሳካለት ሰው ስለት የተሳለውን ነገር ማለት፦ ሰውም፣ እቃም፣ ከብትም፣ ገንዘብም ሁሉ እንደስለቱ አይነት ያስገባል።

## ቶስ 56

የእኛ "ቤተክርስትያን" ማለት አድባራችን ነው። እዛ ስር ሆነን ፈጣሪያችንን ስለተለያዩ ጉዳዮች መለመን ወይም ማመስገን እንችላለን። ለዚህም ተግባር መጀመሪያ ለአድባሩ ቤት ይሰራል። ቀጥሎም ጥቁርና ቀይ በሬ ወይም በግ ይታረዳል። ይህም ፈጣሪያችን ጥሩ አዝመራ እንዲሰጠን ስንለምን ነው። ለምሳሌ ጥቁር በሬ ለጥሩ የበቆሎ አዝመራ፣ ቀይ በሬ ደግሞ ለጥሩ የማሽላ (ዶንቃ) አዝመራ ፈጣሪ እንዲሰጠን ስንለምን መስዋዕት እናቀርባለን። በተጨማሪም በሰቀልነው ቀፎ ውስጥ ንብ ገብቶ ጥሩ የማር ምርት

ይተከላሉ። የዚያን ጊዜ በየቦታው ጡሩንባ ይነፋል። የሰው ልጅም በእውነተኛ ስራው ይፈረድበታል።

### ቶስ 60

እንስሳት ጥንት ከሰው ልጅ ጋር በተቀራረበ አካባቢ አብረው ይኖሩ ነበር። ይሁን እንጂ ከእነዚህ እንስሳት አብዛኞዎቹ ሰርቶ መኖርን አልወደዱም። በዚህም ዛፍ ላይ የሚኖሩት መሬት ወርዶ ከመስራት፣ ምድር ላይ የሚኖሩት ወደ ሰው ልጅ ቀርቦ እየተጋገዙ ከመስራት ይልቅ የሰው ልጅ የሚያመርተውን እህል መፍጀትን ስራቸው አደረጉ። በዚህም ሁሉንም የፈጠረው የሮ (አምላክ) እነዚህን እንስሳት በመሉ ወደ ጫካ እንዲባረሩ አደረገ።

### ቶስ 61

የሮስንዶ ከፈጠራቸው እንስሳት መሀከል ላም (ዲያንት) ከነኀሽ ጋር ተባራ ጫካ ውስጥ ትኖር ነበር። በኋላ ላይ ግን የሮስንዶ መረጣትና የሰውን ልጅ እንድታገለግል ብሎ ወደ ቤት መለሳት። ከሰው ጋርም መኖር ጀመረች። ከዚህን ጊዜ ጀምሮ ከዘሮቿ ከነኀሽ ተለየች።

### ቶስ 62

የሮስንዶ የፈጠራቸውን እንስሳት እንድትኀበኝ ሴቷን (መጀመሪያ የፈጠራትን የሰው ልጅ) ላከ። እርሷም መጀመሪያ ወደ ውሻ ጋ ነው የሄደችው። በስሙም "አኩኜ" ብላ ጠራች። ውሻም ዝም አለች። ይህንን የውሻ ድርጊት የተመለከተው ፈጣሪ (የሮስንዶ) ውሻን ከዛሬ ጀምሮ በአፍሽ መናገር አትችይም፤ "ኡንከም ጋህ!" ጭራሽን በማወዛወዝ ተናገሪ ብሎ ረገማት። ከዚህን ጊዜ ጀምሮ ውሻ ባለቤቷንም ሆነ የምታውቀው ሰው ስታገኝ ሰላምታዋን የምትገልፀው ጭራዋን በማወዛወዝ ነው።

### ቶስ 63

የሮሰንዶ ከፈጠራቸው ፍጡሮች መሀከል እባብ ተንኮለኛ ሆነ። በዚህ የተነሳም ሁል ጊዜ "ቤትህን ጥለህ ሽሽ!" ብሎ ረገመው። በዚህ የተነሳም እባብ እስከ ዛሬ ቆዳውን ከላዩ ላይ አውልቆ እየጣለ ይኖራል።

## ቶስ 64

ጥንት ጨረቃ ከላይ ትወድቅና ስርጤ ስር አረፈች። በዚህ የተነሳም ሀገር ሁሉ ድርቅ ሆነ። ይሁን እንጂ በዚህ ድርቅ ዘመን በሬ ውሃ ፈልጎ፣ ፈልጎ አገኝና ጠጣ። ወደ ቤቱም በተመለሰ ጊዜ ሽንት ሲሸና የሰው ልጅ ተመለከተና "ይህ በሬ ውሃ ከየት አግኝቶ ቢጠጣ ነው ሽንቱን የሸና" በማለት ውሃ የት እንደሚገኝ ለማወቅ ፈለገና ጭድ ሰብስቦ በሬው ጭራ ላይ በማሰር ለቀቀው። በሬውም በሄደበት ቦታ ሁሉ ጭራው ላይ የታሰረው ጭድ ይንጠባጠብ ስለነበር ይህን እየተከታተለ መንዝ ላይ የነበረው የሰው ልጅ በሬው ውሃ የሚጠጣበት ቦታ ደረሰ፣ ሲደርስ ውሃ አየ። ቀረብ ብሎ ተመለከተና ጎንበስ ብሎ ጠጣሁ። ከዛን ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጅ ውሃ መጠጣት ጀመረ ይባላል።

## ቶስ 65

በባህላችን የአዝመራ ወቅት ሲደርስ አንድ አይነት ዘር ብቻ አይዘራም። ለምሳሌ በቆሎ ስንዘራ ፍሬው ትልልቅ (ወንዴ) እና ፍሬው ትንንሽ (ሴቱ) የሆነውን ዘር መርጦን ነው። ሲያፈራም በአንድ እንጨት አራት አምስት ራስ በቆሎ ይሰጣል። ዛሬ ግን ይህንን ባህል ስለተውን ብናመርትም የምናገኘው አነስተኛ ነው። አይበረክትምም።

## ቶስ 66

በኛ በቤንች ባህላዊ እምነት (ካህ) ማንኛውም እህል ወይም ተክል ብቻውን አይዘራም ወይም አይተከልም። በቆሎ ሲዘራ አብሮ አደንጓሬ ወይም ሌላ ነገር ይዘራል። ቅጠላቸው ሰፋፊ የሆኑት እንደ እንሰት (ቆጮ) ያሉት ቅጠላቸው ቀጫጭን ከሆኑት እንደ ከቺ (ስሩ የሚበላ) ጋር ጎን ለጎን አብረው ይተከላሉ። ይህ ካልሆነ የሚዘራው እህል ጥሩ ምርት አይሰጥም፤ በረከትም አይኖረውም ተብሎ ይታመናል። (አባ ማትዮስ ሻሽንቴት)

## ቶስ 67

አንድ እናት ላም እና የወለደቻት ጥጃ ደርሳ ብትወልድ የእናትና የልጇ ወተት ታልቦ የሚጠራቀመው ለየብቻ ነው። ምክንያቱም ይህንን የተደበላለቀ ወተት (የእናትና የልጇ) እንዲጋጣሚ የሚጠጣ/የምትጠጣ ልጅ ሲያድግ አንደበቱ መናገር የማይችል ይሆናል ተብሎ ነው (እውነት የሁለቱ ወተት አይደባለቅም?) አምን በእኛ በቤንች ባህል ተዳባልቆ አይቀመጥም።

## ቶስ 68

ልጆች ስታሳድግ የምታልበውን ትኩስ ወተት እያጠጣሀቸው አታሳድግ። ለምን ብትል ትኩስ ወተት ስለሚያወፍር እነዚያ ላሞች በሚነጥፉበት ጊዜ ያ ልጅ የለመደውን ትኩስ ወተት ያጣና እሳት ዳር ሄዶ ኩርምት ብሎ ይቀመጥና ሆድና ደረቱን ማከክ ይጀምራል።

## ቶስ 69

እፍኝት እባብ መልኳ ያምራል። አይ ይቺ ነገር መልኳ ያምራል። እስኪ ወገቤ ላይ እንደቀበቶ ልሰራት የሚል ሰው በእፍኝቷ ተነድፎ ይሞታል። የሰው ምክርም የማይሰማ ሰው እንደዚሁ ነው። መጨረሻው ክፉ ሞት ነው ይባላል!

## ቶስ 70

አንድ የታወቀ ገበሬ ትልቅ በሬ ነበረው። ይህ በሬ በስራው እየለገመ ስላስቸገረው በሚጠምድበት ጊዜ በሀይል ይገርፈው ነበር። ይህ ሰነፍ በሬም ዱላ ስለበዛበት ሞተ። ከሞተም በኋላ ቆዳው ተገፈፈና ደርቆ ከበሮ ተሰራበት። ከበሬው የተሰራው ከበሮም በየአጋጣሚ ሲመታ ሲመታ መጨረሻ ላይ ተበሳ። ክፉ ሰውም መጨረሻው እንደዚህ በሬ የማያምር ነው ይባላል።

## ቶስ 71

ሚዳቋ አንድ ቀን ዘላ ዘላ ስትሮጥ ሼቤንች ደረሰች። የዛኔ ገበያ ውስጥ የተነጠፈ የሚዳቋ ቆዳ አየችና "እኔ ያለሁት እዛ (ደቡብ ቤንች) ቆዳዬ ከመቼ እዚህ ደረሰ፡ አለች አሉ።

## ቶስ 72

አባትና ልጅ በሀሳብ ከተግባቡ አንድ የሚዳቋ ቆዳ ለሁለቱም ይበቃቸዋል። ካልተስማሙ ግን ትልቅ ነው የሚባለው የበሬ ቆዳ እንኳን አይበቃቸውም።

## ቶስ 73

እድል ይሁን አጋጣሚ አይታወቅም አንዳንዴ ነገሮች በተቃራኒ ሲፈፀሙ ይታያል። (ተመልከት አንድ ታሪክ ልንገርህ።) በሬ መሬት አርሶ፣ አለስልሶ በቆሎ ይዘራል፡ ቡቃያ ሲሆን እንደገና በዛው በሬ ማሳው ይሸለሸላል። (አንድ ቦታ የበዛውን ቡቃያ ለመቀነስ ወይም

እንዳይደራረብ ለማድረግ ነው) ታድያ ምርቱ ደርሶ ወደ ጎተራ ከገባ በኂላ ለልዩ ልዩ ምግብ አይነቶች መስሪያ ይሆናል፡፡ ተመልከት! በቆሎ ይለነቀጥና ተጨምቆ ቂጣ ይጋገራል፡፡ ለበሬ የሚሰጠው (ፋጭ) ገለባ (ሲጨመቅ ወንፊቱ የሚያስቀረው ማለት ነው) ነው፡፡ ሆኖም ከዛ ቂጣ ባለቤቷ ቆርሳ የምትሰጠው ምንም ሳይሰራ ቀኑን ሙሉ ከቤት ጥላ ስር ተኝቶ ለሚውለው ውሻ ነው፡፡ የለፋው ተቀምጦ ያልሰራው ተጠቀመ ይላሉ አባቶቻችን፡፡

## ቶስ 74

ድሮ ነው አሉ ዋንዛ ብዙ ፍሬ ታፈራለች፡፡ እነዚህ የዋንዛ ፍሬዎች ደግሞ በየወደቁበት ይበቅሉና እናታቸውን (ትልቋን) ዋንዛ ወደ ላይ እየተመለከቱ፡-

"እማዬ እንደምንነሽ?" ብለው ይጠይቋታል፡፡

"ደህና ነኝ ልጆቼ" ብላ ስትመልስላቸው

"ደህና ነኝ ስትይ ምን ማለትሽ ነው? አልገባንም" ብለው መልሰው ይጠይቋታል፡፡

"አይ ልጆቼ እናንተን እስካልተውኳችሁ ድረስ እኮ ደህና ነኝ ማለት ነው" ብላ ዋንዛዋ መለሰችላቸው ብለው አባቶቻችን ይነግሩን ነበር፡፡

## ቶስ 75

አፍ ልክ ጥዋት ላይ ጆሮን ትጠራና "ኧረ ለመሆኑ እንዴት ነሽ ደህና ነሽ ወይ?" ብላ ትጠይቃታለች፡፡ ጆሮም "አንቺ በውስጥሽ ደብቀሻት ያለችው (ምላስን ነው) እያለች ምን ደህና እሆናለሁ፡፡ ጠዋት ማታ በጥፊ እጠፈጠፋለሁ!" አለቻት አሉ፡፡ (በምላስ የተነሳ ነው የምደበደበው ማለቷ ነው)

## ቶስ 76

ነብርን በእጅህ አትጠንቀለው፡፡ ከጠነቀልከው ዘሎ ይይዝህና ይበላሀል፡፡ እንዲሁም በማታውቀው ነገር ውስጥ አትግባ፡፡ በማያውቀው ነገር ውስጥ ዘሎ የሚገባ ሰው መጨረሻው ጥሩ አይሆንም፡፡ እንቅፋትም ደጋግሞ የሚመታው በችኮላ የሚራመድን ሰው ነው ይባላል፡፡

## ቶስ 77

አንድን ነገር አርቆ አለማየት ጉዳት ያመጣል አሉ፡፡ ለምሳሌ እኔ እዛ ማዶ የሚታየውን ያንን ጋራ ሄጀ አርሼ በማገኘው ምርት በሬ እገዛለሁ ልበል፡፡ ሚስቴ እንግዲህ

ችኩል ከሆነች "በሬውን ከገዛህ ይታረድና ቆዳውን እኔ ነኝ የምወስደው ትላለች።" ባጠገባችን ህፃናት/ልጆች ካሉ አንዱ ይነሳና አንቺ እማዬ ቆዳውን ከወሰድሽ እኔ ደግሞ በሬው ታርዶ በሚገፈፍበት ጊዜ ቆዳው ላይ ተጣብቆ የሚቀረውን ልፋጩን ገፍፌ እወስዳለሁ" ይላል። ይችው እናት የልጇን ሀሳብ አልተረዳችምና "ተው ልፋጩን ለማስለቀቅ ብለህ በትገፍ ለእኔ የተሰጠኝን ቆዳ ትበሳዋለህ!" ብላ ትኮረኩመዋለች ይላሉ አባቶቻችን።

# አባሪ ሶስት

## ቃል በቃልና አዛማጅ ትርጉም በቤንች ቋንቋ ወደ አማርኛ የተተረጎሙ የቤንች ኤሸሽ ቃላዊ ዝርው ተረኮች

### ኤሸሽ 1

እጅና እግር የሌላት ኩንድሌ የምትባል ልጅ ነበረች። ወንድምየው ለስራ ሄዶ እስኪመለስ ድረስ ጅብ እንዳይበላት በለት በቅል ውስጥ ደብቋት ይሄድ ነበር። ከስራ ውሎ ሲመለስም ያመጣላትን ምግብና የሚጠጣ ነገር ለመስጠት

"ኩንድሌ ቲድን!
እጅ የለሽ ቲድን!
እግር የለሽ ቲድን!
በላሽ ወይ ቲድን!
ጠጣሽ ወይ ቲድን!"

እያለ ወንድሟ በሚጠራት ጊዜ እርሷም ድምፁ የወንድሟ መሆኑን ካረጋገጠች በኋላ፡-

"ጋሽዬ! ቲድን!
ወንድምዬ! ቲድን!
ሊበላኝ መጥቶ ሄደ! ቲድን!
ሊጠጣኝ መጥቶ ሄደ! ቲድን!
እኔ ግን አለሁ! ቲድን!"

በማለት ስትመልስለት ያመጣላትን ምግብ ሰጥቷት ሌላ የሚበላ ነገር ፍለጋ ይሄድ ነበር። በዚህ ሁኔታ ወንድምየው እህቱን በመንከባከብ ላይ እያለ አንድ ቀን ጅብ በወንድምና እህት መሀከል የሚደረግን ንግግር ተደብቆ ሰማና የኩንደሌ ወንድም እንደሄደ ልክ ወንድሟ እንደሚጠራት አስመስሎ፡-

"ኩንድሌ ቲድን!
እጅ የለሽ ቲድን!
እግር የለሽ ቲድን!

በላሽ ወይ ቲድን!

ጠጣሽ ወይ ቲድን!"

እያለ ሲጠራት ድምፁ ጉርናና እና የወንድሟን ስለማይመልስ ፀጥ ብላ ተደበቀች፡፡ ምንም መልስ አልሰጠችም፡፡ የወንድሟን እግር መውጣት እየጠበቀ ኩንድሌ ለማሳሳት ያደረገው ሙከራ ሁሉ አልሳካ አለው፡፡

የኩንድል ወንድም እንደተለመደው የሚበላ ነገር ይዞላት መጣና

"ኩንድሌ ቲድን!

እጅ የለሽ ቲድን!

እግር የለሽ ቲድን!" ብሎ ሲጠራት እሷም፡-

"ወንድምዬ! ቲድን!

እንኳን ደረስክ! ቲድን!

ሊበላኝ ነበር! ቲድን!

ሊጠጣኝ ነበር! ቲድን!

እኔ ግን ዝም አልኩ! ቲድን!" ብላ መለሰችለት፡፡

ኩንድሌን ለመብላት እጅግ የከጀለው ጅብ ባይሳካለትም ተስፋ አልቆረጠም፡፡ ምናልባት ሀሳብ/ዘዴ ላገኝ እችላለሁ ብሎ የድኩላ ቃልቻን ሊያማክር ሄደ፡፡ ድኩላውም፡- "አንተ እኛንስ አሳደህ ትበላን የለም ወይ! ስለምን ብለን ነው ላንተ የምንጠነቁል! እባክህ ጊዜህን ሳታጠፋ ሌላ ጋ ሂድ" ብሎት አሰናበተው፡፡

ጅብም ሌላ ቃልቻ አሰበና፣ የጦጣ ቃልቻን ለመጠየቅ ሄደ የጦጣ ቃልቻም "እኛ ሰው የዘራውን እህል በልተን ስናመልጥ አንተ አይደለህም ወይ እየተደበቅህ አድፍጠህ ስትበላን የነበረው፡፡ ስለዚህ ላንተ አንጠነቁልም" አለው፡፡

ተስፋ ያልቆረጠው ጅብም፡- "እስቲ እድሌን ልሞክር" ብሎ ወደ ጉሬዛ ቃልቻ ጋ ሄደ፡፡ የጉሬዛ ቃልቻም የጅቡን ንግግር አዳመጠና እንዲህ አለው፡-

"አሁን ቶሎ ወደ ቤትህ ሂድና ግቢህን አፅዳ፡፡ እያፀዳህም እንዳለህ ከግቢህ አጥር አንዱ ቅግ ስትደርስ ድቡልቡል ድንጋይ ታገኛለህ፡፡ ያንን ድንጋይ እሳት ውስጥ ከተህ አግለው፡፡ ድንጋዩ ግሎም ቀይ ሲሆን ቶሎ አውጣና በሞራ ጠራርገህ ዋጠው፡፡ የዛኔ ጉሮሮህ ይሰፋል" አለው፡፡ ጅብም የጉሬዛ ቃልቻ በመከረው መሠረት ወደ ቤቱ ተመልሶ ግቢውን ሲያፀዳ ድቡልቡል ድንጋይ አገኘ፡፡ ያንንም ድቡልቡል ድንጋይ አጋለና በሞራ ጠራርጎ

ሲውጠው ጠባብ የነበረው ጉሮሮው ሰፋ! ድምፁን እንደሰው ልጅ በፈለገው መለዋወጥ ቻለ። በዚህ ጉዳይ የተደሰተው ጅብ ወደነ ኩንድሌ ቤት እየሮጠ ሄደ። ድምፁንም እንደሚያቱሽ (ወንድሟ ነው) በማስመሰል፦

"ኩንድሌ ቲድን!

እጅ የለሽ ቲድን!

እግር የለሽ ቲድን!

መጣሁልሽ ቲድን!"

ብሎ ሲጠራት የጅቡ ድምፅ የወንድሟ መሰላትና መልስ ሰጠችው። ጅብም የተደበቀችበትን ቦታ አገኘና አወጣት። አዝሏት ጉዞ ጀመረ።

ጅቦ! እኔ በእዝል አልሄድም። ሲከባይ በሚባል እንሰት ጠቅልለህ ካልተሸከምከኝ አልሄድም አለችው።

ጅብም እንዳዘዘችው ሄዶ ሲያመጣ በቦሲ ቅጠል ከተሸከምከኝ እንጂ በዚህስ አልሄድም አለችው። (እንዲህ የምታደርገው ወንድምየው እስኪመጣለት ድረስ ጊዜ ለማግኘት ነው) ኩንድሌ ያዘዘችውን የእንሰት ዘር ሁሉ ቆራርጦ ስለጨረሰ መጨረሻም የምትለው ጠፋትና ጅቡ አዝሏት መንገዱን ቀጠለ። ተሸክሟት እየተጓዘም ሳለ አንድ ወንዝ አጠገብ ደረሰ። ጂቡም ኩንድሌን እንደተሸከመ ወንዙን ለመሻገር ሲገባ ኩንድሌ አንድ ሐረግ ያዘችና ለመሸከሚያዋ ባዘጋጀው ማቶት ላይ አሯን ሞልታ ተንጠልጥላ ቀረች።

ኩንድል ሀረጉን ይዛ ተንጠልጥላ ብትቀርም ጅብም እርሷን ለመሸከም ይመቸው ዘንድ እንደማቶት አድርጎ ራሱ ላይ ባስቀመጠው እቃ ሙሉ አሯን ሞልታበት ስለነበር ጅቡ የኩንድልን መጥፋት አላወቀም ነበር። ጅቡ ቤቱ ደርሶ እናቱን ጠራና

"እማዬ ነይ ይህን ከጭንቅላቴ ላይ የተሸከምኩትን ነገር ቀስ ብለሽ አውርጅልኝ" አለ። የጅቡ እናትም ለማውረድ ብላ ብድግ ስታደርገው በጭንቅላቱ ላይ ያለው የአር ክምር መሆኑን አወቀች። ወድያውም "ጭንቅላትህ ላይ የተሸከምከው እኮ አር ነው" ምንድነው ብዬ ነው የማወርድልህ ልጄ!" አለችው።

በተፈጠረው ሁኔታ እጅግ የተናደደው ጅብ "ኩንድልን ላገኛት እችላለሁ" ብሎ የመጣበትን አቅጣጫ ተከትሎ መጓዝ መረ። ቅድም ተሻግሮት የመጣውን ወንዝ ለመሻገር ብሎ ገና ወደ ውሃው ሲገበ በወንዙ ውስጥ የኩንድልን ምስል አየ። እሷ ያለችው ሐረጉ ላይ ተንጠልጥላ ከላይ ነው። ጅቡም አላያትም ነበር" በዚህ ሁኔታ የተደሰተው ጅብ "እንኳን

አገኘሁሽ፤ ዛሬ መቼም አንላቀቅም" ብሎ ምስሉን (ጥላዋ መሆኑን አላወቀም) ኩንድልን አገኘሁ ብሎ ውሃውን ሁሉ አጎንብሶ መጠጣት ጀመረ፡፡ ካለመጠን የጠጣው ውሃም በቂጡ በኩል መፍሰስም ጀመረ፡፡

በዚህ ሁኔታ ኩንድሌን ከነነፍሷ እይዛለሁ ብሎ ውሃውን ሲጠጣ የዋለው ጅብ ደከመውና ለማረፍ ብሎ ቀና ሲል ኩንድሌን ሐረጉ ላይ ተንጠልጥላ አያት፡፡

ከዚያም ቀስ ብሎ አወረዳትና ወደ ቤቱ ወስዶ ለእናቱ "እማዬ ይቺያትና አመጣኋት፡፡ አርደን እንበላታለንና ውሃ እሳት ላይ ጣጅ እስከዚያ ዘመዶቻችንን አሰባስቤ ልምጣ" ብሎ ከቤት ወጣ፡፡

የኩንድሌ ወንድም እንደልማዱ ሲሰራ ውሎ ወደ ቤቱ ለእህቱ የሚሆን ምግብ ይዞ ሄደ፡፡ ቤቱ እንደደረሰም ቢጣራ! ቢጣራ የኩንድልን መልስ አጣ፡፡ ሄዶ የምትደበቅበትን ቅል ከፍቶ ቢያይ የለችም፡፡ በድንጋጤ ውስጥ ሆኖ ትንሽ አሰብ አደረገና "ድሮም ቢሆን እህቴን ሊበላ የሚፈልግ ጠላት ጅብ ብቻ ነው" በሎ ወደ ጅብ ቤት ጦሩን እየሰበቀ በፍጥነት ሄደ፡፡ ልክ የጅቡ ቤት እንደደረሰ ዘው ብሎ ሲገባ የጅቡ እናት ኩንድሌን ለመቀቀል የጣዱት ውሃ ሲፍለቀለቅ አየ፡፡ ከምድጃው ጥግም ኩንድል ተቀምጣ አያት፡፡ የዚህን ጊዜ በያዘው ጦር የጅቡን እናት ወጋና ሲወድቁ ኩንድልን ለማረድ በተዘጋጀው ገጀራ ቆራረጠና ስጋቸውን እሚፍለቀለቀው ውሃ ውስጥ ከተተውና ደጃፉ ላይ ቁጭ አለ፡፡ ጅቡም ዘመዶቹን ጠርቶ ወደ ቤቱ ሲመጣ ደጃፍ ላይ ተቀምጦ የነበረው የኩንድሌ ወንድም ጅቡን፡-

"አማቼ! አማቼ! እግሬ ውስጥ እሾህ ገብቶ መቆም አቅቶኛልና እባክዎትን ቢላ ከያዙ ይስጡኝ" አለው፡፡ ጅቡም አማቼ ሲለው እውነት መሰለውና ጩቤውን አውጥቶ ሲሰጠው፣ የኩንድል ወንድም ጅቡን በራሱ ጩቤ ሆዱን ዘርግፎ ይጥለውና እህቱን ይዞ ወደ ቤቱ መጓዝ ይጀምራል፡፡

በጅብ ከመበላት የተረፈችው ኩንድሌን ወንድሟ ተሸክሟት በመጓዝ ላይ እንዳለ ከመንገዳቸው ዳር ገላጣ በሆነ ቦታ ላይ የሀገሩ አዋቂዎች ተሰብስበው ጥሬ ከቺ ሲመገቡ ደረሰ፡፡ በዚህ ድርጊት የተገረመው ወንድሟ ቆም ብሎ አዋቂዎቹን፡-

"ጥሬ ከቺ ይበላል ወይ?" ብሎ ጠየቃቸው፡፡

"ታዲያ! እንዴት ተደርጎ ነው የሚበላ?" ብለው ጠየቁት፡፡

"በስሎ ነው የሚበላ" ብሎ መለሰላቸው፡፡

አዋቂዎቹም "እስቲ! እንዴት በስሎ እንደሚበላ" አሳየን አሉት፡፡ እሱም "ለእህቴ እግርና እጅ የምትሰሩልኝ ከሆነ ቀቅዬ አበላችዋለሁ" አላቸው፡፡

አዋቂዎቹም "ይህማ በጣም ቀላል ነው። ሂድና አንተ ከቺያችንን አብስል፤ እኛ እስከዚያው ለእህትህ እጅና እግር እንሰራላታለን" አሉት።

አዋቂዎቹም በገቡለት ቃል መሠረት ኩንድልን እግርና እጅ አበጅተውላት፤ ጫማ አድርገውላት፣ ቀሚስና ነጠላ እንዲሁም ሻሽ አስረውላት አጠገባቸው ካሉት በርካታ ልጆች መሀከል አስቀመጧት።

የኩንድሌ ወንድምም በታዘዘው መሠረት ከቹውን ቀቅሎ አመጣና አዋቂዎቹ አቅርቦ መብላት ጀመሩ። የተቀቀለውን ከቺ አዋቂዎቹ በልተው እንደጨረሱም፡-

"እህቴስ የታለች" ብሎ ጠየቃቸው።

አዋቂዎቹም "ከእነርሱ (ከተቀመጡት ልጆች) መሀከል እህትህን ለይተህ ውሰድ" አሉት።.እሱም እህቱን ያገኘ መስሎት የሚነካቸው ልጆች ሁሉ ቁጣ ሲያሰሙት አልፎ ሄደና መጨረሻ ላይ የነካት ልጅ የእህቱን ድምፅ አሰማችው። እርሱም "የእኔ እህት ይቺ ናት" አላቸው። እነርሱም "አንተም ከቼውን በደንብ አብስለህ አቀረብክ። እኛም ጣፍጦን በላን። ስለዚህም እኛም እህትህን ይዘህ እንድትሄድ ፈቅደናል" ብለው መረቁት። እሱም እህቱን ይዞ ወደ ቤቱ ሄደ።

አንድ ቀን ወንድሟ በገንዳ ውስጥ ወተት ሞላና ኩንደሌን ጠርቶ እንዲህ አላት "በዚህ ውስጥ ገብተሽ ተጫወቺ እኔ የሆነ ቦታ ደርሼ እመጣለሁ" ብሎ ሄደ። ኩንድል በወተት የተሞላ ገንዳ ውስጥ ተቀምጣ በመጫወት ላይ እንዳለች "ሶቴት የላከው ውሻ ከወንዝ መጥቶ እሳት እንድትሰጠው ጠየቃት። እርሷም እሳት ሳይሆን አይብ አወጣችና ሰጠችው። በልቶ እንደጨረሰም እሳቱን ተቀበላትና ወደ መጣበት ተመለሰ። ቀጥሎም የጫርቴት ውሻ እሳት እንድትሰጠው ጠየቃት። እሷም መጀመሪያ አይብ ቀጥሎም እሳቱን ሰጠችውና ሄደ።

ውሻው እሳቱን እንዳደረሰ ለሶቴት የኩንድልን ውበት ደጋግሞ እየነገረው "እርሷን የማያገቡ ከሆነ ከእርስዎ ጋር መኖር አልፈልግም" አለው። የጫርቴትም እንዲሁ አለው።

ኩንድሌ አንድ ቀን ወንድሟ ከሄደበት ሲመለስ "ወንድሜ ሆይ የእናቴን ጨሌ እያንጠባጠብኩ እሄዳለሁ። አንተም ይህንኑ እየተከታተልክ ፈልገኝ። ጨሌው እመንገዳችን ላይ ያለውን ወንዝ ተሻግሮ ካገኘህ የጫርቴት ልጅን አግብቻለሁ ማለት ነው። ይሁን እንጂ ጨሌው ወንዙን ሳይሻገር ካለቀ የሶቴት ልጅን አግብቻለሁ ማለት ነው።" አለችው።

ወንድምየውም እህቱ በነገረችው መሠረት በየመንገዱ የተጣሉትን የእናቱን ጨሌዎች እየተከተለ ሲጓዝ ጨሌውን ያኘው እመንገዳቸው ላይ እስካለው ወንዝ ዳር ድረስ ብቻ ሆነ፡፡ በዚህን ጊዜ የያዘውን ቦክንቦክ አወጣና እየነፋ ሽረሽረ መጫወት ጀመረ፡፡

የሽሪሾሪውን ድምፅ እንደሰማች ኩንድሌ ሰቴትን (የውሃ ጌታ) "ይህ የምትሰማው ሽሪሾሪ የወንድሜ ነው" አለችው፡፡ ሶቴትም "ወንድምሽ ከሆነ ታዲያ ይግባ?" ብሎ ጠየቃት፡፡ በእርሷ ፍቃድ መሠረትም ጠባቂዎቹን ላከና ወደ ቤቱ አስገባው (ውሃ ውስጥ) የኩንድል ወንድም ወደ አማቹ (ሰርቴት) ቤት ሲገባ የቤቱ ግድግዳ በሙሉ የተሰራው በእባብ ማገር መሆኑን ባየ ጊዜ ደነገጠ፡፡ ሆኖም ከሶቴት ጋር ስለነበረ ድንጋጤው ለብዙ ጊዜ አልቆየም፡፡ እየዋለ እያደረም ኑሮውን ተለማመደ፡፡

አንድ ቀን ሶቴት ኩንድሌን ጠራትና "ይህ ወንድምሽ አሁን አገሩን ለምዷል ለምን አንድረጠውም?" አላት፡፡ ኩንድሌም በሀሳቡ ተስማማችና የቃምጡት ልጅ (ጭራቅ) ዳሩለት፡፡ የኩንድሌ ወንድም ከተዳረችለት ሚስቱ ጋር በመኖር ላይ ሳለ አንድ ቀን በተኛበት አንገቱን ቆረጠችውና ቀቅላ በላችው፡፡ ሆኖም የተቆረጠውን የባሏን አንገት ሳትቀቅለው ከእሳት ዳር ካለው መሶብ ውስጥ አስቀምጣው ነበር፡1 ኩንድሌ "የወንድሜ የኑሮ ሁኔታ እንዴት እንደሆነ ማየት አለብኝ" ብላ ሶቴትን ደጋግማ ስለጠየቀች" ሄደሽ አይተሽው ተመለሽ" ብሎ ፈቀደላትና ወደ ወንድሟ ቤት ሄደች፡፡

ኩንድሌ እወንድሟ ቤት ደረሳ ከሚስቱ ጋር ስትጫወት ቆየች፡፡ ሆኖም ወንድሟ ብቅ አላለም፡፡ የዚህን ጊዜ ሚስቱን

"እኔ ከመጣሁ ብዙ ቆየሁ ወንድሜ ምነው ብቅ አላለ?" ብላ ጠየቀቻት፡፡

"አይ ምናልባት ስራ በዝቶበት ይሆናል" አለቻት፡፡ ኩንድሌም ወንድሟን ለማየት መጀመሪያ ወደ "ጤፉ እርሻ ቦታ ሄደች፡፡ አላገኘችውም፡፡ ቀጥሎ ወደ ገብስ ማሳው ሄደች፡፡ እዛም የለም፡፡ በነገሩ ጥርጣሬ ገባትና ተመልሳ ሚስቱን "ወንድሜ ከሄደበት ምነው ሳይመለስ ቆየ" ብዬ ስጠይቅሽ "ምናልባት የእርሻው ስራ በዝቶበት ነው፡፡" ባልሽኝ መሠረት መጀመሪያ ከጤፍ እርሻ ቦታው፣ ቀጥሎ ደግሞ እገብስ ማሳው ድረስ ሄጄ ሳገኘሁ ሞከርኩ፡፡ ሆኖም እሁለቱም ቦታ የለም፡፡ ብላ ነገረቻት፡፡ ሚስቱም ፈጠን ብላ "ምናልባት እንግዲህ ከብቶችን ሊመለከት ራቅ ወዳለ ቦታ ሄዶ ይሆናል፡፡ ምን ይሆናል ብለሽ ነው? ይመጣል፡፡ ባይሆን እስከዚያው ድረስ ፀጉሬን ቅማል ቅመይልኝ" አለቻት፡፡

ኩንድሌ የወንድሟን ሚስት ፀጉር ቅማል ለመልቀም ብላ የመሀል አናቷን ፀጉር ከፈት ስታደርገው ጥርስ አገኘች፡፡ ይህንኑ ጥርስም ትኩር ብላ ባየችው ጊዜ የወንድሟ

ጥርስ መሆኑን አወቀች፡፡ የዚህን ጊዜ ሀዘን ተሰማት ሳታውቀውም እንባዋ ፈሰሰ፡፡ የዚህን የወንድሟ ሚስት "ይህ ጀርባዬ ላይ የሚንጠባጠበው ምንድነው?" አለቻት ኩንድሌም "አይ የእናታችን እንባ ይሆናል" አለቻት፡፡ ጥቂት ቆይቶም የኩንድሌ እንባ እንደገና መውረድ ጀመረ፡፡ የዚህን ጊዜ ሴትየዋ እጅ ላይ ጠብ ጠብ የሚለው ምንድነው?" አለቻት፡፡ ኩንድሌ ፈጠን ብላ "የአባታችን እንባ ነው" አለቻት፡፡ ኩንድሌ የወንድሟን ሚስት ፀጉር ቅማል መልቀሙ ስላደከማት "ወንድሜ በልቶት ያስተረፈው ምግብ የለም? እራበኝ" ብላ ሚስቱን ጠየቀቻት፡፡ እርሷም "እስቲ ሂጅና ጓዳ ውስጥ ፈልጊ" አለቻት፡፡ ኩንድሌ የሚበላ ነገር ይገኛል ብላ ጓዳ ውስጥ ያገኘችውን መሶብ ስትከፍተው የወንድሟን የተቆረጠ ጭንቅላት ከነፀጉሩ (ሳይላጭ) አገኘችው፡፡ (ድንጋጤ ወረራት) ወድያው የወንድሟን የተቆረጠ ጭንቅላት ብድግ አድርጋ ያዘችና ወደ ቤቷ ሮጠች፡፡ ቤቷም እንደደረሰች ለባሏ ለሶቴት እያለቀሰች አስረከበችው፡፡ ሶቴትም ኩንድሌን ካረጋጋት በኋላ የሰጠችውን የወንድሟን ጭንቅላት ወሰደና በአንድ ጎድጓዳ እቃ ውስጥ አስቀመጠው፡፡ ቀጥሎም ወተትና ማር አፈሰሰባት (በእቃው ሞላባት)፡፡ ጥቂት ቆይቶም ጭንቅላቱ ቀስ በቀስ ወደ ትልነት ተለወጠ፡፡ ቀጥሎም ቀስ በቀስ ሙሉ ሰው ሆነ (ዳነ)፡፡ ይህ ሁኔታ እንዳበቃም ሶቴት ወደ ሚስቱ (ኩንድሌ) ቀረብ አለና "ይኸውልሽ ፈጣሪያችን ወንድምሽን አድኖት ከሞተበት ወደ ሰውነት ለውጦታል" አላት፡፡ እርሷም በውንድሟ ወደ ሰውነት መመለስ እጅግ ተደስታ እያለች! "እንግዲህ ተነሽና ወንድምሽን ወደ ቤቱ ውሰጅው!" አላት፡፡ ኩንድሌ ወንድሟን አስከትላ ቤቱ ደረሰች፡፡ ቀጥሎም "ይኸውልህና ያንተ ቤት! አንተንም ገድላ የበላችህ ሚስትህ ይቺ ናት" አለችው እርሱም አንገቷን ቀልቆ ሚስቱን ገደላት፡፡ ሚስቱም ወደ ትልነት ተለወጠች፡፡ የኩንድሌ ወንድምም ሌላ ሚስት አግብቶ በሰላም መኖር ጀመረ ይባላል፡፡

## ኤሽሽ 2

አንድ የራበው ነብር በመንገድ ሲሄድ አንድ መንገደኛ ሰው ጋር ይገናኛል፡፡ በዚህን ጊዜ መንገደኛው ለህይወቱ ሲል የነብሩን ጭራ ቀጽ አድርጎ ይይዛል አሉ፡፡ ጭራውን የተያዘው ነብርም ዞሮ መንገደኛውን ለመንከስ ይቸግረዋል፡፡ ሁለቱም ህይወታቸውን ለማትረፍ ብዙ ይታገላሉ፡፡ በኋላ ላይ አንድ አልፎ ሂያጅ መንገደኛ እንደ አጋጣሚ በቦታው ይደርሳል፡፡ በዚህን ጊዜ ከነብሩ ጋር ብዙ ሲታገል የዋለው ሰውዬ "እባክህን! በወንድ ልጅ አምላክ ናና እርዳኝ!" ብሎ ለመነው፡፡ በዚህን ጊዜ የተለመነው ሰውዬ "አንተ ሰው ሞኝ ነህ ወይ?" ብሎት በአጠገቡ አልፎት ሄደ፡፡ በዚህ ሁኔታ ሰውየውም የነብሩን ጭራ ላለመልቀቅ፣

ነብሩን ከሰውየው ለማምለጥ ሲታገሉ ውለው አደሩ። በነጋታው ጠዋት አንድ እንጨት ቆራጭ ወደ ጫካ እንጨት ፍለጋ በመሄድ ላይ ሳለ እንደ አጋጣሚ ነብሩና ሰውየው ተያይዘው እወደቁበት ቦታ ይደርሳል። በዚህን ጊዜ የነብሩን ጭራ ይዞ ሲታገል ውሎ ያደረሰው ሰውዬ "በወንድ ልጅ አምላክ! እንደው ባትመታው እንኳን ናና እስኪ ቦታዬ ላይ ሆነህ ጭራውን ያዝልኝና ዱላ አምጥቼ ጭንቅላቱን መትቼ ልግደለውና አብረን እንሂድ" ብሎ ለመነው። እንጨት ቆራጩም እሽ ብሎ የነብሩን ጅራት እንደያዘ እኔ ይገፍው አንግቻለሁኝ አንተ ደግሞ ይዘህ ዋልበት" ብሎት ሄደ ይላሉ።

ኤሽሽ 3

አንድ መንገደኛ እየተጓዘ ሳለ የሞላ ትልቅ ወንዝ ጋ ደረሰ። እወንዙ ዳርም በውሃው ሙላት የተነሳ መሻግር አቅቶት የነበረ እባብን አየ። ወዲያውኑም እባቡ ሰውየውን

"እባክህን በፈጠረህ ጌታ ይህንን ወንዝ አሻግረኝ" ብሎ ለመነው መንገደኛው፣ ፈጣሪውን ስለሚያምን ራርቶ

"አንተ እባብ/አውሬ ነህ፣ እንዴት አድርጌ ይገፍ ነው የማሻግርህ?" ብሎ ጠየቀው። እባቡም "ችግር የለም! እኔም የእግዚአብሄር ፍጡር ስለሆንኩኝ ጎንበስ በልና አንገትህ ላይ ተጠምጥሜ ወንዙን ካሻገርከኝ በኋላ እወርዳለሁ" አለው መንገደኛው ሰውዬም እሽ ብሎ አንገቱን ዝቅ ሲያደርግ እባቡ ተጠመጠመበትና የሞላውን ወንዝ አሻገረው። ውሃውን እንዳሻገረውም እባቡ መንገደኛውም "እኔ እንግዲህ አልወርድም! የምወርድበትም ምክንያት የለም የፈለገው ይምጣ!" አለው። መንገደኛውን "እረ በለመንከው ፈጣሪህ ውረድልኝ" ብሎ ቢለምነው እንቢ አለ። ሁኔታው በዚህ እንደቀጠለ "እንግዲህ አልወርድም ካልክ ወደ ዳኛ ጋ እንሂድ" አለውና ወደ ቀበሮ ጋ ተያይዘው ሄዱ። ቀበሮም "ምንድነው ጉዳያችሁ" ብሎ ጠየቀ። መንገደኛው ሰውዬ "እኔ መንገዴን እየተጓዝኩ ሳለሁ አንድ ትልቅ ወንዝ ጋ ደረስኩ። ውሃው ሞልቶ ነበርና ይህ እባብ "እንዳሻግረው በፈጣሪ ስም ለመነኝ፤ እኔም ጎንበስ አልኩለትና በአንገቴ ላይ ተጠመጠመ። ወንዙን ካሻገርኩት በኋላ አልወርድም አለኝ" አቤቱታዬ ለዚህ ነው።

ቀበሮም "አቶ እባብ ከሰውዬው አንገት ላይ ውረድና በግራ በኩል ቁም፣ አንተ ሰውዬውም በቀኝ በኩል ቁምና ዳኝነቱን ልንገራችሁ" አለ።

እባብም እሽ ብሎ ወረደ መሬት ከመንካቱ ቀበሮ መንገደኛውን "አንተ ሰውዬ ብትርህ በጅህ፤ ልብህ በውስጥህ/በደረትህ ስር ነው አለ!" ብላ ፍርድ ሰጠችው። ሰውዬም እባቡን

በያዘው ዱላ እናቱን ቀጥቅጦ ገደለው። ከመሄዱ በፊትም የበግ ግልገል እንደሚይመጣለት ለቀበሮ ቃል ገባና ቀጠሮ ተቀብሎ ተለያዩ። ቃል ገብቶ በሄደው መሠረት በቀነ ቀጠሮው እቦታው ላይ ውሻ ቢጆንያ ተሸክሞ ቀበሮን እንዲቀበለው ጠራው። ቀበሮም ጥሪውን ሰምቶ እንዲመጣ "ይኸውና በቃሌ መሠረት አምጥቻለሁና ና ተቀበለኝ" አለው። ቀበሮም "ሰውዬው በል እየትጎተተ በእግሩ ይመጣል እንጂ ድሮ ነው ዛሬ በጆንያ ሰው ተሸክሞ የሚያመጣው" አለው። ሰውዬውም የጆንያውን አፍ ፈትቶ ውሻውን ለቀቀውና "ያዘው" ሲል ቀበሮ "አይ የሰው ልጅ ላንተስ ሞት ያንስሃል" አለው ብሎ ሮጠ ይባባል።

## ኬዝ 4

አንድ ጊዜ ነው አሉ። ጦጣ ከሌሎች እንስሳት ሁሉ ተለይታ እየሰረቀች አስቸገረች። ይህንን የስርቆት ድርጊት የሚፈፅመው ማን እንደሆነ ለመለየት ተብሎ ሁሉም እንስሳ ሲፈተሽ በስርቆት የተሰማሩ እንስሳት ሲያዙ እርሷ ግን ለማዳ (አመለኛ) በመሆኗ በቀላሉ ለመያዝ አልተቻለችም።

ይህንን ጉዳይ የሰማው አንድ አዋቂ፡- ማር በስልቻ አድርጎ አንጠለጠለና "እዚህ ላይ ቀድሞ በመውጣት የሚወስደው ማነው?" ብሎ እንስሳትን ጠየቀችው። የዚህን ጊዜ የስርቆት ልምምድ ያላት ጦጣ ቀደም ብላ በመውጣት ያንን ማር ለመውሰድ ቸኩላ በመውጣቷ "ከዚህ በፊትም የጠፉትን እቃዎች በሙሉ የሰረቀች እርሷ ናት" ተባለ። ወዲያውኑም በዙሪያው ከበው ሲመለከቱ የነበሩት ሰዎች ጦጣን ይዘው መንገድ ዳር በማሰር ደብድበው ለማግደል ፈለጉና ዱላ ቆርጠው ለማምጣት ወደ ጫካ ሄዱ።

ሰዎቹ ዱላ ለመቁረጥ እንደሄዱ፡- አንድ እጅግ በጣም አድርጎ የራበው ጅብ ምግብ ባገኝ ብሎ ሲፈልግ ነበርና እመንገድ ዳር ከታሰረችው ጦጣ ጋር ባጋጣሚ ተገናኙ።

ጅቡም "አንቺ ጦጢት ምንድነው የምትሰሪው?" ብሎ ሲጠይቃት፤

ጦጢትም "የእኔ እናትና አባት መሞታቸውን ታውቃለህ፤ ዛሬ የተዝካራቸው ቀን ነበር፤ ዘመዶቼ ምግብ አዘጋጅተው አመጡና ብይ አሉኝ። እኔም አልበላም አልኳቸው። በዚህ የተነሳ ተናደዱና አሰሩኝ" አለችው።

ጅቡም በጦጣዋ መልስ ተደስቶ "ታዲያ ምናለ! እኔ ባንቺ ቦታ ታስሬ ልቀይርሽ፤ አንቺም ሂጅና ያ እንቢ አልበላም ያልሽውን የቱዝካር ምግብ ታመጭልኛለሽ ወይ?" አላት።

ጦጣም "እሺ!" አለችው። ጅቡም ወድያውኑ የታሰረችበትን ገመድ ፈታ። ቀጥሎም ጦጣዋ ልክ እርሷን ሰዎቹ አስረዋት እንደነበረው አድርጋ በቦታዋ አሰረችውና አመለጠች።

ጦጣዋን ለመግደል ዱላ ቆረጣ ወደ ጫካ ሄደው የነበሩት ሰዎች ዱላቸውን ይዘው ሲመለሱ ጦጣን ባሰሩበት ቦታ ላይ ጅብን አገኙት። በዚህን ጊዜ በአጋጣሚው የተገረሙት ሰዎች "እንዲያውም ከጦጣ የበለጠውን አደገኛ አውሬ አገኘን" በማለት ደብድበው ገደሉት ይባላል።

## ኤሸሸ 5

አንድ ሩቅ ሀገር እየተመላለሰ የሚነግድ ነጋዴ ነበር። በተለይም የሚታወቀው በበርበሬ ነጋዴነቱ ነው። በዚህ ስራው ላይ ብዙ ጊዜ አሳልፏል። ይህ ነጋዴ ከየቦታው የሚገዛውን በርበሬ ወደ መሸጫ ቦታው የሚያመጣው በአህያ እየጫነ ነው።

አንድ ቀን ይህ የበርበሬ ነጋዴ "ኩሪ" የተባለች አህያውን እንደተለመደው የገዛውን በርበሬ ጭኖ ወደ ቤቱ በመመለስ ላይ እያለ አህያው በጣም ደከመችበት። "ቢደበድባት! ቢደበድባት!" አልፈጥን አለችው። ይባስ ብላ ቀጥ ብላ ቆመች። ቀኑ ደግሞ እየመሸበት መጣ። በአህያዋ ሁኔታ በጣም የተናደደው ነጋዴ ቀስ ብሎ አህያዋ ከተጫነችው በርበሬ የተወሰኑ ዛላዎች አወጣና የአህያውን ቂጥ (ፊንጢጣ) ቀባው። የዚህን ጊዜ ደክማ የነበረችው አህያ በፍጥነት መራመድ ጀመረች። ባለቤቷንም ጥላ ሄደች ከፍጥነቷ የተነሳም ነጋዴው ሊደርስባት አልቻለም። እንዲያውም እየደከመው ሄደ። ከርቀት ያለችውን አህያውን "ኔሽ! ኔሽ! ..." እያለ ቢጠራትም አልቆም ብላ ጉዞዋን ቀጠለች። የዚህን ጊዜ ነጋዴው "አህያዋ ከድካሟ ተላቃ እንዲህ በፍጥነት መጓዝ የጀመረችው በርበሬው ምን ቢያደርግላት ነው አለና አህያዋን ለመቀባት አውጥቶ የተረፈውን በርበሬ ቂጡን መቀባት ጀመረ። ወዲያውም የተቀባው በርበሬ እንደ እሳት ስለለበለበው እንደ አህያዋ በሮ ጠፋ ይባላል።

## ኤሸሸ 6

አራት ቅንድብ የነበራት አንዲት ሴት ልጅ ነበረች። አባቷን በውሃ ገንዳ ወተት ሙላልኝና እዛ ውስጥ ገብቼ እየዋኘሁ ልጫወት አለችው። አባትየውም በውሃው ገንዳ ወተት ሞላላትና እዛ ውስጥ ገብታ ስትጫወት የመብረቅ ልጅ ከብቶቹን ሊያግድ ሽረሾረ እየነፋ ሲሄድ ሲሄድ አያትና፡-

"አዲኬ! አዲኬ!
በጠጅና በወተት የምትጫወቺ!
የት አግኝቼ ባገባሁሽ

ሽሪሾሪ! ሽሪሾሪ!"

እያለ ቦክንቦኩን እየነፋ ሲሄድ እሷም የጫርቱት ልጅ ሽሪሾሪ መልዕክት ለእርሷ መሆኑ ገባትና

ጋጋ! አንተ የመብረቁ ልጅ
ተገኝተህ ነው ወይ
ምን ችግር አለ!
ቶሎ ናልኝ!

ብላ መልስ ሰጠችው፡፡ የዚህን ጊዜ ፈጥኖ ይመጣና ለቀም አድርጎ ያዛት፡፡ በሀፍረት እንደመግደርደር በማለት የጀመሩት ልፊያ (ትግል) እቤት ውስጥ ያለን እቃ ሰባብራ ጨረሰችው፡፡ በኋላም እናትና አባቷ ከስራ መጥተው "የቤቱን እቃ በሙሉ ሰባብሮ የጨረሰው ምንድነው?" ብለው ሲጠይቋት እኔ "ዲኬ ዶኪ እያልኩ ገንዳየ ውስጥ ስጫወት ነበር እንጂ መች ቤቱን ጠብቂ ብላችሁኝ ሄዳችሁ" ብላ መለሰች፡፡ በተፈጠረው ሁኔታ አዝነው ልጃቸውን መልሶ ሳይሰጧት ሄዱ፡፡ ቀኑም መሸ ሁሉም ተኛ፡፡ ጠዋት ተነስተውም የልጅቷ እናትና አባት ወደ ተለመደው ስራቸው ሄዱ፡፡ የመብረቁ ልጅም ረፋዱ ላይ፡-

አዲኬ አዲኬ!
በማር፣ በወተት የምትጫወች
የት አግኝቼ ባገባሁሽ
የት ላግኝሽ

እያለ ሽሪሾሪውን እየተጫወተ መጣ፡፡ እርሷም ወዲያውኑ "ጋጋ! የመብረቅ ልጅ ሆይ ምንም አትፍራ እዚህ ነው ያለሁት ና አለችው፡፡" ልክ እንደ ትናንቱ ወደ እርሷ ሄደና ሊይዛት ሲል በተፈጠረው ግብግብ በአባቷ ጓሮ የነበረው ቆጮ ተሰባብሮ አለቀ፡፡

የልጅቷ አባት ከስራው ተመልሶ ትንሽ አረፈና ጓሮውን ለማየት ሲሄድ ቆጮ በሙሉ ተሰባብሮ አልቋል፡፡ በዚህም "ትናንትና የቤቱ እቃ ተሳባብሮ አለቀ፤ ዛሬ ደግሞ የጓሮዬን ቆጮ እንዲህ አድርጎ ሰብሮ የጨረሰው ማነው?" አለ፡፡

ልጅቷም ፈጠን ብላ "እኔ ዲኬ ዲኬ" እያልኩ በማርና በወተት እየተጫወትኩ ነበር እንጂ "የጓሮውን ቆጮ ጠባቂ አይደለውም" ብላ መለሰች፡፡ በሁኔታው የተበሳጨው አባቷ ይህንን መሰል ድርጊት በቤቱና በግቢው ላይ የሚፈፀመውን ሰው ለመከታተል አሰበ፡፡

እንደተለመደው "ወደ ስራ ሄጃለሁ ብሎ ተደብቆ መከታተል ጀመረ።" ረፋዱ ላይ የጫርቴት ልጅ እንደተለመደው ሽሪሽሪውን እየነፋ!

"አዲኬ! አዲኬ!
በማር፣ በወተት የምትጫወች
አንቺ ውብ ልጅ
የት ነው የማገኝሽ!" እያለ በመጫወት ሽሪሽሪውን ነፋ።

አዲኬም የሽሪሽሪው ድምፅ የእርሱ መሆኑን አወቀችና፣
"ጋጋ! ጋጋ!
አንተ የጫርቴት ልጅ፣
አንተ የሜርቴት ልጅ
እኔ እዚህ አለሁልህ!
ናልኝ! ናልኝ አለሁልህ!" ብላ መለሰችላት።

የመብረቁ ልጅም ወደ እርሷ ሄደ። ቀጥሎም እንደተለመደው ከልጅቷ ጋር በመላፋት ላይ እያለ ተደብቆ ሲከታተል የነበረው የልጅቷ አባት በያዘው ጦር ውርውሮ ወጋውና ሞተ። የልጅቷ አባት የልጁን ሬሳ አነሳውና ወስዶ በቤቱ የጓሮ በር በኩል በሚገኘው የከብቶች እበት ማውጫ ውስጥ ቆፍሮ ቀበረው።

ጫርቴት (የመብረቅ ጌታ) ከብት ሊያግድ ከቤት የወጣው ልጁ እንደወጣ ሳይመለስ መቅረቱ አሳሰበውና ሊፈልገው ወደ መሬት ወረደ።

"ጉቤ! ባቤ! ከብቶች አግደህ!
ውለህ የምትመለሰው ልጄ!
ዛሬ የት ቀረህ!
የእኔን ልጅ ደፍሮ ሚወስድ ማነው?
ጉቤ ባቤ! ጉቤ ባቤ!"

እያለ በየመንደሩ እየዞረ ልጁን ይፈልግ ጀመር። እንዳጋጣሚ ጫርቴት በወተት የተሞላ ገንዳ ሆና የምትጫወትን ልጃገረድ ልጅ ተመልክቶ ጠጋ አለና፦

"በማርና በወተት ያደግሽ!
በወተት ገንዳ የምትጫወቺ!

•

አንቺ ቆንጆ ልጃገረድ!

የእኔን ልጅ አላየሽም ወይ!" ብሎ ጠየቃት፡፡

እርሷም ለጫርቴት "ያንተን ልጅ እንድጠብቅልህ አደራ ሰጥተኸኛል ወይ?" ብላ መለሰችለት፡፡ በመልሷ የተናደደው ጫርቴት በእጆቿ በያዘው መብረቁ ሊመታት ሲል፡- "ልጅህ ጠልፎ ሊወስደኝ ብሎ ሲታገለኝ የእኔ አባት ድንገት ደረሰና በጦር ወግቶት ገደለው፡፡ በኋላም እዚያ (በእጆቿ እየጠቆመች) እበት መውጫው ስር ቆፍሮ ቀብሮታል" ብላ ነገረችው፡፡

የዚህን ጊዜ ጫርቴት ልጁ የተቀበረበትን ቦታ አራት ጊዜ በመብረቅ ሲመታው ሞቶ የተቀበረው ልጁ ተነሳ፡፡ አባቱም ልጁን ይዞ ወደ ሰማይ ወጣ፡፡ እዛም ደርሶ እያለ የልጅቷ አባት አስራ ሁለት ከብቶች ተቀብሎ ልጅቷን ዳራት፡፡ በሰርጉ ቀንም ሙሽራና ሙሽሪቱ ከልጅቷ አባት ቤት ተሰናበተው እንደወጡ ጫርቴት የልጁን አጥንት ከላይ ከሰማይ ወደ መሬት ሲወረውር የልጅቷ መሀል አናት (ጭንቅላት) ላይ አረፈና ልጅቷ ሞተች፡፡

በሙሽሪይቱ ድንገተኛ ሞት ሙሽራውና የልጅቷ አባት አምርረው አለቀሱ፡፡ በዚህን ጊዜ ሚጀን ሲያፈቅራት የነበረውና ለእርሷ ብሎ በአባቷ የተገደለው የጫርቴት ልጅ መሀል መንገድ ላይ ቆሞ፡-

"አንተ የአዲኬ አባት!

ጥጋበኛ!

ያንተ ልጅም ጥጋበኛ!

ምን ችግር አለባችሁ!" ብሎ ሲጠይቅ

አንተ የሰው ልጅ እኔ ልጀ ሞታብኝ በሀዘን ላይ ነኝ በሀዘኗ ተሰቃይቼ እያለቀሱ እያየህ ለምን እንዲህ ክፉ ቃል ትናገረኛለህ" አለው፡፡

ልጁም "እኔኮ አንተ ወግተህ፣ ገድለህ፣ የከብት እበት መውረጃ ቆፍረህ የቀበርከኝ ነኝ" አለው፡፡ በዚህም በልጁ ሞት ክፉኛ ያዘነው አባት፣ እናትና ሌሎችም ዘመዶቻቸውን ክፉ አስደነገጠ አሉ፡፡

## ኤሸሽ 7

ድሮ ጊዜ ነው አሉ አንዴ ውሻ ከበሬ ኋላ ቁሞ ሳለ ድንገት የበሬ ቆለጥ (ፍሬዎች) ተንጠልጥሎ ታያለች፡፡ በሬው በተንቀሳቀሰ ቁጥር ቆለጡ ከግራ ወደ ቀኝ ሲንቀሳቀስ "ወድቆልኝ እበላለሁ" እያለች ቀኑን ሙሉ ስትከተለው ትውላለች፡፡ የበሬው ቆለጥም

የሚበጠስ አይደለምና አልወደቀም። በሬው ቀኑን ሙሉ ሳር ሲግጥ እሷም አብራው ውላ ትመጣለች። ይቺው ውሻ ማታ ላይ በሬን ቀኑን ሙሉ ሲበላ የዋለውን ሳር በሚያመነዠግበት ጊዜ ምናልባት ያ ቀኑን ሙሉ ይወድቃል ብላ የጠበቀች ቆለጡ በአፉ ይወጣል ብላ በአፉ በኩል ብትጠብቅ አይወጣም። በኋላ ነገሩ ገርሟት "አንተ በሬ ሆይ ከኋላህ ሆኜ ብጠብቅ ብጠብቅ ቆለጥህ ተበጥሶ አይወድቅም፤ ስታመነዥግ ምናልባት ባፍህ ይወጣል ብዬ ብጠብቅ አልወጣም! ኧረ ነገሩ እንዴት ነው" ብላ ጠየቀችው። የዚህን ጊዜ በሬው "እንዴት ያልለፋሽበትን የሌላውን ነገር አገኛለሁ ብለሽ ትጠብቂያለሽ" (የሌላውን ነገር/ያልለፋበትን ነገር አገኛለሁ ብሎ መጠበቅ) ጥሩ አይደለም" ብሎ አላት ይባላል።

## ኤሽሽ 8

አንድ ነብር ጎሽ አድኖ በልቶ ጠግቦ ሲሄድ ድኩላን እንዳጋጣሚ እመንገዱ ላይ አገኛት አለ። ነብሩ ድኩላዋን እንዳገኛት እንዳይበላት በጣም ጠግቧል፤ እንዳይተዋትም ታመልጠኛለች ብሎ አሰበና ዱኩላን ጠርቶ እንዲህ አላት፡-

"ከእንግዲህ ወዲህ የምንፈራራበት ነገር የለም። አብረን መኖር አለብን። ከእኔና ካንቺ መሀከል መጥፎ የሚሰራ ካለ ክፋቱ ለልጅ ልጁ ይድረስ" በማለት ይራገምና አግባብቷት እስኪርበው ድረስ አቆይቶ ሊበላት አሰበ። በዚህ ሁኔታ አብረው እንደቆዩ አንድ ቀን ይርበውና ዱኩላዋን ይዞ ሊበላት ሲል እርሷም ህይወቷን ለማዳን ስትንፈራፈር ቀንዷ ሄዶ የነብሩን አንጀት ዘረገፈው። የነብሩ አንጀት ተዘርግፎ እንደወጣ ድኩላዋ አምልጣ ሮጠች ነብሩም እያዘገመ ደረሰባት። ወዲያውም።

"አንቺ እና እኔ የተማማልነው እኮ ጥፋታችን በእኛ ላይ ሳይሆን በልጅ ልጆቻችን ላይ እንዲደርስ ነበር። እንጂ አንቺ በእኔ ላይ በደል ብታደርሽ ባንቺ ላይ እንዲደርስ ወይም እኔ ብበድልሽ ብድሩ በእኔ እንዲደርስ አልነበረም" ሲላት ድኩላዋም መልሳ "እኔ ምን አውቅልሀለው። የተማማልነውም እንዳልከው ነበር። ምናልባት አያቶቻችን የተፈጋገሙት በእኛ ላይ ደርሶ አንተ ላይ ተፈፀሞ ይሆናል ብላ ተናገረችና ለማምለጥ ስትሮጥ ነብሩ እሷን ለመያዝ በሀይል ሲዘል አንጀቱ ሁሉ ተዘርግፎ ወጣና ሞተ ይባላል።

## ኤሽሽ 9

ባልና ሚስት ነበሩ። አንድ ጊዜ ገበያ ሂዱና ፍየል ገዝተው መጡ። ቤት እንደደረሱ ሰውየው ፍየሉን አሰረና ለስራ ከቤቱ ወጣ። ይህቺ ፍየል የመናገር ችሎታ የነበራት ነበረች።

ልክ የቤቱ ባለቤት ከቤት እንደወጣ የእሱን ሚስት የለመዳት (የሚያማግጣት) ጎረቤቱ መጣና ከሴትዬዋ ጋር ተገኘ። ይህንን ሁሉ ድርጊት ስትመለከት የነበረችው ፍየል "ሚያአ! ሚያአ!" እያለች ጮኸች። ያም ሰውዬ "ምን አይነት ፍየል ነች!" እያለ ፈጥኖ ከሴትዬዋ ተለየና ሄደ። የቤቱ ባለቤት ከሄደበት ሲመለስ አየችውና ፍየሊቷ "ሚያአ! ሚያአ!" እያለች በተደጋጋሚ ጮኸች። ባለቤቷም በሁኔታዋ ተናዶ ከመሬት ድንጋይ አነሳና ዝም እንድትል ብሎ ሆዷ ላይ መታትና ጥሏት ሊሄድ ሲል "ቆይ የምነግርህ ነገር አለ!" አለችው። "ዛሬ ደግሞ አፍ አወጣች ይቺ ፍየል!" አለና በድጋሚ ድንጋይ ከመሬት አንስቶ መታት!" ፍየሏ በድጋሚ "ዛሬ የምነግርህ ነገር አለ!" አለችው። ባለቤቷም "ይቺ ፍየል ሰይጣን ይዟታል" አለና ወደ ጓሮ አዞረና አስሯት ሄደ። የእርሱን እግር መውጣት ተከትሎ ያ ሴትዬዋን እያማገጠ ያለው የጎረቤት ሰውዬ ሲመጣ ፍየሊቷ አየችና "ሚያእ! ሚያእ!" እያለች ጮኸች። አሁንም ለአፍታ ያህል ቆየችና "ሚያእ!" እያለች ጮኸች። የዚህን ጊዜ ሰውየው "ይቺ ፍየል ያየችው ነገር አለ እንዴ?" ብሎ ሴትዬዋን ጠየቃት። በዚህን ጊዜ ሴትዬዋ "የዚች ፍየል ነገር አላማረኝምና ወደ እኔ አትጠጋ!" አለች። እርሱም በፍየሏ ሁኔታ ተደናግጦ ሄደ።

አንድ ቀን የፍየሏ ባለቤትን ጎረቤቱ (ጎባን) ሰውዬ "ይቺ ፍየል እየጮኸች አስቸገራለች፤ ለምን ቅርጫ አርደን አንበላትም?" አለው። ባለቤቷም "እኔማ ይቺን ፍየል አልበላትም ከፈለክ አንተ ውሰድና አርደህ ብላት!" አለው። የፍየሏ ባለቤትን ምላሽ እንደሰማም ሰውየው ውድያው ፍየሏን ወስዶ አርዶ በላት። ሆኖም ፍየሏ ከታረደች በኂላም በሰውዬው ሆድ ውስጥ "ሚያእ! ሚያእ!" እያለች መጮዋን ቀጠለች።

በሁኔታው ግራ የተጋባው ሰውዬ መጀመሪያ ላይ ሴትዬዋን ለማባበል ስሄድ "ሚያአ!" እያለች ያስቸገረችኝ ፍየል አርጄ ከበላኃት በኂላም አሁን "ሚያአ!" እያለች ሆዴ ውስጥ ጩኸቷ አስቸገረኝ። ምን ይሻለኛል ብሎ ተጨነቀና ወደ አዋቂ (ጠንቋይ) ቤት ሄደ። አዋቂ (ጠንቋዮ) ቤት እንደደረሰም የደረሰበትን ሁሉ ገልፃ አስረዳው።

ጠንቋዮ (አዋቂውም) "አይ ይቺ ሆድ ውስጥ ገብታ የምትጮኸው ፍየል ሆድህ ተቀድዶ ካልወጣች በስተቀር ጥሩ አይደለም፤ የሄድክበት ተከትላህ እየጮኸች ምስጢርህን ታወጣብሃለች" አለው። ሰውዬውም አይ "ሆዴ ገብታ ሚያእ!" እያለች መጮህዋ አንስዎ ምስጢሬን ተናግራ ከምታዋርደኝ ሆዴ ተቀዶ ወጥታ ልገላግል አለና ሆዱን ሲቀደው ጊዜ ተተርትሮ ሞተ። ፍየሊም "ሚእ! ሚእ! ... እያለች ወጣች ይባላል።

## ኤሽሽ 10

ውሻና አህያ አንድ ዘመን ጓደኞሞች ስለነበሩ በጋራ አንዲት ላም ገዙ። ይቺን የጋራ ንብረት አብረው በጋራ ይጠብቋት ነበር። ሆኖም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ላሚቷን ውሻ እንዲጠብቃት ሆነ። ይሁን እንጂ ውሻው ይቺን የጋራ ላም አንድ ቀን ሲርበው ጊዜ በላት። አህያም "ጓደኛዬ ወሻ ሆይ በጋራ የገዛናት ላም የት ገባች" ብሎ ጠየቀው።

ውሻውም በንዴት፡- "እንዴት እንደዚህ አይነት ጥያቄ ትጠይቀኛለህ? እኔ አላየሁም" ብሎ መለሰለት።

አህያም "የዚህ አይነት መልስ እንዴት ትሰጠኛለህ? ላሚቷን የበላሀት አንተ ነህ" አለው።

በውሻና በአህያው መሀከል የተፈጠረው ግጭት ተባባሰ። የዚህን ጊዜ ውሻው "በል ጓደኛየ ስልህ ካላመንከኝ እውነተኛ ዳኛ ይፍረደን" ስለዚህም ትልቅ ረግረግ ያለበት ቦታ እንሂድ ተባባሉና ረግረጋማ ቦታ ፍለጋ ሄዱ።

እረግረጋማው ቦታም እንደደረሱ፣ ውሻው ቀደም ብሎ በል እንግዲህ "እውነት እኔ ላሚቷን በልቼ ከሆነ ይህንን ረግረጋማ ቦታ ሳቋርጥ ስጥሜ ልሙት" አለና ወደ ረገረጉ ዘሎ ገባ። ክብድቱ ቀላል ስለነበር ተሻገረ። የዚህን ጊዜ አህያ "እውነተኛው እኔ እንጂ አንተ አይደለህም!" አለና እንደ ውሻው ረገረጉን ለማቋረጥ ብሎ ዘሎ ገባ። የዚህን ጊዜ አህያው ክብደቱ ከፍ ያለ ስነበር መስመጥ ጀመረ። የዚህን ጊዜ ውሻው "አንተ የሰመጥከው ውሸታም ስለሆንክ ነው" አለውና ዞሮ ተመልሶ መጥቶ ጓደኛውን (አህያውን) መብላት ጀመረ።

ይህንን የውሻና የአህያ ታሪክ አንበሳ ሰማ አሉ። "እስቲ አንተ ብትሆን ለማን ትፈርድ ነበር?" አሉት "አይ የውሸት ጓደኛ ጥሩ አይደለም። ከማይመስላችሁ ሰው ጋር አትማማሉ። ቃል አትግቡ እኔ እንደሆንኩ ማንንም አልፈራም።" አለ ብለው በልጅነታችን አባቶቻችን ይነግሩናል።

## ኤሽሽ 11

በአንድ ቤት ውስጥ በጓደኝነት የሚኖሩ አንድ ውሻና አንድ አህያ ነበሩ። አንድ ቀን ስለኑሮኣቸው በመነጋገር ላይ ሳሉ ውሻ ቀደም ብላ "አህያ ጓደኛዬ ስሚ! አንቺ እስከመቼ ድረስ ነው ያልወለድሽውን ልጅ እየተሸከምሽ የምትኖሪ? (ያልወለድሽው ልጅ ማለቷ የምትጫንበትን ዳውላ ነው) እኔስ እስከመቼ ድረስ ያልሰራሁትን የሰው ቤት እየጠበቅሁ የምኖረው?" አለቻት።

አህያ "እውነትሽን ነው ጓደኛየ፡፡ በቃ ከዛሬ ጀምሮ ይህንን የሰው ቤት ለቅቀን እንጥፋ" አለቻት፡፡

አህያ ባቀረበችው ሀሳብ ተስማሙና ተያይዘው ጠፉ፡፡ ቀኑን ሙሉ ሲሄዱ ሲሄዱ ዋሉና አመሻሽ ላይ ባለቤቱ ጥሎት የሄደው አንድ ኦና ቤት አገኙ፡፡ ወደ ቤቱ ውስጥ ገብተው ዙሪያውን በደንብ አድርገው ፈተሹ፡፡ ምንም እንደሌለበት አረጋገጡና እዛው ለመኖር ወሰኑ፡፡

ውሻ የቀኑ ጉዞ አድክሟት ስለነበር እንቅልፍ ያዛትና ጥቅልል ብላ ተኛች፡፡ አህያ ግን እንቅልፍ አልይዛት ስላለ ወደ ውጭ ለመናፈስ ወጣች፡፡ የዚህን ጊዜ ያገኘችውን ለምለም ሰርዶ ጋጥ ጋጥ አደረገችና ጠገበች፡፡ አዲሱ ኑሮዋ ተስማሚ ሆነላት፡፡

ውሻ በአዲሱ ቤታቸው የጀመሩት ኑሮ አላስደሰተውም፡፡ ቢያይ ቢያይ የሚላስ የሚቀመስ ነገር ማግኘት እየከበደው ሄደ፡፡ አህያዋ ግን ኑሮዋ በጣም ስለደላት አንድ ቀን ተነሳችና ውሻዋን፡-

"አንቺዬ እስኪ ዛሬ ብቻ ፍቀጅልኝና አንዴ ላናፋ" አለቻት! ውሻዋ ግን "አንቺዬ ያለንበት ቦታ ጥሩ አይደለም፡፡ ዝም በይ እኔ እኮ ለአንቺ ብዬ ነው እንጂ ርሃብ በጣም እየጎዳኝ ነው" አለቻት፡፡

አህያዋ ግን የጓደኛዋን ምክርና ልመና ችላ ብላ እየደጋገመች አናፋች፡፡ አህያ በተደጋጋሚ በምታናፋበት ጊዜ ርቦት ምግብ ፍለጋ ሲባዝን የነበረ ጅብ ሰምቶ መጣና ዘረጣጣት፡፡ መብላት እንደጀመረም ያቺ የራባት ውሻ መጣችና ከእርሱ ትይዩ ቆመች፡፡ ጅብም አያትና

"እንዴ! ምን ልታደርጊ ነው እዚህ የመጣሽ?" አላት

ውሻዋም "አይ ጌታዬ እርሶዎ የአህያዋን ብልት ሲያወጡ አየሁና እንዳይደክምዎት ላግዝዎት ብዬ ነው" አለችው፡፡

ጅብም "ብድግ አለና በይ ቶሎ ቶሎ በይና የአህያዋን ስጋ አቅርቢልኝ!" አላት፡፡ ውሻዋ እንደታዘዘችው አድርግ ስታቀርብ ከስጋ ብልቶች መሀከል ልብ የለም፡፡ "አሀ! የአህያዋ ልብስ የታለ?" ብሎ ጠየቃት፡፡

ውሻዋ "አይ ጌታዬ! ልብ ቢኖራትማ መች እዚህ ትመጣ ነበር" አለችው፡፡ በመልሷ የተናደደው ጅብ ሊበላት ሲነሳ ውሻዋ "ቆይ ጌታዬ እኔን ከሚበሉኝ አህያውን በልተዋና የአህያውን ባለቤት ላሳይዎት!" አለችው፡፡ ተያይዘው ሄዱ፡፡ የአህያው ባለቤት መኖሪያ አካባቢ ሲደርሱም "ጌታዬ እዚህ ይጠብቁኝ!" ብላ አህያው ባለቤት ጋ ሄደች፡፡ ባለቤቱም "ውሻ

የት ጠፍተሽ መጣሽ?" ሲላት ውሻዋም "አይ! ጌታዬ የጠፋሁት ጓደኛዬ አህያን ጅብ በላትና በዚህ አዝኜ ነው" አለችው፡፡ ባለቤቱም በድንጋጤ "የታለ አሁን ጅቡ!" ብሏት ጦሩን ሊይመጣ ወደ ጓዳ ሲገባ፤ ውሻዋ ሮጣ ሄዳ ለጅቦቹ "በሉ የመንገዱን ዳርና ዳር ያዙና አድፍጣችሁ ባለቤቱን ጠብቁት!" ብላ እየሮጠች ወደ አህያዋ ባለቤት መጣችና እየመራችው ስትሄድ የተደበቁት ጅቦች ያዙትና በሉት፡፡

ጅቦቹ ሰውየውን በልተው እንደጨረሱ ውሻዋ እየመራቻቸው ወደ ሟቹ ሰውዬ ቤት ሄደው ገቡ፡፡ ልክ እንደገቡ ጅቦቹን እቤቱ ውስጥ አስቀመጠችና ሹልክ ብላ ሄዳ የሰፈሩን ሰዎች፡-

"እናንተ ሰዎች፤ ምነው የጎረቤታችሁን አህያ ቀጥሎም የአህያዋን ባለቤት የበሉ ጅቦች መጥተው በሟቹ ቤት ተቀምጠው እያሉ ዝም ብላችሁ ታያላችሁ ወይ?" ስትላቸው ሰፈርተኛው በሙሉ ያለ የሌለ መሳሪያውን ይዞ ቤቱን ከቦ አደፈጠ፡፡ የዚህን ጊዜ ውሻዋ ወደ ጅቦቹ ሄዳ "በሉ ቶሎ ውጡ አንድ ትልቅ ሙክት በግ ያለበትን ላሳያችሁ" አለቻቸው፡፡ የዚህን ጊዜ ጅቦቹ እውነት መስሏቸው ከቤቱ ተከታትለው ሲወጡ እነዚያ አድፍጠው የነበሩት ሰዎች ደብድበው ገደሏቸው፡፡ ውሻ እንደዚህ አድርጋ ጓደኛዋን የበሉ ጅቦችን፣ እየጫነ ያስመረራትን ያህያዋን ባለቤት አጠፋቻቸው ይባላል፡፡

## ፌሽሽ 12

አንድ የደከመ ቅጠል ለብሶ ባጠገቡ እያለፈ የነበረ መንገደኛን "እባክህ ደክሞኛልና ተሸከመኝ?" ብሎ ይለምነዋል፡፡ መንገደኛው ሰውዬም

"አንተ ሰውን የምትበላ አውሬ ነህ፤ ለምን ብዬ ነው የምሸከምህ?" ብሎ ይመልስለታል፡፡ በቅጠል ራሱን ሸፍኖ የነበረው አውሬም "ኧረ እባክህ በፈጠረህ? ዝም ብለኸኝ አትለፍ" ይለዋል፡፡ መንገደኛውም "እንደፈለግክ አድርገኝ እንጂ እኔ እንደሆነ አልሸከምህም" ብሎ ይመልስለታል፡፡ ይሁን እንጂ አውሬው አስተዛዝኖ በተደጋጋሚ ስለለመነው ሰውዬው አዝኖ ከነተጠቀለለበት ቅጠል ተሸከመው፡፡ ሆኖም ሰውዬው ረዥም መንገደ ተሸክሞት ቢጓዝም አውሬው ዝም ብሎ ከመጓዝ ሌላ የተናገረው ነገር የለም፡፡ መንገደኛው ሰውዬም ደከመውና "በል እንግዲህ የተቻለኝን ያህል አግዤህ እዚህ ደርሰሀል፤ ከዚህ በኋላ ሌላም ሰው ስለምታገኝ እነርሱም እንዲረዱህ ጠይቅ" ይለዋል፡፡ ይሁን እንጂ አውሬው "አንተ ሰው ሞኝ ነህ እንዴ! ለምንድነው የምወርደው ይልቅስ ዝም ብለህ ተሸክመኸኝ ብትጓዝ ይሻልሀል" አለው፡፡

መንገደኛው ሰውዬው በአውሬው ምላሽ ተደናግጦ "በል ወዳጄ እስካሁን የረዳሁህ መስሎኝ ተሸክሜህ ነበር። ከላሄ ላይ አልወርድም ካልክ እውነተኛ ፍርድ የሚሰጠንን እስከምናገኝ ድረስ እንጓዝ" አለውና መንገዳቸውን ቀጠሉ። ሆኖም ጥቂት እንደተጓዙ አሳማና ድኩላን አገኙ። ሰውየውም ቀጥ ብሎ ቆመና "እባካችሁ አንድ ጊዜ አድምጡኝ። ይህ በትከሻዬ ላይ የተቀመጠውን አውሬ ደክሞት መንገድ ዳር ወድቆ ነበርና ጥቂት መንገድ ተሸክሜው እንድጓዝ ለመነኝ። እኔም አሳዘነኝና ተሸከምኩት። አሁን "ሽክሙና መንገዱ አደከመኝ ውረድልኝ ብለው እንቢ አለ" ይህንን ጉድ ስሙና ፍረዱኝ አለ።

አሳማ (ቀደም ብሎ) "መጀመሪያ ወደህ ነው የተሸከምከው ስለሆነም ማውረድ አትችልም። አንተ! ቅጠል የተሸፋፈንከው አንዳትወርድ" አለው። ቀጥላም ድኩላ "አንተ ሰው! እንዲያውም ልትበላ ይገባሃል" አለችው። በሁለቱ ዳኞች የተሰጠው መልስ ግርም ብሎት መንገደኛው ከነሸክሙ መንገዱ ቀጠለና ጥቂት እንደተጓዘ ጦጣና ሚዳቋን አገኘ። ሰውዬው "ይኸውላችሁ ይህ ከላዬ ላይ ቅጠል ለብሶ የተቀመጠው አውሬ ደክሞት ነበርና መንገድ ዳር ባገኘሁት ጊዜ እንድሸከመው የፈጣሪን ስም ጠርቶ ለመነኝ። እኔም ተሸከምኩት። አሁን ድክሞኛልና ውረድልኝ ብለው እንቢ አለ" ፍረዱኝ አላቸው። ሚዳቋም "ባላንጋራ ባላንጋራውን ተሸክሞ ፍርድ አልሰጥም ከእኔ ፍርድ ከፈለጋችሁ እስቲ "እርሶ ከላይ የተቀመጡት መሬት ይውረዱና አብራችሁ ጎን ለጎን ስትቆሙ ነው ፍርድ የምሰጥ" አለች። በዚህን ጊዜ ሰውዬው ላይ ተቀምጦ የነበረው አውሬ መሬት ላይ ዱብ ሲል እባብ ሆነ። የዚህን ጊዜ ጦጣዋ "አንተ ሰውዬ ዱላህ በእጅህ፣ ልብህ በደረትህ አይደለም ወይ!" አለችው። በዚህን ጊዜ ፍርዱ ገባውና የእባቡን ጭንቅላት ቀጥቅጦ ገደለው። ሰውዬውም በሁለቱ ሽበቶዎች (ጦጣና ሚዳቋ ፊታቸው ላይ ነጣ ነጣ ያለ ፀጉር ይበዛልና ነው) ውሳኔ ነፍሱን አትርፎ ሄደ ይባላል።

## ኤሸሸ 13

ድሮ ጊዜ አንድ የነብርና አንድ የድኩላ ልጅ ነበሩ አሉ። እናቶቻቸው ወደ ምግብ ፍለጋቸው ከሄዱ በኋላ ሁለቱ ግልገሎች ሳይተዋወቁ ይገናኙና ሲጫወቱ ውለው ማታ ወደ ቤት ይመለሳሉ። አንድ ቀን ማታ ከእናቶቻቸው ጋር ሲጫወቱ ቀን ላይ ስላጋጠማቸው ጉዳይ ተናገሩ።

የነብር ልጅ:- "እማየ! ቀን ላይ ምን የመሰለች የምታምር ልጅ እንዳጋጣሚ ተገናኘንና ከእኔ ጋር ስትጫወት ውላ ሄደች" ብላ ለእናቷ ትናገራለች።

የነብሪቷ እናት፡- "ምነው ልጅ እሷ እኮ የምትበላ ነገር አልነበረችም ወይ? እኔ እናትሽ ዘር ማንዘራቸውን እየበላሁ፣ አባትሽም የእነሱን ዘር እየበላ አይደለም ወይ አንችን የወለድነው! እንዴት እሷን አግኝተሽ ለቀቅሻት? ስለዚህ ነገ ብታገኛት ቀስ ብለሽ አባብለሽ ያዣትና እኔ ስመጣ እንበላታለን" ብላ ለልጇ መከረቻት አሉ።

በሌላ በኩልም የድኩላዋ ልጅ ለእናቷ የቀኑ ውሎዋን እንዲህ ብላ ነገረቻት፡-

የድኩላ ልጅ፡- "እማዬ አንዲት የምታምር ዝጉርጉር አውሬ መጥታ ከእኔ ጋር ስትጫወት ሁላ ሄደች። ምንም ነገር አላደረገችኝም" ብላ ስትነግራት

የድኩላዋ እናት፡- "አንቺዬ ዘር ማንዘርሽን ሁሉ እኮ የጨረሱት የእነርሱ ዘሮች ናቸው። እኔ ጫካ ለጫካ ከእነሱ ዘር ስደበቅ ቆይቼ ነው እኮ አንቺን የወለድኩት። ልጅ ሁለተኛ ያቺን ዝንጉርጉር አውሬ እንዳትቀርቢያት። ብላ ልጇን መከረቻት አሉ። በነጋታው ጠዋት የነብሪቷ ልጅ እንደተመከረችው ቀድማ ትናንት የተጫወቱበት ቦታ በመገኘት "ድኩሊት! ድኩሊት!" ቶሎ ነይና እንደትናንቱ አብረን እንጫወት!" ብላ ጠራቻት። የድኩላዋ ልጅም ጥሪዋን እንደሰማች "ያንቺ እናት እንደመከረችሽ ሁሉ የእኔ እናትም መክራኛለችና አልመጣም!" ብላት አለች አሉ።

## ኤሽሽ 14

አንድ ጊዜ ትንሽ የአይጥ ግልገል ድመት ዘንድ ትሄድና "ክርስትያን መሆን እፈልጋለሁ" ብላ ደጋግማ ለመነቻት አሉ። በዘመኑም የክርስትያኖች ሀላፊ የነበረው ድመት ነበርና ቢግልገሏ አይጥ ንግግር በጣም ተደነቀ።

"ሀሳብሽ ጥሩ ነው። ለመሆኑ ቁጥራችሁ (ብዛታችሁ) ምን ያህል ነው?" አለና ድመት ጠየቃት።

"አይ ቁጥራችን እንኳን እጅግ ብዙ ነው።" አለችው አይጧ።

"በይ እንግዲህ ልክ የዛሬ ሳምንት ጠቅላላ ዘመዶችሽን ይዘሽ ነይና ክርስትና ትነሳላችሁ" አላት። ድመቷም ሄደችና ጠቅላላ ዘመዶቿን ይዛ በተባለው ቀን መጣች። ድመቱም አይጦቹን እንደተመለከተ፡-

"አሁን ክርስትያን ለመሆን ነው የመጣችሁ?"

"አዎን"

"እውነታችሁን ነው?"

"አዎን" አሉት። የዚህን ጊዜ ድመቱ፡-

"ጥሩ ነው። በሉ እንግዲህ እኔ የውሃ መቅጃ ስልቻ እስከማዘጋጅ ድረስ ቤታችሁ ደርሳችሁ ኑ" ብሎ አሰናበታቸው።

አይጦቹ ቤታቸው ሰነባብተው ሲመለሱ ድመቱ ትልቅ የውሃ ስልቻ አዘጋጅቶ ጠበቃቸው። እንደተገናኙም "በሉ እንግዲህ ክርስትና የምትነሱት እየተጠመቃችሁ ነውና ትልልቆቹ ከፊት ለፊት ትንንሾቹ ደግሞ ከኋላ በቅደም ተከተል ተሰለፉ" አላቸው። እነርሱም ተሰለፉ። ድመቱ ቀጠለና "እንግዲህ ክርስትና የማነሳችሁ በውሃ እያጠመቅሁ ነውና ምናልባት በማጠምቅበት ጊዜ "ፒጥ! ፒጥ! ..." እያለ የሚጮህ ከመሀከላችሁ ካለ እርሱ ሰይጣን ያለበት ነው። ሌሎቻችሁ በፍፁም እንዳትደነግጡ" አላቸው። ባንድ ድምፅ "እሺ!" አሉት። ድመቱ ቀጠለና "በሉ እንግዲህ ሁላችሁም በያላችሁበት ተንበርከኩና አይናችሁን በእጃችሁ ሸፍኑ" አላቸው።

ድመቱ ይህንን መሰል ተደጋጋሚ ትዕዛዝ ሲያባዛ አየችና ያቺ መጀመሪያ መጥታ "ክርስትያን ካላደረግሽን" ስትል የነበረችው ትንሿ አይጥ ከሰልፉ መጨረሻ ላይ ቆመች።

"ድመቱም ሁላችሁም አይናችሁን ሸፍናችኋል አይደል? እኔ እንግዲህ ማጥመቅ መጀመሬ ነው" ሲል ያቺ መጨረሻ ላይ የተሰለፈችው አይጥ እንደሌሎቹ ለመንበርከክ ጎንበስ ብላ ጉድጓድ መቆፈር ጀመረች።

ቀጥሎም ድመቱ አይጦቹ በሙሉ "ፒጥ! ፒጥ! ..." እያሉ በየተራ እየያዘ ስልቻው ውስጥ ከተታቸው። ልክ ትንሿ አይጥ ጋ ሲደርስ ከቆፈረችው ጉድጓድ ገባችና አመለጠችው። የተቀሩትን በሙሉ ከስልቻው ውስጥ እያወጣ በልቶ ጨረሳቸው። በዚህም የተነሳ በእድሜ ከፍ ከፍ ያሉት በሙሉ በሞኝነታቸው በድመቱ ተበልተው ሲያልቁ ትንሿ አይጥ ግን በብልጠቷ አመለጠችው ይባላል።

## ኤሽሽ 15

አንድ ሽማግሌ ነበሩ። እንሮአቸው ከነበረው ቆጮ ውስጥ የሚኖር አንድ ትልቅ እባብ ምሽት ላይ እየመጣ ከቤታቸው ውስጥ ካለው ምድጃ አመድ ላይ ያድራል። አንድ ቀን ማታ ላይ ጅብ ዘፈን መዝፈን ይጀምራል። ይህን ዘፈን የሰሙ ሁለቱ የሽማግሌው ልጆች ሄደን ካለየን ብለው ያስቸግሯቸዋል። የዚህን ጊዜ ሽማግሌው "ልጆቼ ይህ የምትሰሙት እኮ የጅብ ዘፈን ነው። እንዴት አድርጋችሁ ነው የምትሄዱት? ይቅርባችሁ" እያሉ መከሯቸው። ሆኖም ልጆቹ አይ ሄደን የጅቡን ዘፈን ማለት አለብን ብለው ሄዱ። ልክ ሁለቱ

እህትማማቾች እሚዘፈንበት ቦታ ሲደርሱ ጅቦቹ "አረ ሰው አግኝተናል!" ብለው ያዟቸውና እቤት ወስደው ዘጉባቸው፡፡

ጅቡ ለስጋ የሚሆኑ ሁለት ልጆች ስላገኘ አይጦችን ጠርቶ "ይህንን ጤፍ ፈጭታጭሁ ጠብቁኝ!" ብሎ ዘመዶቹን ሊጠራ ሄደ፡፡ ጤፍ ለመፍጨት የመጡት አይጦች ጅቡ መሄዱን እንዳረጋገጡ አንዷ በጓሮ በኩል ዙራ ገባችና ቤት ተዘግቶባቸው የነበሩትን እህትማማቾች "እናንተዬ ጅቡ ሊበላችሁ አስቦ ዘመዶቹን ሊጠራ ሄዷል፡፡ ታዲያ ዝም ብላችሁ ከምትበሉ ለምን አታመልጡም" ብላ መውጫ ቀዳዳ አሳየቻቸው፡፡ ልጆቹም አይጧ እንደነገረቻቸው ወጡና አመለጡ ይባላል፡፡

## ኤሽሽ 16

ውሃ ውስጥ የሚኖር አዞ ነበር፡፡ ዝንጀሮ ደግሞ አንድ በጣም ጣፋጭ ፍሬ በሚያፈራ ዛፍ ላይ ይኖር ነበር፡፡ ዝንጀሮ ሁል ጊዜ ከዛፍ ላይ ያለውን ጣፋጭ ፍሬ እየቆረጠ ለአዞው ይወረውርለትም ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ጓደኝነታቸው እየጠነከረ ስለመጣ አንድ ቀን አዞው ዝንጀሮው እንዲህ አለው፡፡

"ጓደኛዬ ዝንጀሮ! አንተ ሁል ጊዜ ከዛፍ ላይ ያለውን ፍሬ እየቆረጥክ ጋብዘኸኛል፡፡ እኔ ደግሞ ዛሬ ወደ ቤቴ ወስጄ ልጋብዝህ ፈልጌያለሁ፡፡ በል ወረድና እንሂድ" አለው፡፡

ዝንጀሮም "ግብዣህ ጥሩ ነበር፡፡ እኔ እንዴት አድርጌ ውሃውን ተሻግሬ ነው አንተ ቤት የምደርሰው" አለው፡፡

"ይህማ በጣም ቀላል ነው፡፡ እኔ በጀርባዬ ተሸክሜ አደርስሃለሁ" አለው፡፡

ዝንጀሮውም በአዞው ሀሳብ ተስማማና ከፍሬው ዛፍ ላይ ወርዶ አዞው ጀርባ ላይ ተቀመጠ ጉዞ ተጀመረ፡፡ እወንዙ መሀከል ሲደርሱ አዞው፡-

"ጓደኛዬ ዝንጀሮ በጣም አዝናለሁ፡፡ ዛሬ ወደ ቤቴ ለምን እንደጋበዝኩህ ልንገርህ፡፡ ይኸውልህ ባለቤቴ በጣም ስለታመመች አዋቂ ጋ ሄደች፡፡ ያአዋቂ የተባለውም ከበሽታሽ የምትድኚው የዝንጀሮ ልብ ከበላሽ ብቻ ነው" አላት፡፡ እኔም አሁን ታዲያ ቢጨንቀኝ አንተን ጓደኛዬን "ልጋብዝህ" ብዬ አመጣሁህ፡፡ "ቤቴ ስንደርስ ትታረድና ልብህን አውጥቼ ለሚስቴ እሰጣለሁ" አለው፡፡ ዝንጀሮውም መታለሉ ገባውና "ታዲያ ለሚስትህ ህመም የዝንጀሮ ልብ መድሃኒት ከሆነ ምን ችግር አለው፡፡ እኛ ዝንጀሮዎች ከዛፍ ላይ ወደ መሬት ስንወርድ ሁል ጊዜ ልባችንን ዛፍ ላይ አስቀምጠን ነው፡፡ በል ቶሎ ወደ ተነሳንበት መልሰኝና ልቤን ከዛፍ ላይ አውርጄ ልስጥህ" አለው፡፡

አሆውም የዝንጀሮው መልስ አሰጣጥ አሳመነውና ወደ ኂላ ተመልሶ እተነሱበት አደረሰው። ዝንጀሮውም ፈጠን እያለ ተራምዶ እዛፍ ላይ ወጣና "አዞ ሞኙ ሆይ ከመቼ ወዲህ ነው ዝንጀሮ ልቡን እዛፍ ላይ ትቶ የሚሄድ!" ብሎ ሳቀበትና "ለካስ ጓደኛዬ መስለህ ስትከተለኝ የኖርከው ልትበላኝ ነበር። እኔስ አምኜህ ስኖር ነበር። ከዛሬ ጀምሮ አታገኘኝም። ሚስትህም አትድንም በጓደኛን መካድና መበደል ጥሩ አይደለም።" ብሎት ሄደ ይባላል።

## ኤሸሸ 17

ጦጣ፣ ዝንጀሮና ተኩላ ሶስቱ የአንበሳ አሽከሮች ነበሩ ይባላል። ሶስቱም በዚህ አገልግሎት ላይ ተሰማርተው እያሉ የሚቀመስ ነገር ሲመጣ ጦጣ ቀደም በማለት "ሽበታም ሽበታሙን እየተመለከታችሁ በቅድሚይ አስቀምሱ" ትላለች። የሽክም እቃ ሲመጣ ደግሞ "ማጅራታም ማጅራታሙን እየተመለከታችሁ ስጡ" እያለች ታስቸግራለች። በዚህ የተነሳም ዝንጀሮና ተኩላ ይሰቃያሉ። ምክንያቱም የሚሸከም ነገር ሲመጣ ትከሻቸው ሰፊ (ፈርጣማ) በመሆኑ እነርሱ ይሸከማሉ። የሚቀመስ ነገር ሲመጣ ደግሞ ሽበታም ሽበታሙን እያያችሁ ስጡ ስለሚባል ተጠቃሚዋ እርሷ ብቻ ሆነች። በዚህ የተናደዱት ዝንጀሮና ተኩላ በመናደድ የምትገደልበትን መንገድ ያሰላስሉ ጀመሩ።

አንድ ቀን አንበሳ ጋ ቀርበው ጌታ ሆይ "ጦጣ እኮ ጫማ መስፋት ትችላለች፤ እርስዎ በእግርዎ የሚሄዱት እስከ መቼ ድረስ ነው" በማለት ነገሩት። አንበሳም በጣም ተገርሞ ጦጣን አስጠራና "አንቺ ጦጢት"

"አቤት"

"ጫማ መስራት ትችያለሽ?"

"አዎ"

"በምንድነው የምትሰሪው?"

"ጌታዬ! በዝንጀሮ ጅማትና በተኩላ ቆዳ ነው።"

ይህን የሰማው አንበሳ ሁለቱን ዝንጀሮና ተኩላን አስገድሎ የዝንጀሮን ጅማትና የተኩላን ቆዳ አስረከባት። ጦጣም እንደተረከበች ተሸክማ ስትጓዝ አንድ ትልቅ ኩሬ አጠገብ ደረሰች። በድንገት ወደ ኩሬው ስትመለከት የራሷን መልክ ታያለች። በዚህን ጊዜ በጣም ትደሰትና የተሸከመችውን የዝንጀሮና የተኩላ ቆዳ ወደ ኩሬው ውስጥ ትወረውረውና ወደ ቤቷ ተመልሳ መጣች። በዚህን ጊዜ አንበሳው፣

"ጫማውን ሰርተሽ አመጣሽ ወይ?" ብሎ ይጠይቃታል። ጦጣም

"ጌታዬ! ከእርሶ የበለጠ ጫማዎን ነጥቆኝ ወሰደው" ብላ መለሰችለት፡፡ በዚህን ጊዜ አንበሳ ሆዬ!

"እንዴት! ባክሽ ከእኔ የበለጠ በሀገር ላይ አለ ወይ? እንዴት ያለ ጀግና ነው የእኔን ጫማ የሚነጥቅ?" ብሎ እንደተናደደ ዘሎ ተነሳና በፍጥነት እየተራመደ ሄዶ ኩሬው አጠገብ ደረሰ፡፡ እንደደረሰም ወደ ኩሬው ውስጥ ሲመለከት እርሱን የመሰለ ግዙፍ መልክ ብቅ አለ፡፡ በዚህን ጊዜ ቀድሜ ወረድኩበት ብሎ ዘሎ እኩሬው ውስጥ ገብቶ ሞተ፡፡ በዚህ ሁኔታ ሶስቱንም ያጠፋች ጦጣ "እኔ ጦጢት ባንድ ጊዜ ጌታና አሽከሮቹን አጠፋሁዋቸው!" በማለት ፎከረችና ዘላ ዛፍ ላይ በመውጣት "ከዛሬ ጀምሮ መኖሪያዬ እዚህ ነው" አለች ይባላል፡፡

## ኤሸሸ 18

ጅንጀሮና ንብ በጋብቻ ዝምድና እንመስርታለን ብለው ተማከሩ፡፡ ይህንንም የጋብቻ ዝምድና ለመመስረት ቃል ከተግባቡ በኋላ "መጀመሪያ ሠርግ ደግሶ የሚጠራው ማነው?" ለሚለው ጥያቄ ተስማሙና ንብ የመጀመሪያውን ድግስ እንዲያዘጋጅ ሆነ፡፡ በስምምነቱ መሠረት ንብ ለዝንጀሮ ሰርገኞች ከሰሩት ማር በብዛት አውርደው አቀረቡላቸው፡፡ ዝንጀሮም የቀረበለትን ማር ግጥም አድርጎ በልቶ ሄደ፡፡

ሁለተኛውን የሠርግ ዝግጅት ለማድረግ ዝንጀሮ በተስማማው መሠረት ቀነ ቀጠሮው ደረሰ፡፡ ይሁን እንጂ ዝንጀሮ ለራሱ ጫካ ለጫካ እየዞረ ያገኘውን በልቶ የሚያድር ስለሆነ ለሰርጉ ዝግጅት እንደ ንብ የሚያቀርበው አጣ፡፡ በዚህም የተነሳ ዝንጅሮዎች በመሉ ተሰበሰቡና ተማከሩ፡፡

ከንብ ጋር የጋብቻ ዝምድና እንመስርት ተባብለን ተስማማን፡፡እኛ በመረጥነው መሠረት የመጀመሪያውን ድግስ እነርሱ አደረጉ፡፡ ዝግጅታቸውም መልካም ነበር፡፡ እኛም በተስማማነው መሠረት ሁለተኛውን ድግስ ለማዘጋጀት ተስማምተን ነበር፡፡ የእኛ የዝንጀሮዎች ኑሮ ደግሞ ጫካ ለጫካ ዞረን ያገኘውን ወዳፍ ነው፡፡ ታዲያ ለዚህ ድግስ ዝግጅት ምን ብናቀርብ ይሻለናል?" ተባባሉ፡፡ ብዙ ሀሳብ ከቀረበ በኋላ አንዱ ዝንጀሮ ተነሳና ይኸንን ያህል ለሰርጉ ዝግጅት ብዙ መጨነቅ የለብንም "እነርሱም እኮ ያደረጉት አራቸውን ሰብስበው ነው ያቀረቡልን፡፡ እኛም ከአንድ ዛፍ ስር ተሰብስበን አራችንን እንቆልል ቀኑ ደረሶ የንብ ሠርገኞች ሲመጡ ያውላችሁ እንበል፡፡" አለ፡፡ በዚህም ሀሳብ ሁሉም የዝንጀሮ መንጋ ተስማማ፡፡ በኋላ ቀኑ ደርሶ የንብ ሠርገኞች ሲመጡ ከትልቅ ዛፍ ስር የተከመረውን የዝንጀሮ አር ያውላችሁ ብለው አቀረቡ፡፡

በጋብቻ እንዛመድ ሲሉ የነበሩ ዝንጀሮዎች ይህን የመሰለ አስፀያፊ ነገር ድግስ ብለው ማቅረባቸው የንብ ሰርገኞችን በጣሙን አስገረመ። ወዲያው አንድ የንብ ተወካይ ተነሳና "ወንድሞቻችን ዝንጀሮዎች እንዛመድ አላችሁ እኛም እሺ አልን። የመጀመሪያውን የሠርግ ድግስ ደግሱ አላችሁ እኛም የእናንተን ወዳጅነት ስለፈለግን ድግሱን በአምላካችንና በሰፊው ፊት በሚቀርበው ማር አደረግን። ታዲያ አሁን ይህንን የመሰለ አስፀያፊ (የአር ክምር) ድግስ ብላችሁ ማቅረባችሁ ተገቢ ነው ወይ?" ብሎ ጠየቀ። ወዲያውኑም ንቦቹ በንዴት "እኛ የእናንተን ዝምድና ፈልገን ብንመጣ እንዲህ አደረጋችሁን! እንገናኛለን" ብለው ወጡ። ዝንጀሮዎችም "እስቲ ምን እንደምታደርጉን እናያለን" አሏቸው።

በዚህም የተነሳም በንብና በዝንጀሮ መሀከል የተፈጠረው ግጭት ተባብሶ ለፍልሚያ ቀን ተቀጣጠሩ። በቀነ ቀጠሮውም መሠረት ዝንጀሮዎቹ ረዥም ዱላ ቆርጠው በመያዝ "ቶሎ ንቦቹ መጥተው ተፋልመን ልክ ካገባናቸው በኋላ ወደ ጫካችን ገብተን የሚበላ ነገር እንፈልግ" ብለው በመመካከር ላይ እያሉ ንቦቹ መጡና ዛፍ ላይ አረፉ። (ዝንጀሮዎቹ አላዩም እንጂ ንቦቹ ማታ መጥተው ሶስት ትልልቅ ዛፎች ላይ ነበር ያደሩት።) ሆኖም ዝንጀሮዎቹ ለፍልሚያው ስለቸኮሉ "በሉዋ ውረዱ እንፋለምና ይለይልን" እያሉ ጮሁ። ንቦችም "ቆይ አትቸኩሉ ትንሽ ፀሐይዋ ሞቅ ትበል?" እያሉ ወዲያውኑ ወደ ፍልሚያው ሜዳ አልገቡም ነበር። ሆኖም ፀሐይዋ ሞቅ እያለች ብትሄድም ንቦቹ ቶሎ ፍልሚያውን አልጀምር በማለታቸው ዝንጀሮዎቹ "በሉዋ ይኸውና ፀሐይዋ ማቃጠል ልትጀምር አይደለም እንዴ!" በማለት ሲጮሁ ንቦቹ ከሰፈሩበት ዛፍ ላይ ተነሱና ብትንትን አሉ። የዚህን ጊዜ ዝንጀሮዎቹ እየጮሁ "አስፈራናቸው፣ አስበረገግናቸው፣ ፈሪዎች ..." በማለት ተናገሩ። የዚህን ጊዜ ሽሽት ጀመሩ የተባሉት ንቦች በሌላ አቅጣጫ ዞረው መጡና ዝንጀሮዎችን ይነድፏቸው ጀመር። በዚህን ጊዜ ዝንጀሮዎቹ እርስ በእርስ እየተጣራሩ "እባክህ ከጭንቅላቴ ላይ ንቀልልኝ እባክህ ናና ከትከሻዬ ላይ ንቀልልኝ ... ሲባባሉ" ጠጋ ብሎ የንቧን እሾህ በእጅ ከመንቀል ይልቅ ንቧን ያገኘ እየመሰለው በያዘው ረዥም ዱላ አንዱ ዝንጀሮ ሌላውን ራስ ራሱን፣ ወገብ ወገቡን ይመታ ጀመር። በዚህም የንቦቹ ጥቃት እየበረታ የእርስ በርሱም መደባደብ ያስፈራቸው ዝንጀሮዎች "ከዚህ በኋላ ከንብ ጋር አንጣላም፣ እንዛመዳችሁ ብለን አንናገርም" እያሉ ከንብ ጥቃት ለማምለጥ ሲሮጡ ከገደል ውስጥ ገብተው አለቁ ይባላል።

## ኤሽሽ 19

ጓደኛሞች የሆኑ አንድ በግና ፍየል ነበሩ፡፡ አንድ ቀን የለመለመ ሳር ፈልገው ለመብላት እየሄዱ ሳለ ነብር ጠረኖቻቸውን ይዞ (እያሸተተ) ተከትሎ ይደርስባቸዋል፡፡ ነብሩ በሚደርስባቸው ጊዜ ፍየሊቷ ብልጠት ስላላት ዘላ ዛፍ ላይ ወጣችና ቆም ብላ ወደ ታች ስታይ ከዛፉ ስር ያለችው ጓደኛዋ በግ በፍርሃት ትንቀጠቀጣለች፡፡ ነብሩ ደግሞ እያደባ ወደ ዛፉ ቀረበና እየተንቀጠቀጠች ያለችውን በግ "ይቺ ደግሞ ምን ያንቀጠቅጣታል?" አለ፡፡ ፍየልን ግን አላየም፡፡ ከዛፍ ላይ ወጥታ የነበረችው ፍየል "አንተን ልትበላህ ነዋ!" አለችው፡፡ በበጓ መንቀጥቀጥና ከዛፍ ላይ ሆና መልስ የሰጠችው ፍየል ሁኔታ ያስፈራው ነብር ወደ ኋላ ዞሮ መንገዱን በፍጥነት ቀጠለ፡፡ ጥቂት እንደተጓዘም የራበው አንበሳ ተኝቶ ያገኛል፡፡ አንበሳም ነብሩን "ከየት እየመጣህ ነው?" ይለዋል፡፡

ነብር "ርቦኝ ምግብ ፍለጋ ስዞር አንድ ፍየልና በግ አገኘሁ፡፡ በጓን ልይዛት ስጠጋ በጣም ተንቀጠቀጠች፡፡ ምን ሆና ነው የምትንቀጠቀጠው?" ስል ለካስ እዛፍ ላይ ወጥታ የነበረች ፍየል ነበረችና "አንተን ልትበላህ ነው?" ስትል የበጓ ሁኔታ አስፈርቶኝ እየሮጥኩ መጣሁ አለ፡፡ አንበሳውም "እስቲ የት እንዳሉ ውሰደኝና ልያቸው" አለው፡፡ ነብሩም አንበሳውን እየመራው ፍየሏና በጓ ያሉበት ቦታ አደረሰው፡፡ የሁለቱን መምጣት ከርቀት ስትመለከት የነበረችው ፍየል በጓን "ቀስ ብለሽ ዛፍ ላይ ውጪ" አለቻት፡፡ በጓም እንደምንም ተጣጥራ ዛፍ ላይ ወጣችና ፍየሏ አጠገብ ደረሰች፡፡ ወዲያውኑም በጓ ፍየሏን ጠርታ፡-

"ሽንቴ መጣብኝ፡፡ ወዴት ልሽናው?" አለችና ጠየቀቻት

"ሽንትሽን ወደ ታች የለቀቅሽው እንደሆነ ጠረኑን እያሸተቱ ይመጡና ይጨርሱናል፡፡ ስለዚህ እንግላል ተኝተሽ በፀጉርሽ ላይ ልቀቂው፡- ወደ መሬት ጠብ እንዳይል" ብላ መከረቻት፡፡ ሁለቱ ይህንን እየተመካከሩ ሳለ ለካስ አንበሳና ቅድም ፈርቶ የሸሸው ነብር እዛፉ አጠገብ ደርሰዋል፡፡

በጊቷ ጓደኛዋ ፍየል እንደመከረቻት ተንጋላ ሽንቷን እላይዋ ላይ ለመሽናት ስትሞክር ተንከባለለችና እመሬት ላይ ወደቀች፡፡ በምትወድቅበት ጊዜ ፍየሏ ከላይ ሆና "እንዳትለቀው ያዝው! ያዥው! … ነብሩን አይደለም! አንበሳውን፣ ያዥው! እንዳትለቀው አንበሳውን ያዥው ያዥው …" እያለች ጮኸች፡፡ በዚህም ነብሩ እኔ ልቅደም፣ አንበሳውም እኔ ልቅደም እያሉ ፈርተው በድንጋጤ እየሮጡ ከአካባቢው ጠፉ ይባላል፡፡

## ኤሸሽ 20

አንበሳና ጦጣ አንድ ላይ ይኖሩ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን በመሀከላቸው ግጭት ተፈጠረ፡፡ የዚህን ጊዜ ጦጣ አንበሳን "እንግዲህ ከፈለግክ እንዋጋና አሸናፊው ይለይ!" ብላ ጠየቀች፡፡ አንበሳም "አንቺ ጦጣ ነሽ ከእኔ ጋር የምትዋጊ?" ብሎ ደጋግሞ ጠየቃት፡፡ ጦጣዋም "አዎ!" ብላ መለሰችለት፡፡ በሁኔታዋ የተገረመው አንበሳም "እሺ!" ብሎ ለፍልሚያው ቀን ያዙ፡፡ አንበሳም ትላልቅ የሆኑ እንስሳትን እንዲመርጥ፤ ጦጣም መሰሎቿን ይዛ እንድትመጣና "ውጊያቸው ጠዋት በሶስት ሰዓት ላይ እንዲጀመር ተስማምተው ተለያዩ!"

በቀጠሮው ቀን አንበሳ፣ እንደ ዝሆንና ጎሽ የመሳሰሉ ትላልቅ እንስሳትን ይዞ ቦታው ላይ ተገኘ፡፡ ጦጣን ቢጠብቋት፣ ቢጠብቋት ብቅ አልልም አለች፡፡ መጨረሻ ላይ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ለውጊያ የተቀጣጠሩበት ቦታ ደረሰች፡፡ ሆኖም አንገቷ ላይ ሶስት ቅሎችን ከማንጠልጠሏ ውጭ አጠገቧ ማንም አልነበረም፡፡

ጦጣዋ እነአንበሳ አጠገብ እንደደረሰች "ለውጊያ እየጠበቃችሁኝ ነው አይደል?" ብላ በመጠየቅ ቀና ብላ አየቻቸው፡፡ ፈጠን ብላም መሀከላቸው ዘላ ገባችና አንገቷ ላይ ካንጠለጠለችው ቅል አንዱን ፈታ መሬት ላይ ስትጥለው ተሰበረና በውስጡ ተሞልቶ የነበረው ጉንዳን አካባቢውን አጥለቀለቀው፡፡ ወዲያው አንበሳ፣ ዝሆንና ሌሎች ትልልቅ አውሬዎች በጉንዳኖቹ ንክሻ መዝለል ጀመሩ፡፡

ጦጣዋ ትንሽ ቆየችና ሁለተኛውን ቅል እመሀከላቸው ስትወረውር በውስጡ የነበሩት ተርቦች ተበተኑና የአውሬዎቹን እግር መንደፍ ጀመሩ፡፡ በዚህን ግዜ እርስ በእርሳቸው መረጋገጥ ሲጀምሩ ሶስተኛውን ቅል ከአንገቷ ፈትታ አውሬዎቹ ላይ ወረወረችው፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጡ የነበሩት ንቦች ተዘረገፉና አንበሳንና ዝሆንን የመሳሰሉ አውሬዎችን ነድፈው ገደሉ፡፡ ጦጣ እንደዚህ አድርጋ በብልጠቷ አንበሳንና ትላልቆቹን አራዊቶች አሸነፈች ይባላል፡፡


BENCH MAGI ZONE
GAMBELA
SHEKA
KEFICHO
SUDAN
DEBUB OMO
1
2
3
4
5
6
7
8
9
LEGEND
1, GURAFERDA
2, SHECO
3, BENCH
4, SHY BENCH
5, MEINIT GOLDYA
6, " " SHASHA
7, BERO
8, MAGI
9, SURMA
SCALE 1:2,000,000


N

# መግለጫ

ይህ ቴሲስ (የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ) የኔ ወጥ ሥራ (Original Work) ሲሆን፣ ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርሲቲ የዲግሪ ማሟያ ጥናት ሆኖ አልቀረበም። ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀሙኩባቸውን መረጃዎችም በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን አረጋግጣለሁ።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድህረምረቃ ትምህርት ቤት

ሰኔ 1999 ዓ.ም.